# አሪት ዘመሳፍንት

ዜና ዘመሳፍንት ሲል ነው፣ የመሳፍንትን ነገር የሚናገር መጽሐፍ ይህ ነው ፣ ይህንም ፹ቱ ፩ ለመጻሕፍት አርእስት ሲሰጡ አርእስት ሰጥተውታል፣ ነገሩን (ኃይለ ቃሉን) ግን ወኮነ እምድኅረ ሞተ ኢያሱ ብሎ ይጀምራል ፡፡

## ምዕራፍ ፩

፩፤ ወኮነ እምድኅረ ሞተ ኢያሱ ፣

ኢያሱ ከሞተ በኋላ እንዲህ ሆነ፣ ስለምን በዋዌ ጀመረ ቢሉ ወሞተ ኢያሱ ብሎ ነበርና ከዚያ ለማያያዝ ይህስ እምድኅረ ሞተ ኢያሱ ያለው ይበቃል ብሎ ለመጻሕፍት በዋዌ መጀመር ልማድ ነው «ወሀሎ ፩ ብእሲ በሀገረ አውስጢድ ዘስሙ ኢዮብ» እንዲል ኢያሱንስ ስለ ምን አነሳው ቢሉ ኢያሱ ከሞተ በኋላ እስራኤል ጣዖት አመለኩ ብሎ ነበርና በመካከል ነገር እንዳልቀረ ሲያጠይቅ በኢያሱ ዘመን ኋላም በተነሱ በደጋጉ መሳፍንት ዘመን ጣዖት አላመለኩም ለማለት ፤

ተሰአሉ ደቂቀ እስራኤል ኀበ እግዚአብሔር ፣

ኮነ ያለውን ተሰአሉ ብሎ ገለጠው ከያዕቆብ የተወለዱ እስራኤል (የእስራኤል ልጆች) ከእግዚአብሔር ዘንድ ለመኑ ፤ አንድም ቃለ እግዚአብሔር ጠየቁ፤

እንዘ ይብሉ መኑ የዐርግ ለነ ኀበ ከናኔዎን መልአክ ዘይትቃተሎሙ ለነ ፣

«ወመጽኡ ከናኔዎን ይንበሩ ውስተ ይእቲ ምድር» ብሎ ነበርና ፤ ኢያ. ም፲፯ ቊ.፲፫ ወደ ከናኔዎን ወጥቶ የሚዋጋ ልን አለቃ ማነው ብለው ቃለ እግዚአብሔር ጠየቁ ፤

፪፤ ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ይሁዳ ይዕርግ ወናሁ አግባእክዋ ለምድር ውስተ እዴሁ ፣

እግዚአብሔርም ምድረ ከነዓንን በጁ ጥያታለሁ እና (ሰጥቸዋለሁና) ነገደ ይሁዳ ይዝመት ፤ አንድም ይሁዳ የሚባል ሰው ይዝመት አላቸው ፤

፫፤ ወይቤሎ ይሁዳ ለስምዖን እኁሁ ዕርግ ምስሌየ በውስተ መክፈልትየ ወንትቃተሎሙ ለከነዓን ፣

ነገደ ይሁዳም ነገደ ስምዖንን ፣ አንድም ይሁዳ የሚባል ሰው ስምዖን የሚባል ወንድሙን በኔ እጣ አብረኸኝ ዝመትና የከነዓንን ሰዎች እንውጋቸው ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአሐውር አነኒ ምስሌከ በውስተ መክፈልትከ ወሖረ ስምዖን ምስሌሁ ፤

እኔም ባንተ ዕጣ ካንተ ጋር እዘምታለሁ አለው ፤ ስምዖንም ከርሱ ጋራ ሔደ (ዘመተ) ፤

፬፡ ወዐርገ ይሁዳ ወአግብአሙ እግዚአብሔር ለከናኔዎን ወለፌርዜዎን ውስተ እዴሁ ወቀተሎሙ በባዜቅ እልፈ ብእሴ ፤

«ይሁዳ ይዕርግ» ብሎት ነበርና ይሁዳ ዘመተ፤ እግዚአብሔርም በከናኔዎን እና በፌርዜዎን የሚኖሩ አሕዛብን በእጁ ጣላቸው፤ በባዜቅም እልፍ (አሥር ሺህ) ሰው ገደለላቸው ፤

፭፡ ወረከብዎ ለአዶንቤዜቅ በባዜቅ ወተቃተልዎ ፤

አዶንቤዜቅንም ሊረዳ መጥቶ በባዜቅ አግኝተው ወጉት ፤

ወቀተልዎሙ ለከናኔዎን ወለፌርዜዎን ፤

በከናኔዎንና በፌርዜዎን የሚኖሩ ሰዎችንም ነገደ ይሁዳ ከነገደ ስምዖን ጋር አጠፏቸው ፤

፮፡ ወጐየ አዶንቤዜቅ ወዴገንዎ ወተለውዎ ወአኀዝዎ ወመተሩ አርእስተ እደዊሁ ወእገሪሁ ፤

አዶንቤዜቅም የነዚያን ጥፋት አይቶ ሸሸ እግር በእግር ተከትለው ይዘው የእጁንና የእግሩን አውራ ጣቶች ቆረጡት ፤

፯፡ ወይቤሎሙ አዶንቤዜቅ ለሰብአ ነገሥት አርእስተ እደዊሆሙ ወእገሪሆሙ ምቱራት ሀለዉ አስተጋቢእየ በታሕተ ማዕድየ ወበከመ ገበርኩ ከማሁ ፈደየኒ እግዚአብሔር ፤

አዶንቤዜቅም አብረው የተያዙትን ሰዎች (የተማረኩትን ሰዎች) እንዲህ አላቸው፤ ከዚህ አስቀድሞ የወጋኋቸው የሰብአው ነገሥታት የእጃቸውና የእግራቸው ቁራጭ በሰደቃዬ በታች ተሰብስቦ አለ ማለት እጃቸውንና እግራቸውን ቆርጬ ጉልበት ገበታዬን አብልቻቸው ነበር፤ እግዚአብሔርም በእነሱ እንዳደረግሁት መጠን ፍዳውን ከፈለኝ አላቸው ፤

ወወሰድዎ ኢየሩሳሌም ወሞተ ህየ ፤

እጁን እግሩን ቆርጠው ኢየሩሳሌም ወሰዱት ፤ በዚያ እንደተጋዘ ሞተ፤ (ሐተታ) ማጋዝስ አላጋዙትም ንጉሥ ነውና ሠራዊቱ አልቅሰው ይቀበሩት ብለው ወስደውታል ፤ ይህን ያህልም አያዝኑለትም ብሎ ወደፊት «ወተቃተሉ ደቂቀ ይሁዳ ምስለ ኢየሩሳሌም» የሚል ነውና ጌታችን አለ መስሏቸው ጸንተው እንዳይወጓቸው ለአፍርሆ ለአደንግፆ ይህን ያየህ ተቀጣ እንደማለት ፤



፰፡ ወተቃተሉ ደቂቀ ይሁዳ ምስለ ኢየሩሳሌም ወአስተጋብእዋ ወቀተልዋ በአፈ ሐፂን ወአውአዩ ሀገራ በእሳት ፤

ነገደ ይሁዳም ኢየሩሳሌም ገብተው በከተማው ከቀሩ አሕዛብ ጋር ተዋጉ ፤ ሰውን በስለት ሀገሯን በእሳት አጥፍተው ኢየሩሳሌምን እጅ አደረጓት ፤

፱፡ ወእምዝ ወረዱ ደቂቀ ይሁዳ ይትቃተልዎሙ ለከናኔዎን እለ ይነብሩ ውስተ አድባር ፤

ነገደ ይሁዳም ኢየሩሳሌምን እጅ ካደረጉ በኋላ በአንባ ውስጥ የሚኖሩ አሕዛብን ያጠፉ ዘንድ ከደጋ ወደ ቈላ ወረዱ ፤

፲፡ ወሖረ ይሁዳ ውስተ ከናኔዎን እለ ይነብሩ ውስተ ኬብሮን ወወፅኡ ሰብአ ኬብሮን ወተቀበልዎሙ ፤

ይሁዳም በቈላ የሚኖሩ አሕዛብን ካጠፉ በኋላ በኬብሮን ውስጥ ወደሚኖሩ አሕዛብ ዘመተ የኬብሮን ሰዎችም ወንድ ይሉን ሴት ብለው ወጥተው ገጠሟቸው ፤

ወስማ ለኬብሮን ትካት ቀርያርቦቅሴፌር ወቀተልዎሙ ለሴሲ ወለአኪማም ወለታሚዓ ትውልደ ኤናቅ ፤

የኬብሮንም ስሟ ቀድሞ ቀርያርቦቃሴፌር ይባል ነበር፤ ወደሷም ገብተው ከኤናቅ የተወለዱ ሦስቱን ነገደ አሕዛብ አጠፏቸው ፤

፲፩፡ ወሖሩ እምህየ ኀበ እለ ይነብሩ ዳቤር ወስማ ለዳቤር ትካት ሀገረ መጽሐፍ ፤

እነዚያንም ካጠፉ በኋላ በዳቤር ወደሚኖሩ አሕዛብ ሔዱ ፤ የዳቤርም ስሟ ቀድሞ የወግ የታሪክ አገር ትባል ነበር ፤

፲፪፡ ወይቤ ካሌብ ለዘቀተላ ለሀገረ መጽሐፍ ወአስተጋብኣ እሁቦ አስካሃ ወለትየ ትኩኖ ብእሲተ ፤

ካሌብም የወግ የታሪክ አገርን ወግቶ እጅ ላደረጋት ሚስት ልትሆነው ልጄ አስካን እሰጠዋለሁ አለ ፤

፲፫፡ ወአስተጋብኣ ጎቶንያል ወልደ ቄኔዝ እኁሁ ለካሌብ ዘይንእስ ፤

የካሌብ የታናሽ ወንድሙ የቄኔዝ ልጅ ጎቶንያል ወግቶ እጅ አደረጋት፤ እሱም ሚስት ልትሆነው ልጁ አስካን ሰጠው ፤

፲፬፡ ወሶበ ለሐዊር አምከራ ጎቶንያል ትስአሎ ለአቡሃ ይጸግዋ ዓፀደ ወፍር ፤

ተንሥአት ያለበት ነው ፤ ለመሔድ በተነሣች ጊዜ የመሠማሪያ ቦታ እንዲሰጣት አባቷን ትለምነው ዘንድ ጎቶንያል መከራት ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአንጉርጉረት በዲበ አድግ ወጸርሐት ወትቤ ውስተ ብሔረ አዝያብ ፈነውከኒ ወይቤላ ካሌብ ምንተ ኮንኪ ፡፡

በበቅሎዋ ላይ ሁና ወደ በረሀ አገር ሰደድኸኝ ብላ ጩሐ አን ጉራጉረች (አለቀሰች)፡፡ ካሌብም ምን ሆንሽ አላት ፡፡

፲፭፡ ወትቤሎ አስካ ሀበኒ በረከተ እስመ ብሔረ አዝያብ ፈነውከኒ ወሀበኒ ቤዛ ማይ ፡፡

በበረሀ ወደ አለ አገር ሰደኸኛ ልና የውሃ መገገር ጉልት (እርሻ) ስጠኝ አለችው ፡፡ አንድም አን ጉርጉረት ወጸርሐት ብሎ ነበ ርና የእንባዬን ዋጋ ስጠኝ አለ ችው ፡፡

ወወሀባ ካሌብ በከመ ትፈቲ በልባ ቤዛ ሕማም ወቤዛ ትካዝ ፡፡

ካሌብም በልቧ እንደ ተመኘ ችው የኀዘንዋንና የልቅሶዋን ዋጋ ቤታኔስን ሰጣት ፡፡

፲፮፡ ወደቂቀ ዮባብ ቄንያዊ ሐሙሁ ለሙሴ ዐርጉ እምሀገረ ፊንቆን ኀበ ደቂቀ ይሁዳ ውስተ ሐቅለ ይሁዳ ዘመንገለ ዓዜብ ውስተ ሙራደ አራድ ወሖረ ወነበረ ምስሌሆሙ ፡፡

«ዐርጉ እምሀገረ ፊንቆን ውስተ ሐቅለ ይሁዳ» ብሎ ይገጥሟል፡፡ የሙሴ አማት የቄንያው ሰው የዮባብ ልጆችም ፊንቆን ከም ትባል አገር በአራድ መውረጃ በስተግራ በኩል ወደ አለች ወደ ይሁዳ ዕጣ ወጡ (ሔዱ)፡፡ እሱም ሔደ ፡፡ ከነሱ ጋር ተቀመጠ ፡፡

፲፯፡ ወሖረ ይሁዳ ምስለ ስምዖን እኁሁ ወቀተልዎሙ ለከናኔዎን እለ ይነብሩ ውስተ ሴፍር ወአኀረምዋ ወአጥፍእዋ ፡፡

ነገደ ይሁዳም ከወንድሙ ከነገደ ስምዖን ጋር ዘምቶ በሴፍር የሚ ኖሩ አሕዛብን አጠፏቸው፡፡ አገ ሪቱንም እርም አድርገው አጠ ፏት ፡፡ አንድም ሥርዓተ ሞት ሠሩባት ፡፡

፲፰፡ ወኢተዋረሳ ይሁዳ ለጋዛ ወለ ደወላ ለአስቀሎና ወለደወላ ለአቃ ሮን ወለደወላ ለአዛጦን ወሙፋራ ቲሃ ፡፡

ነገደ ይሁዳም ጋዛን ከአውራጃዋ ጋር፡፡ አስቀሎናንም ከአውራጃዋ ጋር ፡፡ አቃሮንንም ከአውራጃዋ ጋር ፡፡ አዛጦንን ከመሠማሪያ ዎቿ ጋር አልወረሰም ነበር ፡፡

፲፱፡ ወሀለወ እግዚአብሔር ምስለ ይሁዳ ወተዋረሰ ደብረ ፡፡

እግዚአብሔርም ከነገደ ይሁዳ ጋር በረድኤት አለና ደጋውን አገር ወረሰ ፡፡

ወስእነ ተዋርሶቶሙ ለእለ ይነብሩ ውስተ ቈላት እስመ ሠረገላተ ሐፂን ቦሙ ፡፡

የብረት ሠረገላ ነበራቸውና በቈላ የሚኖሩ አሕዛብን አጥ



ፍቶ ቈላውን አገር መውረስ ግን ተሳነው ፡፡

፳፡ ወወሀብዎ ለካሌብ ኬብሮን በከመ ይቤ ሙሴ ወተዋረሰ እምህየ ፫ አህጉረ ወአሰሰሎሙ እምህየ ለ፫ቱ ደቂቀ ኤናቅ ፡፡

ካሌብም ሙሴ እንዳዘዘ ኬብ ሮንን ሰጡት ፡፡ ከዚያም ሠላሳ ያህል አገሮችን እጅ አድርጎ ከኤናቅ የተወለዱ ሦስቱን ነገ ድም ከኬብሮን አጠፋቸው ፡፡

፳፩፡ ወለኢያቡሴዎን እለ ይነብሩ ውስተ ኢየሩሳሌም ኢያሰሰልዎሙ ደቂቀ ብንያሚ ወነበሩ ኢያቡሴዎን ምስለ ደቂቀ ብንያሚ እስከ ዛቲ ዕለት ፡፡

ነገደ ብንያምም በኢየሩሳሌም የሚኖሩ አሕዛብን አላስለቀቋቸ ውም ነበር ፡፡ እነዚህም አሕዛብ ከነገደ ብንያም ጋር እስከዚች ቀን ኖሩ ፡፡

፳፪፡ ወዐርጉ ደቂቀ ዮሴፍ እሙንቱኒ ውስተ ቤቴል ወእግዚአብሔር ምስሌሆሙ ፡፡

የዮሴፍም ልጆች ወደ ቤቴል ዘመቱ፡፡ እግዚአብሔርም በረድ ኤት ከነርሱ ጋር ነበር ፡፡

፳፫፡ ወተዓየኑ ወርእይዋ ለቤቴል ወስማ ለይእቲ ሀገር ትካት ሎዛ ፡፡

ተሰብስበውም ቤቴልን ጐበ ኟት ፡፡ የዚችም አገር ስሟ ቀድሞ ሎዛ ትባል ነበር ፡፡

፳፬፡ ወርእዩ ሰብአ ማዕቅብ ብእሴ እንዘ ይወጽእ እምሀገር ወአኀዝዎ ወይቤልዎ አርእየነ ምብዋዓ ለሀገር ወንገብር ምሕረተ ምስሌከ ፡፡

ዘብ (በሩን) የሚጠብቁ ሰዎችም ከከተማ ሲወጣ አንድ ሰው አይ ተው ይዘው ወደ ከተማ የምን ገባበት ሥርጥ (ልዩ) መንገድ አሳየን፡፡ ላንተም ይቅርታን እና ደርግልሃለን አሉት ፡፡

፳፭፡ ወአርአዮሙ እንተ ኀበ ይበውእዋ ለሀገር ወቀተልዋ ለይእቲ ሀገር በአፈ ሐፂን ወለዝክቱሰ ብእሲ ወለ አዝማዲሁ አግዓዝዎሙ ፡፡

እሱም ተሠውረው ወደ ከተማ የሚገቡበትን ሥርጥ መንገድ አሳያቸው ፡፡ እነሱም ገብተው ሰውን በስለት አገሩን በእሳት አጠፉት፡፡ መንገድ ያሳያቸውን ያን ሰው ግን ከነዘመዶቹ ነፃ አወጡት ፡፡

፳፮፡ ወአተወ ውእቱ ብእሲ ውስተ ምድረ ኬጤኤን ወነደቀ በህየ ሀገረ ወሰመየ ስማ ሎዛ ወውእቱ ኮነ ስማ እስከ ዮም ፡፡

ኬጤኤንም ይላል፡፡ ይህም ሰው ወደ ኬጤኤን አውራጃ ገብቶ በዚያ አገር አቅንቶ ኖረ ፡፡ ስሟ ንም በቀደመ ሀገሩ ስም ሎዛ ብሎ ጠራት ፡፡ ከዚያም ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ስሟ ሁኖ ኖረ ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፳፯፡ ወኢተዋረሰ ምናሴ ቤተሶን እንተ ሀገረ ሰቂቶን ወአዋልዲሃ ወኢቀጸአድ ወአዋልዲሃ ፤

ምናሴም በሰቂቶን አገር ያሉ አሕዛብን አጥፍቶ ቤተሶንን ከጥቃቅን አገሮቿ ጋር፤ አድዋሊሃ ቢል ከአውራጃዋ ጋር ፤ ቀጸአድንም ከጥቃቅን አገሮቿ ጋር አልወረሰም ፤

ወኢእለ ይነብሩ ውስተ አዶር ወአዋልዲሃ ወኢእለ ይነብሩ ውስተ ዮብለዓም ወአዋልዲሃ ወኢእለ ይነብሩ ውስተ መጌዶ ወአዋልዲሃ ወኢእለ ይነብሩ ውስተ ዮብለዓም ወአዋልዲሃ ፤

በአዶር የሚኖሩትንም አጥፍቶ ከጥቃቅኑ አገሮቿ ጋር በዮብለዓም የሚኖሩትንም አጥፍቶ ከጥቃቅን አገሮቿ ጋር በሜጌዶና በዮብለዓም የሚኖሩትንም አጥፍቶ ከጥቃቅን አገሮቻቸው (ከአውራጃዎቻቸው) ጋር አልወረሰም ፤

ወአኀዙ ከነዓን ይንበሩ ውስተ ይእቲ ምድር ፤

የከነዓን ሰዎች ግን በዚች አገር ውስጥ ይኖሩ ነበር ተርትሮ የተናገረውን ውስተ ይእቲ ምድር ብሎ አጸፋው ፤

፳፰፡ ወእምዝ ሶበ ጸንዑ እስራኤል መጸብሐ ረሰይዎሙ ለከነዓን ወአጥፍኦሰ ኢያጥፍእዎሙ ፤

እስራኤልም ከበዙ በኋላ በጸኑ ጊዜ የከነዓንን ሰዎች ገባር አደረጓቸው፤ ማጥፋትን ግን አላጠፏቸውም ፤

፳፱፡ ወኤፍሬምኒ ኢያጥፍእዎሙ ለከናኔዎን እለ ይነብሩ ውስተ ጋዜር ወነበሩ ከናኔዎን ማዕከሌሙ ውስተ ጋዜር ወኮንዎሙ መጸብሔ ፤

ነገደ ኤፍሬምም በጋዜር የሚኖሩ አሕዛብን አላጠፏቸውም ፤ የከናኔዎን ወገኖችም በጋዜር የነገደ ኤፍሬም ገባር ሁነው በመካከላቸው ኖሩ ፤

፴፡ ወዛብሎንሂ ኢያጥፍእዎሙ ለእለ ይነብሩ ውስተ ቄድሮን ወለእለ ይነብሩ ውስተ አማን ወነበሩ ከናኔዎን ማዕከሌሙ ወኮንዎሙ መጸብሔ ፤

ነገደ ዛብሎንም በአማንና በቄድሮን የሚኖሩ አሕዛብን አላጠፏቸውም ፤ የከናኔዎንም ሰዎች ለነገደ ዛብሎን ገባር ሁነው በመካከላቸው ኖሩ ፤

፴፩፡ ወአሴርሂ ኢያጥፍእዎሙ እለ ይነብሩ ውስተ አካ ወኮንዎሙ መጸብሔ ፤

ነገደ አሴርም በአካ የሚኖሩ አሕዛብን አላጠፏቸውም፤ እነሱም ገባር ሆኗቸው ፤

ወለእለ ይነብሩ ውስተ ዶር ወለእለ ይነብሩ ውስተ ዶላፍ ወለእለ ይነብሩ ውስተ ሲዶና ወለእለ ይነብሩ ውስተ አስኮድ ወኬድያ ወአፌቅ ወሮአብ ፤

በዶላፍና በዶር የሞኖሩትን በሲዶናና በአስኮድ እንደዚህም ሁሉ



በኬዴያድ በአፌቅና በሮአብ የሚኖሩትን ሰዎች አላጠፏቸውም ፤ አንድም እነዚህ ሁሉ ለነገደ አሴር ገባር ሁነው ኖሩ ፤

፴፪፡ ወነበረ አሴር ማዕከለ ከናኔዎን እለ ይነብሩ ውስተ ይእቲ ምድር እስመ ስዕነ አጥፍኦቶሙ ፤

«ተርትሮ የተናገረውን ውስተ ይእቲ ምድር ብሎ አጸፈ» ፤ ነገደ አሴርም እነዚህን (አሕዛብን) ማጥፋት ስለተሳነው በዚች አገር ውስጥ በሚኖሩ አሕዛብ መካከል ኖረ ፤

፴፫፡ ወንፍታሌምሂ ኢያጥፍእዎሙ ለእለ ይነብሩ ውስተ ቤተ ሳሚስ እስመ ስዕኑ አጥፍኦቶሙ ፤

የንፍታሌም ወገኖችም በሳሚስ የሚኖሩ አሕዛብን አላጠፏቸውም እነሱን ማጥፋት ተስኗቸዋልና ፤

ወኢእለ ይነብሩ ውስተ ቤቴኔስ ወነበሩ ማዕከለ ከናኔዎን ለእለ ሀለው ውስተ ይእቲ ምድር ወኮንዎሙ መጸብሔ እለ ይነብሩ ውስተ ቤተ ሳሚስ ወውስተ ቤቴኔስ ፤

በቤቴኔስ የሚኖሩትን አሕዛብ አላጠፏቸውም፤ የከናኔዎን ወገኖችም በዚያች አገር በሚኖሩ ሰዎች መካከል ኖሩ ፤ በቤቴኔስና በቤተሳሚስ የሚኖሩ ሰዎችም ለነገደ ንፍታሌም ገባር ሁነው ኖሩ ፤

፴፬፡ ወአጠቅዎሙ አሞሬዎን ለደቂቀ ዳን በውስተ አድባር እስመ ኢያበውኅዎሙ ይረዱ ውስተ ቈላት ፤

የአሞሬዎን ወገኖችም በደጋ የሚያስጨንቋቸው ነገደ ዳንን በቈላ አስጨነቋቸው ነገደ ዳን ወደ ቈላ ይወርዱ ዘንድ የአሞሬዎን ወገኖችን አላሰናበቷቸውምና (መብት አልሰጧቸውምና)፤

፴፭፡ ወአኀዙ አሞሬዎን ይንበሩ ውስተ ደብረ መርስኖኖስ ዘቦ ውስቴቱ ድብ ወቈናጽል ፤

የአሞሬዎን ወገኖች ቀበሮና ኸርብ (ግስላ) በሚኖሩበት መርስኖኖስ በሚባል ተራራ ይኖሩ ጀመር ፤

ወጸንዓት እዴሆሙ ለቤተ ዮሴፍ ላዕለ አሞሬዎን ወኮንዎሙ መጸብሔ ፤

የነገደ ዮሴፍ ሥልጣን ግን ከአሞሬዎን ወገኖች ጋር ጸንታ ኖረች እነሱም ገባር ሆኗቸው ፤

፴፮፡ ወደብረ አሞሬዎን ወኢዶሜዎን ላዕላይ ዘአቅራቢን እለ ውስተ ላዕላይ ኩኵሕ ፤

ታሕታይ አለና ላዕላይ አለ ፤ ወደ አቅራቢን በሚያደርስ በኢዶሜዎንና በአሞሬዎን ደጋ በዋሻ የሚኖሩ ሰዎችም ለነገደ ዮሴፍ ገባር ሆኗቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፪

፩፡ ወሀርገ መልአከ እግዚአብሔር እምገልገላ ላዕለ ቀላውትሞናስ ወላዕለ ቤቴል ወላዕለ ቤተ እስራኤል ፣

ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ ከገልገላ በቀላውትሞናስና በቤቴል ወደአሉ ወደእስራኤል ወገኖች መጣ ፤ አንድም እምጌልጌላ ይላል ፣ ጌልጌላ ከሚባል ሰማይ መጣ ፤

ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ይቤ አውጻእኩክሙ እምግብጽ ወአባእኩክሙ ውስተ ምድር ዘመሐልኩ ለአበዊክሙ ከመ አሁብክሙ ወእቤለክሙ ኢየኀድግ ኪዳንየ ዘምስሌክሙ ለዓለም ፣

እንዲህም አላቸው ከግብፅ አውጥቼ አወርሳችሁ ዘንድ ለአባቶቻችሁ ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ ወደማልሁላቸው ምድር ወደ ከነዓን አገባኋችሁ፣ ለአባቶቻችሁ የማልኩትንም መሐላዬን ከናንተ ጋር ለዘለዓለሙ አጸናለሁ አለ እግዚአብሔር ፤

፪፡ ወአንትሙኒ ኢትትካየዱ ኪዳነ ምስለ እለ ይነብሩ ውስተ ዛቲ ምድር ወኢለአማልክቲሆሙ ኢትስግዱ ሎሙ ፣

እናንተም በከነዓን ከሚኖሩ አሕዛብ ጋር አትማማሉ፣ ለጣዖቶቻቸው አትስገዱ ፣ ለካህናተ ጣዖቱም አትገዙ ፤

ወግልፎሆሙኒ ቀጥቅጡ ወምሥዋዒሆሙኒ ንሥቱ ወኢሰማእክሙኒ ቃልየ እመ ገበርክሙ ዘንተ ፣

የተቀረጸ ጣዖታቸውን ሥበሩ፣ ምሥዋዓ ብርታቸውንም አፍርሱ አልኋችሁ ፣ ነገር ግን ይህን ካላደረጋችሁ የነገርኋችሁን ነገር አልሰማችሁኝም ፤

፫፡ ወአነኒ እቤ ኢይደግም አሰስሎቶሙ ለአሕዛብ እለ እቤ ከመ አውፅአሙ እምቅድሜክሙ ወይከውኑክሙ ለኀዘን ወአማልክቲሆሙኒ ይከውኑክሙ ለዕቅፍት ፣

እኔም ከፊታችሁ አውጥቼ እሰዳቸው ዘንድ የነገርኋችሁ አሕዛብን እንግዲህ ወዲህ ዳግመኛ ከፊታችሁ አላርቃቸውም አልሁ ፣ እነሱም ለኀዘን ይሆኗችኋል ማለት ያሳዝኗችኋል ፣ ያስለቅሷችኋል፣ ጣዖቶቻቸውም መሰናክል ይሆኗችኋል ማለት ዕቅፍተ ነፍስን ዕቅፍተ ሥጋን ያመጡባችኋል ብሏችኋል አላቸው ፤

፬፡ ወእምዝ ሶበ ይቤሎሙ መልአከ እግዚአብሔር ለኵሉ እስራኤል ዘንተ ነገረ ጸርሐ ኵሉ ሕዝብ ወበከየ ፣

ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክም ለእስራኤል ሁሉ ይህን ነገር በነገራቸው ጊዜ እምዝ ጸርሐ ብሎ ይገጥሟል ፣ ከዚህ በኋላ ሕዝብ ሁሉ ጮኾ አለቀሰ ፤



፭፡ ወበእንተ ዝንቱ ተሰምየ ስሙ ለውእቱ መካን መካነ ብካይ ወሦዑ በህየ ለእግዚአብሔር ፣

ስለዚህም ነገር የዚያ ቦታ ስሙ የልቅሶ ቦታ ተባለ፣ እስራኤልም በዚያ ባለቀሱበት ቦታ መሥዋዕት አቀረቡ ፤

፮፡ ወፈነዎሙ ለሕዝብ ወአተዉ ደቂቀ እስራኤል ኵሎሙ ውስተ አብያቲሆሙ ወውስተ ርስቶሙ ከመ ይትዋረስዋ ለምድር ፣

መልአኩ (ኢያሱ) ሕዝቡን አሰናበታቸው ፣ የእስራኤል ልጆች ሁሉ ከነዓንን ይወርሷት ዘንድ ወደቤታቸው እና ወደርስታቸው ገቡ ፤ አንድም በየርስታቸው ወዳለ ቤታቸው የወረሷትስ በኢያሱ ጊዜ ነው ፣ የተደረገውን ለመግለጽ ደግሞታል ፤

፯፡ ወተቀንዩ ሕዝብ ለእግዚአብሔር በኵሉ መዋዕሊሁ ለኢያሱ ወበኵሉ መዋዕሊሆሙ ለሊቃናት ፣

ሕዝቡም በኢያሱ ዘመን ሁሉ በአለቆቹም ዘመን ሁሉ ለእግዚአብሔር ተገዙ ፤

ወኵሉ እለ ኖኁ መዋዕሊሆሙ እምድኅረ ኢያሱ ኵሎሙ ዘአእመሩ ኵሎ ግብረ እግዚአብሔር ዓቢየ ዘገብረ ለእስራኤል ፣

እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገውን ታላቅ ታምራት ያወቁ ሁሉ ከኢያሱ በኋላ ዘመናቸው የበዛ ሰዎች ሁሉ ለእግዚአብሔር ተገዙ ፤

፰፡ ወሞተ ኢያሱ ወልደ ነዌ ገብረ እግዚአብሔር እንዘ ወልደ ምዕት ወ፲ቱ ዓመት ፣

የእግዚአብሔር አገልጋይ የነዌ ልጅ ኢያሱ መቶ አሥር ዓመት ሲሆነው ሞተ ፤

፱፡ ወቀበርዎ ውስተ ደብረ ርስቱ ውስተ ተምናስራሕ ውስተ ደብረ ኤፍሬም እመንገለ መስዑ ለደብረ ገአስ ፣

በገአስ ተራራ በስተቀኝ በነገደ ኤፍሬም ዕጣ ባለች ርስቱ በምትሆን በተምናስራሕ ቀበሩት ፤ (ሐተታ) ይህንማ ተናግሮት አል ነበረምን ስለምን ደገመው ቢሉ «ወእምዝ አምለኩ ደቂቀ እስራኤል አስጠራጢን ወአስጣሮት» ብሎ እንደ አርእስት ተናግሮ ነበርና ከመካከል እንዳልቀረው ሲያጠይቅ አሁን «ወተንሥአት ካልዕት ትውልድ» የሚል ነውና በኢያሱ ዘመን ከኢያሱም በኋላ በተነሡ በበጎዎቹ ዘመን እስራኤል ኃጢአት አልሠሩም ጣዖት አላመለኩም ለማለት ፤

### ጉባዔ

፲፡ ወኵላ ይእቲ ትውልድ አተዉ ኀበ አበዊሆሙ ወተንሥአት ካልዕት ትውልድ እምድኅሬሆሙ ኵሉ

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፪

፩፡ ወዐርገ መልአከ እግዚአብሔር እምገልገላ ላዕለ ቀላውትሞናስ ወላዕለ ቤቴል ወላዕለ ቤተ እስራኤል ፤

ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ ከገልገላ በቀላውትሞናስና በቤቴል ወደአሉ ወደእስራኤል ወገኖች መጣ ፤ አንድም እምጌልጌላ ይላል ፤ ጌልጌላ ከሚባል ሰማይ መጣ ፤

ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ይቤ አውጻእኩክሙ እምግብጽ ወአባእኩክሙ ውስተ ምድር ዘመሐልኩ ለአበዊክሙ ከመ አሀብክሙ ወእቤለክሙ ኢየነድግ ኪዳንየ ዘምስሌክሙ ለዓለም ፤

እንዲህም አላቸው ከግብፅ አውጥቼ አወርሳችሁ ዘንድ ለአባቶቻችሁ ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ ወደማልሁላቸው ምድር ወደ ከነዓን አገባኋችሁ፤ ለአባቶቻችሁ የማልኩትንም መሐላዬን ከናንተ ጋር ለዘለዓለሙ አጸናለሁ አለ እግዚአብሔር ፤

፪፡ ወአንትሙኒ ኢትትካየዱ ኪዳነ ምስለ እለ ይነብሩ ውስተ ዛቲ ምድር ወኢለአማልክቲሆሙ ኢትስግዱ ሎሙ ፤

እናንተም በከነዓን ከሚኖሩ አሕዛብ ጋር አትማማሉ፤ ለጣዖቶቻቸው አትስገዱ ፤ ለካህናተ ጣዖቱም አትገዙ ፤

ወግልፎሆሙኒ ቀጥቅጡ ወምሥዋዒሆሙኒ ንሥቱ ወኢሰማእክሙኒ ቃልየ እመ ገበርክሙ ዘንተ ፤

የተቀረጸ ጣዖታቸውን ሥበሩ፤ ምሥዋዓ ብርታቸውንም አፍርሱ አልኋችሁ ፤ ነገር ግን ይህን ካላደረጋችሁ የነገርኋችሁን ነገር አልሰማችሁኝም ፤

፫፡ ወአነኒ እቤ ኢይደግም አሰስሎቶሙ ለአሕዛብ እለ እቤ ከመ አውፅአሙ እምቅድሜክሙ ወይከውኑክሙ ለኀዘን ወአማልክቲሆሙኒ ይከውኑክሙ ለዕቅፍት ፤

እኔም ከፊታችሁ አውጥቼ እሰዳቸው ዘንድ የነገርኋችሁ አሕዛብን እንግዲህ ወዲህ ዳግመኛ ከፊታችሁ አላርቃቸውም አልሁ ፤ እነሱም ለኀዘን ይሆኗችኋል ማለት ያሳዝኗችኋል ፤ ያስለቅሷችኋል፤ ጣዖቶቻቸውም መሰናክል ይሆኗችኋል ማለት ዕቅፍተ ነፍስን ዕቅፍተ ሥጋን ያመጡባችኋል ብሏችኋል አላቸው ፤

፬፡ ወእምዝ ሶበ ይቤሎሙ መልአከ እግዚአብሔር ለኵሉ እስራኤል ዘንተ ነገረ ጸርሐ ኵሉ ሕዝብ ወበከየ ፤

ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክም ለእስራኤል ሁሉ ይህን ነገር በነገራቸው ጊዜ እምዝ ጸርሐ ብሎ ይገጥሟል ፤ ከዚህ በኋላ ሕዝብ ሁሉ ጮኾ አለቀሰ ፤



፭፡ ወበእንተ ዝንቱ ተሰምየ ስሙ ለውእቱ መካን መካነ ብካይ ወሦዑ በህየ ለእግዚአብሔር ፤

ስለዚህም ነገር የዚያ ቦታ ስሙ የልቅሶ ቦታ ተባለ፤ እስራኤልም በዚያ ባለቀሱበት ቦታ መሥዋዕት አቀረቡ ፤

፮፡ ወፈነዎሙ ለሕዝብ ወአተዉ ደቂቀ እስራኤል ኵሎሙ ውስተ አብያቲሆሙ ወውስተ ርስቶሙ ከመ ይትዋረስዋ ለምድር ፤

መልአኩ (ኢያሱ) ሕዝቡን አሰናበታቸው ፤ የእስራኤል ልጆች ሁሉ ከነዓንን ይወርሷት ዘንድ ወደቤታቸው እና ወደርስታቸው ገቡ ፤ አንድም በየርስታቸው ወዳለ ቤታቸው የወረሷትስ በኢያሱ ጊዜ ነው ፤ የተደረገውን ለመግለጽ ደግሞታል ፤

፯፡ ወተቀንዩ ሕዝብ ለእግዚአብሔር በኵሉ መዋዕሊሁ ለኢያሱ ወበኵሉ መዋዕሊሆሙ ለሊቃናት ፤

ሕዝቡም በኢያሱ ዘመን ሁሉ በአለቆቹም ዘመን ሁሉ ለእግዚአብሔር ተገዙ ፤

ወኵሉ እለ ኖኀ መዋዕሊሆሙ እምድኅረ ኢያሱ ኵሎሙ ዘአእመሩ ኵሎ ግብረ እግዚአብሔር ዓቢየ ዘገብረ ለእስራኤል ፤

እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገውን ታላቅ ታምራት ያወቁ ሁሉ ከኢያሱ በኋላ ዘመናቸው የበዛ ሰዎች ሁሉ ለእግዚአብሔር ተገዙ ፤

፰፡ ወሞተ ኢያሱ ወልደ ነዌ ገብረ እግዚአብሔር እንዘ ወልደ ምዕት ወ፲ቱ ዓመት ፤

የእግዚአብሔር አገልጋይ የነዌ ልጅ ኢያሱ መቶ አሥር ዓመት ሲሆነው ሞተ ፤

፱፡ ወቀበርዎ ውስተ ደብረ ርስቱ ውስተ ተምናስራሕ ውስተ ደብረ ኤፍሬም እመንገለ መስዑ ለደብረ ገአስ ፤

በገአስ ተራራ በስተቀኝ በነገደ ኤፍሬም ዕጣ ባለች ርስቱ በምትሆን በተምናስራሕ ቀበሩት ፤ (ሐተታ) ይህንማ ተናግሮት አል ነበረምን ስለምን ደገመው ቢሉ «ወእምዝ አምለኩ ደቂቀ እስራኤል አስጠራጢን ወአስጣሮት» ብሎ እንደ አርእስት ተናግሮ ነበርና ከመካከል እንዳልቀረው ሲያጠይቅ አሁን «ወተንሥአት ካልዕት ትውልድ» የሚል ነውና በኢያሱ ዘመን ከኢያሱም በኋላ በተነሡ በበጎዎቹ ዘመን እስራኤል ኃጢአት አልሠሩም ጣዖት አላመለኩም ለማለት ፤

### ጉባዔ

፲፡ ወኵላ ይእቲ ትውልድ አተዉ ኀበ አበዊሆሙ ወተንሥአት ካልዕት ትውልድ እምድኅሬሆሙ ኵሉ

www.ethiopianorthodox.org

እለ ኢየአምርዎ ለእግዚአብሔር ወግብረ ዘገብረ ለእስራኤል ፤

ይእቲ ትውልድ ካለ አተወት አተዉም ካለ ውእቶሙ ባለ በቀና ነበር ፤ ልማደ መጽሐፍ ነው ፤ እነዚህም ወገኖች ሁሉ ሙተው አባቶቻቸው ወደተቀበሩበት መቃብር ገቡ (ወረዱ)፤ ከነሱም በኋላ እግዚአብሔርን የማያውቁ ለእስራኤል ያደረገውንም ታምራት የማያውቁ ሌሎች ትውልድ ተነሡ ፤

፲፩፤ ወገብሩ ደቂቀ እስራኤል እኪተ ቅድመ እግዚአብሔር ወአምለኩ በዓሊምሃ ፤

የእስራኤልም ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ሠሩ ፤ በዓሊም የተባለ ጣዖትንም አመለኩ ፤

፲፪፤ ወኀደግዎ ለእግዚአብሔር አምላከ አበዊሆሙ ዘአውጽኦሙ እምድረ ግብፅ ወተለዉ ባዕዳነ አማልክተ አሕዛብ እለ ዓውደሙ ወሰገዱ ሎሙ ወአምእዕዎ ለእግዚአብሔር ፤

ከግብፅ ያወጣቸውን ያባቶቻቸውን ፈጣሪ እግዚአብሔርን ትተው በዙሪያቸው ያሉ ልዩ የሆኑ የአሕዛብን ጣዖታት አምልከው ሰገዱላቸው፤ እግዚአብሔርንም ኃጢአት በመሥራትና ጣዖት በማምለክ አሳዘኑት ፤

፲፫፤ ወኀደግዎ ለእግዚአብሔር ወአምለክዎሙ ለበዓሊም ወለአስጠራጢም ፤

ፈጣሪያቸው እግዚአብሔርን ትተው በሰው አምሳል የተሠራ ጣዖትን እነሦስቶን እነስድስቶን አመለኩ ፤

፲፬፤ ወተምዐ እግዚአብሔር መዓተ ላዕለ እስራኤል ወአግብኦሙ ውስተ እደ እለ ይዔውውዎሙ ፤

እግዚአብሔርም በእስራኤል ላይ ፈጽሞ ተቆጣ (ፈረደ) ፤ ማርከው በሚወስዷቸው በአሕዛብም እጅ ጣላቸው ፤

ወዔወውዎሙ ወአእተውዎሙ ውስተ ምድረ ፀሮሙ እለ ዓውደሙ ወኢክህሉ ተቃውሞ ቅድመ ፀሮሙ በኵሉ ዘበርበርዎሙ ፤

እነሱም ማርከው ወስደው በዙሪያቸው ወደ አሉ ጠላቶቻቸው አገር አገቧቸው ፤ እስራኤልም ረድኤተ እግዚአብሔር ተለይቷቸዋልና በዘረፏቸው ፤ ማርከው በወሰዷቸው በጠላቶቻቸው ፊት ቁሞ መዋጋት አልቻሉም ፤

፲፭፤ ወእደ እግዚአብሔር ላዕሌሆሙ በእኪት በከመ ይቤ እግዚአብሔር ወበከመ መሐለ እግዚአብሔር ወሣቀዮሙ ጥቀ ፤

እግዚአብሔር «ኢይደግም አሰስሎቶሙ ለአሕዛብ ወይከውኑ



ክሙ ለኀዘን» ብሎ በመሐላ እንደተናገረ የእግዚአብሔር ሥልጣን በእስራኤል ላይ በመዓት ጸንታ ኖረች፤ በአሕዛብም አድሮ ፈጽሞ መከራ አጸናባቸው ፤

፲፮፤ ወአቀመ እግዚአብሔር መሳፍንተ ወአድኀኖሙ እምእደ እለ ዔወውዎሙ ፤

መከራ በጸናባቸውም ጊዜ ስለተመለሱ እግዚአብሔር መሳፍንትን አስነሥቶ ማርከው ከወሰዷቸው ከአሕዛብ እጅ አዳናቸው ፤

፲፯፤ ወለመሳፍንቲሆሙኒ ኢሰምዕዎሙ እስመ ዘመዉ ወተለዉ አማልክተ ባዕድ ወሰገዱ ሎሙ ወአምዕዕዎ ለእግዚአብሔር ፤

ነገር ግን እስራኤል ልዩ የሆኑ የከነዓንን ጣዖታት ተከትለው ሰስነዋልና ለጣዖትም እየሰገዱ እግዚአብሔርን አሳዝነዋልና ቢመክሯቸው ቢያስተምሯቸው መሳፍንቱን አልሰሟቸውም ፤

ውኀደግዋ ፍጡነ ለፍኖት እንተ ባቲ ሖሩ አበዊሆሙ ከመ ኢይስምዑ ቃለ እግዚአብሔር ወኢገብሩ ከማሁ ፤

የእግዚአብሔርን ቃል ወይም ትእዛዝ እንዳይሰሙ አባቶቻቸው ጸንተው የኖሩባትን ሕግ ፈጥነው ተዋት፤ እግዚአብሔር እንዳዘዘም አላደረጉም ፤ አንድም እግዚአብሔር የሾመላቸው መስፍኑም እንዳዘዛቸው አላደረጉም ፤ (ሐተታ) ዕፀው አእባንን አምልከው፤ እንስሳት አራዊትን እነዚህንም አምልከው ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብትን ያመልካሉና ዘመዉ አለ ፤

፲፰፤ ወሶበ አቀመ ሎሙ እግዚአብሔር መሳፍንተ ወሀለወ እግዚአብሔር ምስለ ውእቱ መስፍን ወአድኀኖሙ እምእደ ፀሮሙ በኵሉ መዋዕሊሁ ለውእቱ መስፍን ፤

እግዚአብሔርም ዳግመኛ መሳፍንትን ባስነሣላቸው ጊዜ እግዚአብሔር ከዚያ መስፍን ጋራ በረድኤት ኖረ (ዋዌውን ታግሦ ነው) ፤ በዚያ መስፍን ዘመንም ሁሉ ከጠላቶቻቸው እጅ አዳናቸው ፤

እስመ ተሣሀሎሙ እግዚአብሔር እምሕማሞሙ በቅድመ እለ ይትቃተልዎሙ ፤

በሚዋጓቸው በአሕዛብ ፊት እግዚአብሔር ከመከራው ይቅር ብሏቸዋልና ፤

፲፱፤ ወእምዝ ሶበ ሞተ ውእቱ መስፍን ይገብኡ ካዕበ ወይኤብሱ ፈድፋደ እምአበዊሆሙ ፤

እግዚአብሔር ያደረበት ያ መስፍን በሞተ ጊዜ ዳግመኛ ከአምልኮተ እግዚአብሔር ወደ አምልኮተ ጣዖት ተመልሰው ካባቶቻቸው ይልቅ ፈጽመው ይበድላሉ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወየሐውሩ ወይተልዉ ድኅረ አማል
ክተ ባዕድ ወያመልክዎሙ ወይሰግዱ
ሎሙ ወኢየኅድጉ እከዮሙ ወኢይገ
ብኡ እምፍኖቶሙ እኪት ፤

የከነዓንን ጣዖታት በግብር ተከ
ትለው ይሄዳሉ፤ አምላክ እያ
ሉም ይሰግዱላቸዋል፤ ክፉታቸ
ውን አይተውም ፤ ከክፉ ሥራ
ቸውም አይመለሱም ነበር ፤

፳፡ ወተምዐ እግዚአብሔር መዓተ
ላዕለ እስራኤል ወይቤ እስመ ኀደጉ
እሉ ሕዝብ ኪዳንየ ዘአዘዝክዎሙ
ለአበዊሆሙ ወኢሰምዑ ቃልየ ፤

እግዚአብሔርም በእስራኤል ላይ
ፈጽሞ ተቆጣ (ፈረደ)፤ እነዚህ
ወገኖች ላባቶቻቸው ያዘዝኳቸ
ውን ቃል ኪዳኔን አፍርሰዋልና
ቃሌንም አልሰሙምና ፤

፳፩፡ ወአነኒ ኢይደግም እንከ አሰ
ስሎ ብእሲ እምኔሆሙ ወእምቅድሙ
እምነ አሕዛብ እለ አትረፈ ኢያሱ ፤

እኔም ከእንግዲህ ወዲህ ከእስ
ራኤል ፊት ኢያሱ ካስቀራቸው
አሕዛብ ወገን ሰውን አላጠፋም
አለ ፤

፳፪፡ ውኀደጎሙ ከመ ያመክሮሙ
ቦሙ ለእስራኤል እመ የዐቅቡ ፍኖተ
እግዚአብሔር ወየሐውሩ ባቲ በከመ
ዐቀቡ አበዊሆሙ ወእመ አልቦ ፤

አባቶቻቸው እንደ ጠበቁ የእግ
ዚአብሔርን ሕግ ይጠብቁ እንደ
ሆነ፤ በሷም ጸንተው ይኖሩ እን
ደሆነ፤ አይኖሩም እንደሆነ እስ
ራኤልን ይፈትንባቸው ዘንድ
አሕዛብን ሳያጠፉ ተዋቸው ፤

፳፫፡ ውኀደጎሙ እግዚአብሔር ለእሉ
አሕዛብ ወኢያሰሰሎሙ ፍጡነ ወኢያ
ግብኦሙ ውስተ እዴሁ ለኢያሱ ፤

እግዚአብሔር እነዚያን አሕዛብ
ፈጥኖ ሳያጠፉ ተዋቸው በኢያ
ሱም እጅ አልጣላቸውም ፤
ከላይ የተናገረውን ለማጽናት
ደገመው ::

## ምዕራፍ ፫

፩፡ ውኀደጎሙ እግዚአብሔር ለእሉ
አሕዛብ ከመ ያመክሮሙ ቦሙ ለእ
ስራኤል ወኵሎሙ እለ ኢየአምሩ
ኵሎ ጸብኦሙ ለከነዓን ፤

እግዚአብሔር እነዚህን የተዋ
ቸው (ከጥፋት ያቆያቸው) እስ
ራኤልን ሊፈትንባቸው ነው ፤
ሁሉም የከነዓንን ሰዎች ጦርነት
የማያውቁ ናቸው ፤

፪፡ ዳዕሙ በእንተ ትውልዶሙ ለደ
ቂቀ እስራኤል ከመ ይምሀርዎሙ
ቀትለ ፤

ለእስራኤል ልጆች ሰልፍን ያስ
ተምሯቸው ዘንድ ነው እንጂ ፤

፫፡ ወባሕቱ እለ እምቅድሜሆሙኒ
ኢያእመርዎሙ ለእሉ ፭ቱ አሕዛበ
ኢሎፍሊ ወበኵሉ ከነዓን ወሲዶና
ወኤዌዎን እለ ይነብሩ ውስተ ሊባ



ኖስ እምደብረ ባላሄርሞን እስከ
ሙባዓ ኤማት ፤

ነገር ግን ከነሱ አስቀድመው
የነበሩ አባቶቻቸው እነዚህን አም
ስቱን የኢሎፍሊ ወገኖች በማ
ጥፋት (በጦርነት) አላወቋቸ
ውም ፤ እነዚህም በከነዓን ሁሉ
በሲዶናና በኤዌዎንም ከባላሄር
ሞን ተራራ ጀምሮ እስከ ኤማት
ድረስ በደጋ የሚኖሩ ናቸው ፤

፬፡ ወተርፉ ከመ ያመክሮሙ ቦሙ
ለእስራኤል ከመ ያእምር እመ ይሰ
ምዑ ትእዛዘ እግዚአብሔር ዘአዘዞሙ
ለአበዊሆሙ በእደ ሙሴ ፤

እግዚአብሔር በሙሴ ቃል ለአ
ባቶቻቸው ያዘዘውን ትእዛዝ ይሰ
ሙም እንደሆን አይሰሙም እን
ደሆን ያውቅ ዘንድ እስራኤልን
ሊፈትንባቸው እነዚህ አሕዛብ
ሳይጠፉ ቀሩ (ቆዩ) ፤

፭፡ ወነበሩ ደቂቀ እስራኤል ማዕ
ከለ ከናኔዎን ወኬጤዎን ወአሞሬ
ዎን ወፌርዜዎን ወኤዌዎን ወኢያ
ቡሴዎን ፤

የእስራኤልም ልጆች በኬጤዎ
ንና በከናኔዎን ፤ በፌርዜዎንና
በአሞሬዎን ፤ በኢያቡሴዎንና
በኤዌዎን ፤ ከነዚህ ሁሉ በተ
ወለዱ አሕዛብ ተከበው ኖሩ ፤
አንድም አሁን ልጆቻቸውን
አገቡ ፤ የሚል ነውና ከነዚህ
ሁሉ ጋር ተስማምተው ኖሩ ፤

፮፡ ወነሥኡ አዋልዲሆሙ ወአው
ሰቡ፤ ወአዋልዲሆሙኒ ወሀቡ ለደቂ
ቆሙ ወአምለኩ አማልክቲሆሙ ፤

የአሕዛብን ሴቶች ልጆች ወስ
ደው አገቡ፤ ሴቶች ልጆቻቸው
ንም ለአሕዛብ ወንዶች ልጆች
ሚስት ሊሆኑ ሰጡ ፤ ጣዖቶቻ
ቸውንም አመለኩ ፤

፯፡ ወገብሩ ደቂቀ እስራኤል እኩየ
ቅድመ እግዚአብሔር ወረስእዎ ለእ
ግዚአብሔር አምላኮሙ ወአምለክ
ዎሙ ለበዓሊም ወለአስጣሮት ፤

የእስራኤል ልጆች ክፉ አደረጉ፤
ፈጣሪያቸው እግዚአብሔርን
በሕግ በአምልኮት ዘንግተው
በዓሊምና አስጣሮት የሚባሉ
ጣዖታትን አመለኩ ፤

፰፡ ወተምዐ መዓተ እግዚአብሔር
ላዕለ እስራኤል ወአግብኦሙ ውስተ
እደ ኵስአርስቴም ንጉሠ ሶርያ
ዘመስጴጦምያ አፍላግ ወተቀንዩ
ደቂቀ እስራኤል ለኵስአርስቴም
፰ተ ዓመተ ፤

እግዚአብሔርም በእስራኤል
ተቆጥቶ በመስጴጦምያ ወንዞች
መካከል ባለች በሶርያ ንጉሥ
በኵስአርስቴም እጅ ጣላቸው፤
የእስራኤልም ልጆች ለኵስአር
ስቴም ስምንት ዓመት ተገዙ ፤
ኵስአርስቴም ማለት ዓማፂ
እምዓማፅያን ማለት ነው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፱፡ ወገዓሩ ደቂቀ እስራኤል ኀበ እግዚአብሔር ወአቀመ ሎሙ እግዚአብሔር መድኃኒተ ለእስራኤል ወአድኀኖሙ ጎቶንያል ወልደ ቄኔዝ እኁሁ ለካሌብ ዘይንእስ እምኔሁ ወተአዘዙ ሎቱ ፤

የእስራኤልም ልጆች መከራው ቢጸናባቸው ወደ እግዚአብሔር ጮሁ አለቀሱ ፤ እግዚአብሔርም ጩኸታቸውን ሰምቶ የሚያድናቸውን መስፍን አስነሣላቸው ፤ የካሌብ ታናሽ ወንድሙ የቄኔዝ ልጅ ጎቶንያልም በመስፍንነት ተነሥቶ አዳናቸው ፤ ለሱም ተገዙለት ፡፡

፲፡ ወኮነ ላዕሌሁ መንፈሰ እግዚአብሔር ወኰነኖሙ ለደቂቀ እስራኤል ፤

በእርሱ የእግዚአብሔር ረድኤት አደረበት ፤ የእስራኤልንም ልጆች መስፍን ሁኖ ገዛቸው ፡፡

ወወዕአ ጸብአ ወአግብአ እግዚአብሔር በውስተ እዴሁ ለኲስአርስቴም ንጉሠ ሶርያ ፤

ወደ ሰልፍ ወጣ ፤ እግዚአብሔርም የሶርያ ንጉሥ ኲስአርስቴምን አሳልፎ በእጁ ጣለው ፡፡

፲፩፡ ወአዕረፈት ምድር ፵ተ ዓመተ ወሞተ ጎቶንያል ወልደ ቄኔዝ ፤

ምድረ ከነዓንም ከመከራ ለአሕዛብ ከመገዛት አምስት ዓመት አረፈች ፡ አንድም ጠላት ጠፍቶላት ተዘልላ ኖረች ፤ ከዚያ በኋላ የቄኔዝ ልጅ ጎቶንያል ሞተ ፡፡

፲፪፡ ወደገሙ ደቂቀ እስራኤል ገቢረ እከይ ቅድመ እግዚአብሔር ወአጽንዖ እግዚአብሔር ለኤግሎም ንጉሠ ሞዓብ ላዕለ እስራኤል እስመ ገብሩ እኪተ ቅድመ እግዚአብሔር ፤

የእስራኤልም ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ሠሩ ፤ ክፉ ነገር ስላደረጉም እግዚአብሔር የሞዓብ ንጉሥ ኤግሎምን አስነሣው (አጸናው) ፡፡

፲፫፡ ወአስተጋብአ ላዕሌሆሙ ኲሎ ደቂቀ አሞን ወአማሌቅ ወሖረ ወቀተሎሙ ለእስራኤል ወተዋረሳ ለሀገረ ፊንቆን ፤

የአሞንንና የአማሌቅን ልጆች ሁሉ ሰብስቦ ዘመተ እስራኤልንም ወግቶ ፊንቆን የምትባል አገራቸውን ወረሳት (እጅ አደረጋት) ፡፡

፲፬፡ ወተቀንዩ ደቂቀ እስራኤል ለኤግሎም ንጉሠ ሞዓብ ፲ተ ወ፰ተ ዓመተ ፤

የእስራኤል ልጆችም ለሞዓብ ንጉሥ ለኤግሎም አሥራ ስምንት ዓመት ተገዙለት ፡፡

፲፭፡ ወገዓሩ ደቂቀ እስራኤል ኀበ እግዚአብሔር ወአቀመ ሎሙ እግዚአብሔር መድኅኒተ ለእስራኤል

www.ethiopianorthodox.org



ናዖድሃ ወልደ ጌራ ወልደ ኢያሚን ብእሴ ዘክልዔሆን እደዊሁ የማን ወፌነዉ ደቂቀ እስራኤል አምኃ ለኤግሎም ንጉሠ ሞዓብ ፤

የእስራኤል ልጆች መከራው ቢጸናባቸው ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፤ እግዚአብሔርም የሚያድናቸውን መስፍን ሁለት እጆቹ ቀኝ የሆኑ የኢያሚን የልጁ የጌራ ልጅ ናዖድን አስነሣላቸው ፤ እነሱም ለሞዓብ ንጉሥ ለኤግሎም ከሱ ጋራ (በሱ አማካይነት) እጅ መንሻ ላኩ ፡ «ዘክልዔሆን እደዊሁ የማን አለው» አሁን በቀኝ እጁ ታጥቆ በግራ እጁ ወጋው የሚል ነውና ፡፡

፲፮፡ ወገብረ ሎቱ ናዖድ መጥባሕተ እንተ ክልኤ አፉሃ ወእንተ ስዝር ኑኀ ወቀነታ ታሕተ ቅናቱ ውስተ ሐቌሁ መንገለ የማኑ ፤

ናዖድም ቁመቷ ስንዝር፤ ስለቷ በሁለት ወገን የሆነ ሰይፍ አሠራ፤ ከመታጠቂያው በታች በቀኝ ጎኑ ታጠቃት ፡ ሐተታ ከንጉሥ ፊት ሰይፍ ታጥቆ የሚገባ የለምና እንዳይታይበት «ገብረ ሎቱ ማለቱም አሁን በዚህ ወግቶ ገደለው የሚለው ነውና» እንተ ስዝር ኑኀ ማለቱም ወአብአ እስከ ለኢታ የሚል ነውና ፡፡

፲፯፡ ወአብአ ሎቱ አምኃሁ ለኤግሎም ንጉሠ ሞዓብ ወኤግሎምሰ ቄጢጥ ብእሲሁ ውእቱ ጥቀ ፤

ናዖድም ለሞዓብ ንጉሥ ለኤግሎም እጅ መንሻውን አገባለት (አቀረበለት)፤ ኤግሎም ግን ፈጽሞ ቀጭን ሰው ነበር፤ አሁን በስንዝር ሰይፍ እስከ ጀርባው አማሰለው የሚል ነውና ፡፡

፲፰፡ ወእምዝ ሶበ ፈጸመ ናዖድ አብአ ሎቱ አምኃሁ ፈነዎሙ ለእለ ፆሩ አምኃሁ ፤

ከዚህ በኋላ ናዖድ ለኤግሎም እጅ መንሻውን አግብቶ ከፈጸመ በኋላ እጅ መንሻ ተሸክመው የመጡትን ሰዎች አሰናብቶ ሰደዳቸው ፡፡

፲፱፡ ወገብአ ኤግሎም እምቤተ አማልክት ምስለ ገልገል ፤

ኤግሎምም እጅ መንሻውን ተቀብሎ ከጨረሰ በኋላ ገልገል ከሚባል ሰው ጋር ፡ አንድም ሰው ከማስከልከል ጋር ከጣዖቱ ቤት ገባ ፡ አንድም ከቤተ ጣዖት ወደ ቤተ መንግሥት ገባ ፡፡

ወይቤሎ ናዖድ ብየ ኀቡዕ ነገር ኀቤከ ንጉሥ እንተ ባሕቲትከ ወአዘዘ ኤግሎም ይፃእ ኲሉ እምኀቤሁ ወወፅኡ ኲሎሙ እለ ይቀውሙ ኀቤሁ ፤

ናዖድም ተከትሎ በቆይታ የምነግርህ ምሥጢር አለኝ አለው

ኤግሎምም ከእሱ ዘንድ ሰው
ሁሉ ይመለስ ብሎ አዘዘ፣ ከእሱ
ዘንድ የቆሙ ሰዎችም ሁሉ ወጡ
ንጉሥ በቆይታ ሲነጋገር ከዚያ
የሚቆይ ሰው የለምና ፤

፳፤ ወቦአ ናዖድ ኀቤሁ ወይነብር
ውእቱ ባሕቲቱ ውስተ ጽርሑ ወሐ
ጋይ ውእቱ ወይቤሎ ናዖድ ብየ
ነገር ዘእነግረከ ንጉሥ ወተንሥአ
ኤግሎም እመንበሩ ወቀርበ ፣

ናዖድም ተጠርቶ ወደእሱ ገባ፣
እሱም በእልፍኙ ብቻውን ተቀ
ምጦ ነበር፣ ወራቱም በጋ ነበረ፣
ወንዝ ተሻግሮ ሲሔድ ውሃው
አለመከልከሉ በጋ ቢሆን ነው
ለማለት፣ ናዖድም ቢርቀው እን
ዲቀርበው ንጉሥ የምነግርህ
ነገር አለኝ አለው፣ ኤግሎምም
ከዙፋኑ ተነሥቶ ወደ እሱ ቀረበ፤

፳፩፤ ወሰበ ተንሥአ አልአለ ናዖድ
እዴሁ እንተ ፀጋም ፣

ኤግሎም ቀና ብሎ ከዙፋኑ
በተነሣ ጊዜ ናዖድ ግራ እጁን
ከፍ ከፍ አድርጎ ፤

ወመልሐ መጥባሕቶ እምገቦሁ ዘየ
ማን ፣

ከቀኝ ጐኑ ሰይፍን መዘዘ ፤

ወረገዞ ውስተ ከርሡ ለኤግሎም ፣

ኤግሎምን ሆዱን ወጋው ፤

፳፪፤ ወአብአ እስከ ለአታ ፣

እስከ ውላጋዋ (መያዣዋ) ድረስ
አገብቶ ፤

ወበርበሮ እስከ ዘባኑ ፣

እስከ ጀርባው ድረስ ሰበቀው
(አማሰለው) ፤

ወኢመልሐ መጥባሕቶ እምነ ከርሡ ፣

ሾተሉን መዝዞ አላወጣውም ፣
ከሆዱ ውስጥ ትቶት ሔደ ፤
አንድም ወመልሐ መጥባሕቶ
ይላል አብነት ፣ ከዚያ በኋላ
ሰይፉን ከሆዱ መዝዞ አወጣው ፤

፳፫፤ ወወፅአ ናዖድ ጸናፌ ወአጸወ
ኆኅተ ጽርሑ ላዕሌሁ ወቀተረ ፣

ናዖድም የእልፍኙን ደጃፍ የኋ
ሊት ዘግቶ ወደ በር ወጣ ፤

፳፬፤ ወወፂአ ውእቱ ቦኡ ደቂቁ ወር
እዩ ወረከቡ ኆኅተ ጽርሕ ዕጹወ ፣

እሱ ወጥቶ ከሄደ በኋላ የእል
ፍኝ አሽከሮቹ ገቡ አሁን ገብ
ተው አይደለም፣ የኋላውን መና
ገር ነው ፤ አንድም ከውጭ ወደ
አዳራሹ ገቡ ፣ የእልፍኙን በር
ቢያዩ ተዘግቶ አገኙት ፤

ወይቤሉ የጊ ባሕቲቱ ይነብር ጽምወ
ውስተ ምግኃሠ ጽርሑ ቅሥፌ ፣

ወይም እንጂ ወደ እዳሪ መውጫ
ባደረገው አንበሳ መደብ ብቻ
ውን ተቀምጦ ይሆናል፣ ድምፅ
ሳያሰማ አንገባበትም ብለው ፤

፳፭፤ ወጸንሑ እስመ ኀፍሩ ወአ
ልቦ ዘአርኀወ ኆኅተ ጽርሕ ወነሥኡ



መርኆ ወአርኀዉ ወረከብዎ ለእግዚ
እሙ ውዱቀ ውስተ ምድር ምውተ ፣

ድምፅ ሳያሰማ መግባቱን አፍረ
ዋልና እስኪከፍትላቸው ድረስ
ባዳራሽ ቆዩ፣ በኋላ ግን የእልፍ
ኙን በር የሚከፍትላቸው እንደ
ሌለ አውቀው መክፈቻ አምጥ
ተው ቢከፍቱ ጌታቸው ኤግ
ሎም ሙቶ በድኑ ከመሬት
ወድቆ አገኙት ፤

፳፮፤ ወናዖድሰ አምሠጠ እስከ እሙ
ንቱ ይትሀወኩ ወአልቦ ዘአእመሮ ፣

ናዖድ ግን እነሱ እስኪታወኩ
ድረስ ማለት በድንጋጤ (በሽ
ብር) ሳሉ አመለጠ፣ ያወቀውም
አልነበረም ፤

ወውእቱሰ ኀለፈ እምአማልክቲሆሙ
ወአምሠጠ ውስተ ሴይሮታ ፣

እሱ ግን ጣዖቶቻቸው ካሉበት
ቦታ አልፎ ፤ አንድም ከግዛታ
ቸው ቦታ አልፎ ሂዶ ሴይሮታ
ከምትባል አገር ገብቶ አመ
ለጠ ፤

፳፯፤ ወእምዝ ሰበ በጽሐ ውስተ
ምድረ እስራኤል ነፍሐ ቀርነ ውስተ
ደብረ ኤፍሬም ወወረዱ ምስሌሁ
እምደብር ደቂቀ እስራኤል ወውእቱ
ቅድሚሆሙ ፣

ከዚህ በኋላ ከሴይሮታ ወጥቶ
ወደ እስራኤል ሀገር በደረሰ
ጊዜ በኤፍሬም ነገድ ዕጣ ውስጥ
ባለ ተራራ ላይ ቁሞ መለከት
ነፋ ፤ አንድም ውጋ ውጋ የሚል
የነጋሪት ድምፅ አሰማ ፣ የእስራ
ኤል ልጆችም እሱን ተከትለው
ከተራራው ወረዱ ፣ እሱም በፊ
ታቸው ይሔድ ነበር ፤ አንድም
ፊታውራሪ ሁኖ መራቸው ፤

፳፰፤ ወይቤሎሙ ረዱ ትልዉኒ
እስመ አግብኦሙ እግዚአብሔር ለፀ
ርነ ሞዓብ ውስተ እዴነ ፣

እግዚአብሔር ጠላቶቻችንን የሞ
ዓብን ሰዎች በእጃችን ጥሏቸዋ
ልና ተከትላችሁኝ ውረዱ አላ
ቸው ፤

ወወረዱ ወተለውዎ ወበጽሑ ማዕ
ዶተ ዮርዳኖስ ወአኀዙ ምዕዳወ ዮር
ዳኖስ ዘሞዓብ ወኢያብሑ ሰብአ
ይዕዱ ፣

እስራኤልም ተከትለውት ወረዱ፣
ሒደውም ዮርዳኖስ በደረሱ ጊዜ
የሞዓብ ክፍል የምትሆን የዮር
ዳኖስን መሻገሪያ ያዙ ወደ ሞዓ
ብም ይሻገር ዘንድ ሰውን አላ
ሰናበቱም ፤ አንድም ሰው ወደ
ሞዓብ ይሻገር ዘንድ አላሰናበ
ቱም ፣ ሊወጓችሁ መጡ ብለው
እንዳይነግሩባቸው ፤

፳፱፤ ወቀተልዎሙ ለሞዓብ በእማ
ንቱ መዋዕል ወየአክሉ እልፈ ብእሴ
ኵሎሙ መስተቃትላን ወኵሉ ዕደወ

www.ethiopianorthodox.org

ኃይሎሙ ወአልቦ ዘአምሠጠ እም ኔሆሙ ወኢ፩ዱ ብእሲ ፡፡

በዚያም ወራት የሞዓብን ሰዎች አጠፏቸው፣ የጠፉትም አርበኞች እልፍ ያህል ወይም አሥር ሺህ ይሆናሉ ፡ አንድም የእስራኤል ዓርበኞች እልፍ ያህል ይሆኑ ነበር ፣ የሠራዊቶቻቸውንም አለቆች ሁሉ አጠፉ ፣ ከሞዓብ ሰዎች አንድ ሰውስ እንኳ አላመለጠም ፡ አንድም ከእስራኤል ወገን አንድ ሰውስ እንኳ ከድቶ የሸሸ የለም ፡

፴፡ ወገብኡ ሞዓብ በእማንቱ መዋዕል ውስተ እዴሆሙ ለእስራኤል ወአዕረፈት ምድር ፹ ዓመተ ወኰነኖሙ ናዖድ እስከ ሞተ ፡፡

የሞዓብም ሰዎች በዚያ ወራት በእስራኤል እጅ ወደቁ፣ ምድረ ኢየሩሳሌምም (የእስራኤል አገር) ሰማንያ ዓመት ከመከራ አርፋ ኖረች ፡ አንድም ጠላት ጠፍቶላት ተዘልላ ኖረች፣ ናዖድም እስኪሞት ድረስ እስራኤልን መስፍን ሁኖ ገዛቸው ፡

፴፩፡ ወእምድኅረዝ ቆመ ሴሜጌር ወልደ ሐናት ወቀተለ እምኢሎፍሊ ፮ተ ምእተ ብእሴ በማኅረስ ላህም ወውእቱኒ አድኀኖሙ ለእስራኤል ፡፡

ናዖድ ከሞተ በኋላም የሐናት ልጅ ሴሜጌር በመስፍንነት ተነሣ ፣ ኩዳድ ከሚያስኮድዱበት ቦታ ከኢሎፍላውያን ስድስት መቶ ያህል ሰው በማረሻ አጠፋ ፡ አንድም ኩዳድ በሚያሳርስበት ማረሻ ልብ ልባቸውን እያደቀቀ ገደላቸው ፣ ሴሜጌርም እስራኤልን ከጠላት አዳናቸው፣ ከኃጢአት ጠበቃቸው ::

## ምዕራፍ ፬

### ጉባዔ

፩፡ ወደገሙ ደቂቀ እስራኤል ገቢረ እኩይ ቅድመ እግዚአብሔር ወናዖድስ ሞተ ፡፡

የእስራኤል ልጆች ዳግመኛ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ሠሩ፣ ናዖድ ወዴት ሒዶ ትለኝ እንደሆነ ናዖድስ አስቀድሞ ሙቷል ፡ አንድም ናዖድ አስቀድሞ ሙቷልና የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ሠሩ ፡

፪፡ ወአግብኦሙ እግዚአብሔር ውስተ እደ ኢያሚን ንጉሠ ከናኔዎን ዘነግሠ በሶርያ ፡፡

ከናኔዎን መሳው ሶርያ መዲናው ነው፣ እግዚአብሔርም እስራኤልን በሶርያ በነገሠ በከናኔዎን ንጉሥ በኢያሚን እጅ አሳልፎ ጣላቸው ፡



ወመልአከ ሠራዊቱ ሲሳራ ወውእቱስ ይነብር ውስተ አሴሮት ዘአሕዛብ ፡፡

የሠራዊቱም አበጋዝ (ቢትወደዱ) ሲሳራ ይባላል ፣ እሱም ግን የአሕዛብ ዕጣ ክፍል በምትሆን በአሴሮት ውስጥ ይኖር ነበር ፡

፫፡ ወገዐሩ ደቂቀ እስራኤል ኀበ እግዚአብሔር እስመ ቦ ፱ቱ ፻ ሠረገላት ዘሐፂን ወውእቱ አሕመሞሙ ለእስራኤል እንዘ ይሣቅዮሙ ፳ ዓመተ ፡፡

ሲሳራ በዘመተበት ወራት (በዘመተባቸው ጊዜ) የእስራኤል ልጆች ወደ እግዚአብሔር ጮኹ አለቀሱ ፣ ዘጠኝ መቶ የብረት ሠረገላ ነበረውና ፣ እሱም ሃያ ዘመን ሥቃይ አጽንቶ እስራኤልን አስጨነቃቸው ፡

፬፡ ወዲቦራ ብእሲት ነቢይት ብእሲቱ ለፊዶት ይእቲ ትኴንኖሙ ለእስራኤል በእማንቱ መዋዕል ፡፡

ነቢይት የምትሆን የፊዶት ሚስት የነበረች ዲቦራ በዚያ ወራት እስራኤልን መስፍን ሁና ትገዛቸው ነበር ፡ አንድም ነቢይት ሁና ትመክራቸው ታስተምራቸው ነበር ፡

፭፡ ወዲቦራስ ትነብር ኀበ ፊንቂ ማዕከለ ኢያማ ወማዕከለ ቤቴል ውስተ ደብረ ኤፍሬም ወሀርጉ ሶቤሃ ደቂቀ እስራኤል ከመ ይትኳነኑ ፡፡

ዲቦራ ግን በኤፍሬም ዕጣ ባሉ በቤቴልና በኢያማ መካከል በፊንቆን ትኖር ነበር ፣ የእስራኤልም ልጆች ይፈራረዱ ዘንድ ወደሷ ይወጡ ነበር ፡ አንድም መጋቢያ ከሷ ዘንድ ያደርጉ ነበር ፡

፮፡ ወፈነወት ዲቦራ ወጸውአቶ ለባርቅ ወልደ አቤኔሄም እምቃዴስ ዘንፍታሌም ወትቤሎ አኮኑ ኪያከ አዘዘ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ከመ ትሑር ውስተ ደብረ ታቦር ፡፡

ዲቦራም ልካ የአቤኔሄም ልጅ ባርቅን የንፍታሌም ዕጣ ከምትሆን ከቃዴስ አስጠርታ ታቦር ወደሚባል ተራራ ትሄድ ዘንድ የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር አንተን አዟልና ሒድ ብላ ላከችው ፡

ወንሣእ ምስሌከ እልፈ ዕደወ እም ደቂቀ ንፍታሌም ወእምደቂቀ ዛብሎን ፡፡

ከንፍታሌምና ከዛብሎን ልጆች አወጣጥተህ እልፍ ሰው ይዘህ ሒድ ፡

፯፡ ወእወስደከ ኀበ ፈለገ ቂሶን ላዕለ ሲሳራ መልአከ ሠራዊቱ ለኢያሚን ወሠረገላቲሁ ወብዙኁ ወአገብኦ ውስተ እዴከ ፡፡

በኢያሚን ቢትወደድ በሲሳራ ላይ በሠራዊቱና በሠረገላዎቹም

www.ethiopianorthodox.org

ላይ ኃይል (ጦርነት) ታደርግ ዘንድ ወደ ቂሶን ወንዝ እወስድሃለሁ ፣ እሱንም በእጅህ አሳልፌ እጥለዋለሁ (በእጅህ እንዲወድቅ አደረግዋለሁ) አለችው ፤

፰፡ ወይቤላ ባርቅ እመ ተሐውሪ ምስሌየ አሐውር ወእመሰ ኢተሐውሪ ምስሌየ ኢየሐውር እስመ ኢየአምር ዕለተ እንተ ባቲ ይፌቅድ እግዚአብሔር ይፈኑ መልአኮ ምስሌየ ፣

ባርቅም አንቺ ከእኔ ጋራ ብትሔጂ እሔዳለሁ ፣ አንቺ ካልሔድሽ ግን አልሔድም ፣ እግዚአብሔር መልአኩን ከእኔ ጋር ወደእኔ ይሰደው ዘንድ የሚፈቅድበትን ቀን አላውቅምና አላት ፤

፱፡ ወትቤሎ ዲቦራ አሐውር ምስሌከ ወባሕቱ አአምር ከመ ኢይከውነከ ክብረ ዘቀዲሙ ቃልከ በፍኖት እንተ ሖርከ እስመ ውስተ እደ ብእሲት ያገብኦ እግዚአብሔር ለሲሳራ ፣

ዲቦራም እንዲህ አለችው፣ ያለ አንቺ አልሔድም ካልክ አብሬህ እሔዳለሁ፣ ነገር ግን «እመ ተሐውሪ ምስሌየ አሐውር» ብለህ የተናገርኸው ቃልህ በሔድህበት መንገድ ክብር እንዳይሆንህ ማለት እንዳያስመሰግንህ እወቅ አለችው ፣ እግዚአብሔር ሲሳራን በሴት እጅ ይጥለዋልና አሁን ወደፊት የኮቤር ሚስት ኢያኤል ገደለችው የሚል ነውና ፤

ወተንሥአት ዲቦራ ወሖረት ምስለ ባርቅ እምቃዴስ ፣

ዲቦራም ይህን ተናግራ ከቃዴስ ተነሥታ ከባርቅ ጋር ዘመተች ፤

፲፡ ወአዘዞሙ ባርቅ ለዛብሎን ወለንፍታሌም በቃዴስ ከመ ይትልውዎ ወዐርጉ ምስሌሁ እልፍ ብእሲ ወዲቦራሂ ዐርገት ምስሌሁ ፣

ባርቅም በቃዴስ የሚኖሩ የንፍታሌምና የዛብሎን ወገኖች ይከተሉት ዘንድ አዘዛቸው ከነዚህ ወገን እልፍ (አሥር ሺህ) ሰዎች ተወጣጥተው ተከተሉት ወይም አብረውት ዘመቱ ዲቦራም አብራው ዘመተች ፤

፲፩፡ ወእለ ቅሩቡ ለቄኔዝ ተፈልጡ እምደቂቀ ኢዮባብ ሐሙሁ ለሙሴ ወነደረ ትዕይንቱ ኀበ ዕፅ ለበይት ኀበ ቅሩበ ቃዴስ ፣

የቄኔዝ አቅራቢያ የሚሆኑ ሰዎችም ከሙሴ አማት ከኢዮባብ ልጆች በምክር (በፍቅር) ተለዩ፣ ይህንንም «ጥንተ ዜና ነገር ዘኢያኤል» ይለዋል፣ የባርቅም ሠራዊት በቃዴስ አቅራቢያ ለማደር በወይራ ወይም በግራር ሥር ሰፈረ ፤ አንድም ከዚያ ከወይ



ራው አጠገብ ከተማ አድርጎ ሰፈረ ፤

፲፪፡ ወዜነውዎ ለሲሳራ ከመ ዐርገ ባርቅ ወልደ አቤኔሄም ውስተ ደብረ ታቦር ፣

ሠራዊቱን ያዩ ሰዎችም የአቤኔሄም ልጅ ባርቅ ታቦር ወደሚባል ተራራ እንደወጣ (እንደ ዘመተ) ለሲሳራ ነገሩት ፤

፲፫፡ ወአምጽአ ሲሳራ ኵሎ ሠረገላቲሁ እስመ ፱፻ ሠረገላ ዘሐፂን ቦቱ ወኵሎ ሕዝቢሁ እምአሴሮት ዘአሕዛብ ውስተ ፈለገ ቂሶን ፣

ሲሳራም ዘጠኝ መቶ የብረት ሠረገላ ነበረውና ሠረገላውን ሁሉ ወገኖቹንም ወይም ሠራዊቱን ሁሉ የአሕዛብ ክፍል ከምትሆን ከአሴሮት ይዞ ቂሶን ወደሚባል ወንዝ ዘመተ ፤

፲፬፡ ወትቤሎ ዲቦራ ለባርቅ ተንሥእ እስመ ዛቲ ይእቲ ዕለት እንተ ባቲ ያገብኦ እግዚአብሔር ለሲሳራ ውስተ እዴከ ወናሁ እግዚአብሔር የሐውር ቅድሜከ ፣

ዲቦራም ባርቅን እግዚአብሔር ሲሳራን በእጅህ አሳልፎ የሚሰጥባት ቀን ይህች ናትና ተነሥ እነሆ እግዚአብሔርም በረድኤት አብሮህ ይሄዳል፤ አንድም ፊታውራሪ ሆኖ በፊትህ ይሄዳል አለችው «እስመ ኢየአምር ዕለተ እንተ ባቲ ይፈቅድ እግዚአብሔር ይፈኑ መልአኮ» ብሏት ነበርና እንዲህ አለችው ፤

ወወረደ ባርቅ እምደብረ ታቦር ወ፲፻ ብእሲ ይተልውዎ ፣

ባርቅም የዲቦራን ቃል ሰምቶ ከታቦር ተራራ ወረደ እልፍ ሰዎችም ተከትለዉት ወረዱ ፤

፲፭፡ ወአደንገጾ እግዚአብሔር ለሲሳራ ወለኵሉ ሠረገላቲሁ ወለኵሉ ትዕይንቱ አውደቆሙ ቅድመ ባርቅ በአፈ ሐፂን ወወረደ ሲሳራ እምላዕለ ሠረገላሁ ወጐየ በእግሩ ፣

እግዚአብሔርም ሲሳራን በባርቅ ፊት እንዲደነግጥ አደረገው ፣ ሠረገላውን እየሰበረ ሠራዊቱን በሰይፍ እየመታ ከባርቅ ፊት አጠፋቸው፤ (ሐተታ) አሁን እግዚአብሔር ሰይፍ መዝዞ ጦር ወርውሮ ገድሏቸው አይደለም፣ ኃይል መንሣቱን በረድኤት መለየቱን መናገር ነው ፣ ሲሳራም በሠረገላ የሆነሁ እንደ ሆነ ያውቁኛል ብሎ ከሠረገላው ወርዶ በእግሩ ሸሽቶ አመለጠ ፤

፲፮፡ ወዴገኖ ባርቅ ወተለወ ሠረገላቲሁ ወዴገነ ትዕይንቶ እስከ አኀለቀ አሕዛቢሁ ወሞተ ኵሉ ትዕይንተ ሲሳራ በአፈ ሐፂን ወኢተርፈ ወኢአሐዱ ፣

ባርቅም የሲሳራን ሠራዊት እስኪያጠፋ ድረስ ሠራዊቱንና ሠረገላውን ተከትሎ ሄደ ፣ የሲሳራ

www.ethiopianorthodox.org

ወገን የሆነ ሁሉ በጦር እየተወጋ በሰይፍ እየተመታ ሞተ ፤ ከሠራዊቱ አንድስ እንኳ ከሞት አልቀረም ፡፡ አንድም ከባርቅ ሠራዊት አንድስ እንኳ ከጦር አልቀረም ፡፡

፲፯፡ ወሲሳራሰ ጐየ በእግሩ ውስተ ትዕይንተ ኢያኤል ብእሲተ ኮቤር ካልዑ ለቄኔው እስመ ሰላም ውእቱ ማዕከሎሙ ለኢያቢን ንጉሠ ሶርያ ወማዕከለ ቤተ ኮቤር ቄንያዊ ፤

ሲሳራ ግን በእግሩ ሸሽቶ የቄኔው ወዳጅ ወይም ወንድም ከሚሆን ከኮቤር ሚስት ከኢያኤል ድንኳን (ሠፈር) ገባ፣ በሶርያው ንጉሥ በኢያሚንና በቄንያው ሰው በኮቤር ወገን መካከል ፍቅር ነበርና «የወዳጅ ወዳጅ ወንዝ ያሻግራል» እንዲሉ የጌታዬ ወዳጅ ከሞት ያድነኛል መስሎት ፡፡

፲፰፡ ወወፅአት ኢያኤል ወተቀበለቶ ለሲሳራ ወትቤሎ ገኀሥ እግዚእየ ኀቤየ ወኢትፍራህ ወግኀሠ ኀቤሃ ውስተ ደብተራሃ ወከደነቶ ሠቀ ፤

ኢያኤልም ሲሳራን ሲመጣ አይታ ወጥታ ተቀብላ ጌታዬ ወደ እኔ ግባ አይዞህ ምሥጢር ታወጣብኛለች ብለህም አትፍራ አለችው ፤ ሲሳራም እሷ ወደ አለችበት ድንኳን ገባ፣ ከልብሱ ተራቁቶ ብታየው ማቅ አለበሰችው ፡፡ አንድም ሠራዊቱ አልቀውበት አዝኗልና ልብሰ ኀዘን አለበሰችው ፡፡

፲፱፡ ወይቤላ ሲሳራ አስትይኒ ንስቲተ ማየ እስመ ጸማእኩ ወፈትሐት ሣዕረ ሐሊብ ወአስተየቶ ወከደነቶ ገጾ ፤

ሲሳራም ጠምቶኛልና ጥቂት ውሃ አጠጭኝ አላት፣ እሷም የወተቱን ጮጮ (ቋጫውን) ከፍታ አጠጣችው፣ የደከመው ሰው እህል ውሃ ሲቀምስ እንቅልፍ እንቅልፍ ይለዋልና ዝሎ እንዲተኛ ወይም እንዲያሳልበው ብላ ያለበሰችውን ማቅ አከናነበችው ፡፡

፳፡ ወይቤላ ቁሚ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ወእመቦ ዘመጽአ ኀቤኪ ወይቤለኪ ህለወኑ ዝየ ብእሲ በሊ አልቦ ወከደነቶ ሠቀ ፤

ሲሳራም ኢያኤልን ከድንኳኑ ደጃፍ ቁመሽ ሰው ወደ አንቺ መጥቶ ከዚህ የመጣ ሰው አለን ቢልሽ የለም ብለሽ መልሽው አላት እሷም ያንኑ ማቅ ደራርባ አለበሰችው ፡፡

፳፩፡ ወነሥአት ኢያኤል ብእሲተ ኮቤር መትክለ ደብተራ ወዕብነ በካልዕት እዴሃ ወቦአት ወጸቀወቶ ወተከለት ውእተ መትክለ ውስተ መልታሕቱ ወጐድአቶ እስከ ደመረቶ



ምስለ ምድር ወተራገጸ ውእቱ ማዕከለ እገሪሃ ወተሰጥሐ ወሞተ ፤

የኮቤር ሚስት ኢያኤልም የድንኳኑን ካስማ ነቅላ በግራ እጇ ካስማውን፣ በቀኝ እጇ ደንጊያውን ይዛ ገብታ ዓይነ ስቡን ከምድር ጋር ቀላቅላ ወጋችው፣ ሲሳራም በእግሯ መካከል ተንፈራገጠ ሞተ ፡፡ አንድም የእንግሊሳ ተንዘራግቶ ሞተ ፡፡

፳፪፡ ወበጽሐ ባርቅ እንዘ ይዴግኖ ለሲሳራ ወመጽአት ኢያኤል ወተቀበለቶ ለባርቅ ወትቤሎ ነዓ አርኢከ ብእሲ ዘተኀሥሥ ፤

ባርቅም ሲሳራን ተከታትሎት ደረሰ፣ ኢያኤልም ግዳይ ለማሳየት ወጥታ ባርቅን ተቀብላ የምትፈልገውን ሰው ና ላሳይህ አለችው ፡፡

ወቦአ ኀቤሃ ወረከቦ ለሲሳራ ውዱቀ በድኖ ወመትከል ውስተ መልታሕቱ ፤

ባርቅም ተከትሏት ቢገባ ሲሳራን ዓይነ ስቡ በካስማ ተወግቶ ሬሳው ከመሬት ወድቆ አገኘው ፡፡

፳፫፡ ወአኅሠሮ እግዚአብሔር ለኢያሚን ንጉሠ ከነዓን በይእቲ ዕለት በቅድሜሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ፤

እግዚአብሔርም በዚያች ቀን የከነዓን ንጉሥ ኢያሚንን በእስራኤል ልጆች ፊት አጐሰቈለው (አዋረደው) ፡፡ (ሐተታ) የጠፉ ቢትወደዱና ሠራዊቱ አይደለም? ስለምን እሱን አኀሠሮ አለ ቢሉ የሠራዊቱ ጥፋት የንጉሡ ኀሣር ነውና ፡፡

፳፬፡ ወሖረት እዴሁ ለእግዚአብሔር ምስለ ደቂቀ እስራኤል ወጸንዓት ላዕለ ኢያሚን ንጉሠ ከነዓን እስከ አጥፍኦ ፤

የእግዚአብሔርም ሥልጣን (ኃይል) ከእስራኤል ልጆች ጋር ጸንታ ኖረች ፤ በከነዓን ንጉሥ በኢያሚን ላይም ፈጽሞ እስኪያጠፋው ድረስ ጸናች ፡፡

## ምዕራፍ ፭

፩፡ ወነለየት ዲቦራ በይእቲ ዕለት ቅድመ ባርቅ ወትቤ እንዘ ተሐሊ ፤

ዲቦራም ሲሳራ በሞተባት ቀን ከባርቅ ፊት እየጮኸች አመሰገነች ፡፡ አንድም ባርቅ እያያት እየዘፈነች አመሰገነች ፤ የምስጋና ዘፈን አለና እንደ ዓውደ ዓመት ካህን «ውነለዩ ባርቅ ወዲቦራ» የሚል አብነት ይገኛል ፤ ባርቅና ዲቦራ ሲሳራ በሞተባት ቀን ባንድነት አመሰገኑ ፡፡

፪፡ ሶበ አኀዙ መሳፍንተ እስራኤል በሕሊና ሕዝብ ይባርክዎ ለእግዚአብሔር ፤

በ በግዕዝ ቦታ የገባ ነው፣ የእስራኤል ሹማምንት የሕዝቡን

www.ethiopianorthodox.org

ልቡና በያዙ ጊዜ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል ፣ የዕገሌን ልቡና ይገዞዋለሁ እንዲሉ ፤ አንድም አሕዛብን አጥፍተው የጠላቶቻቸውን አገር በያዙ ጊዜ በሕዝቡ ተገብተው እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል ፤

፫፡ ስምዑ ነገሥት ወአጽምዑ መኳንንት ጽኑዓን ፣

ከሞት የቀራችሁ የአሕዛብ ነገሥታት እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገላቸውን ቸርነት ስሙ ፣ ኃያላን የምትሆኑ መኳንንቱም አድምጡ ፤

ወአንሰ አነዝኩ አነሊ ለእግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ፣

አንቺሳ ምን አደረግሽ ? ትሉኝ እንደሆነ እኔስ ባደረገልኝ ቸርነት ለእስራኤል ፈጣሪ ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀርባለሁ ፤

፬፡ እግዚኦ በጸአትከ እምነሴይር ሶበ ተንሣእከ እምሐቅለ ኤዶም ምድር አድለቅለቀት ወሰማይኒ ደንገፀት ወደመናት አንጠብጠቡ ማየ ፣

«በጸአትከና ሶበ ተንሣእከ ፣ እምነ ሴይርና እምሐቅለ ኤዶም አንድ ወገን፣ ሳባዖቿ ለእስራኤል የተደረገላቸውን ተአምራት እያነሣች ታመሰግናለች ፣ አቤቱ ወገኖችህ እስራኤልን ከግብፅ ይዘህ በወጣህ ጊዜ ፤ አንድም በሙሴ በአሮን አድረህ ከሥዋሬ በተገለጽኸ ጊዜ ምድረ ግብፅ ተነዋወጠች ማለት ፣ ተሳቦ ፣ ቀንዳማ ትል ፣ ዛጒል ልብሱ አወጣች ፣ ሰማይ ደነገጠች፣ ደመናትም ውሃን አንጠበጠቡ አለ አስገኙ ፣ እሳትና በረድ አንድ ሁኖ ዘንሟልና ፤ (ሐተታ) እንደ አሪት ዘፀአት ፤ ዘፀ. ም. ፲፬ቁ.፳፫ ፤

፭፡ ወአድባርኒ ተከውሱ እምቅድመ እግዚአብሔር ዝንቱኒ ሲና እምቅድመ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ፣

ተራሮች ከእግዚአብሔር መገለጽ የተነሣ ተነዋወጡ ፣ ይህም ደብረ ሲና በእስራኤል ፈጣሪ በእግዚአብሔር ፊት ተነዋወጠ፣ ደብረ ሲና ሲነዋወጥ ከበታቹ ያሉ ጥቃቅኑ ተራሮች ሁሉ ተነዋውጠዋልና ፤ አንድም ንጉሡ ድል ከመሆኑ የተነሣ መኳንንቱ ሁሉ ድል ሆኑ ፣ ንጉሡ ከወደቀ ሠራዊቱ አይቆምምና ፤

፮፡ በመዋዕለ ሴሜጌር ወልደ ቄኔት ወበመዋዕለ ኢያኤል ኀልቁ ነገሥት ወሖሩ ፍና መብእሰ ወፍናዋተ ግፍቱዓተ ፣

በቄኔት ልጅ በሴሜጌር እና በኢያኤል ዘመን ነገሥታቱ አለቁ ፣ በተሰነካከለና ግልብጥ ብጥ ባለ ጐዳና ሔዱ ፣ ማለት ጽኑ መከራ ተቀበሉ ሴሜጌርን



ከዚያ ወልደ ሐናት ከዚህ ወልደ ቄኔት አለው አይጣላም ? ቢሉ አይጣላም ፣ ላንድ ሰው ሁለት ስም አለው፣ አንዱ ያባቱ አንዱ ያያቱ ፤ አንድም አንዱ የወለደው አንዱ ያሳደገው ነው ፤

፯፡ ወኀልቁ መፈክራን እምእስራኤል እስከ ተንሥአት ዲቦራ ወቆመት እመ ለእስራኤል ፣

ዲቦራም (በናትነት በመስፍንነት) እስክትነሣ ድረስ ከእስራኤል ገድለው ሰልበው የሚያገሩ የሚደነፉ አርበኞች ጠፉ ፤ አንድም ዲቦራ በነቢይነት እስክትነሣ ድረስ ከእስራኤል ኃላፍያትን መጻእያትን የሚናገሩ ካህናት ጠፉ ፤

፰፡ ወሠምሩ በአማልክተ ከንቱ ከመ ኀብስተ ሰገም ሶበ ይከድንዎ ውእቱ አርማሕ ፬ቱ ፻ አርማሐ ልብያስ ፣

ዲቦራ በነቢይነት እስክትነሣ ድረስ እስራኤል ከንቱ የሆኑ ጣዖታትን ወደዱ፣ ስለዚህም አርማሕና አርማሐ አንድ ወገን፣ የገብስ እንጀራ (አንባሻ) ሞግዱን በገጠሙት ጊዜ አርሮ ከስሎ እንዲገኝ አራት እልፍ አርበኞች ጠፉ ፤ አንድም እየራሱ ለማውጣት ዘአርማሐ ልብያስ ይላል ፣ ባለ ሽፈፍ ዘገር ያላቸው አራት እልፍ አርበኞች ጠፉ ፤ አንድም በኃያላኑ ጦር ጠፉ ፤

፱፡ ውስተ ዘተአዘዘ ለእስራኤል ኃያላኒሆሙ ለእስራኤል ባርክዎ ለእግዚአብሔር ፣

ለእስራኤል ረዳት (አጋዥ) ሁኖ በአሕዛብ በታዘዘው መቅሠፍት የእስራኤል አርበኞች እግዚአብሔርን አመስግኑት ፤

፲፡ እለ ትጼዕኑ ላዕለ አዕዱግ ዕዕድዋን ወትነብሩ ውስተ ብርሃን ንብቡ ቃለክሙ ፣

በነጫጭ አህዮች (በቅሎች) የምትቀመጡ በብርሃን ረድኤቱ ተጠብቃችሁ የምትኖሩ እስራኤል ምስጋናችሁን አቅርቡ ፤

፲፩፡ ወሰንቅዉ ማዕከለ ብዙኃን ወበህየ ይሁቡ ጽድቀ ለእግዚአብሔር ጽድቀ ወጽንዓ በውስተ እስራኤል ፣

ደስ ብሏቸው በሚኖሩ በብዙ ወገኖቻችሁ መካከል መሰንቆን ምቱ ፤ አንድም ንቅዉ ይላል ፣ እየጮሃችሁ አመስግኑ በእስራኤልም ዘንድ ባደረገው ተአምራት በእውነት የሚገባ ምስጋናን በየቦታው ለእግዚአብሔር ያቀርባሉ ፤

ወይእተ አሚረ ወረደ ውስተ አህጉሪሁ ሕዝበ እግዚአብሔር ፣

አህጉሪሁ ለሲሳራ ነው ፣ ሲሳራ በጠፋ ጊዜ ሕዝበ እግዚአብሔር

www.ethiopianorthodox.org

እስራኤል ወደ ሲሳራ አገር ወረደ ፤ አንድም ሲሳራ ከጠፋ በኋላ የእግዚአብሔር ወገን እስ ራኤል በየርስቱ ሒዶ ተቀ መጠ ፤

፲፪፤ ተንሥኢ ዲቦራ ወአንሥኢ አዕ ላፈ ምስለ ሕዝብ ተንሥኢ ተንሥኢ ምስለ ማኅሌት ፤

ዲቦራ አእላፈ ንፍታሌምን ከአ እላፈ ዛብሎን ጋር ይዘሽ ተነሽ ፤ ከምስጋና ጋር ፈጽመሽ ተነሽ ፤ አንድም እያመሰገንሽ ተነሽ ፤

ወበኃይል ተንሥእ ባርቅ ወአጽንኢዮ ዲቦራ ለባርቅ ወዔውው ዔዋከ ባርቅ ወልደ አቤኔሂም ከመ አመ አብየ ኃይሉ ፤

ባርቅም በኃይል ተነሥ ፤ ዲቦ ራም ባርቅን አጽኝው ፤ የአቤ ኔሂም ልጅ ባርቅም የእግዚአ ብሔር ኃይሉ በተገለጠ ጊዜ እንደተገለጠ መጠን ምርኮህን ማርክ ፤ «እግዚአ አድክሞሙ ማንሻ» ፤ አንድም የእግዚአብ ሔር ኃይል በተገለጠ ጊዜ ግብ ፃውያንን እንዳደከምክ ፤

፲፫፤ እግዚአ አድክሞሙ ሊተ ለእለ ይጸንዑኒ ፤

አቤቱ የሚበረታቱብኝ እለ ሲሳ ራን አድክምልኝ (አድክመህ አጥፋልኝ) ፤

፲፬፤ ሕዝበ ኤፍሬም ወቀሠፎሙ በውስተ ቈላት እጉከ ፤

«ምንተ ኮንከ ያለበት ነው» ነገደ ኤፍሬም ምን ሆንክ ? ወን ድምህ ዛብሎን ወንድምህ ንፍ ታሌም እለ ሲሳራን በቈላ ውስጥ አጠፋቸው፤ አንተ ምን ሁነህ ቀረህ ?፤

ብንያም በሕዝብከ እምነ ማኪር ወረዱ ይፍትኑ ፤

«አኃፍር ያለበት ነው» ብንያም በወገንህ አፍራለሁ ፤ ከማኪር ወገን ይዘርፉ ይማርኩ ዘንድ ወረዱ አንተ ግን በመቅረትህ አፍራለሁ ፤

ወእምዛብሎን እግዚአብሔር ይጸብእ ሊተ ወእምኃያላን እምህየ ወትረ በኃይለ ነገር ፤

ለኔስ እግዚአብሔር ከዛብሎ ንና ከንፍታሌም ወገን በኃያ ላኑ አድሮ ዘወትር በሚነገረው ኃይሉ በደብረ ታቦር ድል ይነ ሣልኛል ፤

፲፭፤ ወእምውስተ ይሣኮር ምስለ ዲቦራ ፈነወ አጋሪኒሁ ከመ ትንበር አንተ ማዕከለ ከናፍር ፤

ከነገደ ይሣኮርም ውስጥ ዓርበ ኞችን ከዲቦራ ጋር ወደ ቈላ ላከ ፤ ብንያም ምላስ በከንፈር መካከል እንዲኖር አንተ በይ



ሁዳና በስምዖን ዕጣ መካከል ትኖር ዘንድ ፤

ወሰፍሐ በእገሪሁ ነፍቆ ሮቤል ዓቢይ ጥይቅና ልቡ ፤

እግሩን ከአልጋው ዘርግቶ አን ድም ነፊቆ ይላል እግሩን አን ፈራጥጠ ዘርግቶ ለምን ቀረ ? «ልቡ ለሮቤል ሲል ነው» የሮ ቤል የልቡናው ዕውቀት ደገኛ ነበር ፤ ወንድሙ ዮሴፍን ለጊ ዜው ከወንድሞቹ አድኖት ነበ ርና ፤

፲፮፤ ወለምንት ለከ ትነብር ውስተ መስፈ·ተም ከመ ታጽምዕ ከመ ይት ፋጸዩ እለ ይነሥኡ ከመ ይኅልፉ ውስተ ዘሮቤል ፤

የምትሰፋ ሴት በቤት እንድት ውል በቤት ትውል ዘንድ ለምን ቀረህ ? መስፈትም ካሉ ሰዎች ጋር ትኖር ዘንድ ለምን ቀረህ ? ድል ነሥተው የሚመለሱ ሰዎች በሮቤል ዕጣ ውስጥ ሲአልፉ ፤ አንድም ገድለው ማርከው ሲአ ገሩ ሲደነፉ ትሰማ ዘንድ ለምን ቀረህ ?

፲፯፤ ዓቢይ ዓሥረ ልቡ ለጋድ ውስተ ማዕዶተ ዮርዳኖስ ኀደረ ወዳን ለም ንት ይነብር ውስተ አሕማር ፤

ጋድ የልቡ ዕውቀት ታላቅ ነበር ፤ ታላቅ ሲሆን በዮርዳ ኖስ ማዶ ለምን ቀረ ? ነገደ ዳንም መርከብ በወደብ እንዲ ኖር በጽንፈ ባሕር ባለ አገሩ ለምን ቀረ ?

ወአሴርሰ ነበረ ውስተ ሐይቀ ባሕር ወውስተ ወሰኑ ነበረ ፤

አሴርስ በባሕር ዳርቻ ባለ ሀገሩ ተቀመጠ ፤

፲፰፤ ዛብሎን ዘአየረ ነፍሶ ለሞት ወንፍታሌም ውስተ መልዕልተ ሐቅል ፤

መጠወ ሲል ነው፤ አልሰማሁም እንዳይልም ሰውነቱን ለሞት አሳልፎ የሰጠ ነገደ ዛብሎን በወሰኑ ነበር ፤ ነገደ ንፍታሌ ምም ከበላዩ ባለ ምድረ በዳ አገሩ ነበር እነሱ ሲሔዱ እያየ ለምን ቀረ ?

፲፱፤ ወመጽኡ ነገሥት ወተቃተሉ ይእተ አሚረ ተቃተሉ ነገሥተ ከነ ዓን በቶናህ በኀበ ማየ መጊዶ ወኢ ነሥኡ በትዕግልት ብሩረ ፤

ነገሥትና ነገሥተ ከነዓን አንድ ወገን ፤ እነባርቅ በዘመቱ ጊዜ የከነዓን ነገሥታት እነሲሳራ የሚ ጊዶ ውሃ በሚፈስበት በቶናህ መጥተው ተዋጉ ፤ ያለፈውን መናገር ነው ፤ ማየ መጊዶ ማየ ሥራዊ ማየ ድምሳሴ ሲል ነው ፤ ሲሳራን ከንጉሡ አስጠግቶ ነገ ሥት አለ ፤ አንድም አብረውት የዘመቱ ጥቃቅን ነገሥታት

www.ethiopianorthodox.org

አሉና እነ ሲሳራ ድል ከሆኑ በኋላም ባርቅ ወርቅ ብር ዘርፎ አልወሰደም ፤ በመጸየፍ ነው ፤

፳፡ ወበሰማይ ተጻብኡ ከዋክብት እምቀትሎሙ ወተቃተሉ ምስለ ሲሳራ ፤

ከእስራኤል ሰልፍ የተነሣ እን ኳን ሰው በሰማይ ያሉ ከዋክብት ሰልፍ አደረጉ ከሲሳራ ጋርም ተዋጉ ፤ (ሐተታ) ዲቦራ ቀኖና ገብታ ቃለ እግአብሔር ብት ጠይቅ በጽንፈ እስራኤል እና በጽንፈ አሕዛብ ያሉ ከዋክብት ሰልፍ አድርገው ሲዋጉ በእስራ ኤል በኩል ያሉ ከዋክብት በአ ሕዛብ በኩል ያሉትን ከዋክብት ድል ሲያደርጓቸው ታይተዋል ፤ እስራኤል አሕዛብን ድል ለማ ድረጋቸው ምሳሌ ፤ አንድም ከነባርቅ ሰልፍ የተነሣ በሰማይ ያሉ መላእክት ከነሲሳራ ጋር ተዋጉ ፤ በእስራኤል ሠራዊት አድረው መረዳታቸውን መና ገር ነው ፤ አንድም ከዋክብት እስራኤል ከሰልፋቸው ጽናት የተነሣ ከሲሳራ ጋር ተዋጉ ፤

፳፩፡ አውጽአሙ ፈለገ ቂሶን ወፈ ለገ ቴሂሜን ወተቃተሉ በፈለገ ቂሶን ነፍስየ ጽንዒ ፤

ወደ ቴሂሜንና ወደ ቂሶን ወንዝ አወጣቸው፤ በቂሶን ወንዝ ተዋጉ ማለት ቴሂሜን ከሚባል ወንዝ አውጥቶ በቂሶን ወንዝ ሲደርስ ተዋግቶ ድል ነሳው ፤ ሰውነቴ በልተሽ ጠጥተሽ ጸንተሽ ኑሪ ከዚያ አስቀድሞ በትህርምት ነበረችና ፤

፳፪፡ ወይእተ አሚረ ተቀጥቀጠ ሰኩና አፍራሲሆሙ ለአምዳሮት ወኃ ያላኒሁ ለማዠር ይረግምዎ ፤

ያን ጊዜም ጽኑዓን የሆኑ ሰዎች የፈረሶቻቸው ሰኰና አኅበኅበ (ተሰባበረ) ፤ አንድም ምድር ያለ ውን ሲያበዛ አምዳሮት ይላልና ከምድሩ ጽናት የተነሣ የፈረሶ ቻቸው ሰኰና እየወለቀ ወደቀ ፤ የሲሳራም ዓርበኞች ጣዖቱን ይረ ግሙት ነበረ፤ ላያድነን እንዴት አመለክነው እያሉ ፤

፳፫፡ ወይቤ መልአከ እግዚአብሔር በመርገም ርግምዎሙ ለእለ ውስተ አብያቲሃ እስመ ኢመጽኡ ውስተ ረድኤተ እግዚአብሔር እመስተቃ ትላን ጽኑዓን ፤

የእግዚአብሔር መልአክም በየ ቤታቸው የቀሩ ሕዝቡን እርገ ምዋቸው አለ ፤ ጽኑዓን ከሚሆኑ ከዛብሎንና ከንፍታሌም ነገድ ጋር እግዚአብሔር ወደሚያደ ርገው ረድኤት ፤ አንድም የእ ግዚአብሔር ረድኤት ወደተገለ ጠበት ቦታ አልመጡምና ፤



፳፬፡ ቡርክተ ትኩን እምአንስት ኢያ ኤል ብእሲተ ክቤር ቄንያዊ እምነ አንስት ቡርክት ፤

ቡርክትና ቡርክት አንድ ወገን፤ የቄንያው ሰው የከቤር ሚስት ኢያኤል ከሴቶች ተለይታ የከ በረች የተባረከች ትሁን ፤ አን ድም ከሴቶች ወገን ቡርክት የምትሆን የከቤር ሚስት ኢያ ኤል ከሴቶች ተለይታ የተባረ ከች ትሁን ፤

፳፭፡ በውስተ ደብተራ ማየ ሰአላ ወሐሊበ ወሀበቶ ወበዓይገን ዓቢይ አቅረበት ሎቱ ዕቋነ ፤

ምን አደረገች ትለኝ እንደሆነ በድንኳኗ ውስጥ ውሃ ቢለም ናት ወተት ሰጠችው፤ ምግብም ቢለምናት በታላቅ መንቀል እርጎ (ወገሚት) አቀረበችለት ፤

፳፮፡ ወበእዴሃ እንተ ጸጋም ተመጠ ወት መትክለ ወበየማና ጉድዓት ወቀ ተለቶ ለሲሳራ ወቀጥቀጠቶ ርእሶ ወደመቀቶ መልታሕቶ ፤

በግራ እጇ ካስማውን ተቀብላ በቀኝ እጇ ከመሬት መትታ ሲሳራን ገደለችው ፤ ራሱን ከሰ ከሰችው ፤ ጉንጩንም ጨፈለ ቀችው ፤

፳፯፡ ወተራገጸ በማዕከለ እገሪሃ ወበ ነበ ተራገጸ በህየ ኀሥረ ፤

በእግሯ መካከል ተንፈራገጠ በተንፈራፈረበት ቦታም ሬሣ ሸሸ ጣለ ፤

፳፰፡ ወእንተ መስኮት ትሔውጽ እሙ ለሲሳራ እንተ ሰቅሰቅ ትሬኢ እመቦ ዘገብአ እምነበ ሲሳራ ፤

እንተ መስኮትና እንተ ሰቅሰቅ ፤ ትሔውጽና ትሬኢ አንድ ወገን ነው ፤ የሲሳራም እናት ይህን ጊዜ ከሲሳራ ዘንድ የተመለሰ ሰው እንዳለ ብላ በመስኮት ትጎ በኝ ይሆናል ፤

ወበበይነ ምንት ተድኀረ ሠረገላሁ ለሲሳራ በጺሐ ወበበይነ ምንት ጉን ደየ እግረ ሠረገላሁ ጠቢባት ፤

ቀሲሳት ክውዋት ሲል ነው ፤ የሲሳራ ሠረገላ ወደ እሷ ከመ ድረስ ስለምን ዘገየ ? ፈጣን ፈጣን የሆኑ የሠረገላዎቹ እግ ርስ ወደ ቤቱ ከመመለስ ስለ ምን ወደ ኋላ አለ ትል ይሆ ናል ፤

፳፱፡ ወላእካቲሃ ላቲ አውሥአሃ ወእ ማንቱስ አውሥአሃ በከመ ቃላ ፤

ላእካቲሃ ያሉዋን እማንቱ ብሎ አጸፈ ፤ ገረዶቿም እንደ ቃሏ መለሱላት ማለት እሷ እንደም ታስበው በጎውን ነገር መለሱ ላት ፤

፴፡ አኮኑ ረከብዎ እንዘ ይከፍል ምህ ርካ ወይትአረክ አእርክተ በላዕለ አርእስቲሆሙ ለኃያላን ፤

ብዙ ምርኮ አግኝቷል እና ያን ሲከፍል የኃያላኑንም ቸብቸቦ

www.ethiopianorthodox.org

ቆርጦ ግዳይ እያስጣለ ወዳጅ ይገዛ ይሆናል ፤

ወበርበረ ውእቱ ሲሳራ በርበረ ኅብር ወዘዘዚአሁ ጥምዓተ ኅበሪሁ ወአሥቅ ውስተ ክሣዱ ዘበርበረ ፤

አለባበሱ አጠላለቁ ወይም አወ ላለቁ ልዩ ልዩ የሚሆን ሽልማት ሲሰጥ ይሆናል፤ እሱም አራት ኅብር አምስተኛ ወርቀ ዘቦ ያለ በት ግምጃ ባንገቱ ሲያጠልቅ ይሆናል የዘገየ እያሉ ይመል ሱላት ይሆናል ፤

፴፩፡ ከማሁ ለይትኀጐሉ ኵሎሙ ፀርከ እግዚኦ ወእለሰ ያፈቅሩከ ከመ ሠርቀ ፀሐይ በኃይሉ ፤

አቤቱ አንተን የማይወዱ ጠላ ቶችህ (አንተን የማያመልኩ ጠላ ቶችህ) ሁሉ ሲሳራ እንደ ጠፋ ይጥፉ፤ አንተን የሚወዱህ (የሚ ያመልኩህ) ግን ፀሐይ በብር ሃኑ ጸንቶ እንዲኖር በተድላ በደ ስታ ጸንተው በረድኤት ተጠብ ቀው ይኑሩ ፤

ወአዕረፈት ምድር ፵ ዓመተ ፤

ምድረ ኢየሩሳሌምም ሲሳራ ከጠፋ በኋላ አርባ ዘመን ለአ ሕዛብ ከመገዛት አረፈች ፤ አን ድም ጠላት ጠፍቶላት መከራዋ ርቆላት ተዘልላ ኖረች ።

# ምዕራፍ ፮

## ጉባዔ

፩፡ ወገብሩ ደቂቀ እስራኤል እኩየ ቅድመ እግዚአብሔር ወአግብአሙ እግዚአብሔር ውስተ እደ ምድያም ፯ተ ዓመተ ፤

ዲቦራ ከሞተች በኋላ የእስራ ኤል ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገር አደረጉ ማለት ኃጢአት ሠሩ፤ ጣዖት አመለኩ፤ ሰባት ዓመት በምድያም ሰዎች እጅ ጣላቸው ፤

፪፡ ወጸንዓት እዴሆሙ ለምድያም ላዕለ እስራኤል ወገብሩ ሎሙ ደቂቀ እስራኤል እምቅድመ ምድያም በዓ ታተ ወአጽዋናተ ውስተ አድባር ወው ስተ አጽዳፍ ፤

በዓታተ ውስተ አጽዳፍ ወአጽ ዋናተ ውስተ አድባር ነው ፤ የእስራኤልም ልጆች ከምድያም ሰዎች ፊት የሚድኑበት በየተ ራራው አምባ ፤ በየገደሉ ዋሻ አበጁ ፤

፫፡ ወእምዝ ሶበ ይዘርኡ ሰብአ እስ ራኤል የዐርጉ ምድያም ወአማሌቅ ወደቂቀ ጽባሕ የዐርጉ ላዕሌሆሙ ፤

ከዚህ በኋላ እስራኤል ዘር በሚ ዘሩበት ጊዜ የምድያም ሰዎች በምሥራቅና በምዕራብ ያሉ አሕዛብን አስከትለው የተዘራ ውን ዘር ለማጥፋት በእስራኤል ላይ ይዘምታሉ ፤



፬፡ ወይትዓየኑ ዲቤሆሙ ወያማስኑ ፍሬ ገራውሂሆሙ እስከ ይበጽሑ ውስተ ጋዛ ፤

ዘምተውም ጋዛ እስኪደርሱ ድረስ በተዘራው እርሻቸው ላይ ሠፍረው የበቀለውን ለመንጋ አብልተው ያልበቀለውን አስ ጠቅጥቀው ያጠፉባቸዋል ፤

ወኢያትረፉ ሎሙ ወኢምንተኒ በዘ የሐይዉ ለእስራኤል ወመራዕይሆ ሙኒ ወላሕሞሙኒ ወአድጎሙኒ ፤

እስራኤል ከችግር በሚድኑ ገን ዘብ የሚድኑበት እህል ምንም አላስቀሩላቸውም የላሞቻቸው ንና የአህዮቻቸውንም መንጋ አይተዉላቸውም ነበር ፤

፭፡ እስመ የዐርጉ ላዕሌሆሙ እሙ ንቱ ወእንስሳሆሙ ወተዓይኒሆሙ ያመጽኡ ወይበጽሕዎሙ ወከመ አን በጣ ብዙኖሙ ፤

የምድያም ሰዎች በእስራኤል ላይ ከብቶቻቸውንና ሠራዊቶ ቻቸውን በብዛት ይዘው እየ መጡ ይዘምቱባቸዋልና ብዛታ ቸውም እንደ አንበጣ ሁኖ ሳያ ስቡት ይደርሱባቸው ነበር ፤

ወአልቦሙ ኍልቈ ኢእሙንቱ ወኢ አግማሊሆሙ ወይመጽኡ ውስተ ምድረ እስራኤል ከመ ያማስንዎሙ፤

ለሠራዊቶቻቸውም ለግመሎቻ ቸውም ስፍር ቍጥር አልነበራ ቸውም፤ ሰዎቹንም ሆነ አገዘመ ራቸውን ያጠፉ ዘንድ ወደ እስ ራኤል አገር ይመላለሳሉ ፤

፮፡ ወነደዩ ጥቀ እስራኤል እምቅ ድመ ምድያም ወገዓሩ ደቂቀ እስ ራኤል ኀበ እግዚአብሔር ፤

«ወኢያትረፉ ሎሙ ወኢምን ተኒ» ብሎ ነበርና እስራኤልም ከምድያም ሰዎች መምጣት የተ ነሣ እጅግ ተቸገሩ ፤ ከመከራ ውም ጽናት የተነሣ ወደ እግ ዚአብሔር ጮኹ አለቀሱ ፤

፯፡ ወሶበ ጸርሑ ደቂቀ እስራኤል ኀበ እግዚአብሔር በእንተ ምድያም ፈነወ ሎሙ እግዚአብሔር ብእሴ ነቢየ ለደቂቀ እስራኤል ፤

የእስራኤልም ልጆች በምድያም ሰዎች ምክንያት ወደ እግዚአብ ሔር በጮኹ ጊዜ እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች አንድ ነቢይ ላከላቸው በአምሳለ ሰብእ ስለ ታያቸው ነው እንጂ መልአክ ነው ፤

፰፡ ወይቤሎሙ ከመዝ ይቤ እግዚአ ብሔር አምላከ እስራኤል አነ ውእቱ ዘአውፃእኩክሙ እምግብፅ እምነ ቤተ ቅንየት ፤

እንዲህም አላቸው ለግብፃውያን ከምትገዙት አገዛዝ ከግብፅ ያወ ጣኋችሁ የእስራኤል ፈጣሪ እግ ዚአብሔር እኔ ነኝ አለ ፤

፱፡ ወአድኀንኩክሙ እምእዴሆሙ ለግብፅ ወእምኵሎሙ እለ ይሣቅዩ

ከሙ ወአውፃእክዎሙ እምቅድመ ገጽክሙ ወወሀብኩክሙ ምድሮሙ ፤

ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ከግብፃውያን እጅ መከራ ከሚያጸኑባችሁ ከአሕዛብ ሁሉ እጅ አዳንኋችሁ፤ ስብአ ከነዓንንም ከፊታችሁ አስወጥቼ ሰደድኋቸው አገራቸውንም ሰጠኋችሁ (አወረስኳችሁ) ፤

፲፤ ወእቤለክሙ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክክሙ ወኢትፍርሁ እምአማልክተ አሞሬዎን እለ እለ ትነብሩ ውስተ ምድሮሙ ወውስተ ሀገሮሙ አንትሙ ወኢሰማዕክሙ ቃልየ ፤

ፈጣሪያችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና በአገራቸው ከምትኖሩባቸው ከእሊህ ከአሞራውያን አማልክት የተነሣ አትፍሩ አልኋችሁ ፤ እናንተ ግን ነገሬን አልሰማችሁኝም ፤

፲፩፤ ወመጽአ መልአከ እግዚአብሔር ወነበረ ታሕተ ዕፅ እንተ ኤፍራታ ዘኢዮአስ አቡሁ ለኢያዝሬ ፤

የእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክም መጥቶ ከኢያዝሬ አባት ከኢዮአስ ሀገር ከኤፍራታ እንጨት ሥር ተቀመጠ ፤

ጌዴዎን ወልዱ ይዘብጥ ሥርናየ ውስተ ፩ዱ ከመ ያምሥጥ እምገጽሚሆሙ ለምድያም ፤

፲፪ ጌድዎንም ከምድያምዎች ፊት ያመልጥ ዘንድ (ያሸሽ) ዘንድ ስንዴውን እያጨደ በአውድማ ይወቃ ነበር ፤

፲፪፤ ወአስተርአዮ መልአከ እግዚአብሔር ወይቤሎ እግዚአብሔር ምስሌከ ጽኑዓ ኃይል ፤

የእግዚአብሔር መልአክም ታይቶ ጽኑዓ ኃይል ጌዴዎን እግዚአብሔር በረድኤት ካንተ ጋር አለ ፤ አንድም ጽኑዓ ኃይል እግዚአብሔር በረድኤት ካንተ ጋር አለ አለው ፤

፲፫፤ ወይቤሎ ጌዴዎን አሆ እግዚአ እግዚእየ ወእመሰ ሀለወ እግዚአብሔር ምስሌነ ለምንት ረከበተነ ኵሉ ዛቲ እኪት ፤

ጌዴዎንም አቤቱ ጌታዬ እግዚአብሔር በረድኤት ከኔ ጋር መኖሩ እሺ በጄ ይደረግልኝ ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በረድኤት ከእኛ ጋር ካለ ይህች ሁሉ መከራ ስለምን አገኘችን ?

ወአይቴ ውእቱ ኵሉ ስብሐቲሁ ዘነገሩነ አበዊነ ወይቤሉነ እምግብፅ አውፅአሙ ለአበዊነ እግዚአብሔር ወይእዜሰ ኀደገነ እግዚአብሔር ወአግብአነ ውስተ እደ ምድያም ፤

እግዚአብሔር አባቶቻችንን ከግብፅ አወጣቸው ብለው የነገሩን ተአምራቱ ሁሉ ወዴት ነው ? (ወዴት ደረሰ)፤ ዛሬ ግን እግዚአብሔር በረድኤት ተለየን ፤ ይኸውም ሊታወቅ በምድያም ሰዎች እጅ ጣለን ፤



፲፬፤ ወነጸሮ መልአከ እግዚአብሔር ወይቤሎ ሑር በኃይልከ ወታድኅኖሙ ለእስራኤል እምእደ ምድያም ወናሁ ፈነውኩከ ፤

እግዚአብሔር የላከው መልአክም አየው እስራኤልን ከምድያም ሰዎች እጅ ታድናቸዋለህና በርትተህ ሒድ ፤ አንድም ከሠራዊትህ ጋር ሒድ እነሆ አሰናብቼሃለሁ አለው ፤

፲፭፤ ወይቤሎ ጌዴዎን አሆ እግዚአ በምንት አድኅኖሙ ለእስራኤል ናሁ አእላፍየኒ ውሑዳን በውስተ ምናሴ ወአነኒ ንኡስ በውስተ ቤተ አቡየ ፤

ጌዴዎንም አቤቱ እሺ በጄ እሔዳለሁ ፤ ነገር ግን እስራኤልን በምን አድናቸዋለሁ ? አለው ፤ እንዲያድናቸውስ ነግሮታል ብሎ እስራኤልን እንዳድናቸው ምልክቱ ምንድን ነው ? አለው፤ እነሆ በነገደ ምናሴ ውስጥ ያሉ ወገኖቼ ጥቂት ናቸውና በአባቴ ወገኖች ውስጥ ያለሁ እኔም ሕፃን ነኝና ፤

፲፮፤ ወይቤሎ መልአከ እግዚአብሔር እስመ እግዚአብሔር ሀለወ ምስሌከ ወትቀትሎሙ ለምድያም ከመ ፩ዱ ብእሲ ፤

ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክም እግዚአብሔር በረድኤት ከአንተ ጋር አለና የምድያምን ሰዎች እንደ አንድ ሰው አድርገህ ታጠፋቸዋለህ፤ አንድን ሰው ሲያጠፉት እንዲያስቸግር አያስቸግሩህም ፤ አንድም ከመሳፍንት እንደ አንዱ ሙሴ ሁነህ ታጠፋቸዋለህ አለው ፤

፲፯፤ ወይቤሎ ጌዴዎን እመረከብኩ ሞገሰ ቅድመ አዕይንቲከ ግበር ሊተ ተአምረ ከመ አንተ ውእቱ ዘትትናገር ምስሌየ ፤

ጌዴዎንም በፊትህ ባለሟልነትን አገኘሁ ፤ ከእኔ ጋር የምትናገር አንተ እንደሆንህ አውቅ ዘንድ ምልክት አድርግልኝ አለው ፤ ኢትሑር ማንሻ ፤ አንድም እውነተኛ መልአክ እንደሆንህ አውቅ ዘንድ ፤

፲፰፤ ኢትሑር እምዝየ እስከ እገብእ ኀቤከ ወአመጽእ መሥዋዕትየ ወእሰይም ቅድሜከ ወይቤሎ አነ ውእቱ ወእጸንሐከ እስከ ትገብእ ፤

መሥዋዕቱን አምጥቼ በፊትህ እንዳኖር እስክመለስ ድረስ ከዚህ አትሒድ አለው ፤ መልአኩም እውነተኛ መልአክ ነኝና እስክትመለስ ድረስ እጠብቅሃለሁ (እቆይሃለሁ) አለው ፤

፲፱፤ ወሖረ ጌዴዎን ወገብረ መሐስአ ጠሊ ወጸፍንተ ናዕት ወአንበረ ውስተ ሥጋ ውስተ ከፈር ወወደየ ደሞ ውስተ መቅጹት ወወሰደ ሎቱ ኀበ ዕፅ ወሰገደ ሎቱ ፤

ጌዴዎንም ሒዶ አንድ የፍየል ጠቦት አንድ አንባሻ ለመሥዋ

www.ethiopianorthodox.org

ዕት አዘጋጀ፣ የሠዋውንም የፍየ ሉን ሥጋ በእንቅብ ደሙን በድ ስት አድርጐ ወስዶ ከዛፍ ሥር ሳለ ሰገደለትና መሥዋዕቱን አቀረበ ፡፡

፳፡ ወይቤሎ መልአከ እግዚአብሔር ንሣእ ሥጋሁ ወኅብስተ ናዕት ወሢም ላዕለ ውእቱ ኰኵሕ ወከዓው ደሞ ወገብረ ከማሁ ፣

የእግዚአብሔር መልአክም ሥጋ ውንና ዳቦውን ከደንጊያ ላይ አኑ ረው ፣ ደሙንም በላዩ አፍስበት አለው ጌዴዎንም መልአኩ እን ዳዘዘው አደረገ ፡፡

፳፩፡ ወአልሀለ መልአከ እግዚአብ ሔር በትሮ ወለከፎ ለውእቱ ሥጋ ወለውእቱ ናዕት ወነደት እሳት እም ይእቲ ኰኵሕ ወበልአቶሙ ለውእቱ ሥጋ ወለውእቱ ናዕት ወሖረ መል አከ እግዚአብሔር እምአዕይንቲሁ ፣

መልአኩም በትሩን አንሥቶ በደንጊያው ላይ የተቀመጠውን ሥጋና ዳቦ ቢነካው ከዚያች ደን ጊያ እሳት ወጥታ ዳቦውንና ሥጋ ውን በላችለት ፡፡ መልአኩም እሳቱን ተረግጦ ጌዴዎን እያየው ዓረገ ፡፡ ሐተታ ለጊዜው «ግበር ሊተ ተአምረ» ብሎት ነበርና ምልክት ሊሆነው መሥዋዕቱ ንም እንደተቀበለለት ሲያጠይቅ ነው፣ ፍጻሜው ግን ምሳሌ ነው፣ መልአኩ የጌዴዎን፣ በትር የኩ ናተ ጌዴዎን፣ እሳት የረድኤተ እግዚአብሔር፣ ሥጋው የሰብአ ምድያም ፣ ከደንጊያው እሳት ወጥቶ መሥዋዕቱን እንደበላ ለት ጌዴዎን በእግዚአብሔር አጋዥነት ሰብአ ምድያምን የማጥፋቱ ምሳሌ ፡፡

፳፪፡ ወአእመረ ጌዴዎን ከመ መል አከ እግዚአብሔር ውእቱ ወይቤ ጌዴዎን አአኰተከ እግዚአ እስመ ርኢኩ መልአከ እግዚአብሔር ገጸ በገጽ እመውት ፣

ጌዴዎንም የእግዚአብሔር መል አክ እንደሆነ አውቆ አቤቱ ፈጣሪዬ መልአከ እግዚአብ ሔርን ፊት ለፊት አይቻለሁና አቤቱ አመሰግንሃለሁ አለ ፡ አን ድም የእግዚአብሔርን መልአክ አይቻለሁና ዘምቼ እሞታለሁ አለ ፡፡

፳፫፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ሰላም ለከ ኢትፍራህ ወኢትመውት ፣

እግዚአብሔርም ጌዴዎንን ሰላም ለአንተ ይሁን ፣ እሞታለሁ ብለ ህም አትፍራ አለው ፡፡

፳፬፡ ወነደቀ ጌዴዎን በህየ ምሥዋዐ ለእግዚአብሔር ወሰመዮ ሰላመ እግ ዚአብሔር እስከ ዛቲ ዕለት ወእንዘ ዓዲሁ ህለወ ውስተ ኤፍራታ አቡሁ ለኢያዝሪ ፣

ጌዴዎንም መልአኩ በታየበት፣ እግዚአብሔር በተነጋገረበት ቦታ ለእግዚአብሔር መሠዊያ



አበጀ፣ ቦታውንም መልአክ ያየ ሁበት እግዚአብሔርን የተነጋ ገርኩበት ቦታ ሲል፣ እስከዚች ቀን ድረስ ሰላመ እግዚአብሔር ብሎ ጠራው፣ ይኸውም የተደ ረገ የኢያዝሪ አባት ኢዮአስ ገና በኤፍራታ ሳለ ነው ፡፡

፳፭፡ ወእምዝ በይእቲ ሌሊት ይቤሎ እግዚአብሔር ንሣእ ላሕመ መግዝዓ ዘአቡከ ወካልዓ ላሕመ ዘ፯ቱ ዓመት ወንሥት ምሥዋዖ ለበዓል ዘአቡከ ወምስለ ዘላዕሌሁ ስብር ፣

በመዓልት ከተነጋገረው በኋላ እግዚአብሔር ዳግመኛ በሌሊት ከአባትህ መንጋ አንድ ገች (ፍሪዳ) ፪ኛም ፯ ዓመት የሆ ነው ላም አቅርብ አለው፣ ሰብአ ምድያም ፯ዓመት ገዝተዋቸው ነበርና አገዛዛችሁን አራቅሁላ ችሁ ሲል ነው ፣ የአባትህ ጣዖት ያለበትንም መሠዊያ አፍርስ በላዩ ላይ ያለውንም ምስል (ጣዖት) ስበረው ፡

፳፮፡ ወንድቅ ቦቱ ምሥዋዐ ለእግ ዚአብሔር አምላክከ ዘአስተርአየከ በውስተ ደብር ዘማእከ ዘበዝንቱ ደወል ወንሣእ ውእተ ካልአ ላሕመ ወግበሮ መሥዋዕተ በውእቱ ዕፅ ዘሰ በርከ ፣

በዚህ አውራጃ ባለ በማእከ ተራራ ለታየህ (ለተነጋገረህ) ለፈ ጣሪህ ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሥራ ያን ሁለተኛውንም ላም በሰበርከው በጣዖቱ መሠዊያ ላይ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርገህ አቅርበው አለው ፡፡

፳፯፡ ወነሥአ ጌዴዎን ፲ተ ወ፫ተ እደወ እምአግብርቲሁ ወገብረ በከመ ይቤሎ እግዚአብሔር ፣

ጌዴዎንም ከባለሟሎቹ (ከቤተ ሰቦቹ) ፲፫ ሰዎች መርጦ እግዚ አብሔር እንዳዘዘው አደረገ ፡

ወእምዝ ሶበ ፈርሀ ቤተ አቡሁ ወሰ ብአ ሀገሩ በዊአ መዓልተ ወሌሊተ ይበውእ ፣

ይህን ካደረገ በኋላ በመዓልት ለመግባት የአባቱን ወገኖችና የሀገሩን ሰዎች በፈራ ጊዜ በሌ ሊት ይገባ ነበር ፡

፳፰፡ ወጌሡ በጽባሕ ሰብአ ሀገሩ ወረከብዎ ንሡተ ለምሥዋዓ በዓል ወምስል ዘላዕሌሁ ስቡር ወላሕም መግዝዕ ግቡር ቦቱ መሥዋዕት በው እቱ ምሥዋዕ ዘነደቀ ፣

የሀገሩ ሰዎችም ለጣዖቱ መሥ ዋዕተ ነግህ ለማቅረብ በጧት ገሥግሠው ቢሔዱ የጣዖቱ መሠዊያ ፈርሶ በላዩ ላይ ያለው ምስል (ጣዖት) ተሰብሮ በዚያ በተሠራው በአዲሱ መሠዊያ ላይም ሌላ መሥዋዕት ተሠው ቶበት አገኙ ፡

፳፱፡ ወተበሃሉ በበይናቲሆሙ መኑ ገብረ ዘንተ ግብረ ወነሠሡ ወሐ

www.ethiopianorthodox.org

ተቱ ወይቤሉ ጌዴዎን ወልደ ዮአስ ገብረ ዘንተ ግብረ ፤

እርስ በርሳቸውም ይህን ሥራ የሠራ ማነው ? ተባብለው ዳኛ አውጥተው ፈለጉ መረመሩ፣ በኋላ ይህን ያደረገ የዮአስ ልጅ ጌዴዎን ነው ብለው ተናገሩ ፤

፴፡ ወይቤልዎ ሰብአ ሀገር ለዮአስ አምጽእ ወልደከ ይቅትልዎ እስመ ነሠተ ምሥዋዓ በዓል ወሰበረ ምስለ ከላዕሌሁ ፤

የሀገሩ ሰዎችም ዮአስን የጣዖ ቱን መሠዊያ አፍርሷልና፣ በላ ዩም ያለውን ምስል (ጣዖት) ሰብ ሯልና ይገድሉት ዘንድ ልጅ ህን አምጣ አሉት፣ ለዳኞቹ ሰጥ ተው ወይም ራሳቸውን አርቀው ይቅትልዎ አሉ ፤

፴፩፡ ወይቤሎሙ ዮአስ ለሰብእ እለ ቆሙ ላዕሌሁ አንትሙኑ ይእዜ ትት ቤቀሉ ቦቱ ለበዓል አው አንትሙኑ ታድኅንዎ ከመ ትቅትሉ ዘገፍአ ፤

ዮአስም በጠላትንት የተነሡብ ትን ሰዎች ዛሬስ ለጣዖቱ ጠላ ቱን እናንተ ልትበቀሉለት ነው ? የበደለውንም ትገድሉ ለት ዘንድ ወይስ ከጥፋት የም ታድኑት እናንተ ናችሁን ፤

ወእመሰ አምላክ ውእቱ እስከ ይጸ ብሕ ለይሙት ዘገፍአ ወይትበቀሎ ለሊሁ ለዘነሠተ ምሥዋዒሁ ፤

በውነት አምላክ ከሆነስ የበ ደለው ሰው እስኪነጋ ፈጥኖ ይሙት ፤ መሠዊያውንም ያፈ ረሰውን ሰው እሱው ተበቅሎ ያጥፋው አላቸው ፤

፴፪፡ ወሰመያ ለይቲ ዕለት ዓውደ በዓል እስመ ነሠተ ምሥዋዖ ፤

ያችንም ቀን ምሥዋዓ ጣዖቱ ስለፈረሰ ለጣዖቱ ሽንጎ የተደ ረገባት ቀን አላት ፤

፴፫፡ ወኵሉ ምድያም ወአማሌቅ ወደቂቀ ጽባሕ ተጋብኡ ላዕሌሆሙ ወዓደዉ ወነደሩ ውስተ ቈላተ ኢይ ዝራኤል ፤

ከመጀመሪያ እንደ አርእስት አንስቷቸው ነበርና አማሌቃው ያንና የምድያም ሰዎች በምሥ ራቅና በምዕራብ ያሉ አሕዛብን ሁሉ ይዘው በእስራኤል ላይ ዘመቱ፣ ከሀገራቸው ወጥተው በኢይዝራኤል ቈላ ሠፍረው አደሩ ፤

፴፬፡ ወአጽንዖ መንፈሰ እግዚአብ ሔር ለጌዴዎን ወነፍሐ ቀርነ ወወ ውዓ አብያዜር በድኅሬሁ ፤

በዚህም ቀን የእግዚአብሔር መንፈስ ረድኤት ጌዴዎንን አጸናው፣ ባለሟሉ አብያዜርም እሱን ተከትሎ ውጋ ውጋ የሚል ነጋሪት እየመታ መለከት እየ ነፋ ያወክ ይደነፋ ጀመረ ፤



፴፭፡ ወፈነወ መላእክተ ውስተ ኵሉ ምናሴ ወአውየወ ውእቱኒ እምድኅ ሬሁ ፤

ወደ ምናሴ ወገኖች ሁሉ እር ዳኝ ብሎ መልእክተኞቹን ላከ ነገደ ምናሴም ጌዴዎንን ተከ ትሎ አወካ ደነፋ ፤

ወፈነወ መላእክተ ውስተ አሴር ወው ስተ ዛብሎን ወንፍታሌም ወዐርጉ ወተቀበልዎሙ ፤

ከዚህም የጦር ስልት ወደ ለመዱ ወደ አሴር ወደ ዛብሎንና ንፍ ታሌም ወገኖች እርዱኝ ብሎ መልእክተኛ ላከ፣ እሊህም ወጥ ተው ተቀበሏቸው ፤ ሐተታ የዛ ብሎንና የንፍታሌምስ ይሁን ነገደ አሴር መቸ ጦር ለመደና እንዲህ አለ ፣ ቢሉ «ወውስተ ወሰኑ ነበረ ዛብሎን» እንዲል በነገደ ዛብሎን አስጠግቶ አነ ሣው ፤

፴፮፡ ወይቤሎ ጌዴዎን ለእግዚአብ ሔር እመ ታድኅኖሙ ለእስራኤል በእዴየ በከመ ትቤ ናሁ አነ እሰ ፍሕ ፀምረ ብዙተ ውስተ ዓውድ ፤

ጌዴዎንም እግዚአብሔርን አሁን እንደተናገርከ በእኔ አድረህ እስራኤልን የምታድናቸው ከሆነ እነሆ እኔ በአደባባይ የተባዘተ ሐር እዘረጋለሁ ፤

፴፯፡ ወእምከመ ወረደ ጠል ውስተ ፀምር በሕቲቱ ወኵሉ ምድር ይቡስ አአምር እንከ ከመ ታድኅኖሙ ለእ ስራኤል በእዴየ በከመ ትቤ ወኮነ ከማሁ ፤

ጠል በምድር ላይ ሳይወርድ በሐሩ ላይ ብቻ ቢወርድ በአ ንተ አድሬ አድናቸዋለሁ እንዳ ልክ እስራኤልን በእጄ እንድ ታድናቸው ያን ጊዜ አውቃ ለሁ አለው፣ እንዳለውም ሆነ ፤

፴፰፡ ወጌሠ ጌዴዎን በሳኒታ ወአ ጸሮ ለውእቱ ፀምር ወወፅአ ማይ እምውእቱ ፀምር ምልአ አይገን ፤

ጌዴዎንም ጠሉ በወረደ በማግ ሥቱ ገሥግሦ ሒዶ ጠል የወረ ደበትን ሐር ቢጠምቀው (ቢጨ ምቀው) ከሐሩ መንቀል ምሉ ውሃ ወጣ ፤ አንድም ወመልአ አይገነ ይላል ከሐሩ የወጣው ውሃ በመንቀል መላ ፤

፴፱፡ ወይቤሎ ጌዴዎን ለእግዚአብ ሔር ኢትትመአዕ በመዓትከ ላዕሌየ ወእንግርከ ካዕበ አሐተ ነገረ ፀምር ይኩን ይቡስ እንተ ባሕቲቱ ወው ስተ ኵሉ ምድር ይረድ ጠል ፤

ጌዴዎንም እግዚአብሔርን ስል ችተህ አትቆጣኝና ዳግመኛ አን ዲት ነገር ልንገርህ ፤ ይኸውም ሐሩ ብቻ ደረቅ ይሁንና በም ድር ሁሉ (በዙሪያው ሁሉ) ጠል ይውረድበት አለው ፤

፵፡ ወገብረ ከማሁ እግዚአብሔር በይ እቲ ሌሊት ወኮነ ይቡስ ፀምር ባሕ

www.ethiopianorthodox.org

ቲቱ ወውስተ ኵሉ ምድር ወረደ ጠል ፤

እግዚአብሔርም በዚያች ሌሊት ጌዴዎን እንደለመነው አደረገ፤ ሐሩ ብቻ ደረቅ ሁኖ በምድሩ ሁሉ ጠል ወረደበት ምሳሌ ነው፤ ፀምር የእስራኤል ፤ ጠል የረድኤት እግዚአብሔር ፤ ዙሪያው መስኩ የአሕዛብ ፤ ጠል በፀምሩ ሲወርድ ዙሪያው ደረቅ መሆኑ ለእስራኤል የወረደው ጠለ ምሕረት ለአሕዛብ አይተርፋቸውምና ፤ አንድም ጠል የመቅሠፍት እግዚአብሔር ፤ በመስኩ (በዙሪያው) ሲወርድ ፀምር ደረቅ መሆኑ በአሕዛብ የወረደ መቅሠፍት ለእስራኤል አይተርፍምና (እስራኤልን አያጠፋምና)፤ አንድም ፀምር የእመቤታችን ፤ ጠል የወልደ እግዚአብሔር ፤ ዙሪያው የሌሎች ሴቶች፤ ጠል በፀምር ላይ መውረዱ በዙሪያው አለመውረዱ ጠለ ምሕረት ወልደ እግዚአብሔርም ከእመቤታችን ሰው ለመሆኑ ፤ በዙሪያው አለመውረዱ በሌሎች ሴቶች ያለማደሩ ምሳሌ ፤ አንድም ጠል የዘርአ ብእሲ፤ በመስኩ ጠል ሲወርድ ፀምር ደረቅ መሆኑ ዘርአ ወራዙት ልማደ አንስት በሌሎች ሴቶች ሲኖር እመቤታችንን አላገኛትምና ።

## ምዕራፍ ፯

፩፡ ወጌሠ ሮብአም ዘውእቱ ጌዴዎን ወኵሉ ሕዝብ ዘምስሌሁ ወኀደሩ ውስተ ምድረ አሮኤድ ፤

ጌዴዎን የተባለ ሮብአምና ከርሱ ጋር የዘመቱ ሕዝቡም ሁሉ ገሥግሠው አሮዔር በሚባል ምድረ በዳ ሰፍረው አደሩ ፤

ወትዕይንቶሙ ለምድያም ወለአማሌቅ እመንገለ መስዕ እምሥዋዕ ዘእንበሬም ውስተ ቈላ ፤

ያማሌቅና የምድያም ሠራዊትም እንበሬም ከሚባል መሠዊያ በቀኝ በኩል በቈላ ውስጥ ሰፍሮ ነበር ፤

፪፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለጌዴዎን ብዙኅ ሕዝብ ዘምስሌከ ከመ ዘኢይክል አግብኦቶሙ ለምድያም ውስተ እዴሆሙ ፤

እግዚአብሔርም ጌዴዎንን ካንተ ጋራ ያሉ ወገኖች በጥቂት ሰው አድሬ የምድያምን ሰዎች በእጃቸው መጣል እንደማይቻለኝ አድርገው በዝተዋል ፤

ከመ ኢይትመከሑ እስራኤል ላዕሌየ ወኢይበሉ እዴነ አድኀነተነ ፤

እስራኤልም እኛ የዳንነ በሥልጣናችን ጽንዓት በጦራችን ብዛት ነው ብለው በኔ ላይ እንዳይመኩ ፤

፫፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለጌዴዎን ንግሮሙ ለሕዝብ ወበሎሙ



ዘይፈርህ እምኔክሙ ወፈራህ ለይግባእ እምነበ ሕዝብ ፤

ከናንተ ወገን የሚፈራ ሰው ቢኖር ወደሕዝቡ ይመለስ ብለህ ለሕዝቡ ንገራቸው አለው ፤

ወተመይጡ እምድረ ገለዓድ ወገብኡ እምሕዝብ ፳ቱ ፼ ወ፳፻ ወተርፉ ፼ ፤

ከገለዓድ አውራጃ ሲደርሱ እልፍ (አሥር ሺህ) ሰዎች ቀርተው ሃያ ሁለት ሺህ ሰዎች ወደ ሕዝቡ ተመለሱ ፤

፬፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለጌዴዎን ዓዲ ብዙኅ ሕዝብ አውርዶሙ ኀበ ማይ ወአመክሮሙ ለከ በህየ ወእለ አነ እቤለከ እሙንቱ ይሑሩ ምስሌከ ወአውረዶሙ ኀበ ማይ ለሕዝብ ፤

እግዚአብሔርም ዳግመኛ ጌዴዎንን አሁንም የቀሩት ሕዝብ ብዙ ናቸው እና ወደ ወንዝ አውርደህ ውሃ በመጠጣት ፈትናቸው ፤ እኔ ይሂዱ ያልኳቸው ካንተ ጋር ይሂዱ አለው ፤ እሱም (ጌዴዎንም) ሕዝቡን ወደ ወንዝ አወረዳቸው ፤

፭፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለጌዴዎን ኵሎ ዘሰትየ በልሳኑ እማይ ከመ ዘይሰቲ ከልብ አቅም እንተ ባሕቲቱ ፤

እግዚአብሔርም ጌዴዎንን ውሻ በምላሱ እየጠለፈ እንዲጠጣ በምላሱ ጠለፍ አድርጎ የሚጠጣውን ሁሉ ለብቻው አድርገህ አቁም ፤

ወኵሎ ዘአስተብረከ በብረኪሁ ከመ ይስተይ አቅም እንተ ባሕቲቱ ፤

«ከመ ላሕም ያለበት ነው» ላም ተጐንብሶ እንዲጠጣ መሣሪያውን እየጣለ (እያኖረ) ውሃ ይጠጣ ዘንድ የተንበረከከውን ሁሉ ለብቻው ለይተህ አቁም አለው ፤

፮፡ ወኮነ ኍልቆሙ ለእለ ሰትዩ በልሳኖሙ ፫ተ ፻ተ ዕደወ ፤ ወእለሰ ተርፉ ሕዝብ አስተብረኩ በብረኪሆሙ ከመ ይስተዩ ማየ ፤

በቀኝ እጃቸው መሣሪያቸውን ይዘው በግራ እጃቸው እየጠለፉ የጠጡት ሰዎች ቍጥራቸው ፫፻ ሆነ የቀሩት ሕዝብ ግን ውሃ ይጠጡ ዘንድ መሣሪያቸውን እያኖሩ ተንበረከኩ ፤

፯፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለጌዴዎን በእሉ ፫፻ ብእሲ እለ ከመዝ ሰትዩ አድኀነክሙ ወአገብኦሙ ለምድያም ውስተ እዴከ ወኵሉ ሕዝብ ይእትዉ ውስተ አብያቲሆሙ ፤

እግዚአብሔርም ጌዴዎንን በግራ እጃቸው ውሃውን ጥልፍ ጥልፍ እያደረጉ በጠጡት በ፫፻ ሰዎች አድሬ አድናችኋለሁ፤ የምድያ

www.ethiopianorthodox.org

ምንም ሰዎች በእጅህ እጥላቸዋ ለሁ ፣ የቀሩት ሕዝብ ሁሉ ግን ወደየቤታቸው ይመለሱ ፤

፰፡ ወይንሥኡ ምስሌሆሙ ስንቀ ሕዝብ ወአቅርንቲሆሙ ወለኵሉ ሰብአ እስራኤል ፈንዎሙ ውስተ አብያቲሆሙ ይእትዉ ፣

ወደ ሀገር ቤት የሚመለሱ የሕ ዝቡን ስንቅና መለከታቸውንም የሚዘምቱት ሦስቱ መቶ ሰዎች ይዘው ይሒዱ ፣ እነዚያን የእስ ራኤልንም ሰዎች ሁሉ ወደየ ቤታቸው ይገቡ ዘንድ አሰናብ ታቸው ፤

ወለእልክቱሰ ፫፻ ብእሲ አቅሞሙ ምስሌከ ወትዕይንተ ምድያም መት ሕቶሙ ውስተ ቈላ ፣

እሊህንም ሦስቱን መቶ ሰዎች ግን ለይተህ አቈያቸው አለው፣ የምድያም ሠራዊትም ከእሥራ ኤል ሠፈር በታች በቈላ ውስጥ ሠፍረው ነበር ፣ አሁን ተንሥእ ወረድ የሚል ነውና ፤

፱፡ ወእምዝ በይእቲ ሌሊት ይቤሎ እግዚአብሔር ተንሥእ ወረድ ፍጡነ እምዝየ ውስተ ትዕይንት እስመ አግ ባእክዋ ውስተ እዴከ ፣

እስራኤልን አሰናብቶ ከተመለሰ በኋላ እግዚአብሔር ጌዴዎንን በዚያች ሌሊት የምድያምን ሰዎች በእጅህ አሳልፌ ጥያቸዋ ለሁና ወደ ምድያም ሰዎች ሠፈር ፈጥነህ ውረድ ፤

፲፡ ወእመሰ ትፈርህ ባሕቲተከ ወሪደ ረድ አንተ ወፋራን ቍልዔከ ውስተ ትዕይንት ፣

ብቻህን መውረድ ብትፈራ ግን ባለሟልህ (ጋሻ ጃግሬህ) ፋራንን አስከትለህ ውረድ ፤

፲፩፡ ወአጽምእዎሙ ዘይትናገሩ ወእ ምዝ ይጸንዓ እደዊከ ፣

የማሰማችሁ ነገር አለና ከድን ኳናቸው አጠገብ ሁናችሁ የሚ ናገሩትን አድምጧቸው ፤ አን ድም አጽምየሙ ይላል ፣ የሚያ ሰማው ለሱ ነውና ነገሩን ከሰ ማህ በኋላም ቀኝ እጅህ ለመ ውጋት፣ ግራ እጅህ ለመመከት ይጸናል አለው ፤

ወወረደ ውእቱ ወፋራን ቍልዔሁ ውስተ ፩ኀብር ዘ፶ እምትዕይንት ፣

ጌዴዎንም «ረድ ፍጡነ» ብሎ ጌታ እንዳዘዘው ጋሻ ጃግሬው ፋራንን አስከትሎ ከሰብአ ምድ ያም ሠፈር አንድ ወገን የአምሳ አለቃ ወደሠፈረበት ወረደ ፤

፲፪፡ ወምድያም ወአማሌቅ ወኵ ሎሙ ደቂቀ ጽባሕ ኅዱራን እሙ ንቱ ውስተ ቈላት ከመ አንበጣ ብዝኆሙ ወአግማሊሆሙ ዘአልቦ ኍልቍ እለ ከመ ኆፃ ዘከንፈረ ባሕር እሙንቱ ብዝኆሙ ፣

ሰብአ ምድያምም በምሥራቅና በምዕራብ ያሉ አማሌቃውያንን ይዘው እንደ አንበጣ በዝተው ሠፍረው ነበር ፣



ውም ብዛት በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ የማይቈጠር ነው ፤

፲፫፡ ወቦአ ጌዴዎን ወናሁ ፩ብእሲ ይነግሮ ለካልዑ ሕልሞ ወይቤሎ ሐለምኩ ሕልመ ወእሬኢ ኅብስተ ሰገም ታንኰረኵር ውስተ ትዕይንተ ምድያም ወቀተለታ ወአውደቀታ ወገፍትዐታ እምሳዕሉ ወወድቀት ትዕይንት ፣

ጌዴዎንም ከሰብአ ምድያም ሠፈር በደረሰ ጊዜ አንድ ሰው ሕልም አይቶ ከተኛበት ተነ ሥቶ ለጓደኛው እነሆ ሕልም አየሁ ብሎ ይነግረው ጀመር፣ ጓደኛውም ምን አየህ ? ቢለው የገብስ ጥረሾ የምታህል እሳት ከተራራ ተንከባላ ወርዳ ከተማ ችንን ገልብጣ ስትጥላት ከተማ ችንም ስትጠፋ አየሁ አለው ፤

፲፬፡ ወአውሥአ ካልኡ ወይቤሎ ኢኮነ ዝንቱ እንበለ ኲናተ ጌዴዎን ወልደ ዮአስ ብእሲ እስራኤላዊ ወአ ግብአሙ እግዚአብሔር ለምድያም ውስተ እዴሁ ወለኵሉ ትዕይንቶሙ ፣

ባልንጀራውም እስራኤላዊ የሚ ሆን የዮአስ ልጅ የጌዴዎን ጦር ነው እንጂ ሌላ አይደለም፣ ገብስ የተናቀ ነው ፣ የነሱም ጦር በኛ ዘንድ የተናቀ ነውና እግዚአብ ሔርም የምድያምን ሰዎች ከተ ማቸውንም ሁሉ በእጁ አሳልፎ ጥሎለታል ፣ የእኛ ነገር አልሆ ነም ብሎ መለሰለት ፤

፲፭፡ ወእምዝ ሶበ ሰምዐ ጌዴዎን ፍካሬ ህልሙ ወዘከመ ነገሮ ሕልሞ ሰገደ ለእግዚአብሔር ወገብአ ውስተ ትዕይንተ እስራኤል ፣

ከዚህ በኋላ ጌዴዎንም አንድ ሰው ሕልም አይቶ ለባልንጀራው እንደነገረው ፣ ሕልሙንም ያ ሰው እንደተረጐመለት ፣ የሕ ልሙን ትርጓሜ በሰማ ጊዜ ይህን ያሰማኸኝ ብሎ ለእግዚ አብሔር ሰግዶ ወደ እስራኤል ሠፈር ተመለሰ ፤

ወይቤሎሙ ተንሥኡ እስመ አግብ አሙ እግዚአብሔር ውስተ እዴነ ለትዕይንተ ምድያም ፣

ተመልሶም እስራኤልን እግዚአ ብሔር የምድያምን ሰዎች በእ ጃችን ጥሏቸዋልና ተነሡ አሳ ቸው ፤

፲፮፡ ወከፈሎሙ ለ ፫፻ ብእሲ ኀበ ፫ቱ ሠራዊት ወወሀቦሙ ቀርነ ለኵ ሎሙ ውስተ እደዊሆሙ ወመሰብ ክተ እሩቃተ ወመኅትወ ውስተ ማእ ከለ ውእቱ መስብክት ፣

ሦስቱን መቶ ሰዎች በሦስት አበጋዝ (አለቃ) ከፍሎ ለሁሉም በየእጃቸው መለከት ሰጣቸው፣ ባዶ የሆኑ ማሰሮዎችንም ሰጣ ቸው ፣ በማሰሮዎቹም ውስጥ መብራት ነበር ፤

፲፯፡ ወይቤሎሙ እምኔየ ርእዩ ወከ ማሁ ግበሩ ወናሁ አነ እበውእ ውስተ

www.ethiopianorthodox.org

ማዕከለ ትዕይንት ወዘከመ ገበርኩ ግበሩ ፤

እኔን አይታችሁ (ከኔ አብነት ነሥታችሁ) እንደኔ አድርጉ አላቸው ፤ የምታደርገው ምንድነው ቢሉት እኔ ወደ ሰብአ ምድያም ሠፈር መካከል እገባለሁና ከዚያ ገብቼ የማደርገውን አድርጉ ፤

፲፰፡ ወእነፍሕ ቀርነ አነ ወኵሉ እለ ምስሌየ፤ ወንፍሑ ቀርነ አንትሙኒ በዓውደ ትዕይንት ወበሉ ኃይል ዘእግዚአብሔር ወኵናት ዘጌዴዎን ፤

እኔና ከእኔ ጋራ ያሉ ሰዎችም ሁሉ መለከት እንነፋለንና እናንተም በምድያም ሰዎች ሠፈር ዙሪያ ሁናችሁ መለከታችሁን እየነፋችሁ የእግዚአብሔር ኃይል የጌዴዎን ጦር ደረሰብህ በሉ አላቸው ፤

፲፱፡ ወቦአ ጌዴዎን ወ፻ ብእሲ ምስሌሁ ውስተ ፩ ኅብረ ትዕይንት በቀዳሚ ሰዓት ዘመንፈቀ ሌሊት እንበለ ይንቅሑ ሰብአ መዓቅብ ወነፍሑ ቀርነ ወነጽሑ እልክተ መሳብክተ ዘውስተ እደዊሆሙ ፤

ጌዴዎንም ይህን ምልክት ለሠራዊቱ ሰጥቶ መቶውን ሠራዊት አስከትሎ አልዋ (ዘብ) የሚጠብቁ ዘበኞች ሳይነቁ ከመንፈቀ ሌሊት በመጀመሪያው ሰዓት ከሰብአ ምድያም ሠፈር ወደ አንዱ ወገን ገባ፤ ከሠፈርም በገቡ ጊዜ በእጃቸው የያዙትን ማሠሮ እየጣሉ መብራቱን አብርተው ው-ጋ ው-ጋ የሚል መለከት ነፉ ፤

፳፡ ወነፍሑ ቀርነ እልክቱ ፫ቱ ሠራዊት ወነጽሑ መሳብክቲሆሙ ወአልዐሉ መኃትዊሆሙ ዘውስተ እደዊሆሙ ዘፀጋም ወዘውስተ እደዊሆሙ ዘየማን ቀርነ ዘቦቱ ይነፍሑ ወጸርሑ ወይቤሉ ኵናት ዘእግዚአብሔር ወዘጌዴዎን ፤

እነዚያም ሦስት ወገን ሁነው የተሰለፉት ሠራዊት መለከቱን ነፉ ፤ ማሠሮዎቻቸውንም እየጣሉ በግራ እጃቸው ያሉ መብራቶቻቸውን ከፍ ከፍ አደረጉ ፤ በቀኝ እጃቸውም የሚነፉትን መለከት እየነፉ ይህ የጌዴዎንና የእግዚአብሔር ሰልፍ ነው ብለው ጮኹ ደነፉ ፤

፳፩፡ ወቆሙ ኵሎሙ በበመካናቲሆሙ በውስተ ዓውደ ትዕይንት ወጕዩ ኵሉ ትዕይንት ወደንገጹ ፤

ሁሉም በሰብአ ምድያም ሠፈር ዙሪያ በያሉበት ቦታ ቁመው ደነፉ የሰብአ ምድያም ሠራዊትም ሁሉ ደንግጠው ሸሹ ፤

፳፪፡ ወነፍሑ ፫፻ተ አቅርንተ ወአግብአ እግዚአብሔር መጥባሕተ ብእሲ ላዕለ ካልዑ በውስተ ኵሉ ትዕይንት ፤

ቢርቀው ደገመው እሊህም ሦስት መቶ ሠራዊት ው-ጋ ው-ጋ



የሚል መለከት ነፉ ፤ እግዚአብሔርም በሰብአ ምድያም ሠራዊት ሁሉ ያንዱን ሾተል ባንዱ ላይ መለሰው ማለት የጌዴዎን ጦር የደረሰብኝ መስሎት አንዱ አንዱን በጦር ወግቶ በሰይፍ መትቶ የሚገድለው ሁኗል ፤

ወጕዩ ትዕይንቶሙ እስከ በሴጣ ወእስከ አቤልሜሁላ ወውስተ ገባያን ፤

ከሞት የተረፉት ሠራዊትም በገባያን ውስጥ እስካሉ እስከ በሴጣና እስከ አቤልሜሁላ ድረስ ሸሹ ፤

፳፫፡ ወአውየዉ ሰብአ እስራኤል እምንፍታሌም ወእምአሴር ወእም ኵሉ ምናሴ ወዴገንዎሙ ለምድያም ፤

ከሊህ ከሦስቱ ነገድ ተወጣጥተው የዘመቱ የእስራኤል ወገኖችም የምድያምን ሰዎች እየደነፉ ተከተሏቸው ፤ (ሐተታ) የዛብሎንና የንፍታሌም ነገድ የዘመቱ በከፊል ነውና እም በማለት ተናገራቸው ፤ ነገደ ምናሴን ኵሉ በማለት ተናገረ በብዛት ዘምተዋልና ፤

፳፬፡ ወፈነወ ጌዴዎን መልእክተ ውስተ ኵሉ ደወለ ኤፍሬም እንዘ ይብል ረዱ ተቀበልዎሙ ለምድያም ወርከብዎሙ በኀበ ማይ እስከ ቤታራ ወዮርዳኖስ ፤

ጌዴዎንም በኤፍሬም አውራጃ [illegible] የምድያምን ሰዎች ወርዳችሁ በጦርነት ተቀበሏቸው፤ እስከ ዮርዳኖስና እስከ ቤታራ ድረስ ወንዝ ለወንዝ ሂዳችሁ መሻገሪያውን ያዙባቸው ብሎ መልእክተኞችን ላከ ፤

ወአውየዉ ኵሉ ሰብአ ኤፍሬም ወቀደምዎሙ ኀበ ማይ እስከ ቤታራ ወዮርዳኖስ ፤

የኤፍሬም ነገዶችም ሁሉ መልእክቱን በሰሙ ጊዜ ደንፍተው ተነሥተው እስከ ዮርዳኖስ እና እስከ ቤታራ ድረስ ወንዝ ለወንዝ ቀደሟቸው ፤

፳፭፡ ወአኀዝዎሙ ለ፪ቱ መላእክተ ምድያም ለሄሬብ ወለዜብ ወቀተልዎ ለሄሬብ በሴሬን ወለዜብ ቀተልዎ በኢያሬቅ ፤

ሁለቱን የምድያም አለቆች ሄሬብና ዜብን ይዘው ሄሬብን በሴሬን ፤ ዜብን በኢያሬቅ ገደሏቸው ፤

ወዴገንዎሙ ለምድያም ወአምጽኡ አርእስቲሆሙ ለሄሬብ ወለዜብ ኀበ ጌዴዎን እማዕዶተ ዮርዳኖስ ፤

የቀሩትንም የምድያምን ሠራዊት ሁሉ ተከትለው ይዘው የሄሬብንና የዜብን ቸብቸቦ ቆርጠው አምጥተው ከዮርዳኖስ ማዶ ሠፍረው ሳለ ለጌዴዎን ግዳይ ጣሉለት ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፰

፩፡ ወይቤልዎ ሰብአ ኤፍሬም ምንት ውእቱ ዝንቱ ነገር ዘገበርከ ላዕሌነ ከመ ኢትጸውአነ እመ ሖርከ ትትቃተሎሙ ለምድያም ወተሳነኑ ምስሌሁ ዓቢየ ተሰናነ ፤

የኤፍሬም ወገኖች ግዳይ ጥለው ከጨረሱ በኋላ በእኛ ላይ ያደረግኸው ይህ ነገር ምንድን ነው ፤ የምድያምን ሰዎች ለመውጋት በሔድህ ጊዜ ሳትጠራን የሔድህ ለምንድን ነው ብለው ? ከጌዴዎን ጋር ጽኑ ወቀሳ አደረጉ ፤ አንድም ጽኑዕ ጠብ ተጣሉ ፤

፪፡ ወይቤሎሙ ምንተ ገበርኩ ይእዜ ከመዝ አንትሙ ኢትኄይሱኑ ቈጽለ ኤፍሬም እምቀስመ አብያዜር ፤

ጌዴዎንም ከአብያዜር ፍሬ የኤፍሬም ቅጠል የሚሻል አይደለምን እንዲህስ ሁሉ ዛሬ ከእኔ እናንተ የምትሻሉ አይደለምን ፤ አንድም ከአብያዜር መዝመት የናንተ አለመዝመት ይሻል የለምን ምን አደረግኹ አላቸው ፤

፫፡ አኮኑ ውስተ እዴክሙ አግብአሙ እግዚአብሔር ለመላእክተ ምድያም ለሄሬብ ወዜብ ወምንተ ክህልኩ ገቢረ ከማክሙ ፤

እግዚአብሔር የምድያምን አለቆች ሄሬብንና ዜብን በእጃችሁ አሳልፎ የጣላቸው አይደለምን (ጥሏቸዋልና) ከእኔማ እናንት የምትሻሉ አይደለምን እኔ እንደ እናንተ ማድረግ ምን ተቻለኝ አላቸው ፤

ወእምዝ ኀደግዎ እንከ ወአዕረፈት ነፍሶሙ እምኔሁ ሶበ ይቤሎሙ ዘንተ ቃለ ፤

ከዚህ በኋላ የሚመልሱለት አጥተው ትተውት ተመለሱ ፤ ይህንም ነገር በነገራቸው ጊዜ ልቡናቸው ከብስጭት ከኀዘን አረፈች ፤ አንድም ጌዴዎን ይህን ነገር ከማድረጉ የተነሣ የእስራኤል ሰውነት ለሰብአ ምድያም ከመገበር መከራ ከመቀበል አረፈች ፤

፬፡ ወመጽአ ጌዴዎን ኀበ ዮርዳኖስ ወአደወ ውእቱ ወእልክቱኒ ፫፻ ብእሲ እለ ምስሌሁ ወአንበዙ ሶበ ርኅቡ ፤

ጌዴዎንም ይህን ተናግሮ ወደ ዮርዳኖስ መጣ ፤ እሱም ከእሱ ጋር የዘመቱ ሦስት መቶ ሰዎችም ዮርዳኖስን ተሻግረው ሔዱ ፤ ስንቅ ባለቀባቸው ጊዜ ፤ አንድም ግሥገሣ በበዛባቸው ጊዜ አእምሮአቸውን አጡ ተበሳጩ ፤

፭፡ ወይቤሎሙ ለሰብአ ሰኮት ሀብዎሙ እክለ ለሕዝብ እለ ምስሌየ እስመ ርኅቡ ወአንሰ እተልዎሙ ለዜብሔል ወለስልማና ነገሥተ ምድያም፤

«አዘዞሙ» ያለበት ነው፤ ጌዴዎንም የሰኮትን ... ለዘመቱ ሰዎች ተርበዋልና ስንቅ ስጧቸው ብሎ አዘዛቸው ፤ እኔ ግን የምድያምን ነገሥታት ዜብሔልንና ስልማናን ተከትዬ እሔዳለሁ አላቸው ፤



፮፡ ወይቤልዎ መላእክተ ሰኮት ቦኑ እዴሆሙ ለዜብሔል ወስልማና ይእዜ ውስተ እዴከ ከመ ነሀቦሙ እክለ ለሠራዊትከ ፤

የሰኮት አለቆችም ዛሬ ለሠራዊትህ ስንቅ እንሰጥ ዘንድ የጌቶቻችን የዜብሔልና የስልማና እጅ በእጅህ ተይዟልን ፤ አንድም በውኑ የዜብሔልና የስልማና እጅ በእጅህ ተይዟልና ዛሬ ለሠራዊትህ ስንቅ እንሰጥ ዘንድ ይገባናል አሉት ፤

፯፡ ወይቤሎሙ ጌዴዎን አኮ ከመዝ እምከመ አግብአሙ እግዚአብሔር ለዜብሔል ወለስልማና ውስተ እዴየ እሰቅል ሥጋክሙ ውስተ ዓቀባት ዘገዳም ወውስተ ክልኤ አርቆሚን ፤

ጌዴዎንም እንዲህ እንደዘበታችሁብኝ የምትቀሩ አይደለም፤ እግዚአብሔር ዜብሔልንና ስልማናን በእጄ የጣላቸው እንደሆነ የእናንተንም ሥጋችሁን በምድረ በዳ ባለ ተራራ ላይ በሁለት መንታ ባላ እሰቅላለሁ አላቸው ፤

፰፡ ወዐርገ እምህየ ውስተ ፋኑሔል ... ሰብአ ፋኑሔል በከመ ይቤልዎ ሰብአ ሰኮት ፤

ይህንም ተናግሮ ከሰኮት ፋኑሔል ወደሚባል አገር ወጥቶ በፋኑሔል የሚኖሩትን ሰዎች ከእኔ ጋር ላሉት ሰዎች ስንቅ ስጧቸው አላቸው፤ እነሱም የሰኮት ሰዎች እንዳሉት መለሱለት ፤

፱፡ ወይቤሎሙ ለሰብአ ፋኑሔል ሶበ ገባእኩ በዳኅን እነሥቶ ለዝንቱ ማኅፈድ ፤

ጌዴዎንም የፋኑሔልን ሰዎች በደኅና ከመለስኝ ይህን ግንብ አፈርሰዋለሁ አላቸው ፤

፲፡ ወዜብሔልሰ ወስልማና ውስተ ቀርቀር ወትዕይንቶሙኒ ምስሌሆሙ ወየአክሉ እልፈ ወሃምሳ ምእተ ኵሎሙ እለ ተርፉ እምኵሉ ተዓይኒሆሙ ለደቂቀ ጽባሕ ፤

ዜብሔልና ስልማና ግን ከሠራዊቶቻቸው ጋር ከዋሻ (ከገዎቻ) ውስጥ ነበሩ ፤ ከሰብአ ምድያም ሠራዊትም ከሞት የቀሩት እልፍ ከአምስት ሽህ (አሥራ አምስት ሽህ) ያህሉ ነበር ፤

ወእለሰ ወድቁ ፻፳ወ፰፻ ብእሲ እለ ይፀውሩ ኵናተ ፤

የሞቱት ግን ለጦር የደረሱ (ጋሻ የሚመክቱ ጦር የሚወረውሩ) አሥር እልፍ ከሁለት ሺህ (መቶ ሁለት ሺህ) ናቸው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፩፡ ወዐርገ ጌዴዎን ፍኖተ እለ ይነ ብሩ ውስተ አዕፃዳት ጽባሐውያን እለ መንገለ ናቤት ላዕለ ዛብሔል ወስል ማና ወቀተለ ትዕይንቶሙ እንዘ ይት አመኑ ፤

ጌዴዎንም በናቤት የሚኖሩ የምሥራቅ ሰዎች ባሉበት ቦታ በሚኖሩ ሰዎች መንገድ ዘምቶ ተዘልለው ሳሉ (ጠላት ይመጣ ብናል ብለው ሳይጠረጥሩ) አደጋ ጥሎ ሠራዊቶቻቸውን አጠፋ ።

፲፪፡ ወጐዩ ዜብሔል ወስልማና ወዴ ገኖሙ ወተለዎሙ ወአኀዞሙ ለ፪ኤ ሆሙ ነገሥተ ምድያም ለዜብሔል ወስልማና ወለኵሉ ትዕይንቶሙ ቀጥ ቀጦሙ ጌዴዎን ፤

ዜብሔልና ስልማናም የሠራዊቶ ቻቸውን ጥፋት አይተው ሸሹ ፤ ጌዴዎንም ሁለቱን የምድያም ነገሥታት ስልማናንና ዜብሔ ልን ተከትሎ ያዛቸው ፤ ሠራዊ ቶቻቸውንም ሁሉ አጠፋ ።

፲፫፡ ወተመይጠ ጌዴዎን ወልደ ዮአስ እምጸብእ እምዓቀበ አሩስ ፤

የዮአስ ልጅ ጌዴዎንም ከጦር ነት ዜብሔልንና ስልማናን ማርኮ ይዞ በአሩስ ወደአለ አምባ ተመለሰ ።

፲፬፡ ወአኀዘ ፩ደ ወልደ እምሰብአ ሰኮት ወሐተቶ ወአጽሐፎሙ ለመላ እክተ ሰኮት ወለሊቃናቲሃ ፸ ወ፯ቱ ብእሲ ፤

በአሩስ አምባ ሠፍሮ ሳለም ባለ ሟሎቹ ከሰኮት ሰዎች አንድ ብላቴና ማርከው አመጡለት፤ የሰኮትን አለቆች ጠየቀው ሰባ ሰባት አለቆች ሽማግሌችን እየ ነገረው በመዝገብ አጻፉቸው መላእክት የመንደር ፤ ሊቃናት የሀገር ።

፲፭፡ ወበጽሐ ኀበ መላእክተ ሰኮት ወይቤሎሙ ነዮሙ ዜብሔል ወስል ማና እለ በሙ ተዓየርክሙኒ ወትቤ ሉኒ ቦኑ እዴሆሙ ለዜብሔል ወስ ልማና ይእዜ ውስተ እዴከ ከመ ነሀቦሙ እክለ ለእለ ርኅቡ ሰብእከ ፤

ወደ ሰኮት አለቆችም በደረሰ ጊዜ ለተራቡ ሠራዊትህ እህል (ስንቅ) እንሰጣቸው ዘንድ ስል ማናና ዜብሔል በውኑ አሁን በእጅህ ተይዘዋልን ብላችሁ በነሱ የተገዳደራችሁብኝ ስል ማናና ዜብሔል እነሆ እነዚህ ናቸው አላቸው ።

፲፮፡ ወነሥአሙ ለሰብአ ሰኮት ወለ ሊቃውንቲሆሙ ወለመላእክቲሆሙ ወሰቀሎሙ ውስተ ዓቀባተ ገዳም ወውስተ በራቅሊም ወሰቀሎሙ ምስ ሌሆሙ ለስብአ ሰኮት ፤

የሰኮትንም ሰዎች ሽማግሌቹ ንና አለቆቹን ይ...



በምድረ በዳ ካለ ተራራ አው ጥቶ ሁለት ባላ ባለው እን ጨት ሰቀላቸው፤ ሠራዊቶቻቸ ውንም ከአለቆቻቸው ጋር ሰቀ ላቸው ።

፲፯፡ ወነሠቶ ለማኅፈደ አናምሔል ወቀተሎሙ ለሰብአ ፋኑሔል ወለሀ ገሮሙኒ ፤

የሰኮትን ሰዎች ካጠፋ በኋላም የአናምሔልን ግንብ ንዶ አፈ ረሰው ፤ በፋኑሔል የሚኖሩትን ሰዎችም አጠፋቸው ፤ አገራቸ ውንም አቃጠለባቸው ።

፲፰፡ ወይቤሎሙ ለዜብሔል ወለስ ልማና አይቴ ዕደው እለ ቀተልክ ምዎሙ በታቦር ፤

የፋኑሔልን ሰዎች ካጠፋ በኋ ላም ዜብሔልንና ስልማናን በታ ቦር የገደላችኋቸው ሰዎች «መነ ይመስሉ» ያለበት ነው ፤ ማንን ይመስላሉ ፤ አንድም እንዴት ያሉ ናቸው አላቸው ።

ወይቤልዎ ከማከ እሙንቱ ወኪያከ ይመስሉ እሙንቱ ወከመ ርእየተ ገጸ ደቂቀ ነገሥት ገጾሙ ፤

ማንን ይመስላሉ ቢላቸው አን ተን ይመስላሉ ፤ እንዴት ያሉ ናቸው ቢላቸውም እንዳንተ ያሉ ናቸው ፤ መልካቸውም የነገሥ ታትን ልጆች መልክ ይመስላል ...

፲፱፡ ወይቤሎሙ ጌዴዎን አኃውየ እሙንቱ ደቂቀ እምየ ወመሐለ ሎሙ ወይቤሎሙ ሕያው እግዚአ ብሔር ሶበ አሕየውክምዎሙ እም ኢቀተልኩክሙ ፤

ጌዴዎንም አለ ፤ እነሱማ የናቴ ልጆች ወንድሞች ናቸው ፤ እነ ሱን ባትገድሏቸው ሕያው እግ ዚአብሔርን ባልገደልኋችሁም ነበር ብሎ ማለ ።

፳፡ ወይቤሎ ለዮቶር በኵሩ ተንሥእ ቅትሎሙ ወኢመልሐ መጥባሕቶ ውእቱ ሕፃን እስመ ንኡስ ውእቱ ወፈርሐ ፤

የበኸር ልጁ ዮቶርንም ጠርቶ በጠላትነት ተነሥተህ ዜብ ሔልንና ስልማናን ግደላቸው አለው ፤ ዮቶርም ሕፃን ነበርና ሰይፉን መዞ መግደልን ፈራ ።

፳፩፡ ወይቢልዎ ዜብሔል ወስልማና ተንሥእ አንተ ወተራከበነ እስመ ከመ ብእሲ ውእቱ ኃይልከ ፤

ዜብሔልና ስልማናም «ተንሥእ ወቅትሎሙ» ያለውን ሰምተው ሕፃን ከሚጫወትበት የሕፃን መጫወቻ ሆኑ ከምንባል ኃይ ልህ እንደአርበኛ ያለ ነውና አንተ ተነሥተህ በጠላትነት ተገ ናኘን ፤ ግደለን አሉት ።

ወተንሥአ ጌዴዎን ወቀተሎሙ ለዜ ብሔል ወለስልማና ወነሥአ ባዝግ

www.ethiopianorthodox.org

ናተ ዘውስተ ክሣዳተ አግማላቲ ሆሙ ፤

ጌዴዎንም ሞታቸውን በራሳ ቸው ካስፈረደ በኋላ በጠላት ነት ተነስቶ ዜብሔልንና ስል ማናን ገደላቸው ፤ በየግመሎ ቻቸው አንገት የነበረ ዝርግፍ ወርቃቸውንም ወሰደው ።

፳፪፤ ወይቤልዎ ሰብአ እስራኤል ለጌዴዎን ተመልአክ ለነ አንተ ወደ ቂቅከ እስመ አድኃንከነ እምእዴ ሆሙ ለምድያም ፤

ከዚህ በኋላ የእስራኤል ሰዎች ተሰብስበው ሒደው ጌዴዎንን ከምድያም ሰዎች እጅ አድነኸ ናልና አንተ ከልጆችህ ጋር ገዥ አለቃ ሁነን (አለቃ ሁነህ ግዛን) አሉት ።

፳፫፤ ወይቤሎሙ ጌዴዎን ኢይት መለአክ አንሰ ለክሙ ወወልድየኒ ኢይትመለአክ ለክሙ እግዚአብሔር ይትመለአክ ለክሙ ፤

ጌዴዎንም እግዚአብሔር ገዥ ይሁናችሁ እንጂ እኔስ ገዥ አልሆናችሁም ፤ ልጄም ገዥ አይሆናችሁም አላቸው ።

፳፬፤ ወይቤሎሙ ጌዴዎን እስእል እምኔክሙ ስእለተ ወሀቡኒ ብእሲ ብእሲ አዕኑገ ዘወርቅ ዘሰለበ እስመ ብዙኃ አዕኑግ ቦሙ እስመ እስማኤ ላውያን እሙንቱ ፤

ጌዴዎንም ከእናንተ ልመናን እለምናለሁ፤ አንዱም አንዱም የዘረፈውን የወርቅ ጉትቻ ስጡኝ አላቸው፤ የምድያም ሰዎች የእ ስማኤል ወገኖች ስለሆኑ ብዙ የወርቅ ጉትቻ ነበራቸውና ።

፳፭፤ ወይቤሎሙ ውሂበ ንሁብ ወሰ ፍሐ ልብሶ ወገደፈ ብእሲ ብእሲ አዕኑገ ዘሰለቡ ፤

እነሱም እሺ እንሰጥሃለን አሉት፤ ጌዴዎንም የዋለ ያደረ እንደ ሆነ ሰይጣን ፍቅረ ንዋይ ያሳድ ርባቸዋል ብሎ ሸማውን ዘርግቶ ከዚህ ላይ ጣሉልኝ አላቸው ፤ አንዱም አንዱም የዘረፈውን የወርቅ ጉትቻ በልብሱ ላይ ጣሉለት ።

፳፮፤ ወኮነ ድልወተ ወርቀ አዕኑጊሁ ዘሰአሎሙ ፲ወ፻፯ተ በሰቅለ ወርቁ ፤

የለመናቸው የወርቁ ጉትቻ ሚዛኑ በተለየ አዋቂ (ሚዛን) ሺህ ዘጠኝ መቶ ወቄት ሆነ ።

እንበለ አውፃባት ወባዝግናት ወኤ ፎት ወመዋጥህ ዘሜላት ዘላዕለ ነገ ሥተ ምድያም ወእንበለ ሐብላተ ወርቅ ዘውስተ ክሣዳተ አግማሊ ሆሙ ፤

ከወርቁ ቀለበትና ከወርቁ ማርዳ በቀር የምድያም ነገሥታት ነጭ ሐር ቀሚሳቸውን ከሚያፍኑበት ከወርቁ አንባርና ከውግሮ ስልሱ በቀር በየግመሎቻቸው አንገት ካለው ከወርቁ [illegible]



አንድም ይህ ሁሉ ሳይቀር ሺህ ዘጠኝ መቶ ወቄት ሆነ ።

፳፯፤ ወገብረ ሎቱ ጌዴዎን ምስለ ወአቀሞ ውስተ ሀገሩ ውስተ ኤፍ ራታ ፤

ጌዴዎንም ይህንን ሁሉ ሰብስቦ የወርቅ ምስል አሠርቶ ለዝክረ ነገር ኤፍራታ በምትባል ሀገሩ አቆመው ፤ አንድም ለመጫወቻ ሊሆን የወርቅ ምስል አሠራ ፤ የሀገራችን ባለጸጎች የወርቅ ቡችላ እንዲያስበጁ (እንዲያ ሠሩ) ።

ወዘመዉ ቦቱ ኵሉ እስራኤል ወተ ለውዎ በህየ ወኮኖ ጌጋየ ለጌዴዎን ወለቤቱ ፤

እስራኤልም ሁሉ በሱ ሳቱ ማለት በደሉ፤ እሱንም አመለ ኩት፤ ይህም በጌዴዎንና በወገ ኖቹ ዕዳ በደል ሆነባቸው ።

፳፰፤ ወተትሕተ ምድያም በቅድሜ ሆሙ ለእስራኤል ወኢደገሙ እንከ አልዕሎ ርእሶሙ ወአዕረፈት ምድር ፵ዓመተ በመዋዕለ ጌዴዎን ፤

የምድያም ሰዎችም በጌዴዎን ዘመን ለእስራኤል በእጃቸው ጭብጥ በእግራቸው እርግጥ ብለው ተገዙ ፤ ዳግመኛ ራሳቸ ውን ከፍ ከፍ አላደረጉም፤ በጌዴ ዎን ዘመንም አገሪቱ አርባ ዘመን ለአርባ ዘመን ከመገዛት አረፈች ።

፳፱፤ ወሖረ ሮብአም ወልደ ዮአስ ወነበረ ውስተ ቤቱ ፤

የዮአስ ልጅ ሮብአም (ጌዴዎን) ወደ ሀገሩ ተመልሶ በቤቱ ተቀ መጠ ።

## ጉባዔ

፴፤ ወቦ ለጌዴዎን ፸ደቂቅ እለ ወፅኡ እምሐቌሁ እስመ ብዙኃት አንስት ያሁ ፤

ሚስቶቹ ብዙዎች ነበሩ እና ለጌዴዎን ከአብራኩ የተከፈሉ ሰባ ልጆች ነበሩት ።

፴፩፤ ወዕቅብቱ ዘውስተ ሰቂማስ ወለደት ሎቱ ወልደ ወሰመየ ስሞ አቤሜሌክ ፤

በሰቂማስ የምትኖር ዕቁባቱም ወንድ ልጅ ወለደችለት፤ ስሙ ንም አቤሜሌክ አለው ፤ እሷ ነገር ያላት ናትና ለይቶ አነ ሣት ፤ ልጁንም ኋላ በደገኛው እስኪያመጣው ድረስ እንደ አር እስት አነሣው ።

፴፪፤ ወሞተ ጌዴዎን ወልደ ዮአስ በሀገረ ሲናት ወተቀብረ ውስተ መቃ ብረ አቡሁ ዮአስ በኤፍራታ ወአብ ያዜር ፤

የዮአስ ልጅ ጌዴዎንም ሲናት በምትባል አገር ሙቶ አባቱ ዮአስ እና ወንድሙ አብያዜር

www.ethiopianorthodox.org

በተቀበሩበት በኤፍራታ ተቀበረ አብያዜር ከእሱ አስቀድሞ ከእሱ በኋላም ቢሉ ሙቶ በዚያ ተቀብሯልና ፤

፴፫፡ ወእምዝ ሶበ ሞተ ጌዴዎን ተመይጡ ደቂቀ እስራኤል ወተለውዎ ለበዓሊም ወተካየዱ ምስሌሁ ለበዓሊም ከመ ይኩኖሙ አምላኮሙ ፡፡

ጌዴዎን ከሞተ በኋላ የእስራኤል ልጆች ከሃይማኖት ወደ ክሕደት፣ ከጽድቅ ወደ ኃጢአት ተመልሰው በዓሊም የሚባል የሰው ምስል ጣዖት አመለኩ ፣ ፈጣሪያቸውም ይሆን ዘንድ ከጣዖቱ ጋር ተማማሉ ፤

፴፬፡ ወኢተዘከርዎ ደቂቀ እስራኤል ለእግዚአብሔር አምላኮሙ ዘአድኀኖሙ እምእደ ኵሉ ፀሮሙ እለ ዓውዶሙ ፡፡

የእስራኤል ልጆችም በዙሪያቸው ካሉ ጠላቶቻቸው እጅ ያዳናቸው እግዚአብሔርን ይፈርድ ብናል ብለው ፤ በሕግ በአምልኮት አላሰቡትም ፤

፴፭፡ ወኢገብሩ ምሕረተ ምስለ ቤተ ሮብአም ዘውእቱ ጌዴዎን በኵሉ ሠናይት እንተ ገብረ ምስለ እስራኤል ፡፡

ለእስራኤል ባደረገላቸው በጎ ሥራ ሁሉ ይኸውም ሮብዓም የተባለ ጌዴዎን ነው ፣ ከሮብአም ወገኖች ጋር ይቅርታ (ወረታን) አላደረጉም ነገሩን ኋላ በደግ እስኪያመጣው ድረስ እንደ አርእስት ተናገረው ፡፡

## ምዕራፍ ፱

፩፡ ወሖረ አቤሜሌክ ወልደ ሮብአም ውስተ ሰቂማ ኀበ አኃወ እሙ ወተናገሮሙ ለኵሎሙ አዝማደ ቤተ እሙ ፡፡

የሮብአም ልጅ አቤሜሌክም በሰቂማ ወደ አሉ ወደ እናቱ ወንድሞች ሒዶ ፤ አንድም የእናቱ ወንድሞች ወደአሉበት ወደ ሰቂማ ሒዶ የናቱን ወገኖች ዘመዶቹን ሁሉ አባበላቸው (ተናገራቸው) ፤

፪፡ ወይቤሎሙ ተናገርዎሙ ሊተ ለሰብአ ሰቂማ ወበልዎሙ ምንት ይኄይስክሙ ሰብዓኑ ብእሲ ይኩንኑ ክሙ ኵሎሙ ደቂቀ ሮብአም አው ፩ዱ ብእሲ ይኩንንክሙ ወተዘከሩ ከመ ሥጋክሙ ወዓፅምክሙ አነ ፡፡

ምን ይሻላችኋል ? የሮብአም ሰባው ልጆቹ ሁሉ ይገዟችሁ ዘንድ ነው ? ወይስ አንድ ሰው ይገዛችሁ ዘንድ ይሻላል? በዚያውም ላይ እኔ የሥጋችሁ ቁራጭ ፣ የአጥንታችሁ ፍላጭ እንደሆንሁ አስቡ ብላችሁ ለሰቂማ ሰዎች ንገሩልኝ (አባብሉልኝ) አላቸው ፤



፫፡ ወተናገሩ ሎቱ አኃወ እሙ ምስለ ኵሉ ሰብአ ሰቂማ ኵሎ ዘንተ ነገረ ወሜጥዎ ለልቦሙ ኀበ አቤሜሌክ ወይቤሉ እኁነ ውእቱ ፡፡

የናቱም ወንድሞች የነገራቸውን ነገር ሁሉ ከሰቂማ ሰዎች ጋር ሁሉ ተነጋገሩለት ፤ አንድም ይህን ነገር ነግረው የሰቂማን ሰዎች ሁሉ አባበሉለት ፣ ባዕድ ከሚገዛን እሱ ወንድማችን ነውና እሱ ይግዛን ብለው ፣ የሰቂማን ሰዎች ልቡና ወደ አቤሜሌክ ጨልጠው ገርኝተው መለሱለት ፤

፬፡ ወወሀብዎ ሰብዓ ብሩረ እምቤተ በዓል ወተዐሰበ ቦን አቤሜሌክ ዕደወ ሐቃልያነ ወመደንግፃነ ወሖሩ ወተለውዎ ፡፡

ምክሩን ከጨረሱ በኋላ የመሣሪያ መግዣ ይሁንህ ብለው ለጣዖቱ ከገባው መባ ሰባ ብር ሰጡት፣ አቤሜሌክም ተቀብሎ መልካቸው የሚያስደነግጥ ቁመታቸው የሚያስፈራ አርበኞችን ተወዳጀበት እነሱም ተከትለውት ሔዱ ፤

፭፡ ወቦአ ውስተ ቤተ አቡሁ ኤፍራታ ወቀተሎሙ ለአኃዊሁ ለደቂቀ ሮብአም ፸ ብእሲ በላዕለ አሐቲ እብን ወተርፈ ኢዮአታም ወልደ ሮብአም ዘይንእስ እስመ ተኀብአ ፡፡

በኤፍራታ ካለ ከአባቱ ቤት [illegible] ወንድሞቹን ሰባውን የሮብአም ልጆች በአንዲት ዕለት ደንጊያ ላይ እያስጣለ ገደላቸው ፣ የሮብአም ታናሽ ልጁ ኢዮአታም ግን ተሠውሮ ነበርና ከሞት ተረፈ ፤

፮፡ ወተጋብኡ ኵሎሙ ሰብአ ሰቂማ ወኵሉ ቤተ መሐሎን ወሖሩ ወአንገሥዎ ሎሙ ለአቤሜሌክ ንጉሠ በኀበ ዕፀ በላኖን እንተ ውስተ ሰቂማ ፡፡

በሰቂማ ያሉ ሰዎችና የመሐሎን ወገኖች ሁሉ ተሰብስበው ሒደው በሰቂማ ውስጥ ባለ በወይራ ወይም በግራር እንጨት አጠገብ አቤሜሌክን ንጉሥ አድርገው አነገሡት ፤ «ሎሙ» የሚረባን የሚጠቅመን ስለመሰላቸው ራሳቸውን ሊጎዱ ፤

፯፡ ወዜነውዎ ለኢዮአታም ወሖረ ወቆመ ውስተ ርእሰ ደብረ ገሪዛን ወጸርሐ ወበከየ ወይቤሎሙ ስምዑኒ ሰብአ ሰቂማ ወይስማዕክሙ እግዚአብሔር ፡፡

የሰቂማ ሰዎች አቤሜሌክን አነገሡት ብለው ለኢዮአታም ነገሩት፣ እሱም ሒዶ በገሪዛን ተራራ እራስ ላይ ቁሞ የሰቂማ ሰዎች እግዚአብሔር ይስማችሁና ስሙኝ ብሎ ጮኾ አለቀሰ ፤ አንድም አልቅሶ ነገራቸው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፰፡ ወሖሩ ዕፀው ያንግሡ ሎሙ ንጉሠ ወይቤልዋ ለዕፀ ዘይት ንዒ ንግሢ ለነ ፤

ነገሩን በምሳሌ ይነግራቸዋል፣ ዕንጨቶች ንጉሥ ያነግሡ ዘንድ ተሰብስበው ሒደው የዘይትን እንጨት ነይ ንገሽልን አሏት ፤

፱፡ ወትቤሎሙ ዕፀ ዘይት እኅድግኑ ቅብዕየ ዘሰብሐ እግዚአብሔር በላዕሌየ ወዕጓለ እመሕያው ወእሑር እንግሥ ላዕለ ዕፀው ፤

ዕፀ ዘይትም ለሰው ቅባት ለቤተ እግዚአብሔር መብራት አድርጎ እግዚአብሔር ያከበረው ቅባቴን (ቅባትነቴን) ትቼ ለእንጨቶች እነግሥ ዘንድ ልሒድን አልነግሥም አለቻቸው ፤

፲፡ ወይቤልዋ ለበለስ ንዒ ንግሢ ለነ ፤

በለስንም ነይ ንገሽልን አሏት ፤

፲፩፡ ወትቤሎሙ በለስ እኅድግኑ ምጥቀትየ ወፍሬየ ቡሩከ ወእሑር እንግሥ ለዕፀው ፤

በለስም ርዝመቴንና እግዚአብሔር ያከበረው ፍሬዬን ትቼ ለእንጨቶች እነግሥ ዘንድ ልሒድን አልነግሥም አለቻቸው ፤

፲፪፡ ወይቤልዎ ኵሉ ዕፀው ለወይን ነዓ ንግሥ ለነ ፤

ወይንንም እንጨቶች ሁሉ ተሰብስበው ሒደው ና ንገሥልን አሉት ፤

፲፫፡ ወይቤሎሙ ወይን እኅድግኑ ወይንየ ወትፍሥሕትየ ዘኀበ እግዚአብሔር ወዘኀበ እጓለ እመሕያው ወእሑር እንግሥ ለዕፀው ፤

ወይንም ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ለሰው ትፍሥሕት መሆኔን ትቼ ለእንጨቶች እነግሥ ዘንድ ልሒድን አልነግሥም አላቸው ፤

፲፬፡ ወይቤልዋ ዕፀው ለራምኖን ንዒ አንቲ ንግሢ ለነ ፤

ዕንጨቶች አስታን (ዶግን) ነይ አንቺ ንገሽልን አሏት ፤

፲፭፡ ወትቤሎሙ ዕፀ ራምኖን ለዕፀው እመ በአማን ታነግሡኒ በጽድቅ ንዑ ታጽልሉ ታሕተ ጽላሎትየ እመ ኢወዕአት እሳት እምነ ራምኖን ወትበልዖ ለአርዘ ሊባኖስ ፤

«እመቦ አማን ታነግሡኒ ጽድቀ» ሲል ነው ፤ ደግሞ ዕፀውን በእውነት በሳያችሁ የምታነግሡኝስ ከሆነ ከጥላዬ በታች ታርፉ ዘንድ ኑ ፤ ከዶግ (ከአስታ) የወጣች እሳት ዋንዛን ባትበላ ታያላችሁ አለቻቸው ፤ (ሐተታ) ወንድሙ የማይገባ ነገር ቢያደርግ እሱም የማይሆን ነገር ተናገረ፣ ይህም ልማድ ነው፣ ዮአስ «አቃኒ ዘውስተ ሊባኖስ ለአከ ኀበ ዕፀወ ቄድሮስ እንዘ ይብል ሀቦ ወለተከ ለወልድየ ትኩኖ ብእሲተ ወመጽአ [illegible]



ወኬድዎ ለአቃኒ እንዳለ» መጽሐፈ ነገ. ካልዕ ፲፬ ቀ.፱ ፤

ሱቱኤል ዕዝራም «ወሖሩ የም ወዕፀወ ገዳም ወተማከሩ ምክረ ወይቤሉ ንዑ ንሑር ወንጽብአ ለየም» እንዳለ ም. ፬ ቀ.፲፫ ፤ ይህም ምሳሌ ነው፣ ዕፀው የእስራኤል ፤ ዘይት በለስ ወይን አንድ ወገን ፤ የጌዴዎንና የልጆቹ፣ ዕፀው ተሰብስበው ሒደው ንገሡልን አሏቸው ማለት እስራኤል ተሰብስበው ሒደው ጌዴዎንን «ተመልአክ ለነ አንተ ወደቂቅከ እምድኅሬከ» ብለውታል ፣ ዘይት በለስ ወይን አንነግሥም አሏቸው ማለት ጌዴዎን አንሰ ኢይትመለአክ ወወልድየኒ ኢይትመለአክ ለክሙ ብሏቸዋል ፤ ዶግ (አስታ) የአቤሜሌክ ፣ ንገሽልን አሏት ማለት እስራኤልም ከዕቅብቱ የተወለደ አቤሜሌክን ንገሥልን ብለውታል ፣ ዶግም (አስታ) በእውነት ታነግሡኛችሁኝስ ኑ ከጥላዬ በታች ዕረፉ አለቻቸው ማለት ፣ አቤሜሌክም ካነገሣችሁኝስ በሥልጣኔ ተጠበቁ ብሏቸዋል ፣ ከዶግ የወጣ እሳት ዋንዛን ዘግባን ባይበላ ታዩ ማለት ፣ ከሰቂማ የወጣ ጦር ሰብአ ሰቂማን ባያጠፉ ታዩ ሰ[illegible]ነው ፤

፲፮፡ ወይእዜኒ እመ በአማን በጽድቅ ገበርክሙ ወአንገሥክምዎ ለአቤሜሌክ ፤

አሁንም ይህን ነገር በእውነት ካደረጋችሁት አቤሜሌክን ካነገሣችሁት «ቡሩካነ ኩኑ» ያለበት ነው ፣ የተባረካችሁ ሁኑ የመርገም ምርቃን ነው ፤

ወበከመ ገበርክሙ ምስለ ሮብአም ወምስለ ቤቱ ወእመ በከመ ዕሤተ እዴሁ ገበርክሙ ሎቱ ፤

ለሮብአምና ለወገኖቹ እንዳደረጋችሁ ለአቤሜሌክ አደረጋችሁ ማለት ፣ አቤሜሌክን ካነገሣችሁት ለበጎ አድራጊው ለሮብአምም እንደእጁ ስጦታ ከመለሳችሁለት የተባረካችሁ ሁኑ ፤

፲፯፡ በከመ ተቃተለ አቡየ ለክሙ ወገደፈ ነፍሶ በቅድሜክሙ ወአድኀነክሙ እምእደ ምድያም ፤

አባቴ እንደተዋጋላችሁ በፊታችሁም ራሱን ለሕማም ለሞት አሳልፎ እንደ ሰጠላችሁ ከምድያም ሰዎች እጅም እንዳዳናችሁ በጎ ብድራት ከመለሳችሁለት ቡሩካን ሁኑ ፤

፲፰፡ ወአንትሙሰ ተንሣእክሙ ላዕለ ቤተ አቡየ ወቀተልክሙ ደቂቆ ፸ ብእሴ በላዕለ አሐቲ እብን ወአንገሥክምዎ ለአቤሜሌክ ወልደ ዕቅ

www.ethiopianorthodox.org

ብቱ ላዕለ ሰብአ ሰቂሞን እስመ እኁክሙ ውእቱ ፣

እንዲህ የምትል ምን አደረግን ትሉኝ እንደሆነ ፣ እናንተ ግን በአባቴ ወገኖች ላይ በጠላትነት ተነሥታችሁ ሰባውን ልጆቹን በአንዲት ዕለት ደንጊያ ላይ እየ ጣላችሁ ገደላችሁ፣ ከዚህም ጋር ወንድማችሁ ስለሆነ ከዕቅብቱ የተወለደ አቤሜሌክን በሰቂሞን ሰዎች ላይ አነገሣችሁት ፤

፲፱፤ ወእመሰ በጽድቅ ወበርትዕ ገበ ርክሙ ምስለ ሮብአም ወቤቱ ፀዛቲ ዕለት ቡሩካኑ ኩኑ አንትሙ ወተፈ ሥሑ በአቤሜሌክ ውእቱኒ ይትፈ ሣሕ ብክሙ ፣

ቡሩካን ኩኑ ሲል ነው ከላይ እንዳለ በዚህ ይታወቃል በዚች ቀን ለሮብአምና ለወገኖቹ በእ ውነትና በሚገባ ነገር ወረታን ካደረጋችሁ እናንተ የተባረካችሁ ሁኑ፣ በአቤሜሌክም መንገሥ ደስ ይበላችሁ፣ እሱም በእናንተ መገዛት ደስ ይበለው ፤

፳፤ ወእመ አኮሰ ትፃእ እሳት እም አቤሜሌክ ወትብልዖሙ ለሰብአ ሰቂ ሞን ወለቤተ መሐሎን ወትፃእ እሳት እምሰብአ ሰቂሞን ወእምቤተ መሐ ሎን ወትብልዖ ለአቤሜሌክ ፣

እንዲህስ ባይሆን ማለት በሚ ገባ ካልሆነ ግን ከአቤሜሌክ እሳት ወጥታ የሰቂሞንንና የመ ሐሎንን ወገኖች ትብላቸው ፣ ከሰቂሞንና ከመሐሎን ወገኖ ችም እሳት ወጥታ አቤሜሌክን ትብላው ማለት ከአቤሜሌክ የወጣች ጦር ሰብአ ሰቂሞንን ፣ ከሰብአ ሰቂሞንም የወጣች ጦር አቤሜሌክን ታጥፋው አላቸው ፤

፳፩፤ ወጕየ ኢዮአታም ወሮፀ ውስተ ፍኖት ወአምሰጠ ውስተ ራራ (አራ ራት) ወነበረ ህየ እምገጸ አቤሜሌክ እኁሁ ፣

ኢዮአታምም ይህን ከተናገረ በኋላ ሸሸቶ አራራት ከሚባል ተራራ ገብቶ አመለጠ ወንድሙ አቤሜሌክንም ከመፍራት የተ ነሣ በዚያ ኖረ ፤

፳፪፤ ወተመልአከ አቤሜሌክ ለቤተ እስራኤል ፫ዓመተ ፣

አቤሜሌክም ለእስራኤል ወገ ኖች ሦስት ዓመት ገዥ ሆነ (ነገሠ) ፤

፳፫፤ ወፈነወ እግዚአብሔር ጋኔነ እኩየ ማእከለ አቤሜሌክ ወእማእ ከለ ሰብአ ሰቂሞን ወክሕድዎ ሰብአ ሰቂሞን ለቤተ አቤሜሌክ ፣

እግዚአብሔርም በሰቂሞን ሰዎ ችና በአቤሜልክ መካከል የሚ ያጣላ ጋኔን አዘዘ የሰቂሞን ሰዎ ችም አቤሜሌክን ከዱት (ተጣ ሉት) ፤



፳፬፤ ከመ ይግባእ ኃጢአት ዘሰብአ ደቂቀ ሮብአም ወደሞሙ ወይትፌ ደዮ ለአቤሜሌክ እኁሆሙ ዘቀተ ሎሙ ወላዕለ ሰብአ ሰቂሞን እለ አጽንዕዋ ለእዴሁ ከመ ይቅትሎሙ ለአኃዊሁ ፣

ከሮብአም የተወለዱ የሰባውን ልጆች ደም ባፈሰሰ በአቤሜሌክ ዕዳ ይሆንበት ዘንድ ወንድሞቹን እንዲገድል ቃሉን ለመምከር እጁን ለመወርወር ባጸኑ በሰቂ ሞን ሰዎችና ወንድሞቹን በገደለ በአቤሜሌክ ላይ ፍዳን ያመጣ ዘንድ ፈነወ ጋኔነ ላለው ፤

፳፭፤ ወአንበሩ ሎቱ ሰብአ ሰቂሞን ማዕገተ ውስተ አርእስተ አድባር ወየ ሐይዱ ኵሎ ዘየኀልፍ ፍኖተ እንተ ላዕሌሆሙ ወዜነውዎ ለአቤሜሌክ፣

የሰቂሞን ሰዎችም አቤሜሌክን የሚይዝ ከባቢ ጦር በአምባ ላይ አኖሩ፣ እነዚህም ከአምባው ላይ ተቀምጠው ወደእነሱ የሚያል ፈውን ሁሉ ይቀሙ ነበር ፣ የተ ቀሙትም ሰዎች ይህን ነገር ለአቤሜሌክ ነገሩት (አቤቱታ አቀረቡለት) ፤

፳፮፤ ወመጽአ ጋድ ወልደ አቤድ ወአኃዊሁ ውስተ ሰቂማ ወኀብሩ ምስሌሆሙ ሰብአ ሰቂማ ፣

የአቤድ ልጅ ጋድም ይህን ሰምቶ ምክር ለማጽናት ወንድሞቹን አስከትሎ ወደ ሰቂማ መጣ ፣ የሰቂማ ሰዎችም ከሱ ጋር በም ክር አንድ ሆኑ ፤

፳፯፤ ወወፅኡ ኃቅለ ወቀሰሙ አዕፃ ዳተ ወይናሆሙ ወአኬዱ ወገብሩ በዓለ ወቦኡ ቤተ አምላኮሙ ወበልዑ ወሰ ትዩ ወረገምዎ ለአቤሜሌክ ፣

ወደ ምድረ በዳ ወጥተው የወ ይናቸውን ፣ አዝመራ ለቅመው አበራዩት ወይኑን አዘጋጅተው በዓል አደረጉ፣ ከጣዖታቸው ቤት ገብተውም በልተው ጠጥ ተው አቤሜሌክን ይረግሙት ጀመር ፣ (ሐተታ) አምላኮሙ ማለቱ ፈጥሮአቸው አይደለም፣ ሰርቀው ስላመለኩት ነው እንጂ ፤

፳፰፤ ወይቤ ጋድ ወልደ አቤድ መኑ ውእቱ አቤሜሌክ ፣ ወመኑ ውእቱ አቤሜሌክ ወልደ ሴኬም ከመ ንት ቀነይ ሎቱ ፣

«መኑ እና መኑ» አንድ ወገን ፣ የአቤድ ልጅ ጋድ እንገዛለት ዘንድ አቤሜሌክ ማነው? ብሎ ቢጠይቅ «ይቤልዎ» ያለበት ነው፣ የሴኬም ልጅ አቤሜሌክ ነዋ አሉት ፤ አንድም የካሽ መላሽ ሁኖ እንገዛለት ዘንድ አቤሜሌክ ማነው ? የሴኬም ልጅ አቤሜሌክ ማነው ? የሴ ኬም ልጅ አቤሜሌክ አይደለ ምን አለ የንቀት አነጋገር ፤

www.ethiopianorthodox.org

አኮኑ ውእቱ ወልደ ሮብአም ወዜቡል ዓቃቢሁ ወገብሩ ወሰብአ ኤሞር አቡሁ ለሴኬም ወለምንት ሎቱ ንት ቀነይ ንሕነ ፤

የዚያ የስንዴ ወቂ የሮብአም ልጅ አይደለምን ራስ ጠባቂው ባለሟሉስ ዜቡል አይደለምን ፤ ረዳቶቹስ የሴኬም አባት የኤሞር ወገኖች አይደሉምን እኛ ለሱ ለምን እንገዛለን ? አለ ፡፡

፳፱፡ ወመኑ እምአግብአ ለዝንቱ ሕዝብ ውስተ እዴየ ወአፍልሶ ለአቤሜሌክ ወእበሎ ለአቤሜሌክ አብዝኀ ኃይለከ ወፃእ ፤

አቤሜሌክን አጠፋው ዘንድ ፤ አንድም ከሀገሩ አስወጥቼ እሰደው ዘንድ ሠራዊትህንም አስከትለህ ውጣ እለው ዘንድ ፡፡ አንድም በአጭር ታጥቀህ ዘገር ነቅንቀህ ውጣ እለው ዘንድ የእስራኤልን ሕዝብ (ወገን) ወደ እኔ ማን በመለሰልኝ ይሆን ፡፡ አንድም የእስራኤልን ወገን በእጄ ማን በጣለልኝ ነበር ፡፡

፴፡ ወሰምዐ ዜቡል መልአከ ሀገር ዘይቤ ጋድ ወልደ አቤድ ወተምዐ መዓተ ፤

የሀገር አለቃ የሆነ ዜቡልም የአቤድ ልጅ ጋድ የተናገረውን ሰምቶ አጥብቆ ተቆጣ ፡፡

፴፩፡ ወፈነወ መላእክተ ኀበ አቤሜሌክ ምስለ አምኃ እንዘ ይብል ናሁ ጋድ ወልደ አቤድ ወአኃዊሁ መጽኡ ውስተ ሰቂማ ወናሁ ይትቃተልዋ ለሀገር በእንቲአከ ፤

ተቆጥቶም አልቀረ የአቤድ ልጅ ጋድና ወንድሞቹ በአንተ ምክንያት ሀገሪቱን ሊያጠፏት ወደ ሰቂማ መጡ ብሎ ከእጅ መንሻ ጋር መልእክተኞቹን ወደ አቤሜሌክ ላከ ፡፡

፴፪፡ ወይእዜኒ ተንሥእ በሌሊት አንተ ወሕዝብ ዘምስሌከ ወእግት ውስተ ኃቅል ወበጽባሕ ጊዜ ይሠርቅ ፀሐይ ጊሥ ወሩጻ ለሀገር ፤

አሁንም አንተ ሠራዊትህን አስከትለህ በመንገድ ትተህ በዱር ፤ በብርሃን ትተህ በጨለማ ገሥግሥህ ከበበው ፤ ጥዋት ፀሐይ በወጣ ጊዜ ገሥግሰህ አገሪቱን (ከተማይቱን) ከበባት ብሎ ላከበት ፡፡

፴፫፡ ወመጽአ ውእቱ ወሕዝብ ዘምስሌሁ በሌሊት ወዐገትዋ ለሰቂማ ፬ቱ ሠራዊት ፤

አቤሜሌክም ሠራዊቱን (ወገኖቹን) አስከትሎ በሌሊት መጥቶ ሰቂማን በአራት አበጋዝ (አለቃ) ሠራዊት ከበቧት ፡፡

፴፬፡ ወሶበ ጸብሐ ወፅአ ጋድ ወልደ አቤድ ወቆመ ኀበ ኆኅተ አንቀጸ ሀገር ወተንሥአ አቤሜሌክ ወሕዝብ ዘምስሌሁ እምኀበ የዐግቱ ፤

በነጋም ጊዜ የዐቤድ ልጅ ጋድ ወጥቶ በከተማው በር ቆመ



አቤሜሌክም ተነሣ፣ ከሱ ጋር ያሉ ወገኖቹም ከከበቡት ቦታ ተነሡ ፡፡

፴፭፡ ወርእየ ጋድ ወልደ ዓቤድ ሕዝበ ወይቤሎ ለዜቡል ናሁ ሕዝብ ይወርድ እምርእሰ ደብር ወይቤሎ ዜቡል ጽላሎተ አድባር ትሬኢ አንተሰ ከመ ሰብእ ፤

የአቤድ ልጅ ጋድም ሰዎቹን አይቶ ዜቡልን እነሆ ከተራራው ራስ ሠራዊት ሲወርድ አየሁ አለው በእውነቱ ፡ አንድም ያን ሲመለከት ሸሽቼ አመልጣለሁ መስሎት ዜቡልም አንተስ የተራራውን ጥላ እንደ ሰው መስሎህ ታያለህ እንጂ ሠራዊት አታይም አለው ፤ ሲያታልለው ነው ፡፡

፴፮፡ ወደገመ ዓዲ ጋድ ብሂሎቶ ወይቤሎ ናሁ ሕዝብ ይወርድ እምነገለ ባሕር ኀበ ኀንብርተ ምድር ወ፩ዱ ሠርዌ ይመጽእ እምፍኖተ ዖም አንፃሮ ፤

ጋድም ዳግመኛ እነሆ ብዙ ሕዝብ በባሕሩ አንፃር ወደ ምድር መካከል ይወርዳል ፤ የአንድ አለቃ ሠራዊትም ዛፍ ባለበት ጎዳና አንፃር ሲመጣ አያለሁ ብሎ ለዜቡል ነገረው ፤ ጦሩ ወደ አንድ ወገን ገንበር ሲል (ገለል) ሲል ሾልኬ አመልጣለሁ መስሎት ፡፡

፴፯፡ ወይቤሎሙ ዜቡል አይቴ ውእቱ ይእዜ ዝክቱ አፉከ ዘትቤ መኑ ውእቱ አቤሜሌክ ከመ ንትቀነይ ሎቱ አኮኑ ዝንቱ ውእቱ ሕዝብ ዘተዓየርከ ፃእኬ ይእዜ ወተቃተሎ ፤

ዜቡልም እንገዛለት ዘንድ አቤሜሌክ ማነው ? ብለህ የተናገርከው ነገር አሁን ወዴት አለ ? የተገዳደርከው (የናቅኸው) ወገን ይህ አይደለምን አሁንም ይልቁንስ ውጣና ግጠመው አለው ፡፡

፴፰፡ ወወፅአ ጋድ እምቅድሜሆሙ ለሰብአ ሰቂማ ወተቃተሎ ለአቤሜሌክ ፤

ጋድም ከሰቂማ ሰዎች ፊት ወጥቶ አቤሜሌክን ተዋጋው ፡፡ አንድም ከሰቂማ ሰዎች ፊት አመልጣለሁ ብሎ ሲሸሽ አቤሜሌክን ገጠመው ፡፡

፴፱፡ ወዴገኖ አቤሜሌክ ወጐየ እምቅድመ ገጹ ወወድቁ ብዙኃን ወተቃተሉ እስከ አንቀጸ ሀገር ፤

አቤሜሌክም ተከተለው ፤ ከፊቱም ሸሽቶ አመለጠ፣ ከወገኖቹም እስከ ሀገራቸው በር ድረስ ተዋግተው ብዙ ሰዎች ወደቁ ፡፡

፵፡ ወነበረ አቤሜሌክ ውስተ አሪማ ወአውፅአሙ ዜቡል ለጋድ ወለአኃዊሁ ወከልአሙ ነቢረ ውስተ ሰቂማ ፤

አቤሜሌክም አሪማ በምትባል አምባ ተቀመጠ፣ ዜቡልም ጋድ

www.ethiopianorthodox.org

ንና ወንድሞቹን ከሰቂማ አስወጥቶ መኖሪያ ከለከላቸው ፤

፵፩፤ ወእምዝ በሳኒታ ወፅአ ሕዝብ ውስተ ገዳም ወዜነውዎ ለአቤሜሌክ ።

ከዚህ በኋላ በማግስቱ ሕዝቡ ወደምድረ በዳ ወጥተው ለአቤሜሌክ ነገሩት ፤

፵፪፤ ወነሥአ ሕዝቦ ወከፈሎሙ ኀበ ፫ቱ ሠራዊት ወሀገተ ቦሙ ወሰበ ይኔጽር ናሁ ሕዝብ ይወፅእ እምሀገር ወተንሥአ ላዕሌሆሙ ወቀተሎሙ ።

አቤሜሌክም ሠራዊቱን ሦስት አበጋዝ ጦር አድርጎ ከፍሎ ጋድ የገባባቸውን ሰዎች ከበባቸው፣ አቅንቶም ወደከተማው ቢመለከት ሕዝቡ ከከተማ ሲወጡ አየ እነዚያንም በጠላትነት ተነሥቶ አጠፋቸው ፤

፵፫፤ ወአቤሜሌክሰ ወሠራዊት ዘምስሌሁ ቆሙ ኀበ ኆኅተ አንቀጸ ሀገር ።

አቤሜሌክና ከእሱ ጋር ያሉት ሠራዊት ግን በከተማው በር ደጃፍ ሸምቀው ቈመው ነበር ፤

፵፬፤ ወእልክቱሰ ፪ቱ ሠራዊት ተዘርዉ ውስተ ኵሉ ገዳም ወቀተልዎሙ ።

ሁለቱ አበጋዝ ሠራዊት ግን በምድረ በዳው ሁሉ ተበትነው ፈርተው የተሠወሩትን ሁሉ ገደሏቸው ፤

፵፭፤ ወአቤሜሌክሰ ይትቃተል ምስለ ሀገር ኵሎ ይእተ ዕለተ ወአስተጋብኦ ለሀገር ወሕዝበሰ እንተ ውስቴታ ቀተለ ወዘርአ ውስቴታ ፄወ ።

አቤሜሌክ ግን ቀኑን ሁሉ በከተማ ካሉ ሰዎች ጋር ሲዋጋ ዋለ ሀገሪቱንም ወግቶ እጅ አደረጋት በውስጧ የሚኖሩትንም ሰዎች ሁሉ አጥፍቶ ጨው ዘራባት ማለት በረሃ አደረጋት ፤

፵፮፤ ወሰምዑ ኵሎሙ ሰብአ ማኅፈደ ሰቂሞን ወቦኡ ውስተ ፀወነ ቤተ በዓል ።

በሰቂሞን አምባ ያሉ ሰዎችም ሁሉ የከተማውን ጥፋት የወገኖቻቸውን ሞት ሰምተው ከጣዖቱ ቤት ገብተው ተማፀኑ ፤

፵፯፤ ወዜነውዎ ለአቤሜሌክ ከመ ተጋብኡ ሰብአ ማኅፈደ ሰቂማ ።

እነዚህንም ያዩ ሰዎች በሰቂማ አምባ ያሉ ሰዎች ሁሉ እንደ ተሰበሰቡ ለአቤሜሌክ ነገሩት ፤

፵፰፤ ወዐርገ አቤሜሌክ ውስተ ደብረ ሔርሞን ውእቱ ወሕዝብ ዘምስሌሁ ወነሥአ አቤሜሌክ ጕድበ ውስተ እዴሁ ወገመደ ዖረ ዕፀው ወነሥአ ወፆሮ ውስተ መታክፈሁ (መታክፍቲሁ) ።

ዕፀወ ዖር ሲል ነው ፣ አቤሜሌክም ይህን ሰምቶ ሠራዊቱን አስከትሎ ሔርሞን ወደሚባል ተራራ ወጣ፣ ወ[illegible]



መውን እንጨት በእጁ በያዘው ገጀሞ ቆርጦ አንሥቶ በጫንቃው ተሸክመው ለሕዝቡ አብነት ለመሆን ፤

ወይቤሎሙ ለሕዝብ እለ ምስሌሁ ዘከመ ርኢክሙኒ እገብር ከማሁ ግበሩ አንትሙኒ ፍጡነ ከመ አነ ገበርኩ ።

ከሱ ጋር ያሉ ወገኖቹንም እኔ ሳደርግ እንዳያችሁኝ እናንተም ፈጥናችሁ እንደዚያው አድርጉ አላቸው ፤

፵፱፤ ወገዘሙ እሙንቱኒ ኵሎሙ ፆሮሙ ወነሥኡ ወተለውዎ ለአቤሜሌክ ወአንበሩ ኀበ ፀወን ወአውዓዩ ላዕሌሆሙ ፀወኖሙ በእሳት ወሞቱ ኵሎሙ ሰብአ ሰቂማ ዘማኅፈድ ወየአክሉ ፲ቱ ፻ ብእሲ ወአንስት ።

እነሱም እንዳዘዛቸው እንጨቱን ቆርጠው ተሸክመው አቤሜሌክን ተከተሉት ፣ የተሸከሙትንም እንጨት ከአምባው አስጠግተው አኑረው ሰዎቹ የተጠጉበትን አምባ በእሳት አቃጠሉት፣ በግንቡ ያሉ የሰቂማ ሰዎችም ሁሉ በእሳት ተቃጥለው ሞቱ፣ የሞቱት ወንዶቹም ሴቶቹም ሺህ ይሆናሉ ፤

፶፤ ወሖረ አቤሜሌክ ውስተ ቴቤስ ወነበሩ ላዕሌሃ ወአስተጋብእዎ ።

ከዚህ በኋላ አቤሜሌክ ወደ ቴቤስ ሔደ እሷንም እጅ አድ[illegible] ፤

፶፩፤ ወቦቱ ማኅፈድ ዓቢይ ውስተ ማእከለ ሀገር ወተፀወኑ ህየ ኵሎሙ ዕደዊሆሙ ወአንስቲያሆሙ ወኵሉ ዓበይተ ሀገር ወዐጸዉ ላዕሌሆሙ ወዐርጉ ውስተ ናሕሰ ማኅፈድ ።

በቴቤስ ከተማ መካከል ታላቅ ግንብ (አምባ) ነበረው፣ ወንዶችም ሴቶችም በሀገር ያሉ መኳንንትም ሁሉ በዚያ ተጠጉ፣ ወደ አምባውም ወጥተው በሩን ዘግተው ተቀመጡ ፤

፶፪፤ ወሖረ አቤሜሌክ ኀበ ናሕሰ ማኅፈድ ወተቃተልዎ ወቀርበ አቤሜሌክ ኀበ ኆኅተ ማኅፈድ ከመ ያውዕዮ በእሳት ።

አቤሜሌክም ወደ አምባው (ግንቡ) እገባለሁ ብሎ ሔደ ፣ እነሱም ተዋጉት፣ አቤሜሌክም ወደ አምባው መውጣት ባይሆንለት በእሳት ያቃጥለው ዘንድ ወደ ግንቡ በር ቀረበ ፤

፶፫፤ ወወገረት አሐቲ ብእሲት ስባረ ማሕረጽ ውስተ ርእሱ ለአቤሜሌክ ወቀጥቀጠቶ ርእሶ ወወፅአ ናላሁ ።

አቤሜሌክም ከቅጽሩ ተጠግቶ ቁሞ ሳለ ከአምባው ውስጥ ያለች አንዲት ሴት በወፍጮ ስባሪ የአቤሜሌክን ራሱን መታችው (ቀጠቀጠችው) ናላው ወጥቶ ወደቀ ፤

፶፬፤ ወጸውአ ፍጡነ ለቍልዔሁ ዘይፀውር ንዋየ ሐቅሉ ወይቤሎ ምላሕ መጥባሕተ ወቅትለኒ ከመ ኢይበ

www.ethiopianorthodox.org

ሉኒ ብእሲት ቀተለቶ ወወግዖ ቀኑል ዔሁ ወሞተ አቤሜሌክ ፤

አቤሜሌክም የበዳፀብቱን (መሣሪያውን) የሚሸከም ጋሻ ጃግሬውን ጠርቶ ሴት ገደለችው እንዳይሉኝ ሰይፍ መዝዘህ ግደለኝ አለው ፤ ጋሻጃግሬውም በሰይፍ ወጋው አቤሜሌክም ሞተ ፤

፶፭፡ ወርእዩ ሰብአ እስራኤል ከመ ሞተ አቤሜሌክ ወአተዉ ኵሎሙ ውስተ አብያቲሆሙ ፤

የእስራኤል ወገኖችም አቤሜሌክ እንደ ሞተ አይተው ከየ ገቡበት አምባ ወጥተው ወደ ቤታቸው ገቡ ፤

፶፮፡ ወፈደዮ እግዚአብሔር ለአቤሜሌክ እኪተ እንተ ገብረ ላዕለ ቤተ አቡሁ ዘቀተለ ሰብዓ አኃዊሁ ፤

እግዚአብሔርም አቤሜሌክን ሰባውን ወንድሞቹን ገድሎ በአባቱ ወገኖች ላይ ስለአደረገው ክፉት (ግፍ) ፈንታ ነገርን ከፈለው ማለት አጽንቶ ተጣላው፤ በጋሻ ጃግሬው እጅ መሞቱ እግዚአብሔር ቢጣላው ነውና ፤

፶፯፡ ወኵሎ እኪቶሙ ለሰብአ ሰቂማ ፈደዮሙ እግዚአብሔር ላዕለ ርእሶሙ ወበጽሖሙ መርገመ ኢዮአታም ወልደ ሮብአም ፤

የሰቂማንም ሰዎች በሠሩት ክፉት ሁሉ እግዚአብሔር ፈርዶ በልጆቻቸው ያይደለ በራሳቸው ላይ ፍዳ አመጣባቸው ፤ የሮአብም ልጅ የኢዮአታም መርገምም ደረሰባቸው ፤ «ኩኑ ቡሩካነ» ብሎ ረግሟቸው ነበርና ፤

## ምዕራፍ ፲

### ጉባዔ

፩፡ ወቆመ እምድኅረ አቤሜሌክ ዘያድኅኖሙ ለእስራኤል ቶላ ወልደ ፎሐ ወልደ እኍሁ ለአቡሁ ብእሲ እምይሳኮር ፤

አቤሜሌክ ከሞተ በኋላም እስራኤልን ከመከራ የሚያድናቸው ፤ አንድም ከአምልኮተ ጣዖት ለአሕዛብ ከመገዛት የሚያድናቸው ከነገደ ይሳኮር የተወለደ የአቤሜሌክ አባት የጌዴዎን የወንድሙ ልጅ የሚሆን የፎሐ ልጅ ቶላ በመስፍንነት ተነሣ ፤ (ሐተታ) ወልደ ፎሐ ብሎ ለቶላ ወልደ እኍሁ ብሎ ለፎሐ ቀጠለ ፤ የፎሐ አባትና ጌዴዎን ወንድምአማቾች ናቸውና ፤ አንድም ወልደ እኍሁ ለአቡሁ ይላል የአባቱ የወንድም ልጅ የሚሆን ብሎ ለቶላ ይቀጥላል ፤ ለፎሐ ታላቅ ወንድም ነበረው ሚስት አግብቶ ሳይወልድ ሙቷል ፤ ፎሐ አቅም ዘርአ ለእኍከ ባለው ትእዛዝ የወንድሙን ሚስት አግብቶ



ቶላን ወልዶለታል በልደት ሥጋዊ ወልደ ፎሐ በልደት ሕጋዊ ወልደ እኍሁ ለአቡሁ አለው ፤

ወውእቱሰ ይነብር ውስተ ሳምር ውስተ ደብረ ኤፍሬም ፤

«ውእቱኒ» ሲል ነው ፤ ቶላም በኤፍሬም ዕጣ ውስጥ ሳምር በምትባል አገር ይኖር ነበር ፤ ሳምር ባለው ሰማርያ ይላል ሠመርናሃ ማለት ነው ፤

፪፡ ወኮነኖሙ ለእስራኤል ፳ወ፫ተ ዓመተ ወሞተ ወተቀብረ ውስተ ሳምር ፤

እስራኤልንም ፳፫ ዓመት በመስፍንነት ገዝቶ ሞተ ፤ በሀገሩ በሰማርያ ውስጥ ተቀበረ ፤

፫፡ ወቆመ እምድኅሬሁ ኢያእር ገለዓዳዊ ወኮነኖሙ ለእስራኤል ፳ወ፪ተ ዓመተ ፤

ቶላ ከሞተ በኋላም የገለዓድ ሰው (ወገን) ኢያእር በመስፍንነት ተነሣ ፤ እስራኤልንም ሃያ ሁለት ዓመት ገዛቸው ፤

፬፡ ወቦኡ ፴ወ፪ቱ ደቂቅ ወይጼዓኑ ላዕለ ፴ወ፪ቱ አዕዱግ ወቦሙ ፴ወ፪ቱ አህጉር ወሰመዮሙ ደብራተ ኢያእር እስከ ዮም ወሀለዋ ውስተ ገለዓድ ፤

ለኢያእር ሠላሳ ሁለት ልጆች ነበሩት፤ እነዚህም የሚቀመጡባቸው ሠላሳ ሁለት የጭን በቅሎዎች የሚገዟቸው ሠላሳ ሁለት አኅሮች ነበሯቸው ፤ እሊህም አገሮች እስከዛሬ ድረስ በገለዓድ ውስጥ ለልጆቹ የሰጣቸው የኢያእር ጉልቶች ተብለው ሲጠሩ ኖሩ ፤

፭፡ ወሞተ ኢያእር ወተቀብረ ውስተ ሪሞ ፤

ኢያእርም የተሰጠውን ዘመን ጨርሶ ሞተ ሪሞ በምትባል አገር ውስጥም ተቀበረ ፤ አንድም ሪም (ጉልት) ሊሆነው በገዛው ቦታ ውስጥ ተቀበረ ፤

፮፡ ወደገሙ ደቂቀ እስራኤል ገቢረ እከይ ቅድመ እግዚአብሔር ወአምለክዎሙ ለበዓሊም ወለአስጣሮት ወለአማልክተ ሶርያ ወለአማልክተ ሲዶና ወለአማልክተ ሞዓብ ወለአማልክተ ደቂቀ አሞን ወለአማልክተ ኢሎፍሊ ወኀደግዎ ለእግዚአብሔር ወኢተቀንዩ ሎቱ ፤

የእስራኤል ልጆችም ዳግመኛ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ሠሩ እነሱስ የሚበድሉ በየጊዜው ነው ፤ ለልጆቻቸው «ደገመ» አለ ፤ በሰውና በከዋክብት አምሳል የተሠሩ ጣዖታትን አመለኩ፤ የሶርያና የሲዶናን የሞዓብንና የዓሞንን የኢሎፍላውያን ንም ጣዖታት አመለኳቸው ፤ እግዚአብሔርንም በሕግ በአምልኮት ተዉት፤ ለርሱም አልተገዙም ፤ (ሐተታ) ምነው አንዱ

www.ethiopianorthodox.org

ጣዖት አይበቃቸውምን ስለምን እሊህን ሁሉ አነሣ ቢሉ ከእገሌ ጣዖት የእገሌ ጣዖት ይበልጣል፤ ገንዘብ ያበዛል ፤ ልጅ ያሳድጋል እያሉ ካንዱ ወዳንዱ ሲባክኑ ይኖራሉና ፡

፯፡ ወተምዓ መዓተ እግዚአብሔር ላዕለ ደቂቀ እስራኤል ወአግብአሙ ውስተ እደ ኢሎፍሊ ወውስተ እዴሆሙ ለደቂቀ አሞን ፤

እግዚአብሔርም በእስራኤል ልጆች ላይ አጥብቆ ተቆጣ፤ ስለ ዚህም በኢሎፍላውያንና በአሞን ልጆች እጅ ጣላቸው ፡

፰፡ ወሣቀይዎሙ ወአጠቅዎሙ ለደቂቀ እስራኤል በማዕዶተ ዮርዳኖስ በምድረ አሞሬዎን በገለዓድ ፤

እነዚህም በዮርዳኖስ ማዶ ባለ በአሞሬዎን አገር በገለዓድ የእስራኤልን ልጆች አስጨነቋቸው መከራም አጸኑባቸው ፡

፱፡ ወአደዉ ደቂቀ አሞን ዮርዳኖስ ይትቃተልዎሙ ለደቂቀ ይሁዳ ወለ ብንያም ወለቤተ ኤፍሬም ወተሣቀዩ ደቂቀ እስራኤል ጥቀ ፤

የአሞን ልጆች የይሁዳንና የብንያምን ልጆች የኤፍሬምን ወገኖች ይወጓቸው ዘንድ ዮርዳኖስን ተሻገሩ ፤ የእስራኤልም ልጆች እጅግ ተሠቃዩ ፡

፲፡ ወገዐሩ ደቂቀ እስራኤል ኀበ እግዚአብሔር ወይቤሉ አበስነ ለከ እስመ ኀደግናከ ለአምላክነ ወአምለክናሁ ለበዓሊም ፤

የእስራኤልም ልጆች መከራው ቢያማታቸው ፈጣሪያችን አንተን ትተን ጣዖትን አምልከናልና አንተን በድለናል እያሉ ወደ እግዚአብሔር ጮኸው አለቀሱ ፡

፲፩፡፲፪ ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ለደቂቀ እስራኤል አኮኑ ግብፅ ወአሞሬዎን ወደቂቀ አሞን ወሞአብ ወኢሎፍሊ ወሲዶና ወምድያም ወአማሌቅ ሣቀዩክሙ ወገዐርክሙ ኀቤየ ወአድኀንኩክሙ እምእዴሆሙ ፤

እግዚአብሔርም የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ በወጣችሁ ጊዜ የነዚህ ወገኖች ሁሉ መከራ ቢያጸኑባችሁ ወደ እኔ አለቀሳችሁ ፤ እኔም ከነዚህ ሁሉ እጅ አዳንኳችሁ ፡

፲፫፡ ወአንትሙሰ ኀደግሙኒ ወአምለክሙ ባዕዳነ አማልክተ በበይነ ዝንቱ ኢያድኀንክሙ ፤

እናንተ ግን እኔን ትታችሁ የማያድኑ ልዩ የሆኑ ጣዖታትን አመለካችሁ ፤ ስለዚህ እኔም አላድናችሁም ፡

፲፬፡ ሑሩ ወጽርሑ ኀበ አማልክት ዘኀረይክሙ ለክሙ ወያድኅኑክሙ በመዋዕለ ምንዳቤክሙ ፤

አሁንም ወደመረጣችኋቸው ጣዖታት ሒዳችሁ ጮኹ፤ በመከራ



ችሁ ቀን እነሱ ያድኗችሁ አላቸው ፡

፲፭፡ ወይቤልዎ ደቂቀ እስራኤል ለእግዚአብሔር አበስነ ረስየነ ዘከመ ትፈቅድ በቅድሜከ ወባሕቱ እግዚኦ አድኅነነ በዛቲ ዕለት ፤

የእስራኤል ልጆችም እግዚአብሔርን አዎን በድለናል ፤ በዚች ቀን ከጠላቶቻችን አድነን እንጂ በፊትህ ነን ፤ አንተ እንደወደድህ አድርገን አሉት ፡

፲፮፡ ወአሰሰሉ አማልክተ ባዕድ እማዕከሎሙ ወአምለክዎ ለእግዚአብሔር ወአሥመርዎ ወአንበዘ እምነ ሥቃይ ደቂቀ እስራኤል ፤

ከዚህ በኋላ ልዩ የሆኑ ጣዖታትን ከመካከላቸው አስወግደው እግዚአብሔርን አመለኩት፤ በሕግ በአምልኮት ደስ አሰኙት፤ ከመከራው ጽናት የተነሣ አእምሮዋቸውን እስከማጣት ደርሰው ጮኹ አለቀሱ ፡

፲፯፡ ወዐርጉ ደቂቀ አሞን ወኀደሩ ውስተ ገለዓድ ወወፅኡ ደቂቀ እስራ ኤል ወኀደሩ ውስተ ደብረ መሴፋ፤

በዚያ ወራት የአሞን ልጆች ለጦርነት ወጥተው በገለዓድ ሠፍረው አደሩ ፤ የእስራኤልም ልጆች ወንድን ይሉን ሴት ብለው ወጥተው መሴፋ በምትባል ተራራ ሠፈሩ ፡

፲፰፡ ወተበሃሉ መላእክተ ሕዝበ ገለ ዓድ በበይናቲሆሙ መኑ ብእሲ ዘይእኅዝ ይትቃተሎሙ ለነ ለደቂቀ አሞን ወይኩን ርእሰ ለኵሉ እለ ይነብሩ ውስተ ገለዓድ ፤

የገለዓድ ወገን አለቆችም እርስ በርሳቸው ከአሞን ልጆች ጋር ይዋጋልን ዘንድ፤ በገለዓድ በሚኖሩ ሰዎችም ሁሉ አለቃ ይሆን ዘንድ መዋጋትን የሚጀምርልን ሰው ማነው ? ተባባሉ ፡ አን ድም አለቃ ሁኖ ያዋጋን ሰው በገለዓድ ለሚኖሩ እስራኤል ሁሉ ገዥ ይሁን አሉ ።

## ምዕራፍ ፲፩

፩፡ ወዮፍታሔ ገለዓዳዊ ጽኑዕ ወኃያል ወወልደ ብእሲት ዘማ ውእቱ ወወለዶ ለዮፍታሔ እምገለዓድ ፤

የገለዓድ ሰው ዮፍታሔም በዚያ ወራት በዕውቀት በጉልበት ፈጽሞ የበረታ ሰው ነበረ፤ እሱም ከሕግ ከወጣች (ከጋለሞታ) ሴት የተወለደ ነበረ ፤ ይህችም ሴት ዮፍታሔን ከገለዓድ ወለደችው ፡

፪፡ ወወለደት ሎቱ ለገለዓድ ብእሲቱ አግዓዚት ደቂቀ ወልሕቁ ደቂቃ ለይ እቲ ብእሲት ፤

በሕግ ያገባት ሚስቱም ለገለ ዓድ ወንዶች ልጆች ወለደች ለት ፤ እነዚህም በአባት አንድ ናቸውና ከዮፍታሔ ጋር በአን ድነት አደጉ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወአውፅእዎ ለዮፍታሔ ወይቤልዎ ኢትወርስ ውስተ ቤተ አቡነ እስመ ወልደ ካልዕት ብእሲት አንተ ።

አባታቸው ገለዓድ ከሞተ በኋላ እነዚህ ልጆቹ ርስት ይጠበናል፤ ገንዘብ ያንሰናል ብለው ዮፍታሔን አንተ ከሕግ ከወጣች ሴት የተወለድህ ነህና ባባታችን ቤት ውስጥ ርስት ወርሶ መኖር አይገባህም ሲሉ ከወንድምነት አወጡት፤ ካወራረስም ለዩት ።

፫፤ ወሖረ ዮፍታሔ እምገጸ አኃዊሁ ወነበረ ውስተ ምድረ ጦፍ ወይጸመድዎ ለዮፍታሔ ሰብእ ነዳያን ወየሐውሩ ምስሌሁ ።

ዮፍታሔም ሲጠሉኝ ብሎ ከወንድሞቹ ፊት ርቆ የአባቱን አገር ለቆ ጦፍ በምትባል ምድረ በዳ አገር አቅንቶ ተቀመጠ፤ ገንዘብ የሌላቸው ሰዎችም ተሰብስበው አብረው እየወጡ እየወረዱ ያገለግሉት ጀመር አሁን ብዛቱን አይተው ነዓ ኩነነ መስፍነ የሚሉት ነውና ።

፬፤ ወእምድኅረ መዋዕል ተቃተልዎሙ ደቂቀ አሞን ለእስራኤል ።

ከዚያም ወራት በኋላ የአሞን ልጆች መጥተው እስራኤልን ይወጓቸው ጀመር ።

፭፤ ወሖሩ ሊቃናተ ገለዓድ ይንሥእዎ ለዮፍታሔ እምድረ ጦፍ ።

የገለዓድ ሽማግሌዎችም ዮፍታሔን ከጦፍ ምድረበዳ አባብለው ያመጡት ዘንድ ሔዱ።

፮፤ ወይቤልዎ ለዮፍታሔ ነዓ ኩነነ መስፍነ ወንትቃተሎሙ ለደቂቀ አሞን ።

ሒደውም ዮፍታሔን የአሞንን ልጆች እንወጋቸው ዘንድ ናመሪ ሁነን አሉት፤ አንድም መሪ ሁነንና የአሞንን ልጆች እንውጋቸው አሉት ።

፯፤ ወይቤሎሙ ዮፍታሔ ለሊቃናተ ገለዓድ አኮኑ አንትሙ ጸላእክሙኒ ወአውፃእክሙኒ እምነ ቤተ አቡየ ወአውፃእክሙኒ እምነ ቤክሙ ለምንት እንከ መፃእክሙ ኀቤየ ይእዜ ሶበ ተመንደብክሙ ።

ዮፍታሔም የገለዓድን ሽማግሎች እናንተማ ጠልታችሁኝ ከአባቴ ቤት አስወጥታችሁኝ አልነበረምን፤ ካጠገባችሁ ከአስወጣችሁኝ በኋላ ዛሬ በመከራ ስትጨነቁ ወደ እኔ ለምን መጣችሁ አላቸው ።

፰፤ ወይቤልዎ ሊቃናተ ገለዓድ ለዮፍታሔ አኮ ከመዝ መጻእነ ኀቤከ ከመ ትሑር ምስሌነ ወትትቃተል ለነ ምስለ ደቂቀ አሞን ወትኩነነ ርእሰ ለኵሉ እለ ይነብሩ ውስተ ገለዓድ



የገለዓድም ሽማግሌዎች ዮፍታሔን ከእኛ ጋራ ሒደህ የአሞንን ልጆች ብቻ ልታጠፋ ልን የመጣን አይደለም «አላ» ያለበት ነው፤ በገለዓድ ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ አለቃ(መሪ) ትሆነን ዘንድ ነው እንጂ ።

፱፤ ወይቤሎሙ ዮፍታሔ ለሊቃናተ ገለዓድ እመ ትኔሥኡኒ አንትሙ ከመ እትቃተሎሙ ለደቂቀ አሞን እምከመ አግብአሙ እግዚአብሔር ቅድሜየ አነ እከውነክሙ ርእሰ ።

ዮፍታሔም የገለዓድን ሽማግሌዎች የአሞንን ልጆች እወጋቸው ዘንድ እናንተ ከወሰዳችሁኝ የአሞንን ልጆች እግዚአብሔር በእጄ አሳልፎ ቢጥላቸው አለቃ መሪ እንድሆናችሁ ስመ እግዚአብሔርን ጠርታችሁ ማሉልኝ አላቸው፤

፲፤ ወይቤልዎ ሊቃናተ ገለዓድ ለዮፍታሔ እግዚአብሔር ስምዕነ በማዕከሌነ ከመ በከመ ትቤ ከማሁ ንገብር ።

ከመና ከመ አንድ ወገን ። የገለዓድ ሽማግሌዎችም ዮፍታሔን ያልከውን እንድ ናደርግ በአንተና በእኛ መካከል ምስክራችን እግዚአ [illegible] ም እግዚአብሔር በአንተ እና በእኛ መካከል ምስክር ይሁን አሉት፤

፲፩፤ ወሖረ ዮፍታሔ ምስለ ሊቃናተ ገለዓድ ወሤምዎ ሕዝብ ሊቃነ ርእሰ ከመ ይኩኖሙ መሥፍነ ወነገረ ዮፍታሔ ኵሎ ቃሎ ቅድመ እግዚአብሔር በመሴፋ ።

ዮፍታሔም እግዚአብሔርን ምስክር አድርጎ ከገለዓድ ሽማግሌዎች ጋራ ወደ ገለዓድ ሔደ፤ በገለዓድ ያሉ ወገኖችም መሪ ይሆናቸው ዘንድ ለነሱ መሪ አድርገው ሾሙት፤ ዮፍታሔም መሴፋ ወጥቶ ነገሩን ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ተናገረ ያለፈውን ፤ አንድም ለእግዚአብሔር ተሳለ፤ ወደፊት የሚያመጣውን ።

፲፪፤ ወፈነወ ዮፍታሔ መላእክተ ኀበ ንጉሦሙ ለደቂቀ አሞን እንዘ ይብል ምንት ብከ ምስሌየ ከመ ትምጻእ ትትቃተለኒ ውስተ ብሔርየ፤

ዮፍታሔም ወደ ሀገሬ መጥተህ ትወጋኝ ዘንድ ከእኔ ጋር ምን ጠብ አለህ ብሎ ወደ አሞን ልጆች ንጉሥ መልእክተኞችን ላከ ።

፲፫፤ ወይቤ ንጉሦሙ ለደቂቀ አሞን ለእለ ለአከ ዮፍታሔ እስመ ነሥኡ እስራኤል ምድርየ አመ የዐርጉ እምግብጽ እምአርኖን እስከ ኢያቦቅ ወእስከ ዮርዳኖስ ።

www.ethiopianorthodox.org

የአሞን ልጆች ንጉሥም ዮፍታሔ ለላካቸው ሰዎች ፳ኤል ከግብጽ በወጡ ጊዜ ከአርኖን ጀምሮ እስከ ኢያቦቅና እስከ ዮርዳኖስ ድረስ ያለ አገሬን ወስደውብኛልና ፤

ወይእዜኒ አግብእ ሊተ በሰላም ወገብኡ እለ ለአከ ዮፍታሔ ኀቤሁ ለዮፍታሔ ፤

አሁንም አንጣላ ካልክ አገሬን በፍቅር መልስልኝ በሉት አላቸው፤ ዮፍታሔ የላካቸው ሰዎችም ይህን መልስ ይዘው ወደ ዮፍታሔ ተመለሱ ፤

፲፬፤ ወፈነወ ዓዲ ዮፍታሔ ሐዋርያተ ኀበ ንጉሦሙ ለደቂቀ አሞን፤

ዮፍታሔም ከቀደመው ይልቅ አበርትቶ ወደአሞን ልጆች ንጉሥ ዳግመኛ መልእክተኞችን ላከ ፤

፲፭፤ ወይቤሎ ከመዝ ይቤ ዮፍታሔ ኢነሥኡ ፳ኤል ምድረ ሞዓብ ወምድረ ደቂቀ አሞን አመ የዐርጉ እምግብጽ ፤

እስራኤል ከግብጽ በወጡ ጊዜ የሞዓብንና የአሞንን ልጆች ሀገር አልወሰዱም ፤

፲፮፤ አላ ሖሩ ፳ኤል ውስተ ገዳም እስከ ባሕረ ኤርትራ ወበጽሑ እስከ ቃዴስ ፤

እስራኤል ከግብጽ ወጥተው ኤርትራን ተሻግረው በምድረ በዳ ተጉዘው ቃዴስ ከሚባል በረሀ ደረሱ እንጂ አለ ብለው ነገሩት ፤

፲፯፤ ወፈነወ ፳ኤል ሐዋርያተ ኀበ ንጉሠ ኤዶም እንዘ ይብል አኅልፈኒ እንተ ምድርከ ወአበየ ንጉሠ ኤዶም ወሀበኒ ንጉሠ ሞዓብ ለአከ ወአበየ ወነበረ ፳ኤል ውስተ ቃዴስ ፤

ያን ጊዜም ፳ኤል ቃዴስ ሲደርስ በሀገርህ ላይ መንገድ ሰጥተህ አሳልፈኝ ብሎ ወደ ኤዶም ንጉሥ መልእክተኞቹን ላከ ፤ የኤዶም ንጉሥም አይሆንም ብሎ መለሰ ፤ ወደ ሞዓብ ንጉሥም ቢልክ አይሆንም ብሎ ላከበት ፤ ፳ኤልም የሚያልፍበት መንገድ ቢያጣ በቃዴስ በረሀ ተቀመጠ ፤

፲፰፤ ወኀለፉ እንተ ገዳም ወዖዱ ምድረ ኤዶም ወምድረ ሞዓብ ወበጽሑ መንገለ ጽባሒሁ ለምድረ ሞዓብ ወኀደሩ ውስተ ማዕዶተ አርኖን ወኢቦኡ ውስተ ደወለ ሞዓብ እስመ አርኖን ይእቲ ደወሎሙ ለሞዓብ ፤

ከብዙ ቀን በኋላ በምድረ በዳው አልፈው የኤዶምና የሞዓብን አገር ዞረው ከሞዓብ አገር ምሥራቅ አንፃር ደርሰው በአርኖን ማዶ ሠፈሩ እንጂ ወደ ሞዓብ አውራጃ አልገቡም፤ አርኖንም የሞዓብ ወሰናቸው ናት ፤



፲፱፤ ወፈነወ ፳ኤል ሐዋርያተ ኀበ ሴዎን ንጉሠ ሐሴቦን አሞራዊ ወይቤሎ ፳ኤል አኅልፈኒ እንተ ምድርከ እስከ ብሔርየ ፤

እስራኤልም ከዚያ ሠፍሮ ወደ አገሬ እስክገባ ድረስ በአገርህ አሳልፈኝ ብሎ ወደ ሐሴቦን ንጉሥ ወደ አሞራዊ ወደ ሴዎን መልእክተኞችን ላከ ፤

፳፤ ወአበየ ሴዎን አኅልፎቶሙ ለ፳ኤል እንተ ደወሉ ወአስተጋብአ ሴዎን ሕዝቦ ወኀደረ ውስተ ኢያሴር ወተቃተሎሙ ለ፳ኤል ፤

ሴዎንም ፳ኤልን በአውራጃው አላሳልፍም ብሎ ሠራዊቱን ሰብስቦ ኢያሴር ከምትባል አገር ሠፍሮ ፳ኤልን ተዋጋቸው ፤

፳፩፤ ወአግብኦሙ እግዚአብሔር አምላከ ፳ኤል ለሴዎን ወለኵሉ ሕዝቡ ውስተ እዴሆሙ ለ፳ኤል ወቀተልዎሙ ወተዋረስዎሙ ፳ኤል ኵሎ ምድሮሙ ለአሞሬዎን እለ ይነብሩ ውስተ ይእቲ ምድር ፤

የ፳ኤል ፈጣሪ እግዚአብሔርም ሴዎንንና ሠራዊቱን በ፳ኤል እጅ ጣላቸው ፳ኤልም በዚያች ምድር የሚኖሩ አሞራውያንን አጥፍተው ምድራቸውን /አገራቸውን/ ወረሱባቸው ፤

፳፪፤ ወተዋረሱ ኵሎ ደወሎሙ እምአርኖን እስከ ኢያቦቅ ወእም ገዳም እስከ ዮርዳኖስ ፤

ከአርኖን እስከ ኢያቦቅ ከቃዴስ እስከ ዮርዳኖስ ያለውን አውራጃቸውን ሁሉ ወረሱ ፤

፳፫፤ ወይእዜኒ እግዚአብሔር አምላከ ፳ኤል አሰሰሎሙ ለአሞሬዎን እምቅድመ ገጾሙ ለ፳ኤል ወአንተኑ ትትዋረስ በዕብሬትከ ፤

የ፳ኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር አሞሬዎንን ከ፳ኤል ፊት አርቋቸዋል /አስወግዷቸዋል/፤ አሁን አንተ ኃይል አገኘሁ ብለህ የ፳ኤልን አገር ልትወርስ ነውን ፤

፳፬፤ አኮኑ ከሞስ አምላክከ ዘአውረሰከ ኪያሁ ዳዕሙ ትትዋረስ ወኵሎ ዘአውረሰነ እግዚአብሔር አምላክነ ቅድሜነ ኪያሁ ንትዋረስ ፤

አምላክህ ከሞስ ያወረሰህን ብቻ የምትወርስ አይደለምን እኛስ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር በፊታችን ያወረሰንን ሁሉ የምንወርስ አይደለምን ፤

፳፭፤ ወይእዜኒ ቦኑ አንተ ትኄይስ እምባላቅ ወልደ ሶፎር ንጉሠ ሞዓብ ቦኑ ባዕሰ ተበአሰ ምስለ ፳ኤል አው ጸብአ ተጻብአሙ ለቤተ ፳ኤል ፤

www.ethiopianorthodox.org

በውኑ ከሞዓብ ንጉሥ ከባላቅ ወልደ ሶፎር አንተ ትበልጣለህን ፤ እሱ ከእስራኤል ጋር ተጣላን ፤ የእስራኤልንስ ወገኖች በሰልፍ ተዋጋቸውን ፤

፳፮፤ በሐሴቦን ወበአዋልዲሃ ወበያዜር ወበአዋልዲሃ ወበኵሉ አህጉር ዘኀበ አርኖን ፫፻ተ ዓመተ ለምንት ኢያድኀንዎሙ ለዝንቱ ባዕል ፤

በሐሴቦንና በጥቃቅን አገሮቿ በአርኖን ባሉ አገሮችም ሁሉ በያዜርና በጥቃቅን አገሮቿ ካንተ አስቀድመው የነበሩ ነገሥታት ሦስት መቶ ዘመን ሲኖሩ ለምን አላዳኗቸውም ፤ አንድም ከአንተ አስቀድመው የነበሩ ነገሥታት ያዳኗቸውን በ፫፻ዘመን ተነሥተህ አንተ ልታድናቸው ነውን ፤

፳፯፤ ወአንሰ ኢአበስኩከ ለከ ወአንተሰ ኢትገብር እኪተ ምስሌየ ከመ ትትቃተለኒ ወይፍታሕ እግዚአብሔር ዘውእቱ ይፌትሕ ዮም ማዕከለ ደቂቀ እስኤል ወማዕከለ ደቂቀ አሞን ፤

እኔ አንተን አልበደልኩህም፤ አንተም ከኔ ጋራ ትዋጋ ዘንድ ክፉ ነገር አታድርግ ፤ አሁንም በእውነት የሚፈርድ እሱ እግዚአብሔር በእስኤል ልጆችና በአሞን ልጆች መካከል ይፍረድ ብሎ ላከበት ፤

፳፰፤ ወአበዮሙ ንጉሠ ደቂቀ አሞን ወኢሰምዐ ቃለ ዮፍታሔ ዘለአከ ሎቱ ፤

የአሞን ልጆች ንጉሥም መልእክተኞቹ የነገሩትን አልተቀበላቸውም ፤ የላከለት የዮፍታሔንም ቃል አልሰማም ፤

፳፱፤ ወመጽአ መንፈሰ እግዚአብሔር ላዕለ ዮፍታሔ ወአደወ እምድረ ገለዓድ ዘምናሴ እመሴፋ ዘገለዓድ ውስተ ማዕዶቶሙ ለደቂቀ አሞን ፤

የእግዚአብሔር መንፈስ ረድኤትም በዮፍታሔ አደረበት /አጸናው/ ፤ የመሴፋ አውራጃ ከምትሆን ከምናሴ ዕፃ ከገለዓድ ተነሥቶ ወደ አሞን ልጆች ማዶ ተሻገረ ፤

፴፤፴፩፤ ወበጽአ ዮፍታሔ ብፅዓተ ለእግዚአብሔር ወይቤ ለእመ አግብኦሙ ለደቂቀ አሞን ውስተ እዴየ ፤

ዘመጽአ ወወፅአ እምኆኅተ ቤትየ ወተቀበለኒ ሶበ ገባእኩ በዳኅን እምኀበ ደቂቀ አሞን ለእግዚአብሔር እሬስዮ መሥዋዕተ ፤

ዮፍታሔም እግዚአብሔር የአሞንን ልጆች አሳልፎ በእጄ ቢጥላቸው ድል አድርጌ ከአሞን ልጆች ዘንድ በደኅና የተመለስኩ እንደሆነ መጀመሪያ ከቤቴ ደጃፍ ወጥቶ የተቀበለኝን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አደርገዋለሁ ብሎ ተሳለ ፤ ይህም አርእስት ነው ፤



፴፪፤ ወአደወ ዮፍታሔ ኀበ ደቂቀ አሞን ይትቃተሎሙ ወአግብኦሙ እግዚአብሔር ውስተ እዴሁ ፤

ዮፍታሔም የአሞንን ልጆች ይወጋቸው ዘንድ ወደ አሞን ልጆች ተሻገረ ፤ እግዚአብሔርም የአሞንን ልጆች አሳልፎ በዮፍታሔ እጅ ጣላቸው ፤

፴፫፤ ወቀተሎሙ እምአሮኤር እስከ ይበጽሕ ውስተ ኤሞኢት እሥራ አህጉር እስከ አቤል አዕፃደ ወይን ዓቢየ ቀትለ ጥቀ ወገረሩ ደቂቀ አሞን ቅድመ ደቂቀ እስኤል ፤

ከአሮኤር ጀምሮ ኤሞኢት እስኪደርስ ድረስ አጠፋቸው፤ እነዚህም ሃያ አገሮች ናቸው፤ የወይን ቦታ እስከሚሆን እስከ አቤል ድረስ እጅግ ጽኑ ሰልፍ አድርጎ እነዚህን ሁሉ አጠፋቸው ፤ ከሞት የቀሩ የአሞንም ልጆች በእስኤል ፊት ወድቀው ተገዙ ፤

፴፬፤ ወአተወ ዮፍታሔ ውስተ መሴፋ ውስተ ቤቱ ወናሁ ወለቱ ወጽአት ወተቀበለቶ ምስለ ከበሮ ወመሰንቆ ወይእቲ ባሕቲታ ሎቱ እንተ ያፈቅራ ወአልቦ ባዕድ ውሉድ ዘእንበሌሃ ኢወልድ ወኢወለት ፤

ዮፍታሔም ድል አድርጎ በመሴፋ ወደ አለ ቤቱ በተመለሰ ጊዜ እነሆ የሚወዳት ልጁ መሰንቆና ከበሮ ይዛ ከባልንጀሮቿ ጋር ወጥታ ተቀበለችው ፤ ለእሱም ከእርሷ በቀር ወንድም ሴትም ልጅ አልነበረውም ፤

፴፭፤ ወሶበ ርእየ ሠጠጠ አልባሲሁ ወይቤ አሌ ሊተ ወለትየ አዕቀጽክኒ ወዕፁበ ኮንክኒ ውስተ አዕይንትየ ወአንሰ ፈታሕኩ አፉየ ኀበ እግዚአብሔር በእንቲአኪ ወኢይክል ዓሊዎቶ ፤

አስቀድማ እንደወጣች ባየት ጊዜም ልብሱን ቀደደ ፤ ትእምርተ ኀዘን፤ ወየውልኝ ልጄ አሰነካከልሽኝ በፊቴም ጭንቅ ሆንሽብኝ አላት ፤እሷም ምን አደረግሁ ብትለው እኔ አንችን እሰዋለሁ ብዬ በእግዚአብሔር ዘንድ ስለት ተስያለሁና የተሳልኩትን ማስቀረት አልችልም አላት፤ ሐተታ አሁን እሷን እሠዋለሁ ብሎ ተስሎ አይደለም ፤ ኀይል ሰጥተኸኝ ድል አድርጌ ብመለስ ከፊቴ ያገኘሁትን እሠዋለሁ ብሎ ተስሎ ነበረ ፤ እንዲህም ማለቱ ድምጹን ሲሰማ ከሩቅ

www.ethiopianorthodox.org

ሲያየው ወጥቶ የሚቀበለው ለማዳ በግ ነበረው በሕሊና እሱን እሠዋለሁ ብሎ ተስሎ ነበር ፤ አስቀድማ እሷ ወጥታ ብትቀበለው «በእንተ አኪ» አለ ፡

፴፮፤ ወትቤሎ አባ ለእመ በእንተ አፃ ፈታሕከ አፉከ ኀበ እግዚአብሔር ረሰየኒ በከመ ወፅአ እምአፉከ እስመ ገብረ ለከ እግዚአብሔር በቀለ እምፀርከ እምደቂቀ አሞን ፤

እሷም አባቴ እኔን እሠዋለሁ ብለህ ወደ እግዚአብሔር ከተሳልክ እግዚአብሔርም ከጠላቶችህ ከአሞን ልጆች በቀልን አድርጎልሃልና ማለት ተበቅሎ ጠላቶችህን አጥፍቶ ልሃልና በአንደበትህ እንደ ተሳልክ ሠዋኝ አለችው ፡

፴፯፤ ወትቤሎ ለአቡሃ ረሲ ሊተ ዘንተ ቃለ አብሐኒ ፪ተ አውራኃ እሑር ወእዕርግ ውስተ አድባር ወእብኪ ላዕለ ድንግልናየ ምስለ ካልዓትየ ፤

አባቷንም ይህን ነገር አድርግልኝ አለችው ፤ ሁለት ወር አሰናብተኝ እና ወደ ተራራ ወጥቼ ከጓደኞቼ ጋር ለድንግልናዬ ላልቅስ አለችው ፤ ድንግልና በዘመናቸው ክቡር ነበርና ፡

፴፰፤ ወይቤላ ሑሪ ወፈነዋ ክልዔተ አውራኃ ወሖረት ይእቲ ወካልዓቲሃ ወበከየት ላዕለ ድንግልናሃ ምስለ ካልአቲሃ በውስተ አድባር ፤

አባቷም ይሁን ሒጂ ብሎ ሁለት ወር አሰናበታት፤ እሷም ከጓደኞቿ ጋር ወደተራራ ወጥታ ለድንግልናዋ ሁለት ወር አለቀሰች ፡

፴፱፤ ወእምድኅረ ኀልቀ ፪ቱ አውራኅ ገብአት ኀበ አቡሃ ወገብረ ዮፍታሔ ብፅዓቲሁ ዘበፅዓ ወይእቲሰ ኢተአምር ብእሴ ወኮነት ዛቲ ሕግ በውስተ ፳ኤል በበዓመት፤

ሁለት ወር ከተፈጸመ በኋላ ወደ አባቷ ተመለሰች ፤ ዮፍታሔም ለእግዚአብሔር የተሳለውን ስለት አደረገ አለ ፤ ልጁን ሠዋ ፤ ይህችም ሕፃን ወንድ አታውቅም ነበር ፤ ይህችም ሕግ በ፳ኤል ዘንድ ጸንታ ኖረች አለ ያምጣው ፡

፵፤ ወለለመዋዕለ ዕለታ የሐውራ አዋልደ ፳ኤል ይብክያሃ ለወለተ ዮፍታሔ ገለዓዳዊ ረቡዓ መዋዕለ ለለዓመት ፤

ለገለዓድ ሰው ለዮፍታሔ ልጅ በዓመት አራት ቀን ያለቅሱላት ዘንድ የ፳ኤል ሴቶች ልጆች በዓመት በዓመት ሊያለቅሱ ወደተሠዋችበት ቦታ ይሔዱ ነበር ፤ «ኮነት ዛቲ ሕግ» ያለውን ተረጒመው ።



## ምዕራፍ ፲፪

፩፤ ወተጋብኡ ደቂቀ ኤፍሬም ወመጽኡ ውስተ ሴፌና ወይቤልዎ ለዮፍታሔ ለምንት ሖርከ ትትቃተሎሙ ለደቂቀ አሞን ወኢጸዋ እከነ ከመ ንሑር ምስሌከ ናውዒ ቤተከ በላዕሌከ በእሳት ፤

የኤፍሬም ልጆችም የአሞንን ልጆች ድል መንሳት ሰምተው ዮፍታሔ ወደ አለበት ወደ ሴፌና ተሰብስበው መጥተው ዮፍታሔን የአሞንን ልጆች ለመውጋት ከአንተ ጋር እንሔድ ዘንድ ሳትጠራን ለምን ሔድህ? ለግዳይ ለምርኮ ሳስተህ አይደለምን ፤ አሁንም ቤትህን በላይህ ላይ በእሳት እናቃጥለዋለን አሉት ፡

፪፤ ወይቤሎሙ ዮፍታሔ ብእሲ ግፉዕ አነ ወሕዝብየ ወደቂቀ አሞን ማተዩኒ ጥቀ ወጸራሕኩ ለክሙ ወኢያድኀንክሙኒ እምእዴሆሙ ፤

ዮፍታሔም እኔ ከነወንድሞቼ የተበደልሁ ሰው ነኝ ፤ የአሞን ልጆች እጅግ መከራ አጸኑብን፤ ለእናንተም ብንጮኽ ከእጃቸው አላዳናችሁንም ፡

፫፤ ወሶበ ርኢኩ ከመ አልቦ ዘያድኅን አማባእክዋ ለነፍስየ ውስተ እዴየ ወአደውኩ ኀበ ደቂቀ አሞን ወአግብአሙ እግዚአብሔር ትድሜየ ወለምንት ዐረግሙ ኀቤየ ... ፤

የሚያድንም ሰው እንደሌለ ባየሁ ጊዜ ሰውነቴን በእጄ አሳልፌ ለሞት ሰጥቼ /ለመሞት ቆርጬ/ ወደ አሞን ልጆች ተሻገርኩ /ዘመትኩ/፤ እግዚአብሔርም ኀዘኔን ሰምቶ በእጄ አሳልፎ ጣላቸው ፡ ዛሬ የነሱን ድል መነሣት የእኔን ድል መንሣት አይታችሁ ልትወጉኝ /ልትጣሉኝ/ ለምን ወደ እኔ መጣችሁ? አላቸው ፡

፬፤ ወአስተጋብአሙ ዮፍታሔ ለኵሎሙ ሰብአ ገለዓድ ወተቃተሎሙ ለሰብአ ኤፍሬም ወቀተልዎሙ ሰብአ ገለዓድ ለኤፍሬም እስመ ይቤልዎሙ ድኅናን ኤፍሬም አንትሙ ፤

ዮፍታሔም በጠብ እንደመጡበት አውቆ በገለዓድ ያሉ ወገኖቹን ሁሉ ሰብስቦ ገጠማቸው ፤ የገለዓድ ሰዎች የኤፍሬምን ወገኖች ድል አደረጓቸው ፤ እናንተ ከነገደ ኤፍሬም የዳናችሁ /ያመለጣችሁ/ የኤፍሬም ልጆች ናችሁ ብለዋቸዋልና ፡

፭፤ ወበጽሕዎሙ በማዕከለ ምናሴ ሰብአ ገለዓድ በውስተ ማዕዶተ ዮርዳኖስ ዘኤፍሬም ወእምዝ ሶበ ይቤሉ ድኅናን ኤፍሬም ንዕዱ ይቤልዎሙ ሰብአ ገለዓድ አንትሙኑ በኑ እምኤፍሬም አንትሙ ወይቤሉ ኢኮነ ፤

www.ethiopianorthodox.org

የሸሹትንም የኤፍሬም ወገኖች የገለዓድ ሰዎች በምናሴ ዕጣ መካከል በዮርዳኖስ ማዶ ባለ በኤፍሬም ዕጣ ደረሱባቸው ከዚህም በኋላ ከኤፍሬም ወገኖች የዳኑት እንሻገር ባሉ ጊዜ የገለዓድ ሰዎች በውኑ እናንተ ከኤፍሬም ወገኖች አይደላችሁም? ቢሏቸው የኤፍሬም ልጆች አይደለንም አሉ ፤

፮፡ ወይቤልዎሙ በሉ መምህጻን ወአበዩ ብሂለ መምሕጻን ወአኀዝዎሙ ወቀተልዎሙ በውስተ ማዕዶተ ዮርዳኖስ ወወድቁ እም ኤፍሬም ይእተ አሚረ ፵፪፻ ወ፳፻ ፤

የገለዓድም ሰዎች የኤፍሬም ልጆች አይደለንም ስትሉ መምሕፃን በሉ አሏቸው ፤ ይኸውም እግዚአብሔር መማፀኛ ይሁንብን ማለት ነው ፤ እነሱም እግዚአብሔር መማፀኛ ይሁንብን አንልም አሉ ፤ ነገደ ኤፍሬም የፀጸ ያሮች ናቸው ፤ መምሕፃን እንላለን ብለው መምሕሳን ብለዋል፤ ዛሬ አገው የቀጸያፍ እንደሆነ በዚህ እየለዩ አጥፍተዋቸዋል ፤ አንድም በሉ ሸኮሊት አሏቸው ፤ ሸኮሊትም ማለት ለገደል ለማዕበል ይሰጠን ማለት ነው ፤ «ወአበዩ ብሂለ ሸኮሊት» ይላል ፤ ለገደል ለማዕበል ይስጠን አንልም አሉ ፤ በዚህ እየለዩ አጥፍተዋቸዋል፤ ያን ጊዜ ከነገደ ኤፍሬም ፵፪፻ ከ፪ሺህ / አርባ ሁለት ሺህ/ ሰዎች በጦር ተደብድበው ወደቁ ፤

፯፡ ወኮነኖሙ ለእስራኤል ዮፍታሔ ገለዓዳዊ ፮ተ ዓመተ ወሞተ ወተቀብረ ውስተ ሀገሩ ገለዓድ ፤

የገለዓድ ሰው ዮፍታሔም እስራኤልን መስፍን ሁኖ ፮ ሰዓት ገዛቸው ፤ ነቢይ ሁኖም አስተማራቸው ከዚያ በኋላ ሙቶ በሀገሩ በገለዓድ ተቀበረ፤

፰፡ ወኮነኖሙ ለእስራኤል እምድኅሬሁ ሐሴቦን ዘእምቤተ ልሔም ዘይሁዳ ፤

እሱ ከሞተ በኋላም የይሁዳ ዕጣ በምትሆን በቤተልሔም የተወለደ ሐሴቦን እስራኤልን መስፍን ሁኖ ገዛቸው ፤ እንደ ነቢይም ሁኖ አስተማራቸው፤

፱፡ ወወለደ ፴ ደቂቀ ወ፴ አዋልደ ወአስተዋሰበ ፴ እምአፍአ ወ፴ አንስተ ነሥአ ለደቂቁ እምአፍአ፤

ይህም ሐሴቦን ሠላሳ ወንዶች፣ ሠላሳ ሴቶች ልጆች ወለደ ፤ ሴቶች ልጆቹን ወደ ውጭ አጋባ ማለት ለአሕዛብ ዳራቸው ፤ ለወንዶች ልጆቹም ከአሕዛብ ወገን ፤ ሠላሳ ሴቶችን አጭ... [illegible]



፲፡ ወኮነኖሙ ለእስራኤል ፯ተ ዓመተ ወሞተ ሐሴቦን ወተቀብረ ውስተ ቤተልሔም ፤

ሐሴቦንም መስፍን ሁኖ እስራኤልን ሰባት ዓመት ገዟቸው ሙቶ በሀገሩ በቤተ ልሔም ተቀበረ ፤

፲፩፡ ወኮነኖሙ እምድኅሬሁ ለእስራ ኤል ኤሎም ዛብሎናዊ ፲ተ ዓመተ፤

ከእሱም በኋላ ከነገደ ዛብሎን የተወለደ ኤሎም እስራኤልን ፲ ዓመት መስፍን ሁኖ ገዛቸው፤ እንደ ነቢይም ሁኖ አስተማራቸው፤

፲፪፡ ወሞተ ኤሎም ዛብሎናዊ በሴሎም ወቀበርዎ ውስተ ምድረ ዛብሎን ፤

ከዛብሎን ወገን የተወለደ ኤሎምም የተሰጠውን ዘመን ፈጽሞ በሴሎም ሙቶ በዛብሎን ዕጣ ውስጥ ቀበሩት ፤

፲፫፡ ወኮነኖሙ ለእስራኤል እምድኅሬሁ ሎቦን ወልደ ኤሎም ኤፍራታዊ ፤

ኤሎም ከሞተ በኋላም የኤፍራታው ሰው የኤሎም ልጅ ሎቦን መስፍን ሁኖ እስራኤልን ገዛቸው ፤

፲፬፡ ወተወልዱ ሎቱ ፵ ደቂቅ ወ፴ ደቂቀ ደቂቁ ወይጼዕኑ ላዕለ ሰብዓ አዕዱግ ወኮነኖሙ ለእስራኤል ፰ ዓመተ ፤

ለሎቦንም ፵ ወንዶች ልጆች ተወለዱለት ፤ የልጅ ልጆቹም ፴ ነበሩ ፤ እነዚህም ፸ው ልጆች በ፸ በቅሎዎች ላይ ይቀመጡ ነበር ፤ እሱም መስፍን ሁኖ እስራኤልን ፰ ዓመት ገዛቸው እንደ ነቢይም ሁኖ አስተማራቸው ፤

፲፭፡ ወሞተ ሎቦን ወልደ ኤሎም ኤፍራታዊ ወቀበርዎ ውስተ ኤፍራታ ውስተ ኤፍሬም ውስተ ደብረ ረንቅ ፤

የኤፍራታው ሰው የኤሎም ልጅ ሎቦንም በተፈጥሮ የተሰጠውን ዘመን ፈጽሞ በሞተ ጊዜ በኤፍሬም ዕጣ ውስጥ ባለ በሀገሩ በኤፍራታ ከኖራ ግንብ ውስጥ አግብተው ቀበሩት ።

## ምዕራፍ ፲፫

### ገባኤ

፩፡ ወደገሙ ደቂቀ እስራኤል ገቢረ እከይ ቅድመ እግዚአብሔር ወአግብኦሙ ውስተ እደ ኢሎፍሊ ፵ ዓመተ፤

የእስራኤልም ልጆች ዳግመኛ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረጉ ማለት ኃጢአት ሠሩ፤ ጣዖት አመለኩ ፤ እግዚአብሔርም ፵ ዘመን በኢሎፍላውያን እጅ አሳልፎ ጣላቸው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፪፤ ወሀለወ ብእሲ ዘእምነ ሶሬሀ ዘእምነገደ ዳን ወስሙ ማኑሔ ወብእሲቱሰ መካን ይእቲ ወኢትወልድ ፤

በዚያ ወራት ከነገደ ዳን የሚሆን ሶራህ ከሚባል ሰው የተወለደ ስሙ ማኑሔ የሚባል ሰው ነበር ፤ ሚስቱ ግን መካን ነበረች ልጅም አልወለደችም ነበር ፤ አሁን በዚህ ምክንያት መልአክ ተነጋገራት የሚል ነውና ፤

፫፤ ወአስተርአየ መልአከ እግዚአብሔር ለብእሲቱ ወይቤላ ናሁ መካን አንቲ ወኢወለድኪ ወትፀንሲ ወትወልዲ ወልደ ፤

ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክም ሚስቱን ታየት ፤ ተነጋገራት ፤ እነሆ አንቺ መካን ሁነሽ ልጅ አልወለድሽምና አሁን ፀንሰሽ ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ አላት ፤

፬፤ ወይእዜኒ ተዐቀቢ ወኢትስተዪ ወይነ ወሚሰ ወኢትብልዒ ኵሎ ዘርኩሰ፤

አሁንም የወይን ጠጅና የማር ጠጅ እንዳትጠጭ ነውር ነቀፋ ያለበትን /ርኩስ የሚያሰኘውን ምግብ ሁሉ እንዳትበይ ተጠበቂ ፤

፭፤ እስመ ናሁ ትፀንሲ ወትወልዲ ወልደ ወኢይለክፎ ርእሶ ሐፂን እስመ ቅዱስ ውእቱ ናዝራዊ ለእግዚአብሔር ውእቱ ሕፃን እምከርሠ እሙ ለውእቱ ይእኅዝ ያድኅኖሙ ለእስራኤል እምእደ ኤሎፍሊ ፤

እነሆ ወንድ ልጅ ፀንሰሽ ትወልጃለሽና ይህም ልጅ ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ አገልጋዩ ነውና፤ በራሱ ላይ ምላጭ አይውጣበት ማለት ራሱን አይላጭ ፤ እሱም እስራኤልን ከኢሎፍላውያን እጅ ያድናቸው ዘንድ ይነሣል፤ «እስመ ቅዱስ ውእቱ ባለው» እስመ ሐዲስ ውእቱ ይላል ፤ አብነት እንደዚህ ያስተረጉማል ፤

፮፤ ወሖረት ይእቲ ብእሲት ወነገረቶ ለምታ ወትቤሎ ብእሲ እግዚአብሔር መጽአ ኀቤየ ወርእየቱ ከመ ርእየተ መልአከ እግዚአብሔር ወግሩም ውእቱ ጥቀ ወተስእልክዎ እምአይቴ ውእቱ ወኢያይድዓኒ ስሞ ፤

ይህችም ሴት ሒዳ መልኩ እንደ መልአከ እግዚአብሔር ያለ የእግዚአብሔር ሰው /ነቢየ እግዚአብሔር/ ወደዚህ መጥቶ ነበር ብላ ለባሏ ነገረችው ፤ መልኩም እጅግ የሚያስፈራ ነው፤ ከወዴትም እንደመጣ ብጠይቀው ስሙን አልነገረኝም አለችው ፤ በአምሳለ ነቢይ ስለታየት ብእሴ እግዚአብሔር አለች እንጂ መልአክ ነው ፤

፯፤ ወይቤለኒ ናሁ ትፀንሲ ወትወልዲ ወልደ ወይእዜኒ ኢትስተዪ ወይነ ወሚሰ ወኢትብልዒ ኵሎ



ዘርኩሰ እስመ ናዝራዊ ውእቱ ሕፃን ለእግዚአብሔር እምከርሠ እሙ እስከ አመ ይመውት ፤

መጥቶ ምን አለሽ ቢላት እነሆ ወንድ ልጅ ፀንሰሽ ትወልጃለሽና የወይን ጠጅ የማር ጠጅ አትጠጭ ፤ በኦሪት የተከለከለውን አትብዪ ፤ ያ ሕፃን ከናቱ ማኅፀን ከተወለደ ጀምሮ እስኪሞት ድረስ ለእግዚአብሔር የተለየ አገልጋዩ ነውና አለኝ አለችው ፤

፰፤ ወሰአለ ማኑሔ ኀበ እግዚአብሔር ወይቤ እግዚኦ ብእሴ እግዚአብሔር ዘፈኖከ ኀቤሃ ለይምጻእ ኀቤነ ወያለብወነ ምንተ ንግበር ለውእቱ ሕፃን ዘይትወለድ ፤

ማኑሔም አቤቱ ከዚህ በፊት ወደ ሚስቴ የላክኸው ነቢየ እግዚአብሔር ወደኛ ይምጣ ለዚያ ለሚወለደውም ሕፃን የምናደርገው ምን እንደሆነ ልብ ያስደርገን ብሎ ወደ እግዚአብሔር አመለከተ ፤ ሐተታ ይህን ተነጋግረው ሁለቱም ቀኖና /ግብር/ ገብተዋል ፤ ማኑሔም ሚስቱን እንደ ቀድሞው ወደ አንቺ የመጣ እንደሆነ መጥተሽ እንድትነግሪኝ ሲል ያስጠነቅቃታል ፤

፱፤ ወሰምዐ እግዚአብሔር ቃሎ ለማኑሔ ወመጽአ መልአከ እግዚአብሔር ኀበ ብእሲቱ ዓዲ ዳግመ እንዘ ትነብር ውስተ ገዳም ወኢሀለወ ማኑሔ ምታ ምስሌሃ፡

እግዚአብሔርም የማኑሔን ልመና ሰማ ፤ «ለይምጻእ ኀቤነ» ብሎ እንዳመለከተ የእግዚአብሔር መልአክ ገና በምድረ በዳ ሳለች ዳግመኛ ወደሚስቱ መጣ ፤ በዚያን ጊዜም ባሏ ማኑሔ ከእሷ ጋር አልነበረም ፤

፲፤ ወሮፀት ብእሲቱ ወአፍጠነት ወነገረቶ ለምታ ወትቤሎ አስተር አየኒ ዝክቱ ብእሲ ኀቤየ ቀዲሙ፤

ሲመጣ እንድትነግሪኝ ብሎ አስጠንቅቋት ነበርና ሚስቱ ፈጥና ሒዳ ከዚህ በፊት ወደ እኔ የመጣ ያ ሰው አሁንም ታየኝ ብላ ለባሏ ነገረችው ፤

፲፩፤ ወተንሥአ ማኑሔ ወተለዋ ለብእሲቱ ወሖረ ኀበ ውእቱ ብእሲ ወይቤሎ አንተኑ ውእቱ ዝክቱ ብእሲ ዘተናገርከ ምስለ ብእሲትየ ወይቤሎ ውእቱ መልአክ አነ ውእቱ ፤

ማኑሔም ሚስቱን ተከትሎ ወደዚያ ሰው ሔደ ፤ ከዚያም ደርሶ ከሚስቴ ጋራ የተነጋገርኸ ያ ሰው አንተ ነህን አለው ፤ ያም መልአክ አዎን እኔ ነኝ አለው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፪፣ ወይቤሎ ማኑሔ ይእዜ ሶበ በጽሐ ቃልከ ምንት ውእቱ ነገሩ ለውእቱ ሕፃን ወግብሩ ፣

ማኑሔም ዛሬ የተናገርከው ነገር ቢደርስ ለዚያ ሕፃን የምናደርገው ነገሩና ሥራው ምንድን ነው አለው ?

፲፫፣ ወይቤሎ መልአከ እግዚአብሔር ለማኑሔ እምኵሉ ዘእቤላ ለብእሲትከ ተዐቀቡ ፣

ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክም ማኑሔን ለሚስትህ የነገርኳትን ነገር ሁሉ ከማድረግ ተጠበቁ አለው ፤

፲፬፣ እምኵሉ ዘይወጽእ እምወይን ኢትብላዕ ወወይነ ወሜሰ ኢትስተይ ወኵሎ ርኩሰ ኢትብላዕ ወኵሎ ዘአዘዝክዋ ተዐቀቡ ፣

መስማትስ ሰምቶታል ፣ ለማናገር ጠይቆታል ፣ አንተስ ያዘዝከው እኛስ የምንጠብቀው ምንድን ነው ቢለው ፣ ከወይን የሚገኘውን ሁሉ አትብላ አለው ፣ እሸቱን ሲል ነው ፣ የወይን ጠጅንና የማር ጠጅንም አትጠጣ ፣ መሥዋዕት የማይሆነውንም ሁሉ አትብላ፣ ለሚስትህ ያዘዝኳትንም ሁሉ ከማድረግ ተጠበቁ አለው ፣ ዘእቤላ ያለውን ዘአዘዝክዋ ለማለት ፤ አንድም ለማጽናት ደገመው ፤

፲፭፣ ወይቤሎ ማኑሔ ለመልአከ እግዚአብሔር ናኄብረከ ወንገብር ለከ ማሕስዐ ጠሊ ቅድሜከ ፣

ማኑሔም ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክን ግድ እንል ሃለን ፣ በፊትህ የፍየል ጠቦት እንረድልህ አለው ፣ ቅድሜከ ማለቱ እንዳይጠራጠር ፤

፲፮፣ ወይቤሎ መልአከ እግዚአብሔር ለማኑሔ እመሰ አገበርከኒ ኢይበልዕ እንከ እክለከ ወእመሰ ለእግዚአብሔር ገበርከ መሥዋዕተ ግበር ሎቱ ፣

ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክም ማኑሔን ግድ ብትለኝም እንግዲህ ወዲህ እህልህን አልበላም አለው ፣ «ዘተናገርከ ምስለ ብእሲትየ» ብሎ አንገራግሮት ነበር እና በእግዚአብሔርም ያለው ይመስላል ፣ ለእግዚአብሔርስ ብለህ ካደረግኸው መሥዋዕት ሠዋለት አለው፣ ማኑሔም ይህን ማለቱ ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ እንደሆነ አላወቀምና ነው ፤

፲፯፣ ወይቤሎ ማኑሔ ለመልአከ እግዚአብሔር መኑ ስምከ ከመ አመ በጽሐ ቃልከ ንሰብሕከ ፣

ማኑሔም ከእግዚአብሔር የታዘዘውን መልአክ ይህ የተናገርከው ነገር በደረሰ ጊዜ እናመሰግንህ ዘንድ ስምህ ማን ነው ? አለው ፤

www.ethiopianorthodox.org



፲፰፣ ወይቤሎ መልአከ እግዚአብሔር ለምንት ዝንቱ ዘትሴአል ስምየ መድምም ውእቱ ፣

ከእግዚአብሔር የታዘዘው መልአክም ይህ የምትጠይቀው ስሜ ድንቅ ነው /ትች/ ፣ ለምን ትጠይቀኛለህ? አለው ስሙን መንገሩ ነው ፣ አንድም ይህን መጠየቅህ ድንቅ ነው ፣ አይመረመርም አለው ፤

፲፱፣ ወነሥአ ማኑሔ መሐስዐ ጠሊ መሥዋዕቶ ወአዕረገ ዲበ ኰኵሕ ለእግዚአብሔር ዘይገብር መድምመ ፣

ማኑሔም «ወእመሰ ለእግዚአብሔር ገበርከ መሥዋዕተ ግበር ሎቱ» ብሎት ነበርና ድንቅ ሥራ /ተአምራት/ ላደረገለት ለእግዚአብሔር ጠቦትበግ መሥዋዕት አድርጎ በደንጊያ ላይ አቀረበ ፤

፳፣ ወርእዩዎ ማኑሔ ወብእሲቱ ሶበ ዐርገ ነድ እማዕከለ ምሥዋዕ ውስተ ሰማይ ዐርገ መልአከ እግዚአብሔር በነደ ምሥዋዕ ውስተ ሰማይ ወማኑሔ ወብእሲቱ ርእዩዎ ወወድቁ በገጸሙ ውስተ ምድር ፣

ከምሥዋዑም መካከል እሳቱ ወደ ሰማይ በወጣ ጊዜ ማኑሔና ሚስቱ አዩት፣ መሥዋዕታቸውን እንደተቀበላቸው ለማጠየቅ ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክም በሥምዋዑ ጢስ ወደ ሰማይ ሲያርግ አይተው ማኑሔና ሚስቱ የደስታ ድንጋጤ ደንግጠው በግንባራቸው ከመሬት ተደፉ ፤

፳፩፣ ወኢደገመ እንከ መልአከ እግዚአብሔር አስተርእዮቶሙ ለማኑሔ ወለብእሲቱ ወይእተ ጊዜ አእመረ ማኑሔ ከመ መልአከ እግዚአብሔር ውእቱ ፣

ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ ከዚያ ቀን ወዲህ ዳግመኛ ለማኑሔና ለሚስቱ አልታያውም ፣ ማኑሔም ተጠራጥሮ ነበርና ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ እንደ ሆነ ያን ጊዜ አወቀ ፤

፳፪፣ ወይቤላ ማኑሔ ለብእሲቱ ሞተ ንመውት እስመ ርኢናሁ ለመልአከ እግዚአብሔር ፣

ማኑሔም ሚስቱን ከእግዚአብሔር የታዘዘውን መልአክ አይተናልና እንሞታለን አላት መልአክ ለመዓት እንጂ ለምሕረት የማይታዘዝ መስሎት፡

፳፫፣ ወትቤሎ ብእሲቱ ሶበሰ ፈቀደ እግዚአብሔር ይቅትለነ እምኢ ተመጠወ እምእዴነ መሥዋዕተነ ወቍርባነነ ወእምኢያለበወነ ዘንተ ኵሎ ወበከመሰ መዋዕሊሁ እምኢ ያስምዐነ ዘንተ ፣

ሚስቱን እግዚአብሔር ሊገድለን ቢወድስ መሥዋዕታችንን ቍርባናችንን ከእጃችን ባልተቀበለን ነበር ፣ ይህንም ነገር ልብ አላስደረገንም ነበር፡

የምንሞትበትስ ቀን ቢደርስ ይህን ባልነገረነም ነበር ፤ አንድም የምንሞትስ ቢሆን በጊዜው ጊዜ የሚደረግ ይህን ነገር ባልነገረንም ፤

፳፬፣ ወወለደት ወልደ ይእቲ ብእሲት ወሰመየቶ ስሞ ሶምሶን ወባረኮ እግዚአብሔር ወልህቀ ውእቱ ሕፃን ፣

ያችም ሴት ወንድ ልጅ ፀንሳ ወለደች ስሙንም ሶምሶን አለችው ፀሐይ ማለት ነው፣ በዓረቡ ሽምሽ እንዲል ፀሐይ ሲል፣ እግዚአብሔርም ይህን ሕፃን ባረከው /አከበረው/ ያም ሕፃን አደገ ፤

፳፭፣ ወአኀዘ መንፈሰ እግዚአብሔር ይሑር ምስሌሁ ውስተ ትእይንተ ዳን ማዕከለ ሦራሕ ወማዕከለ አስታሔል ፣

የእግዚአብሔር ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስም በሦራሕና በእስታሔል መካከል ባለ በዳን ሠፈር ከሱ ጋር ይኖር ጀመር ፤ አንድም በሦራሕና በአስታሔል መካከል ወዳለ ወደ ዳን ከተማ ይሔድ ዘንድ የእግዚአብሔር ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስ ከሶምሶን ጋር በረድኤት ኖረ ፤ አንድም ኃይለ እግዚአብሔር አድሮ በት ኖረ ።

## ምዕራፍ ፲፬

፩፣ ወወረደ ሶምሶን ውስተ ቴምናታ ወርእየ ብእሲተ በቴምናታ እምአዋልደ ኢሎፍሊ ወአደመቶ ቅድሚሁ ፣

ሶምሶንም በዚያ ወራት ወደ ቴምናታ ወረደ ፣ የወረደበት ምክንያት አልታወቀም፣ ጥበበ እግዚአብሔር እንዲወርድ አድርጎታል፣ በቴምናታም ከኢሎፍላውያን ወገን አንዲት ሴት አይቶ ደስ አለችው /ደስ አሰኘችው/ ፤

፪፣ ወዐርገ ወነገሮሙ ለአቡሁ ወለእሙ ወይቤሎሙ ርኢኩ ብእሲተ በቴምናታ እምአዋልደ ኢሎፍሊ ወይእዜኒ ንሥእዋ ሊተ ብእሲተ ፣

ወደ ሀገሩ ገብቶ /ተመልሶ/ በቴምናታ ከኢሎፍላውያን ወገን የምትሆን አንዲት ሴት አይቻለሁና አሁንም ሚስት ትሆነኝ ዘንድ እሷን አጭታችሁ አጋቡኝ ብሎ ለአባቱና ለእናቱ ነገራቸው ፤

፫፣ ወይቤልዎ አቡሁ ወእሙ ቦኑ አልቦ እምአዋልደ አኀዊከ ወበውስተ ኵሉ ሕዝብየ ብእሲት ከመ ትሑር አንተ ወትንሣእ ብእሲተ እምአዋልደ ኢሎፍሊ ቈላፋን ፣



እናትና አባቱ በውኑ ሒደህ ካልተገዘሩ /ከቈላፋን/ ከኢሎፍላውያን ወገን የምትሆን ሴትን ታገባ ዘንድ በውኑ ከወንድሞችህ ፣ ከ፳ኤል ልጆች ሴት የለችምን ፣ አኃዊከ ካለ ሕዝብከ ፣ ሕዝብየም ካለ አኃውየ ባለ በቀና ነበር አኃዊከን ለአባቱ ፣ ሕዝብየን ለእናቱ ሰጥቶ ተናገረ፣ በኔስ በናትህ ወገኖች ውስጥ መልከ መልካም ሴት የለችምን አሉት ፤

ወይቤሎ ሶምሶን ለአቡሁ ኪያሃ ዳዕሙ ንሥኡ ሊተ እስመ አደመተኒ ውስተ አዕይንትየ ፣

ሶምሶንም አባቱን ለዓይኔ አምራኛለችና ፣ ለልቦናየም ደስ አሰኝታኛለችና እሷን ብቻ አጋቡኝ አለው ፤

፬፣ ወኢያእመሩ አቡሁ ወእሙ ከመ እምኀበ እግዚአብሔር ውእቱ እስመ በቀለ ይፈቅድ ውእቱ እምኢሎፍሊ ወበእማንቱ መዋዕለ ኤሎፍሊ ይቀንይዎሙ ለ፳ኤል ፣

አባትና እናቱ እንዲህ ማለታቸው ይህ ነገር በጥበበ እግዚአብሔር እንደተደረገ ባያውቁ ነው ሶምሶን ከኢሎፍሊ በቀልን ሊመልስ ይወዳልና ይህንም እንደ አርእስት አንሥ ቶታል በዚህ ምክንያት ወርዶ ኋላ ከኢሎፍላውያን ብዙ ሰው አጠፋ የሚለው ነውና በዚያም ወራት ኢሎፍላውያን ፳ኤልን ይገዟቸው ነበር ፤

፭፣ ወወረዱ ሶምሶን ወአቡሁ ወእሙ ውስተ ቴምናታ ወተግኅሡ ውስተ ዓፀደ ወይን ዘቴምናታ ወናሁ አንበሳ ተቀበሎ እንዘ ይጥሕር ፣

እናት አባቱና ሶምሶንም ግብር ይዘው በዚያ ወራት ወደ ቴምናታ ወረዱ፣ ቴምናታም ሲደርስ ወደወይን ቦታ ቢገባ አንበሳ እያነፋ ተቀበለው ፤

፮፣ ወመጽአ መንፈሰ እግዚአብሔር ላዕሌሁ ወነጸሐ ከመ ዘይነጽሕ መሐስአ ጠሊ ወከመ ወኢያምንት ኮነ ውስተ እዴሁ ወኢያይድዓ ለአቡሁ ወለእሙ ዘገብረ ፣

የእግዚአብሔር መንፈስ ረድኤት አድሮበት ነበርና የፍየልም ጠቦት አንሥተው እንዲጥሉ አንበሳውን እንደ ኢምንት አድርጎ አንሥቶ ጣለው ፣ ያደረገውንም ለአባቱና ለእናቱ አልተናጋረም ፤

፯፣ ወዐርጉ ወተናገሩ በእንተ ብእሲቱ ወአደመቶ ቅድሚሁ ለሶምሶን ፣

አባቱና እናቱም ወደ ቤት ገብተው የሚስቱን ነገር ተናገሩ በፊቱ ደስ አሰኝታዋለችና ልጃችሁን ለልጃችን ስጡልን ብለው ተናገሩ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፰፣ ወተመይጠ እምድኅረ መዋዕል ከመ ይንሥአ ወተግኅሠ ከመ ይርአዮ ለዝክቱ በድነ አንበሳ ወናሁ ንሕብ ውስተ አፉሁ ለውእቱ አንበሳ ኀደረ ወቦ መዓር ፤

ሶምሶንም ያችን ሴት ያገባ ዘንድ ውል አድርጎ ከጥቂት ቀን በኋላ ወደ ሀገሩ ተመለሰ፣ አንድም ያችን ሴት ያገባ ዘንድ ወደ ኤሎፍሊ ተመለሰ፤ ከወይኑም ቦታ ሲደርስ የገደለ ውን አንበሳ ወደቃ /ሬሳ/ ያይ ዘንድ ወደዱር ቢገባ እነሆ ከሞተው አንበሳ አፍ ውስጥ ንብ ገብቶ ማር ሠርቶ አገኘው ፤

፱፣ ወነሥአ ወበልዐ ወሖረ ወእንዘ የሐውር ይበልዕ ወበጽሐ ኀበ አቡሁ ወእሙ ወወሀቦሙ ወበልዑ ወኢያእድአሙ ከመ እምአፈ አንበሳ አውጽአ ለውእቱ መዓር ፤

ሶምሶንም ከማሩ ቆርጦ በልቶ ሔደ እየበላም ሒዶ እናቱና አባቱ ካሉበት ደረሰ አባቱና እናቱም ከማሩ ሰጧቸው በሉ ፤ ነገር ግን መዓሩን ከአን በሳው አፍ እንዳገኘው አልነገ ራቸውም ፤ ኋላ ሚስቱን እንኳን ላንቺ ለአባት ለናቴም አልነገርኳቸውም የሚላት ነውና እንደ አርእስት አነሣው፤

፲፣ ወወረደ አቡሁ ኀበ ይእቲ ብእሲት ወነበረ ህየ ሶምሶን ሰቡዓ መዋዕለ እስመ ከማሁ ይነብሩ ወራዙት ፤

የሶምሶን አባትም ከዚያች ሴት ዘንድ ነገሩን ጨርሶ ወደ ሀገሩ ወረደ ፤ ሶምሶን ግን በቴምናታ ሰባት ቀን ተቀመጠ ፤ ጐልማሶች ሚስት ሲያገቡ ሰባት ቀን በዓለ መርዓ አድርገው ይቀመጣሉና ፤

፲፩፣ ወእምዝ ሶበ ፈርህዎ ሤሙ ሳዕሌሁ ካልዓነ ፴ ዕደወ ወነበሩ ምስሌሁ ፤

ከዚህም በኋላ ኢሎፍላውያን ቢፈሩት አላማጅ አስመስለው ሠላሳ ሰዎችን ሾሙበት ፤ ቢሆንላችሁ ግደሉት ማለት ነው ፤ እነዚህም ከሶምሶን ጋር ተቀመጡ ፤

፲፪፣ ወይቤሎሙ ሶምሶን እሜስል ለክሙ አምሳለ ወእመ አእዳዕክ ሙኒ አምሳልየ በእላንቱ ሰብዑ መዋዕል ዘበዓል ወረከብክሙ እሁብ ክሙ ፴ ሰንዱናተ ወ፴ አልባሰ፣

ሶምሶንም እነዚያን ሰዎች ምሳሌ መስዬ ልንገራችሁና በዓል በምናደርግባቸው በነዚህ በሰባቱ ቀኖች ምሳሌ ዬን አግኝታችሁ ብትነግሩኝ ሠላሳ መጐናጸፊያ ፤ ሠላሳ ቀሚስ እሰጣችኋለሁ ፤



፲፫፣ ወእመሰ ስእንክሙ አይድዮ ትየ ትሁቡኒ አንትሙ ሊተ ፴ ሰንዱናተ ወ፴ አልባሰ ወይቤልዎ መስል አምሳሊከ ወንስማዕ ፤

ምሳሌዬን መንገር ባትችሉ ግን እናንተ ለእኔ ፴ መጐናጸፊያ ፴ ቀሚስ ትሰጡኛላችሁ አላቸው፣ እነሱም ምሳሌህን መስለህ ንገረን እኛም እንስማ አሉት ፤

፲፬፣ ወይቤሎሙ እምነ በላዒ ወፅአ መብልዕ ወእምነ ጽኑዕ ወፅአ ጥዑም ወስዕኑ አይድዮቶ አምሳሊሁ እስከ ሠሉስ መዋዕል ፤

እሱም ከሚበላ መብል ወጣ ፤ ከብርቱም የሚጣፍጥ ተገኘ አላቸው፣ እስከ ሦስት ቀን ድረስም ምሳሌውን ተርጕሞ መናገር ተሳናቸው ፤

፲፭፣ ወእምዝ አመ ራብዕት ዕለት ይቤልዋ ለብእሲቱ አስፍጢዮ ለምትኪ ወይንግርኪ አምሳሊሁ ከመ ኢናውዒክሙ በእሳት ለኪ ወለቤተ አቡኪ አው ከመ ታንድዩነኑ ጸዋዕክሙነ ፤

ከዚህ በኋላ በአራተኛው ቀን የሶምሶንን ሚስት ባልሽን አባብይልን ፤ አንችንና ያባት ሺን ወገኖች በእሳት እንዳና ቃጥላችሁ ምሳሌውን ይንገ ርሽ ፤ ወይስ የጠራችሁን ታደ ኸዩን ዘንድ ነውን አሏት ፤

፲፮፣ ወበከየት ላዕሌሁ ብእሲቱ ለሶምሶን ወትቤሎ ጸላእከኒ ወኢታ ፈቅረኒ እስመ አምሳሊከ ዘመሰ ልከ ለደቂቀ ሕዝብየ ኢነገርከኒ ሊተ ፤

የሶምሶንም ሚስት የነዚያን ሰዎች ቃል ሰምታ በሶምሶን አለቀሰችበት ፤ እሱም ምን ሁነሽ ታለቅሻለሽ ቢላት ፤ ለወገኖቼ ልጆች የመሰል ከውን ምሳሌ አልነገርከኝምና ጠልተኸኛል አትወደኝም አለችው ፤

ወይቤላ ሶምሶን ናሁ ለአቡየ ወለእምየ ኢነገርክዎሙ ለኪኑ እነግረኪ ፤

ሶምሶንም ለአባት ለእናቴ ያልነገርኳቸውን አሁን ላንቺ እነግርሻለሁን አላት ፤

፲፯፣ ወበከየት ላዕሌሁ ሰቡዓ መዋዕለ ዘበዓል ወእምዝ አመ ሳብዕት ዕለት ነገራ ሶበ አስርሐቶ ወአይድዓቶሙ ለደቂቀ ሕዝባ ፤

ሚስቱም አልነግርሽም ቢላት ከአራተኛው ቀን ጀምራ እስከ ሰባተኛ ቀን ድረስ አለቀሰች በት ፤ ከዚህ በኋላ በዘበዘበ ችው ጊዜ በሰባተኛ ዩቱ ቀን ነገራት ፤ እሷም ለወገኖቿ ልጆች ነገረቻቸው ፤

፲፰፣ ወይቤልዎ እሙንቱ ዕደው እንበለ ይዕርብ ፀሐይ ምንት ይጥዕም እመዓር ወምንት ይጸንዕ እምአንበሳ ፤

www.ethiopianorthodox.org

እነዚያም ሰዎች የነገረቻቸውን ይዘው በ፯ኛው ቀን ፀሐይ ሳይገባ ሒደው ምሳሌህን አገኘነው እንነገርህ አሉት ፤ እሱም በሉ ንገሩኝ አላቸው እነሱም ከመዓር የሚጣፍጥ ከአንበሳስ የሚበረታ ምን አለ ? ከአንበሳ አፍ መዓር አግኝተህ ቆርጠህ በልተሃል አሉት ፤

ወይቤሎሙ ሶምሶን ሶበ ኢያስራሕክምዋ ለዕጐልትየ እምኢረከብክምዋ ለአምሳልየ ፤

ሶምሶንም ሚስቴን ባትዘበዝቧት /ባታደክሟት/ ምሳሌየን ባላገኛችሁት ነበር አላቸው ፤

፲፱፣ ወመጽአ መንፈስ እግዚአብሔር ላዕሌሁ ወወረደ ውስተ አስቀሎና ወቀተለ ፴ብእሴ ወሰለቦሙ አልባሲሆሙ ወወሀቦሙ ለእለ አይድዕዎ አምሳሊሁ ወተምዐ መዓተ ሶምሶን ወአተወ ቤተ አቡሁ፤

የእግዚአብሔር መንፈስ ረድኤት በሶምሶን አደረበት ፤ ወደ አስቀሎናም ወረደ ፤ ፴ ሰዎች ገድሎ ልብሳቸውን ገፎ ምሳሌውን ለነገሩት ለ፴ው ሰዎች ሰጣቸው ፤ ሶምሶንም ሚስቱን ምሥጢር አወጣችብኝ ብሎ ተቆጥቶ ወደ አባቱ ቤት ተመለሰ ፤

፳፣ ወነበረት ብእሲተ ሶምሶን ምስለ መጋቤ መርዓሁ ካልዑ ፤

ፍቁሩ ሲል ነው የሶምሶንም ሚስት ከወዳጁ ከሥር ሚዜው /ከሩዝ ቤቱ/ ጋር ተቀመጠች ማለት እሱን አግብታ ተቀመጠች ፤

## ምዕራፍ ፲፭

፩፣ ወእምድኅረ መዋዕል አመ ማዕረረ ሥርናይ ሐወፃ ሶምሶን ለብእሲቱ ወአምጽአ ላተ መሐስዓ ጠሊ ወይቤ እባእ ኀበ ብእሲትየ ውስተ ጽርሓ ወከልአ አቡሃ በዊአ ኀቤሃ ፤

ከብዙ ቀን በኋላ የስንዴ አዝመራ በደረሰበት ወራት ሶምሶን ሚስቱን ጐበኛት ፤ የፍየል ጠቦት ይዞላት መጥቶ አባቷን ከሚስቴ ዘንድ ወደ እልፍኝ /ወደ ጫጉላው/ ቤት ልግባ ቢለው አባቷ ሚስቱ ወደ አለችበት እንዳይገባ ከለከለው ፤ አሁን አዝመራውን ሁሉ አቃጠለ የሚል ነውና «አመ ወርኃ ማዕረር» ብሎ እንደ አርእስት አንስቶታል ፤

፪፣ ወይቤሎ አቡሃ እስመ ትቤ ጸላእክዋ ወወሀብክዋ ለካልእከ ወባሕቱ ነያ እኅታ እንተ ትንእሳ ወትሤንያ ትኩንከ ህየንቴሃ ፤



ምን አጠፋሁ ? ቢለው አባቷ ጠላኋት ስላልክ እሷን ለሥር ሚዜህ አጋባኋት፤ ነገር ግን በዕድሜ የምታንሣት በሙያ በመልክ የምትበልጣት እኅቷ አለችልህና ስለሷ ፈንታ ሚስት ትሁንህ አለው ፤

፫፣ ወይቤ ሶምሶን ንጹሕ አነ ምዕረ እምኢሎፍሊ እስመ አነ እገብር እኪተ ላዕሌክሙ ፤

ሶምሶንም በእናንተ ላይ ክፉ ነገር አደርጋለሁና እንግዲህ ወዲህ ከኢሎፍላውያን መጋባት ለምኔ ፤ እኔ ከዚህ ነገር ንጹሕ ነኝ አለ ፤

፬፣ ወሖረ ሶምሶን ወአኀዘ ሠለስተ ምእተ ቈናጽለ ወነሥአ ሙኀተወ ወአሠረ ውስተ አዝናቢሆሙ ወወደየ አሐተ ማኅቶተ ማእከለ ፪ቱ አዝናቢሆሙ ፤

ሶምሶንም ይህን ከተናገረ በኋላ ሒዶ ሦስት መቶ ቀበሮዎችን በሩጫ ያዘ ፤ መቶ ሃምሳ ችቦ /ዳቦት/ አበጅቶ ከጅራታቸው አሠረው ፤ በሁለቱ ቀበሮዎች ጅራት መካከልም አንድ አንድ ችቦ /ዳቦት/ አደረገ ፤

፭፣ ወአንተወ እሳተ ውስተ ውእቱ ማኀትው ወፈነዎሙ ውስተ ከላስስት ዘኢሎፍሊ ወአውዓዩ ሰዊተ ወክምረ ዘተአጽደ ዘይቀውም ወዘውጡህ ወአዕፃዳተ ወይን

መቶ ሃምሳውንም ችቦዎች በእሳት አቃጥሎ የኢሎፍላውያን መከር ወደአለበት ሰደዳቸው ፤ እሊህም ሦስት መቶ ቀበሮዎች እየዞሩ ያልታጨደውን እሸቱን የታጨደውን ክምሩን የቆመውን ደረቁን የተሰጣውን ነዶውን ፤ አንድም የተመረተውን ምርቱን የዘይቱንና የወይኑንም ቦታ በእሳት አቃጠሉት ፤

፮፣ ወይቤሉ ኢሎፍሊ መኑ ገብረ ዘንተ ወይቤልዎሙ ሶምሶን ሐሙሁ ለቴምናታዊ እስመ ሄድዎ ብእሲቶ ወወሀብዋ ለካልኡ ወዐርጉ ኢሎፍሊ ወአውዓዩ ቤተ አቡሃ ወኪያሃኒ በእሳት ፤

ኢሎፍላውያንም የተቃጠለውን ቋያውን አይተው ይህን ያደረገ ማነው ? አሉ ፤ ነገሩን የሰሙት ወገኖቻቸውም የቴምናታው ሰው አማች ሶምሶን ነው ፤ አሏቸው ምን ቢያደርጉት ? ቢሏቸው ሚስቱን ቀምተው ለጓደኛው ስለሰጡበት ነው ፤ ኢሎፍላውያንም ይህን ከሰሙ በኋላ ምክንያት ሁነው አገራችንን ያስጠፋሉን ብለው ተቆጥተው ወጥተው ሚስቱን ከአባቷ ወገኖች ጋራ አቃጠሉ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፯፤ ወይቤሎሙ ሶምሶን እመሰ ገበርክሙ ዘንተ ኢይፈቅድ በቀልየሰ እምአሐዱ ለኵልክሙ እምረሰይኩ ፤

ሶምሶንም የሚስቱን ጥፋት አይቶ ኢሎፍላውያንን ይህንስ ከአደረጋችሁ ሳጠፋችሁ አል ወድም ፤ ጥንቱንስ ጠቤ /በቀሌ/ ከአንድ ሰው ብቻ አልነበ ረም፤ ይህንም ባታደርጉ መላ ችሁን ሬሳ ባደረግኋችሁ ነበር አላቸው ፤

፰፤ ወዘበጦሙ ሶምሶን ውስተ አቍያጺ እገሪሆሙ ወኮነ ዓቢይ ቀትል ወወረደ ሶምሶን ወነበረ ውስተ ፈለግ ውስተ ዓዘቅተ ኤጣም ፤

ኢሎፍላውያንም ያንገራግረ ናልን ብለው ቢያንጐራጕሩ ሶምሶን ተነሥቶ ጭን ጭናቸ ውን ሰበራቸው ፤ አንድም ወይቤሎሙ እመ ገበርክሙ ዘንተ ምንም ይህን ብታደርጉ ልተዋችሁ አልወድም ፤ በቀሌ ከአንድ ሰው ብቻ ነውን ጥንቱንስ መምጣቴ መላችሁን ሬሳ ላደርጋችሁ ነው እንጂ ብሎ ተነሥቶ ጭን ጭናቸውን ሰበራቸው ፤ ያን ጊዜም ጽኑ ሰልፍ ሆነ፤ ሶምሶንም እሊህን አጥፍቶ በወንዝ ዳር ካለ ኤጣም ከምትባል ዋሻ ወስጥ ገብቶ ተቀመጠ ፤

፱፤ ወዐርጉ ኢሎፍሊ ወኃደሩ ላዕለ ይሁዳ ወነበሩ ኀበ መንከሰ አድግ ፤

ኢሎፍላውያንም ሶምሶንን መያዝ ባይሆንላቸው ፤ ወደ ሀገሩ ዘመቱ ወርደውም በይሁዳ ዕጣ ባለች በመንከሰ አድግ የአኽያ መንጋጋ ባለበትም ቦታ ሠፍረው አደሩ ፤

፲፤ ወይቤልዎሙ ኵሉ ሰብአ ይሁዳ ለምንት ዐረግሙ ላዕሌነ ወይቤሉ ኢሎፍሊ ከመ ንእሥሮ ለሶምሶን ዐረግነ ወንግበሮ በከመ ገብረነ ፤

በይሁዳም ያሉ ሰዎች ሁሉ ኢሎፍላውያንን ምን አጠፋን፤ ለምን በእኛ ላይ ዘመታች ሁብን አሏቸው ፤ ኢሎፍላው ያንም ሶምሶንን አሥረን እንደ አደረገን እናደርገው ዘንድ ማለት እሱ እንደ አጠ ፋን እናጠፋው ዘንድ መጥ ተናል ፤ አታጥፉን ካላችሁ ከኤጣም ዋሻ ወርዳችሁ ሶምሶንን አምጡልን አሉ ፤

፲፩፤ ወወረዱ ፫፻ ብእሲ እምይ ሁዳ ኀበ በዓተ ኰኵሕ ዘኤጣም ወይቤልዎ ለሶምሶን ኢተአምርኑ ከመ ኢሎፍሊ ይኴንኑነ ለምንት ከመዝ ገበርከ ላዕሌነ ፤

ከይሁዳም ሦስት ሺህ ሰዎች ተመርጠው ሶምሶንን ያመጡ ዘንድ ወደ ኤጣም ዋሻ ወር ደው ሶምሶንን ኢሎፍላውያን እንዲገዙን አታውቅምን ለምን እንዲህ ያለ ሥራ አደረ ግህብን አሉት ፤



ወይቤሎሙ ሶምሶን በከመ ገብሩ ላዕሌክሙ ከማሁ ገበርኩ ላዕሌ ሆሙ ፤

ሶምሶንም እነሱ በእናንተ ላይ ያደርጉት እንደ ነበረ እኔም በእነሱ ላይ አደረግሁባቸው አለ ፤ እንዳጠፉን አጠፋኋቸው አላቸው ፤

፲፪፤ ወይቤልዎ ከመ ንእሥርከ ወረድነ ወናግብእከ ውስተ እደሆሙ ለኢሎፍሊ ፤

እሊህም ሰዎች አሥረን በኢሎ ፍላውያን እጅ አሳልፈን እንሰ ጥህ ዘንድ መጥተናል አሉት ፤

ወይቤሎሙ ሶምሶን መሐሉ ሊተ አንትሙ ከመ ኢትቅትሉኒ ወአግ ብኡኒ ሎሙ ወአንትሙሰ ኢትትራ ከቡ ምስሌየ ወመሐሉ ሎቱ ፤

«መሐሉ ሊተ አንትሙ ኢት ቅትሉኒ አንትሙ » ብሎ ይገጥሟል፤ ሶምሶንም እናንተ በጠላትነት ተነሥታሁ እንዳት ገድሉኝ ማሉልኝ እንጂ ለእኒሱስ አሳልፋችሁ ስጡኝ አላቸው፤ እነሱም በሰጣቸው መሐላ ማሉለት ፤ ኃይሉ በኢሎፍላ ውያን ነው ፤ እንጂ በ፫ኤል አይደለምና ፤

፲፫፤ ወይቤልዎ አልቦ ዳዕሙ ነአሥ ረከ በማዕሠር ወናገብአከ ውስተ እደሆሙ ወቀቲለሰ ኢንቀትለከ ወዓሠርዎ በ፪ቱ መዓምድ ሐዲሳት ወአውዕእዎ እምይእቲ ኰኵሕ ፤

በማሠሪያ ዓሥረን በኢሎፍላ ውያን እጅ አሳልፈን እንጥል ሃለን እንጂ መግደልስ አንገ ድልህም ብለው ሁለት ወገን ሁኖ በተፈተለ በአዲስ ምራን የግንግሪት /የኋሊት/ አሥረው ከኤጣም ዋሻ አወጡት ፤

፲፬፤ ወበጽሐ እስከ ኀበ አጽመ መንከሰ አድግ ወወውዑ ኢሎፍሊ ወተቀበልዎ ወሮፁ ኀቤሁ ፤

መንሰከ አድግም ይላል፤ ሶምሶን የግንግሪት ታሥሮ የአህያ መንጋጋ አጥንት እስከ አለበት ቦታ ደረሰ ፤ ኢሎፍላ ውያንም ሶምሶንን ሲያዩት እልል እልል ብለው ፤ አንድም ፎክረው ወጥተው ተቀበሉት ፤

ወመጽአ ላዕሌሁ መንፈሰ እግዚ አብሔር ወኮኑ እልክቱ መዓምድ እለ ውስተ መዝራዕቱ ከመ ሰበ ያዌኑ ሐሠር እሳተ ወተፈትሐ መሐሜሁ እመዝራዕቱ ፤

በሶምሶንም የለመደው መን ፈስ ቅዱስ አደረበት፤ እሱስ አልተለየውም ብሎ በላቸው የሚል መንፈስ ተነሣሣበት ፤ ክንዱ የታሠረባቸው እሊህም

www.ethiopianorthodox.org

ምራኖች በእሳት አጠገብ እንዳለ ገለባ ሆኑ ፣ በእሳት አጠገብ ያለ ገለባ መሽከ ደቆ እንዲጠፋ ማሠሪያው ከክንዱ ተበጣጥሶ ወደቀ ፤

፲፭፣ ወረከበ ዓፅመ መንከሰ አድግ ግዱፈ ውስተ ፍኖት ወአትሐተ እዴሁ ወተመጠዋ ወቀተለ ባቲ ፲ተ ፻ተ ብእሴ ፣

ሶምሶንም ከደረሰበት መንገድ የወደቀ የአህያ መንጋጋ አጥንት አገኘ ያገኛትንም አጥንት ዝቅ ብሎ በእጁ አንሥቶ ሺህ ሰው ገደለባት /ሐተታ/ አምስቱን ስድስቱን ከገደለባት በኋላ አንዱ በአንዱ ላይ እየወደቀ እርስ በርሳቸው ተላግተው አልቀዋል ፤

፲፮፣ ወይቤ ሶምሶን በዓፅመ መንከሰ እድግ ቀተልኩ ፲ተ ፻ተ ብእሴ ፣

ሶምሶንም በአህያ መንጋጋ አጥንት ሺህ ሰው ገደልኩ አለ ፣ አንድም ሺህ ሰው ገዳይ ብሎ ፈከረ ፤

፲፯፣ ወእምዝ ሶበ አኅለቀ ነቢበ ገደፋ ለይእቲ ዓፅመ መንከሰ አድግ እምእዴሁ ወሰመዮ ለውእቱ መካን ቀትለ ዓፅመ መንከስ ፣

ከዚህ በኋላ ይህን ተናግሮ በፈጸመ ጊዜ ያችን የያዛትን የአህያ መንጋጋ አጥንት ከእጁ ጣላት ፣ ያነንም ቦታ ስሙን በአህያ መንጋጋ አጥንት ሰልፍ የተደረገበት ሺህ ሰው የተገደለበት አለው ፤

፲፰፣ ወጸምአ ጥቀ ወጸርሐ ኀበ እግዚአብሔር ወይቤ አንተ አግባእከ ውስተ እደ ገብርከ ዘንተ ሕይወተ ዓቢየ ወይእዜሰ እመውት በጽምእ ወእወድቅ ውስተ እዴሆሙ ለቈላፋን ፣

ሶምሶንም ሲዋጋ ቆይቷልና እጅግ ውሃ ተጠምቶ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ ማለት ውሃ ስጠኝ ብሎ ለመነ ፣ ይህን ታላቅ ድኅነት በእኔ በባሪያህ እጅ አደረግህ ፣ አሁን ግን በውሃ ጥም እሞታለሁ ፣ በጠላቶቼ በኢሎፍላውያንም እጅ እወድቃለሁ አለ ፤

፲፱፣ ወአርኀወ እግዚአብሔር ንቅዓታ ለይእቲ ዓፅመ መንከሰ አድግ ወወፅአ እምኔሃ ማይ ወሰትዮ ወገብአት ነፍሱ ወአዕረፈ ወበበይነ ዝንቱ ተሰምየ ስሙ ለውእቱ መካን ነቅዓ ዓፅመ መንከሰአ አድግ እስከ ዮም ፣

እግዚአብሔርም ልመናውን ሰምቶ ከዚያች ከአህያ መንጋጋ ውሃን አፈለቀለት፣ ያንንም ጠጥቶ ነፍሱ ተመልሳለት ከውሃ ጥም አረፈ ፣ ስለዚህ የዚያ ቦታ ስሙ እስከ ዛሬ ድረስ ከአህያ መንጋጋ ውሃ የፈለቀበት ተባለ ፤



፳፣ ወኮነኖሙ ለ፳ኤል በመዋዕለ ኢሎፍሊ ፳ ዓመተ ፣

ሶምሶንም በኢሎፍላውያን ዘመን እስራኤልን ሃያ ዘመን መስፍን ሁኖ ገዛቸው እንደ ነቢይም ሁኖ አስተማራቸው ::

## ምዕራፍ ፲፮

፩፣ ወሖረ ሶምሶን እምህየ ውስተ ጋዛ ወርእየ በህየ ብእሲተ ዘማ ወቦአ ኀቤሃ ፣

ሶምሶንም ይህን ከአደረገ በኋላ ከዚያ ወደ ጋዛ ሔደ በጋዛም ጋለሞታ ሴት አይቶ ፣ ከርሷ ዘንድ ገብቶ አደረ ፤

፪፣ ወነገርዎሙ ለሰብአ ጋዛ ወይቤልዎሙ መጽአ ሶምሶን ዝየ ወዖድዎ ወአገትዎ ኵላ ሌሊተ ውስተ አንቀጸ ሀገር ወጸንሑ ኵላ ሌሊተ ወይቤሉ ንጽንሖ ኵላ ሌሊተ ወንቀትሎ በጽባሕ ፣

ሲገባ ያዩትም ሰዎች ሶምሶን ከዚህ መጥቶ አድሯል ብለው ለጋዛ ሰዎች ነገሯቸው ፣ እነሱም ይህን ሰምተው መላ ሌሊቱን የከተማውን በር ከበው ሲጠብቁት አደሩ ፣ ሌሊቱን ሁሉ ጠብቀንሲነጋ እንገድለዋለን ብለው ሲጠብቁ አደሩ ፤

፫፣ ወኖመ ሶምሶን እስከ መንፈቀ ሌሊት ወተንሥአ በመንፈቀ ሌሊት ወአኀዛ ለኆኅተ ሀገር ዘአንቀጽ በ፪ሆን ራግዛቲሃ ወያሮሙ ምስለ ኵሉ ሰብኡ ወተሰክመ ላዕለ መትከፍቱ ወአዕረጎሙ ላዕለ ርእሰ ደብር ዘቅድመ ኬብሮን ወአንበሮሙ ህየ ፣

ሶምሶንም ከሌሊቱ እስከ ስድስት ሰዓት ተኛና በመንፈቀ ሌሊት ተነሥቶ በከተማው በር ያሉ ሁለቱን መቃን መድረኮች ያዘ፣ ከሰዎቹ ሁሉ ጋር በትከሻው ተሸክሞ ወስዶ በኬብሮን አንፃር ወደ አለ ተራራ አውጥቶ በዚያ አፈሰሳቸው ፤ ሐተታ ሶምሶን ያደረበት ቤት ዙሪያውን እድሞ አለው፣ ለእድሞውም ከበሩ ላይ ደጀ ሰላም አለው ፣ ይኸውም ደርብና ምድር ቤት ነው፣ ኢሎፍላውያን ሲወጣ እንይዘዋለን ብለው ከደርቡ ሁነው ይጠብቁታል፣ ሶምሶንም ከዚያ እንዳሉ ተገልጾለት ከምድር ቤቱ ገብቶ አንዱን መድረክ በአንድ እጁ፣ አንዱን መድረክ በአንድ እጁ ነቅሎ ደጀሰላሙን ከነሰዎቹ አንሥቶ በጫንቃው ላይ ተሸክሞ ወስዶ በኬብሮን አንፃር ካለ ተራራ አውጥቶ ወደታች ጥሏቸዋል ፤

www.ethiopianorthodox.org

፬፡ ወእምድኅረ ዝንቱ አፍቀረ ብእሲተ በኀበ ፈለገ ሦራህ ወስማ ደሊላ ፤

ከዚህ በኋላ በሦራህ አውራጃ /በሦራህ ወንዝ/ አጠገብ ስሟ ደሊላ የምትባል ሴት ወዳጅ አበጀ ፤ ደሊላም ማለት የምታታልል /ደላሊት/ ማለት ነው ።

፭፡ ወዐርጉ ኀቤሃ መሳፍንተ ኢሎፍሊ ወይቤልዋ አስፍጢዮ ወአእምሪ በምንት አብየ ኃይሉ ወበምንት ንክሎ ወነአስሮ ከመ ናድክሞ ወንሁበኪ ፲ቱ ፻ብእሲ ፲ተ፻ተ ብሩረ ፤

የኢሎፍላውያን ሹማምንትም ከደሊላ ዘንድ መጥተው ሶምሶንን አታልይልን ፤ ኃይሉ የጸናበት በምን እንደሆነ ፤ እኛም አሥረን እናደክመው ዘንድ የምንችልበት በምን እንደሆነ እወቂ ፤ ሺህ ሰዎች የምንሆን እኛ ሺህ ብር እንሰጥሻለን አሏት ፤ አንድ አንድ ብር አወጣጥተው ፤ አንድም «ወንሁበኪ ምእተ ብሩረ» ይላል መቶ ብር እንሰጥሻለን አሏት በመቶ አሥር አወጣጥተው ።

፮፡ ወትቤሎ ደሊላ ለሶምሶን አይድዓኒ ምንት ውእቱ ኃይልከ ዓቢይ ወበምንት እመ አሠሩከ ትደክም ፤

ደሊላም ሶምሶንን ኀይልህ ጽኑዕ የሆነ በምንድን ነው ? በምንስ ቢያሥሩህ ትደክማለህ ንገረኝ አለችው ።

፯፡ ወይቤላ ሶምሶን እምአሠሩኒ በስብዐቱ አውታር ሐዲሳት እለ አልቦሙ ብትከት እደክም እንከ ወእከውን ከመ አሐዱ እምዕጓለ እመሕያው ፤

ሶምሶንም ባልደረቁ በሰባት እርጥብ ጠፍሮች ቢያሥሩኝ እደክማለሁ ፤ ከዚያም በኋላ ከሰውም ወገን እንደ አንዱ እሆናለሁ አላት ።

፰፡ ወአምጽኡ ሳቲ መሳፍንተ ኢሎፍሊ ሰብአተ አውታረ ሐዲሳተ እለ አልቦሙ ብትከት ወአሠረቶ ቦሙ ፤

የኢሎፍሊም ሹማምንት ይህን ብትነግራቸው አዲሶች የሆኑ መቈረጥ የሌለባቸው ሰባት አውታሮችን አመጡላት ፤ በነዚህም አሠረችው ።

፱፡ ወእለሰ ይጸንሕዎ ይነብሩ ውስተ ውሳጢት ወትቤሎ መጽኡከ ኢሎፍሊ ሶምሶን፤ ወበተከሙ ለእሎንቱ አውታር ከመይትበተክ ፈትል ሶበ ያዔኑ እሳተ ወኢተ አውቀ ኃይሉ ፤

ሶምሶንን የሚይዙ ኢሎፍላውያን ግን በጓዳው ተቀምጠው ይጠብቁ ነበር ፤ እሷም በዚህ



አሥራ ኢሎፍላውያን መጡብህ ብትለው ፈትል ከእሳት በቀረበ ጊዜ ተቈራርጦ እንዲ ወድቅ ሰባቱን አውታር ቈራር ጦአቸው ተነሣ፤ አውታሩም ተቈራርጦ ሲወድቅ ኃይሉ አልታወቀም ፤ አንድም የሶምሶን ኃይሉ የሚደክመ በት አልታወቀም ።

፲፡ ወትቤሎ ደሊላ ለሶምሶን ናሁ አስተሐቀርከኒ ወሐሰተ ተናገርከኒ ወይእዜኒ አይድአኒ በምንት የአሥሩከ ፤

ደሊላም ሶምሶንን እነሆ ሸነገ ልኸኝ ፤ ሐሰት ነገርንም ነገር ከኝ ፤ አሁንም እውነቱን ንገረኝ ፤ በምን ቢያሥሩህ ኃይልህ ይደክማል ? አለችው ።

፲፩፡ ወይቤላ እመ አሠሩኒ በስብዐቱ መፃምድ እለ ኢገብሩ ቦሙ ግብረ እደክም እንከ ወእከውን ከመ ፩ዱ እምነ ዕጓለ እመሕያው፤

ሥራ ባልሠሩባቸው በሰባት ሳመገመድ ፤ ቢያሥሩኝ እደክ ማለሁ ከሰውም እንደአንዱ እሆናለሁ አላት ።

፲፪፡ ወነሥአት ደሊላ ሰብዓተ መጻምደ ሐዲሳተ ወአሠረቶ ቦሙ ወትቤሎ ኢሎፍሊ መጽኡከ ሶምሶን ወእለሰ ይጸንሕዋ ውስተ ውሳጢት ወበተኮሙ እመዝራዕቱ ከመ ፈትል ፤

ደሊላም አዲስ የሆኑ ሰባት ሳመገመድ አምጥታ በነዚያ አሥራ ሶምሶን ኢሎፍላውያን መጡብህ አለችው ፤ ሊይዙ የሚጠብቁት ሰዎችም በጓዳ ተቀምጠው ነበር ፤ እነዚያንም ገመዶች ከክንዱ እንደ ፈትል ቆረጣቸው ።

፲፫፡ ወትቤሎ ደሊላ ለሶምሶን ወይእዜኒ አስተሐቀርከኒ ወሐሰተ ተናገርከኒ ወኢያይዳዕከኒ ጽድቀ አይድዓኒ እንከሰ በምንት የአሥሩከ ፤

ደሊላም ሶምሶንን አሁንም አታለልከኝ ፤ ሐሰት ነገርን ነገርከኝ እንጂ እውነቱን አልነ ገርከኝም ፤ ከወደድከኝስ እውነቱን ንገረኝ ፤ በምን ቢያ ሥሩህ ትደክማለህ አለችው ፤ የፍቅር አስመስላ ለማጥፋት ትቀማጠልበታለች ።

ወይቤላ እመ ጸፈርኪዮን ለስብኡ ቆናዝእየ ዘርእስየ ወተከልኪዮን በሰብዓቱ መታክል ውስተ ዓረፍት እደክም እንከ ወእከውን ከመ ፩ዱ እምዕጓለ እመሕያው ፤

በራሴ ያሉ ሰባቱን ብርንጐ ዎቼን /ጉንጉኖች/ በሰባት ካስማ አሥረሽ በኖራው ላይ ብትመቻቼው ከዚያ በኋላ እደክማለሁ ፤ ከሰውም እንደ አንዱ እሆናለሁ አላት ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፬፤ ወአኖመቶ ደሊላ ወጸፈረቶን ለሰብኡ ቆናዝኢሁ ዘርእሱ በኃይል ወተከለቶን በመታክል ውስተ ዓረፍት ወትቤሎ መጽኡከ ኢሎፍሊ ሶምሶን ፤

ደሊላም አስተኝታ በራሱ ላይ ያሉ ሰባቱን ብርንጐዎቹን ጉንጉኖቹን በኃይል አሥራ በኖራው ላይ በሰባት ካስማ አስመትታ ሶምሶን ኢሎፍ ላውን መጡ ብህ አለችው ፤

ወነቅሐ እምንዋሙ ወነዝዓ ውእተ መትከለ እምነ ዓረፍት ምስለ ቆናዝኢሁ ወኢተዓውቀ ኃይሉ ፤

ሶምሶንም ከእንቅልፉ ተነሥቶ ያን ካስማ ከብርንጐዎቹ ጉንጉ ኖቹ ጋር ከኖራው ነቀለው፤ ችካሉም ተነቃቅሎ ሲወድቅ ኃይሉ አልታወቀም ፤ አንድም የሶምሶን ኃይሉ የሚደክም በት አልታወቀም ፤

፲፭፤ ወትቤሎ ደሊላ እፎ ትቤለኒ አፍቀርኩኪ ወልብየ ምስሌኪ ወናሁ ሣልስከ ዝንቱ እንዘ ታስተ ሐቅረኒ ወኢታየድዓኒ በምንት ውእቱ ኃይልከ ዓቢይ ፤

ደሊላም እወድሻለሁ ልቤም ካንቺ ጋር ነው ለምን ትለኛ ለህ ? እነሆ ስታታልለኝ ይህ ሦስተኛህ ነው ከወደድከኝማ ኃይልህ የሚጸና በምን እንደ ሆነ አትነግረኝምን አለችው ፤

፲፮፤ ወእምዝ ሶበ አስርሐቶ በነቢብ ኵሎ ሌሊተ አጽሐበቶ እስከ ተቆጥዓ ለሞት ፤

ከዚህ በኋላ መላ ሌሊቱን በነገር ባደከመችው ጊዜ ልሙት ብሎ እስኪበሳጭ ድረስ ዘበዘ በችው ፤

፲፯፤ ወአይድዓ ኵሎ ዘውስተ ልቡ ወይቤላ መላፂ ኢለከፈኒ ርእሲየ እስመ ናዝራዊ አነ ለእግዚአብሔር እምከርሠ እምየ ወእምከመ ተላፀ ይኩ የኀድገኒ ኃይልየ ወእደክም ወእከውን ከመ ኵሉ ዕጓለ እመ ሕያው ፤

በልቡ ያለውን ሁሉ ነገራት ፤ እኔ ለእግዚአብሔር የስዕለት ልጅ ነኝና ከናቴ ማሕፀን ከተወለድኩ ጀምሮ ምላጭ ራሴን አልነካኝም ፤ ጠጕሬን ከተላጨሁ ኃይሌ ይለየኛል ፤ እኔም እደክማለሁ ከሰውም እንደ አንዱ እሆናለሁ አላት ፤

፲፰፤ ወአእመረት ደሊላ ከመ አይድዓ ኵሎ ዘውስተ ልቡ ወለአከት ወጸውአቶሙ ለመላእክተ ኢሎፍሊ ንዑ አሐተ ዕርጉ እስመ አይድዓኒ ኵሎ ዘውስተ ልቡ ፤

ደሊላም በልቡ ያለውን ገልጦ እንደነገራት አውቃ በልቡ ያለውን ሁሉ ነግሮኛልና አንድ ጊዜ ኑ /አንድ ሁናችሁ/ ኑ ብላ የኢሎፍሊን አለቆች ልካ አስጠራቻቸው ፤



ወዐርጉ ኀቤሃ ኵሎሙ መሳፍንተ ኢሎፍሊ ወአምጽኡ ወርቀ ምስሌሆሙ ፤

የኢሎፍሊም አለቆች ሁሉ አስቀድመው እንደተናገሩት ዋጋቸውን ይዘው ወደሷ መጡ ፤

፲፱፤ ወአኖመቶ ማዕከለ ብረኪሃ ወጸውዐት ቀራዔ ወቀረጸቶን ለሰብኡ ቆናዝአ ርእሱ ወአኀዘ ይድክም ወኀደጎ ኃይሉ ፤

እሷም እውነቱን እንደነገራት አውቃ የሚተኩስ (ትኩስ ምግብ) አብልታ ፤ የሚያስክር የወይን ጠጅ አጠጥታ ፤ ከጭኗ መካከል አስተኝታ ጠጕር የሚቆርጥ ሰው ጠርታ በራሱ ላይ ያሉ ሰባቱን ብርን ጐዎቹን /ጕንጕኖቹን/ አስቆ ረጠቻቸው ፤ እሱም ይደክም ጀመር ኃይልም ተነሣው ፤ አንድም ኃይል ተነሥቶት እየደከመ ሔደ ፤

፳፤ ወትቤሎ ደሊላ መጽኡከ ኢሎፍሊ ሶምሶን ወነቅሐ እምን ዋሙ ወይቤ እወፅእ ወእገብር ከመ ዘልፈ ወእነጽሖሙ ውእቱሰ ኢያእመረ ከመ ኀደጎ እግዚአ ብሔር ፤

ደሊላም ሶምሶን ኢሎፍላ ውያን መጡብህ አለችው ሳምሶንም ከእንቅልፉ ነቅቶ እንደቀድሞው ተነሥቼ ኃይል አደርጋለሁ ኢሎፍላውያንንም አጠፋቸዋለሁ ቢል እንደ ወትሮው ማድረግ ተሣነው ፤ እሱ ግን እግዚአብሔር እንደ ተለየው አላወቀም ነበር ፤

፳፩፤ ወአኀዝዎ ኢሎፍሊ ወአው ዕኡ አዕይንቲሁ ወአውረድዎ ውስተ ጋዛ ወሞቅሕዎ በመዋቅሕተ ሐዊን ወአንበርዎ ውስተ ቤተ ሞቅሕ ይሐርጽ ፤

ኢሎፍላውያንም ያን ጊዜ ሶምሶንን ያዙት ሁለት ዓይኑንም አጥፍተው ወደ ጋዛ አወረዱት ፤ ጋዛም አውር ደው በእግር ብረት አሥረው እየፈጨ ይኖር ዘንድ በእሥር ቤት አኖሩት ፤

፳፪፤ ወአኀዘ ሥዕርቱ ይብቊል እምዘቀረጽዎ ፤

ጸጕሩም ከተቆረጠ በኋላ እንደገና ይበቅል ጀመረ ፤ ኃይሉም ይመለስ ጀመር ፤

፳፫፤ ወተጋብኡ መላእክተ ኢሎ ፍሊ ከመ ይሡዑ መሥዋዕተ ለአምላከሙ ወከመ ይትፈሥሑ ወይቤሉ አግብአ አምላክነ ለሶምሶን ፀርነ ውስተ እዴነ ፤

ኢሎፍላውያንም የሶምሶን ኃይሉ በተመለሰለት ወራት ለጣዖታቸው መሥዋዕት ይሠዉ ዘንድ ጠላታችን

www.ethiopianorthodox.org

ሶምሶንን አምላካችን አሳልፎ በእጃችን ጣለልን ብለው ተድላ ደስታ ያደርጉ ዘንድ ተሰበሰቡ ፤

፳፬፣ ወሶበ ርእይዎ ሕዝብ አእኰትዎ ለአምላኮሙ ወይቤሉ አግብአ አምላክነ ውስተ እዴነ ዘአማሰና ለምድርነ ወአብዝኃ አብድንቲነ ፣

ኢሎፍላውያንም ሶምሶንን ባዩት ጊዜ አገራችንን ያጠፋት ሬሳችንን ያበዛ ጠላታችንን በእጃችን ጣለው ብለው ጣዖቱን አመሰገኑት ፤

፳፭፣ ወእምዝ ሶበ ተፈሥሑ ይቤሉ ጸውዕዎ ለሶምሶን እምነ ቤተ ሞቅሕ ይትቀነይ በቅድሜነ ፣

መሥዋዕቱን ከሠዉ በኋላ በልተውና ጠጥተው ደስ ባላቸው ጊዜ በፊታችን ይዘፍን ዘንድ /ይጫወት ዘንድ/ ሶምሶንን ከግዞት ቤት ጥሩት አሉ ፤

ወጸውዕዎ ለሶምሶን እምነ ቤተ ሞቅሕ ወተሣለቁ ላዕሌሁ ወአቀምዎ ማዕከለ ፪ቱ አዕማድ ፣

ሶምሶንንም ከግዞት ቤት ጠርተው በሁለቱ ምሰሶዎች መካከል አቁመው ይዘብቱበት ጀመር ፤

፳፮፣ ወይቤሎ ሶምሶን ለወልድ ዘይመርሖ አዕርፈኒ ወአግሥሠኒ አዕማደ እለ ዲቤሆን ይቀውም ዝንቱ ቤት ወአስምከኒ ላዕሌሆን ወገብረ ሎቱ ውእቱ ወልድ ከማሁ፣

ሶምሶንም ያን የሚመራውን ብላቴና ይህ ቤት የቆመባቸውን ምሰሶዎች አስይዘህ አሳርፈኝ ከዚያም አስጠግተህ አቁመኝ አለው ፣ ያም ብላቴና እንደነገረው አደረገለት ፤

፳፯፣ ወመልዑ ውስተ ውእቱ ቤት ዕድ ወአንስት ወሀለዉ ህየ ኮሎሙ መሳፍንተ ኢሎፍሊ ውስተ ናሕስኒ ወየአክሉ ፫፻ተ ዕደው ወአንስት ከመ ያኀድርዎ ለሶምሶን እንዘ ይትዋነይ ፣

ከዚያም ቤት ውስጥ ወንዶችም ሴቶችም መልተው ነበር የኢሎፍሊ መሳፍንትም ሁሉ በዚያ ቤት ደርብ መልተው ነበር ፣ ሶምሶንን ሲዘፍን ያዩት ዘንድ የተሰበሰቡት ወንዶችም ሴቶችም ሦስት ሺህ ይኖናሉ ፤

፳፰፣ ወጸርሐ ሶምሶን ኀበ እግዚአብሔር ወይቤ እግዚኦ እግዚኦ ተዘከረኒ ወአጽንዓኒ /ወአጽምዐኒ/ አሐተ እንከ እትቤቀል በቀለ አሐተ ህየንተ ክልኤሆን አዕይንትየ እምነ ኢሎፍሊ ፣

ሶምሶንም አቤቱ አቤቱ በምሕረትህ አስበኝ ፣ አንዲት



ነገርንም አድምጠኝ እንግዲህ ስለ ሁለቱ ዓይኖቼ ፈንታ ከኢሎፍላውያን አንዲት በቀልን ልመልስ ብሎ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ ፤

፳፱፣ ወአኀዞን ሶምሶን ለእልክቱ ክልኤሆን አዕማድ እለ ማዕከል እለ ዲቤሆን ይቀውም ውእቱ ቤት ወገፍዖን አሐተ በየማኑ ወአሐተ በፀጋሙ ፣

ሶምሶንም ያ ቤት በላያቸው የቆመባቸው /የተደገፈባቸው/ በመካከል ያሉ እነዚያን ሁለት ምሰሶዎች ይዞ አንዲቱን በቀኙ አንዲቱን በግራው ገፍቶ ጣላቸው ፤

፴፣ ወይቤ ሶምሶን ለትሙት ነፍስየ ምስለ ሰብአ ኢሎፍሊ ወአጠቆን በኃይሉ ወወድቀ ውእቱ ቤት ላዕለ መሳፍንተ ኢሎፍሊ ወላዕለ ኵሉ ሕዝብ ዘውስቴቱ ፣

ሶምሶንም ሰውነቴ ከኢሎፍሊ ሰዎች ጋር ትሙት /ትጥፋ/ ብሎ በኃይሉ ነቀነቃቸው ገፋ ቸው ፣ ያም ቤት በውስጡ ባሉ በሕዝቡ ላይና በኢሎፍ ላውያን ሹማምንት ላይ ወደቀ ባቸው ፤

ወኮኑ እለ ሞቱ እለ ቀተለ ሶምሶን በሞቱ ፈድፋደ እምእለ ቀተለ በሕይወቱ ፣

ሶምሶንም በሕይወቱ ሳለ ከገደ ላቸው ይልቅ በሞቱ ጊዜ ያጠፋቸው ሰዎች ብዙ ሆኑ ፤

፴፩፣ ወወረዱ አኀዊሁ ወኵሉ ቤተ አቡሁ ወዐርጉ ወነሥእዎ ወቀበርዎ ማዕከለ ሦራሕ ወማዕከለ ኤስታዎስ ውስተ መቃብረ ማኑሄ አቡሁ ፣

ያባቱ ወገኖችና ወንድሞቹም ሁሉ ወርደው ሬሣውን ይዘው መጥተው አባቱ ማኑሄ በተቀበረበት በሦራሕና በኤስታዎስ መካከል ቀበሩት ፤

ወኰነኖሙ ለእስራኤል ውእቱ ፳ ዓመተ ፣

እሱም እስራኤልን ሃያ ዘመን ገዛቸው ፣ ካለፈው ተናግሮት ነበርና ቢርቀው ፣ ደገመው ፣ ይህ ለጊዜው ተደርጓል ለኋላ ምሳሌው ፣ ሶምሶን የጌታ ፣ ሶምሶን በብሥራተ መልአክ ተፀንሶ ተወልዷል ፣ ጌታም በብሥራተ ገብርኤል ተፀንሶ ለመወለዱ ምሳሌ ፤ አንድም ሶምሶን ከአንበሳ ጉረሮ መዓር ሲበላ ፣ ከአህያ መንጋጋ ውሃ ሲጠጣ አልተጠየፈም ፣ ጌታም የሕዝቡን የአሕዛቡን ሥጋ ሲዋሐድ ላለመጸየፉ ፣ አንድም ሕዝቡ አሕዛቡ የጸለዩትን ጸሎት ፣ የአቀረቡትን መሥዋዕት ለመቀበሉ ምሳሌ፤ አንድም ሶምሶን በሕይወት ሳለ ካጠፋቸው አሕዛብ ትሙት ነፍስየ ብሎ በሞቱ ያጠፋቸው አሕዛብ ይበልጣሉ ፣ ጌታም በሕይወቱ ሳለ ድል ከነሳቸው አጋንንት በሞቱ ያጠፋቸው አጋንንት ይበልጣሉና ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፲፯

### ጉባኤ

፩፤ ወሀለወ ብእሲ ዘእምደብረ ኤፍሬም ዘስሙ ሚካ ፤

በዚያም ወራት ስሙ ሚካ የሚባል ከነገደ ኤፍሬም የተወለደ አንድ ሰው ነበር ፤

፪፤ ወይቤላ ሚካ ለእሙ ዝክቱ ወርቅ ዘትቤልኒ ተሰርቀኒ ወአምሐለኪ ናሁ ወርቁ ኀቤየ ውእቱ አነ ነሣእክዎ ወትቤ እሙ ቡሩክ ወልድየ ለእግዚአብሔር ፤

ሚካም እናቱን ተሰረቀብኝ ብለሽ የምታምይበት ያ ወርቅ እነሆ እኔ ወስጀው ወርቁ ከእኔ ዘንድ ነው አላት ፤ ተሰርቆ እንደጠፋባትም በዚህ ይታወቃል ፤ እናቱም ልጄ ለእግዚአብሔር ቡሩክ ፍጥረት ነህ አለችው ፤ የተላለፈ ንባብ ነው ፤

፫፤ ወአግብአ ውእተ ወርቀ ፲ወ፩ደ ፻ተ ለእሙ ወትቤ እሙ ቀድሶ ቀደስክዎ ለውእቱ ወርቅ ለእግዚአብሔር እምእዴየ ለባሕቲትየ ከመ ይትገበር ግልፎ ወስብክ ወይእዜኒ አገብአ ለኪ ወእኑ በኪዮ ፤

ሚካም ይህን ተናግሮ ሺህ ከአንድ መቶ ወቄት የሚሆን ያንን ወርቅ ለእናቱ መለሰ፤ ከዚህ በኋላ ቡሩክ ወልድየ ቢል ይቀናል ፤ እናቱም ከዚህ አስቀድሞ ይህ ወርቅ ከእጄ ቢገባ ለእግዚአብሔር ተመትቶ የተሠራ አፍ አፍንጫ እጅ እግር የወጣለት ጣዖት ሁኖ ይሠራ ዘንድ ለይቼ እሰጠዋለሁ ብላ ተስላ ነበር ፤ አሁንም መልሼ እሰጥሻለሁ አላት ፤

፬፤ ወወሀበ ውእተ ወርቀ ለእሙ ወነሥአት እሙ ውእተ ወርቀ ወወሀበት እምኔሁ ፪ተ ፻ተ ብሩረ ለዘይሰብኮ ወይገብሮ ግልፎ ወስብኮ ወአንበርዎ ውስተ ቤተ ሚካ ፤

«ነሥአት» ለማለት ደገመው ፤ አንድም ቀድሶ ቀደስክዎ ለእግዚአብሔር ብትለው ሚካም አሁን መልሼ እሰጥሻለሁ ብሎ ያንን ወርቅ መልሶ ሰጣት ፤ እናቱም ያን ወርቅ ተቀበለች ፤ ከተቀበለችውም ወርቅ ሁለት መቶ ብር ከፍላ ጣዖት ለሚሠራ ሰው ሰጠች ፤ ገንዘቡንም ተቀብለው በሚካ ቤት ውስጥ አስቀመጡት ፤

፭፤ ወብእሲሁሰ ሚካ ሎቱ ቤተ አማልክት ወገብረ ምስለ ወተራጺነ ወመልአ እዴሁ ለአሐዱ እምደቂቁ ወኮነ ካህነ ፤

ሚካም ለሚባለው ሰው የጣዖት ቤት ነበረውና በቤቱ የተቀመጠውን ብር ምስልን፤ /ጣዖትና/ የጣዖትንም ልብስ አሠራ ፤ ከልጆቹም የአንዱን እጅ ቀብቶ ካህን አደረገው /አገልጋይ ሆነው/ ፤



፮፤ ወበእማንቱ መዋዕል አልቦሙ ንጉሥ ለደቂቀ እስራኤል ብእሲ ብእሲ ዘአደሞ ቅድመ አዕይንቲሁ ይገብር ፤

በዚያም ወራት ለእስራኤል ልጆች ንጉሥ አልነበራቸውም፤ ኃጢአት መሥራታቸው ጣዖት ማምለካቸው የሚሠራ የሚቀጣ ንጉሥ ባይኖራቸው ነው ለማለት አንዱም አንዱ ሰው በፊቱ የወደደውን ያደርግ ነበር ፤

፯፤ ወሀለወ ወልድ ዘእምቤተልሔም ዘእምሕዝበ ይሁዳ ወእም ዘመደ ይሁዳ ወሌዋዊ ውእቱ ብእሲሁ ወይነብር ህየ ፤

ሕዝበ ይሁዳና ዘመደ ይሁዳ አንድ ፤ ወገን በዚያ ወራት ከነገደ ይሁዳ ተወልዶ በቤተልሔም የሚኖር አንድ ብላቴና ነበር ያም ሰው ካህን ሁኖ በዚያ ይኖር ነበረ ፤

፰፤ ወሖረ ውእቱ ብእሲ እምሀገረ ይሁዳ ወእምቤተልሔም ከመ ይኅድር ኀበ ረከበ ወበጽሐ ውስተ ደብረ ኤፍሬም ኀበ ቤተ ሚካ ከመ ይበት ፤

ይህም ሰው የይሁዳ ዕፃ ከምትሆን ከቤተልሔም ወጥቶ ባገኘው ቦታ ይኖር ዘንድ ሔደ ፤ ሒዶም በኤፍሬም ዕጣ ውስጥ ያድር ዘንድ ከሚካ ቤት ደረሰ የሔደበት ምክን ያት አልታወቀም ፤

፱፤ ወይቤሎ ሚካ ማዕዜ መጻእከ ወይቤሎ ሌዋዊ አነ እምቤተልሔም ዘይሁዳ ወአሐውር እንበር ኀበ ረከብኩ ፤

ሚካም ከቤት ወጥቶ የመጣህ ከወዴት ነው? የምትሔድበትስ ወዴት ነው አለው ፤ ያም ካህን እኔ የመጣሁት የይሁዳ ዕጣ ከምትሆን ከቤተልሔም ነው ፤ የምደርስበትን ግን አላውቅም ባገኘሁት ቦታ እኖር ዘንድ እሔዳለሁ አለው፤

፲፤ ወይቤሎ ሚካ ንበር ምስሌየ ወኩነኒ አበ ወካህነ ወአነ እሁበከ አሥሩ ኀብስተ ለለዕለትከ ወዘውገ አልባስ ወሲሳየከ ፤

ሚካም ይህስ ከሆነ አባትም ካህንም ሁነኝ ፤ ከእኔ ጋር ተቀመጥ ፤ ለለዕለትከ ሲሳየከ ብሎ ይገጥሟል፤ እኔም እያፈራረቅህ የምትለብሰው ሁለት ሁለት ልብስ ፤ በቀን የምትመገበውን አሥር አሥር ዳቦ እሰጥሃለሁ አለው ፤ አንድም አሥሩ ኀብስተ ባለው አሥሩ

www.ethiopianorthodox.org

ብሩረ ይላል ፣ ወሲሳየከን በዋዊ ያወርዳል ፣ ብሩም የወር ጨው ደመወዝ ይመስላል ፤

፲፩፣ ወአኀዘ ውእቱ ሌዋዊ ይንበር ምስለ ውእቱ ብእሲ ወኮኖ ውእቱ ወልድ ከመ አሐዱ እምደቂቁ ፣

ያም ካህን ይህን እየተቀበለ ከሚካ ጋር ይኖር ጀመር ፣ ሌዋዊ ያለውን ውእቱ ወልድ ብሎ ደገመው ፣ ከልጁም እንደ አንዱ ሁኖ ኖረ «ወመልአ እዴሁ ለአሐዱ እምደቂቁ» እንዳለው ፤

፲፪፣ ወመልአ እዴሁ ሚካ ለውእቱ ሌዋዊ ወኮኖ ውእቱ ወልድ ካህነ ወነበረ ውስተ ቤተ ሚካ ፣

እዴሁ ለውእቱ ብሎ ይገጥ ሟል ፣ ሚካም የዚያን ካህን እጁን ቀባው ፤ አንድም ከመ አሐዱ እምደቂቁን ከዚህ ያወርዷል ፣ ከልጆቹም እንደ አንዱ ልጁ አድርጎ ቀባው ውእቱ ወልድን ለልጁም ለሌ ዋዊም ቢሰጡ የተመቸ፣ ያም ብላቴና በሚካ ቤት ውስጥ አገልጋይ ሁኖ ኖረ ፤

፲፫፣ ወይቤ ሚካ ይእዜ አእመርኩ ከመ አሠነየ ላዕሌየ ገቢረ እግዚ አብሔር እስመ ኮነኒ ሌዋዊ ካህነ፣

ሚካም ሌዋዊ ካህን ሁኖል ኛልና እግዚአብሔር ለእኔ በጎ ነገር እንዳደረገልኝ ዛሬ አወቅሁ አለ ፡፡

## ምዕራፍ ፲፰

፩፣ ወበእማንቱ መዋዕል አልቦሙ ንጉሥ ለእ፳ኤል ወበእማንቱ መዋዕል የኀሥሡ ሎሙ ርስተ ሰብአ ዳን ኀበ ይነብሩ እስመ ኢረከቡ እስከ ይእቲ አሚር ርስተ በማዕከለ ፳ኤል ፣

በዚያም ወራት ለእስራኤል ንጉሥ አልነበራቸውም ፣ በዚ ያም ወራት እስከዚያች ቀን ድረስ በእስራኤል መካከል ርስት አላገኙም ነበርና የዳን ወገኖች ለየራሳቸው የሚኖሩ በት ርስት ይፈልጉ ነበር ፣ መውረስስ ወርሰዋል፣ እንደ ወንድሞቻቸው አብዝተው አልወረሱም ሲል ኢረከቡ አለ ፤

፪፣ ወፈነዉ ደቂቀ ዳን እም ሕዝቦሙ ሐምስተ ዕደወ እመክ ፈልቶሙ ደቂቀ ኃይል እምሦራሕ ወእስታሃል ከመ ይርአይዋ ለምድር ወያእምርዋ ወይቤልዎሙ ሑሩ ወርእዩ ለነ ምድረ ፣

የዳን ልጆችም ከወገኖቻቸው ጽኑዓን የሆኑ አምስት ሰዎች መርጠው ከዕጣቸው ከሦራሕና ከአስታሃል ሂዱችሁ ያችን አገር ሰልሉልን ብለው ላኩ ፤ አንድም ኃያላን ወደሆኑ ወደ ሦራሕና ወደአስታሃል ዕጣ አምስት ሰዎችን ልከው ሰደዱ፤



ወበጽሑ ውስተ ምድረ ኤፍሬም ኀበ ቤተ ሚካ ወኃደሩ ህየ እሙንቱ ኀበ ቤተ ሚካ ፣

እነዚያም ሒደው በኤፍሬም ዕጣ ከሚኖር ከሚካ ቤት ደርሰው ከዚያ አደሩ ፤

፫፣ ወአእመርዎ ለውእቱ ወልድ ወሬዛ ሌዋዊ ወቦኡ ህየ ወይቤልዎ መኑ አምጽአከ ዝየ ወምንተ ትገብር በዝየ ወምንት ብከ በዝየ፣

ከሚካ ቤትም በገቡ ጊዜ ካህን ሁኖ በሚካ ቤት የሚኖረውን ጐልማሳ አወቁት ፣ ወገናቸው ነውና ወደዚህ ማን አመጣህ? ከዚህስ ኖረህ ምን ታደርጋለህ? ከዚህስ ምን አለህ አሉት ፤

፬፣ ወይቤሎሙ ከመዝ ወከመዝ ረሰየኒ ሚካ ወአሰበኒ ወኮንክዎ ካህነ ፣

እሱም ሚካ እንዲህ አድርጎ ማለት ደመዎዝ ሰጥቶ ቀጠረኝ ፣ እኔም ካህን አገልጋይ ሆንኩት ፤

፭፣ ወይቤልዎ ተሰአል ለነ ኀበ እግዚአብሔር እመ ይሜርሕ ፍኖተነ እንተ ውስቴታ ነሐውር ንሕነ ፣

ለኛም የምንኼድባት መንገዳ ችንን ቢያቀናልን ወደእግዚአ ብሔር አመልክትልን /ቃለ እግዚአብሔር ጠይቅልን/ አሉት ፤

፮፣ ወይቤሎሙ ውእቱ ካህን ሑሩ በሰላም ይእተ ፍኖተክሙ ቅድመ እግዚአብሔር እንተ ባቲ ተሐውሩ፣

ያም ካህን በእግዚአብሔር ፊት የምትሄዱባት ይህችን ጐዳና ችሁን በፍቅር አንድነት ሒዱ አላቸው ፤

፯፣ ወሖሩ ሐምስቱ ዕደው ወበጽሑ ውስተ ሊሳ ወርእዩ ሕዝበ እለ ይነብሩ ውስቴታ ተአሚኖሙ ይነብሩ በሕገ ሲዶና ኀዱአነ ወዕሩፋነ እገዘ ይትአመኑ ፣

እነዚያም አምስት ሰዎች ሄደው ወደሊሳ ደረሱ ፣ በሊሳም በሲዶና ሥርዓት ጠላት ጠፍቶ ላቸው ተዘልለው የሚኖሩ ወገኖችን አዩ በሲዶና የሚኖሩ ሰዎች በባሕር ተከበው ከመከራ አርፈው ተዘልለው ይኖሩ ነበርና በሕገ ሲዶና አለ ፤

ወኢይክሉ ነቢበ ቃል ውስተ ምድረ ርስት መዝገበ ነገር እስመ ርኁቃን እሙንቱ እምነ ሲዶና ወአልቦሙ ትኅላፍ ምስለ ሶርያ ፣

ነቢበ ቃልና መዝገበ ነገር አንድ ወገን ፣ በምድረ ርስት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በሲዶና የሚኖሩትን ሰዎች መናገር አልቻሉም ፤ አንድም በምድረ ርስት ይህ ተድላ ደስታ ይታ ጣል አይሉም፣ እነሱ ከሲዶና የራቁ ነበሩና ከሶርያ ሰዎች

www.ethiopianorthodox.org

ጋርም መተሳሰፊያ አልነበራቸውምና ፤ አንድም ትኅሳፍ ይሳል ፣ ከሶርያ ሰዎች ጋር በነገር መተዛዘን አልነበራቸውምና ኢትትለኃፊ እኅትየ እንዲል ፣ ጦቢ.፳ቀ. ፳ ፤

፯፣ ወገብኡ እልክቱ ሐምስቱ ዕደው ኀበ አኃዊሆሙ ውስተ ሦራሕ ወአስታሃል ወይቤልዎሙ ምንተ ያነብረክሙ ፣

እነዚያም አምስቱ ሰዎች በሦራሕና በአስታሃል ውስጥ ወደሚኖሩ ወገኖቻቸው ተመልሰው ከዚህ ምን ያስቀምጣችኋል? አሏቸው ፤

፰፣ ተንሥኡ ንሑር ሳዕሌሃ እስመ ቦእናሃ ወአንሶሰውናሃ ለይእቲ ምድር እስከ አጽናፊሃ ወርኢነ ሕዝበ እለ ይነብሩ ውስቴታ በሕገ ሲዶና ወርኁቃን እሙንቱ እምነ ሲዶና ወአልቦሙ ትኅሳፈ ነገር ምስለ ሶርያ ፣

«ሳዕሌሃ ለሊሳ ነውኝ» ፣ ተነሱ ወደሊሳ እንሂድ የሊሳን ምድር ከዳር እስከ ዳር ዞረን አይተናል ፣ በውስጧም በሲዶና ሥርዓት ጸንተው አርፈውና ተዘልለው የሚኖሩ ወገኖችን አይተናል ፣ እነሱም ከሲዶና የራቁ ናቸውና ከሶርያ ሰዎች ጋር በነገር መተዛዘን የላቸውም ፣ ትኅሳፍ ቢል መገናኛ የላቸውም ፤

ወባሕቱ ተንሥኡ ወንዕርግ ሳዕሌሆሙ እስመ ርኢናሃ ለይእቲ ምድር ሠናይት ጥቀ ወአንትሙ አርምሙ ወኢትትሐከዩ ሐዊረ ወበዊአ ከመ ትትዋረስዋ ለይእቲ ምድር ፣

ነገር ግን ያችን አገር እጅግ መልካም እንደሆነች አይተናታልና በእነሱ ላይ እንዘምት ዘንድ ተነሡ ፣ እናንተስ ዝም በሉ ማለት አትከራከሩ ያችን አገር ትወርሷት ዘንድ ወደ እርሷ ሄዶ መግባትን ቸል አትበሉ ፤

፲፣ ወእምከመ ቦእክሙ ትበጽሑ ኀበ ሕዝብ እለ ተአሚኖሙ ይነብሩ ወምድርኒ ረኀብ እስመ አግብአ እግዚአብሔር ውስተ እዴክሙ ብሔረ ዘአልቦ ዘይትኃጣዕ እምኵሉ ቃል ዘተፈጥረ ውስተ ምድር፣

ወደሷም ከገባችሁ ጠላት ጠፍቶላቸው ተዘልለው ወደሚኖሩ ወገኖች ትደርሳላችሁ ፣ አገሪቱም ሰፊ ናት ፣ እግዚአብሔር እርሷን በእጃችሁ ጥሎላችኋልና በዚህ ዓለም ከተፈጠረው ነገር ሁሉ የሚታጣባት ነገር የለም አሏቸው ፤

፲፩፣ ወተንሥኡ እምህየ እምብሔረ ዳን እምነ ሦራሕ ወአስታሃል ፮፻ ብእሲ እለ ቅኑታኒሆሙ ወይፀውሩ ንዋየ ሐቅሎሙ ፣



ከዚያ ከዳን አገር ከሦራሕና ከአስተሃል ስድስት መቶ ሰዎች አሩቻቸውን /ሰይፋቸውን/ ታጥቀው ዘገራቸውን ነጥቀው ተነሱ ፤

፲፪፣ ወዐርጉ ወኃደሩ ውስተ ቀርያታርም ዘይሁዳ ወበእንተዝ ተሰምየ ውእቱ መካን ትዕይንተ ዳን እስከ ዮም መንገለ ድኅሬሃ ለቀርያታርም ፣

ወጥተውም የይሁዳ ዕጣ በምትሆን በቀርያታርም ሰፍረው አደሩ ፣ ስለዚህም ያ ቦታ እስከ አሁን የዳን ሰፈር ተባለ፣ ይኸውም ከቀርያታርም በኋላ ያለው ነው ፤

፲፫፣ ወኃሊፎሙ እምህየ በጽሑ ውስተ ደብረ ኤፍሬም ወመጽኡ እስከ ኀበ ቤተ ሚካ፣

ከዚያም አልፈው በኤፍሬም ዕጣ ውስጥ ካለ ከሚካ ቤት ደረሱ ፤

፲፬፣ ወይቤልዎሙ እልክቱ ፭ቱ ዕደው እለ ሖሩ ይርአይዋ ለይእቲ ምድረ ሊሳ ወይቤልዎሙ ለአኃዊሆሙ ሰበ ተአምሩ ከመ ቦቱ ውስተ ዝንቱ ቤት ምስል ወተራፊን ወግልፎ ወስብኮ ወይእዜኒ አእምሩ ዘትገብሩ ፣

የሊሳንን ምድር ሊሰልሉ የሄዱ እነዚያም አምስቱ ሰዎች ወንድሞቻቸውን በዚህ ቤት ምስል የጣዖትም ልብስ ተመትቶ የተሠራ ጣዖትም እንዳለ ብታውቁስ ዝም ባላችሁም ነበር ፣ አሁንም የምታደርጉትን እወቁ አሏቸው ፤

፲፭፣ ወተግኅሡ ህየ ወቦኡ ውስተ ቤቱ ለውእቱ ወልድ ሌዋዊ ውስተ ቤተ ሚካ ወተአምኃዎ ፣

ከዚያም እልፍ ብለው በሚካ ቤት ወዳለ ካህን ወደሆነው ብላቴና ቤት ገብተው እጅ ነሱት ፤

፲፮፣ ወእልክቱ ፮፻ ብእሲ እንዘ ይፀውሩ ንዋየ ሐቅሎሙ ቅኑታኒሆሙ ተጋብኡ ኀበ ኆኅተ አንቀጽ እለ እምደቂቀ ዳን ፣

እነዚያም ፮፻ መቶ ሰዎች ሰይፋቸውን ታጥቀው ፣ ዘገራቸውን ነጥቀው ከዳን ልጆች ተለይተው ከበሩ ደጃፍ ተሰብስበው ቆሙ ፤

፲፯፣ ወዐርጉ እልክቱ ሐምስቱ ዕደው እለ ሖሩ ቀዲሙ ከመ ይርአዩ ምድረ ወቦኡ ወነሥኡ ዝክተ ምስለ ወግልፎ ወተራፊነ ወስብኮ ፣

ያችን አገር ለማየት አስቀድመው ሄደው የነበሩ እነዚያ አምስቱ ሰዎችም ከሚካ ቤት ገብተው ጣዖቱን ሁሉ ከነልብሱ አንስተው ወሰዱ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወዝክቱሰ ካህን ይቀውም ኀበ ኆኅተ አንቀጽ ወእልክቱኒ ፮፻ ብእሲ ይፀውሩ ንዋየ ሐቅሎሙ ቅኑታኒሆሙ ።

ያ ካህን ግን ከበሩ ደጃፍ ቁሞ ነበር ፤ እያየ አለማስጣሉን መናገር ነው ፤ እነዚያ ፮መቶ ሰዎችም ዘገራቸውን ነጥቀው ፤ ሰይፋቸውን ታጥቀው ቁመው ነበር /ተሰልፈው ነበር/ ፡፡

፲፰፤ ወቦኡ እሙንቱ ዕደው ውስተ ቤተ ሚካ ወነሥኡ ዝክተ ግልፎ ወምስለ ወተራፊነ ወስብኮ ወይቤሎሙ ዝክቱ ካህን ምንተ ትገብሩ አንትሙ ፤

ውስተ ቤተ ሚካ ለማለት ደገመው ፤ እነዚያም ሰዎች ወደ ሚካ ቤት ገብተው ጣዖታቱንና የጣዖቱን ልብስ ወሰዱ፤ ያም ካህን ከበሩ ደጃፍ ቁሞ እናንተ ሰዎች ምን ታደርጋላችሁ ? ቢላቸው፡፡

፲፱፤ ወይቤልዎ አርምም ወደይ እዴከ ውስተ አፉከ ወነዓ ምስሌነ ወትከውነነ አበ ወካህነ ቦኑ ይኄይሰከ ትኩን ካህነ ለአሐዱ ብእሲ እምትኩን ካህነ ለነገድ ወለሕዝበ ፳ኤል ፤

እጅህን ከአፍህ ላይ ጭነህ ዝም ብለህ ከኛ ጋር ሒድ መካሪ አባት ካህን ትሆነናለህ ለ፳ኤል ወገንና ለብዙ ነገድ ካህን ከመሆን ለአንድ ሰው ካህን መሆን ይሻልሃል አሉት ፡፡

፳፤ ወተፈሥሐ ልቡ ለውእቱ ካህን ወነሥአ ውእተ ምስለ ወተራፊነ ወግልፎ ወስብኮ ወቦአ ማዕከለ ሕዝብ ፤

ያም ካህን የነገሩትን ሰምቶ ልቡን ደስ አለውና እነዚያ የያዙትን ጣዖትና ምስል ከነልብሱ ተቀብሎ ከሕዝቡ መካከል ገባ ለማስከበር ነው ፡፡

፳፩፤ ወተመይጡ ወሖሩ ወነሥኡ ኵሎ ቤቶ ወጥሪቶ ወኵሎ ክብሮ ወነድኡ ቅድሜሆሙ ፤

እነዚያም ሰዎች የካህኑን በቤት ያለውን ጥቃቅንና ታላላቅ ገንዘቡን ሁሉ ይዘው ፤ ጓዙን ሁሉ ጭነው በፊት በፊታቸው እየነዱ ወደ አገራቸው ተመል ሰው ሄዱ ፡፡

፳፪፤ ወእንበለ ይርኅቁ እምቤተ መጽአ ሚካ ወዕደው ሕዝብ እለ ቅሩብ ቤቱ ለሚካ ወጸርሑ እምድኅሬሆሙ ለደቂቀ ዳን ወአውየወ ሎሙ ለደቂቀ ዳን ፤

ከቤቱም ሳይርቁ ሚካ መጣ ፤ በሚካ ቤት አቅራቢያ የሚኖሩ ወገኖቹም ሁሉ ይህን ሰምተው መጡ ፤ ለዳን ልጆችም ከወደኋላቸው ሁነው ጮኹላቸው ፡፡

፳፫፤ ወሜጡ ገጾሙ ደቂቀ ዳን ወይቤልዎ ለሚካ ምንተ ኮንከ ዘትጸርሕ ፤



የዳን ልጆችም ፊታቸውን መልሰው ሚካን የምትጮህ ምን ሁነህ ነው ? አሉት ፡፡

፳፬፤ ወይቤሎሙ ሚካ ግልፎየኒ ዘገበርኩ ነሣእክሙኒ ወካህንኒ ወሖርክሙ ወምንተ እንከ ኃደግሙ ሊተ ዘትብሉኒ ምንተ ትጸርሕ ፤

ሚካም የሠራሁትን ጣዖቴን ፤ የቀጠርሁትን አገልጋዬን ይዛችሁብኝ ሄዳችሁ እኔ እንግ ዲህ ምን ተዋችሁልኝና ለምን ትጮኻለህ ትሉኛላችሁ ? አላቸው ፡፡

፳፭፤ ወይቤልዎ ደቂቀ ዳን ኢይስማዕ እንከ ቃልከ ምስሌነ ወእመ አኮሰ ይትራከቡከ ዕደው መሪራነ ነፍስ ወታኀጕል ዓዲ ነፍሰከ ወነፍሰ ቤትከ ፤

የዳን ልጆችም ከኛ ጋር እነጋ ግራለሁ ብለህ እንግዲህ ቃልህ አይሰማ እንቢ ካልህ ግን ከልቡናቸው ቁጡ የሆኑ ሰዎች ይገናኙሃል ዳግመኛ ገንዘብ እፈልጋለሁ ስትል ሰውነት ህንና የወገኖችህን ሰውነት ታጠፋለህ አሉት ፡፡

፳፮፤ ወሖሩ ደቂቀ ዳን ፍኖቶሙ ወርእየ ሚካ ከመ ይጸንእዎ ወተመይጠ ወአተወ ቤቶ ፤

የዳን ልጆች ይህን ተናግረው መንገዳቸውን ሄዱ ፤ ሚካም እንደበረቱበት አይቶ ተመልሶ ወደቤቱ ገባ ፡፡

፳፯፤ ወእሙንቱሰ ነሥኡ ኵሎ ዘገብረ ሚካ ወካህንኒ ወኵሎ ዘቦ ወሖሩ እስከ ሊሳ ላዕለ ሕዝብ ዘተአሚኖ ይነብር ወቀተልዎ በአፈ ሐፂን ወህገሮሙኒ አውዓዩ በእሳት፤

እነሱ ግን ሚካ የሠራውን ጣዖቱን ሁሉ ካህኑንና ያለ ገንዘቡንም ሁሉ ይዘው ሊሳ ደርሰው ጠላት ጠፍቶለት ተዘልሎ ወደሚኖር ወገን ሄደው ሰዎቹን በጦር እየወጉ ፤ በሰይፍ እያረዱ ገደሏቸው ፤ አገራቸውንም በእሳት አቃጠሉ ፡፡

፳፰፤ ወአልቦ ዘድኅነ እስመ ርኁቃን እሙንቱ እምነ ሲዶና ወአልቦሙ ትልህፍ ምስለ ባዕድ ሰብእ ፤

እነሱ ከሲዶና የራቁ ናቸውና ፤ ከሌላም ሰው ጋር በነገር መነዛነዝ አልነበራቸውምና ትህሳፍ ቢል ከሌላ ሰው ጋር መገናኛ አልነበራቸውምና ከነሱ ሸሽቶ የዳነ የለም ፡፡

ወይእቲሰ ውስተ ቈላት እንተ ቤተ ጦብ ወሐነፅዋ ለይእቲ ሀገር ወነበሩ ውስቴታ ፤

ይህችም አገር ወይም ሊሳ በጦብ ወገን ቈላ /በጦብ ቤት አጠገብ/ ባለ ቈላ ያለች ናት ያችኑ አገር አቅንተው ፤ ቅጽሯን ቀጽረው በውስጧ ኖሩባት ፡፡

፳፱፤ ወሰመዩ ስማ ለይእቲ ሀገር ዳን በስመ አቡሆሙ ዳን ዘተወልደ ለእስራኤል ወስማሰ ለይእቲ ሀገር ቀዲሙ ሊሳ ፤

ያችንም አገር ስሟን ከያዕቆብ በተወለደ በአባታቸው በዳን ስም ጠሯት ፤ ቀድሞ ግን የዚያች አገር ስሟ ሊሳ ይባል ነበር ፤

፴፤ ወአቀሙ ሎሙ ደቂቀ ዳን ግልፎ ዘሚካ ወዮናታን ወልደ ጌርሳም ወልደ ሙሴ ውእቱ ወደቂቀ ካህናት እሙንቱ ለሕዝበ ዳን እስከ አመ ፍልስተ ምድሮሙ፤

የዳን ልጆችም ዘርፈው ያመጡት የሚካን ጣዖት አምላክ አድርገው አቆሙ ፤ የሙሴ የልጁ የጌርሳም ልጅ ዮናታንና ልጆቹም አገራቸው እስከ ጠፋ ድረስ ለዳን ወገኖች አገልጋዮች /ካህናተ ጣዖት/ ሁነው ኖሩ ፤

፴፩፤ ወአቀሙ ሎሙ ግልፎ ዘሚካ ዘገብረ በኵሉ መዋዕል አምጣነ ነበረ ቤተ እግዚአብሔር ውስተ ሴሎም ወበእማንተ፡ መዋዕል አልቦሙ ንጉሥ ለእስኤል ፤

ሚካ የሠራውንም ጣዖት የእግዚአብሔር ማደሪያ ደብተራ ኦሪት በሴሎ ተተክሎ የኖረውን ያህል በዘመኑ ሁሉ ተክለው ኖሩ ፤ በዚያም ወራት ለእስኤል ንጉሥ አልነበራቸውም ፤ ይህን ሁሉ ማድረጋቸው የሚሠራ የሚቀጣ ንጉሥ ባይኖራቸው ነው ለማለት እንዲህ አለ ፤ አንድም ንጉሥ የሚነግሥ በት ጊዜ ደርሷልና ሦስት ጊዜ መላልሶ ተናገረው፤ አሁን ሳሙኤልና ዳዊት የሚያጠፏት ናቸውና::

## ምዕራፍ ፲፱

### ገባኤ

፩፤ ወሀሎ ፩ ብእሲ ሌዋዊ ወይነብር ውስተ ፩ዱ.ደብር ዘደብረ ኤፍሬም ወነሥአ ሎቱ ውእቱ ብእሲ ብእሲተ ዕቅብተ እምቤተ ልሔም ዘይሁዳ ፤

በኤፍሬም ዕጣ በአንድ አገር ውስጥ ካህን ሁኖ የሚኖር አንድ ሰው ነበረ ፤ ይህም ሰው የይሁዳ ዕጣ ከምትሆን ከቤተ ልሔም ሕግ የምትጠብቅለትን ሚስት አግብቶ ይኖር ነበር ፤

፪፤ ወተምዕዐቶ ዕቅብቱ ወኃደገቶ ወአተወት ቤተ አቡሃ ቤተልሔም ዘይሁዳ ወነበረት ህየ መዋዕለ ፬ተ አውራኃ ፤

ከዕለታት አንድ ቀን ሚስቱ ተጣላችውና ትታው የይሁዳ ዕጣ በምትሆን በቤተ ልሔም ወደ አለ አባቷ ቤት ሄደች ፤ በዚያም አራት ወር ያህል ተቀመጠች ፤





፫፤ ወተንሥአ ምታ ወሖረ ወተለዋ ከመ ይትአረቃ ወያግብኣ ኀቤሁ ወቍልዔሁ ምስሌሁ ወ፪ቱ አእዱግ ወሖረ ቤተ አቡሃ ወርእዮ አቡሃ ለይእቲ ወለት ወሖረ ወተቀበሎ ፤

ባሏም ታርቆ ወደእርሱ ይመልሳት ዘንድ ተከትሏት ሄደ ፤ ብላቴናውን አስከትሎ ሁለት በቅሎ አስጭኖ ወደአማቱ ቤት ሄደ ፤ የዚያችም ልጅ አባት ሲመጣ አይቶ ሄደ ተቀበለው ፤

፬፤ ወአብኦ ውስተ ቤቱ ወነበረ ምስሌሁ ሠሉሰ መዋዕለ ወበልዑ ወሰትዩ ወቤተ ህየ ፤

ያም ካህን ሚስቱን ታርቆ ከአማቱ ጋር ሦስት ቀን ያህል ተቀመጠ ፤ በሦስተኛውም ቀን በልተው ጠጥተው ከዚያው አደረ ፤

፭፤ ወእምዝ አመ ራብዕት ዕለት ነቅሐ በጽባሕ ወተንሥአ ይሑር ወይቤሎ አቡሃ ለይእቲ ወለት ለሐሙሁ አፅንዕ ልበከ ወብላዕ ፍተ ኅብስት ወእምዝ ተሐውሩ ፤

ከዚህ በኋላ በአራተኛዪቱ ቀን ማለዳ ከእንቅልፉ ነቅቶ ለመሄድ ተነሳ ፤ የዚያችም ብላቴና አባት አማቹን ልብህን አፅንተህ ጥቂት እህል ቅመስ፤ ከዚያ በኋላ ትሄዳላችሁ አለው ፤

፮፤ ወነበሩ ወበልዑ ፪ሆሙ ኅቡረ ወሰትዩ ወይቤሎ አቡሃ ለይእቲ ወለት ለውእቱ ብእሲ ቢት ዮምኒ ወይትፌሣሕ ልብከ፤

ከዚህ በኋላ ሁለቱም ተቀምጠው በአንድነት በሉ ጠጡ ፤ የዚያችም ብላቴና አባት ያን ሰው ዛሬም ልብህን ደስ ብሎት እደር አለው ፤

፯፤ ወተንሥአ ውእቱ ብእሲ ይሑር ወአገበሮ ሐሙሁ ወኅዕበ ቤተ ህየ ፤

ከበሉ ከጠጡ በኋላም ያ ሰው ሊሄድ ተነሣ ፤ አማቱ ግድ ብሎ ማለደው ፤ ዳግመኛ ከዚያ አደረ ፤

፰፤ ወነቅሐ በጽባሕ አመ ሐምስ ዕለት ከመ ይሑር ወይቤሎ ሐሙሁ አቡሃ ለይእቲ ወለት ብላዕ እክለ ወእምዝ ተሐውር እስከ የዓርብ ፀሐይ ወበልዑ ወሰትዩ ፪ሆሙ ፤

በአምስተኛውም ቀን ይሄድ ዘንድ ማልዶ ተነሣ ፤ የዚያች ብላቴና አባትም እህል ብላ ከዚያ በኋላ ፀሐይ እስኪገባ ድረስ ትሄዳለህ አለው ከዚህ በኋላ ሁለቱም ተቀምጠው በሉ ጠጡ ፤

፱፤ ወተንሥአ ውእቱ ብእሲ ከመ ይሑር ውእቱ ወዕቅብቱ ወቍልዔሁ ምስሌሁ ወይቤሎ ሐሙሁ አቡሃ ለይእቲ ወለት ናሁ መስየ

ወተቈልቈለ ፀሐይ ኀድር ዝየ የዖምኒ ወንበር ዝየ ወይትፌሣሕ ልብከ ወትገይሡ በጽባሕ ፍኖተ ከሙ ወተአተ ቤተከ ፤

ከበሉ ከጠጡ በኋላ ያ ሰው ሚስቱን ይዞ ብላቴናውን አስከትሎ ተነሣ ፤ የዚያች ብላቴና አባት አማቱ ፀሐይ ተዘቅዝቋል መሽቷልና ዛሬም ከዚህ እደር ልብህንም ደስ ብሎት ተቀመጥና በማለዳ ተነሥታችሁ ጎሥግሣችሁ ትገባላችሁ አለው ፡

፲፤ ወአበየ ውእቱ ብእሲ በይተ ወተንሥአ ወሖረ ወበጽሐ እስከ ቅድመ ኢያቡሴዎን እንተ ይእቲ ኢየሩሳሌም ወምስሌሁ ፪ቱ አዕዱግ ዕዑናን ወይእቲ ዕቅብቱ ምስሌሁ ፤

ያም ሰው በአምስተኛው ቀን አላደርም ብሎ ተነሥቶ ሄደ፤ ሄደውም በኢያቡሴዎን ፊት ለፊት እስከ አለ አገር ደረሱ ይህችውም ኢየሩሳሌም ናት ከእርሱም ጋር ሁለት የተጫኑ በቅሎች ነበሩ ፤ ሚስቱም ከእርሱ ጋር ነበረች ፡

፲፩፤ ወእንዘ ዓዲሆሙ ሀለዉ አንፃረ ኢያቡሴዎን ፀሐይኒ ተቈልቈለት ጥቀ ወይቤሎ ቍልዔሁ ለእግዚኡ ነዓ ንግኃሥ ውስተ ሀገረ ኢየሩሳሌም ዛቲ ወንቢት ውስቴታ ፤

ገና በኢያቡሴዎን አንፃር ሳሉ ፀሐይ ፈጽሞ ተዘቀዘቀ ፤ ብላቴናውም ጌታውን ኢየሩሳሌም ከምትባል ከዚያች አገር ደርሰን በውስጧ እንደር አለው ፡

፲፪፤ ወይቤሎ እግዚኡ ኢይግኃሥ ውስተ ሀገረ ነኪር እንተ ኢኮነት ዘደቂቀ እስራኤል ንኅልፍ እስከ ገባዖን ፤

ጌታውም ወደገባዖን እንሂድ እንጂ የሌኤል ልጆች ወደ አልሆነች ወደባዕድ አገር አልሄድም አለው ፡

፲፫፤ ወይቤሎ ለቍልዔሁ ነዓ ንግኃሥ ዉስተ ፩ዱ መካን ወንኅድር ውስተ ገባዖን እንተ ስማ ራማ ፤

ውስተ አሐዱ መካን ያለውን ራማ ብሎ ገለጠው ፤ ጌታውም ብላቴናውን ይልቁንስ ና ወደ አንድ ቦታ ሄደን በገባዖን ስሟ ራማ በምትባል ቦታ እንደር አለው ፡

፲፬፤ ወኃለፉ ወሖሩ እስከ ዐረበ ፀሐይ ወበጺሖሙ ገባዖን እንተ ብንያም ግኃሡ በህየ ከመ ይባኡ ወይኅድሩ ውስተ ገባዖን፤

ይህን ተነጋግረው ኢየሩሳሌምን አልፈው እስከ ፀሐይ መግቢያ ድረስ ሄዱ፤ የብንያም ዕጣ ከምትሆን ከገባዖንም ደርሰው ከዚያ ገብተው ያድሩ ዘንድ ተጓዙ ፡



፲፭፤ ወቦኡ ወነበሩ ወስተ መርህበ ሀገር ወአልቦ ዘያበውዖሙ ውስተ ቤት ወዘየኃድሮሙ ፤

ከቤት ውስጥ አስገብቶ የሚያሳድራቸው አልነበርምና ከዚያ ገብተው ከሀገሩ አደባባይ ተቀመጡ ፡

፲፮፤ መወጽአ ብእሲ ልሂቅ እምግብሩ ወብእሲሁሰ እምደብረ ኤፍሬም ወምንባሪሁ ውስተ ገባዖን ወሰብአ ብሔርሰ ደቂቀ ብንያም ፤

ባደባባዩ ተቀምጠው ሳለ ሽማግሌ ሰው መጣ ፤ የዚያም ሰው መኖሪያው በገባዖን ውስጥ ሲሆን ትውልዱ ግን ከነገደ ኤፍሬም ነው ፤ በዚያ አገር የሚኖሩ ሰዎች ግን የብንያም ልጆች ናቸው ፤ ሎጥ ተሰዶ በሰዶም ይኖር እንደ ነበር እርሱም ተሰዶ በገባዖን ይኖር ነበር ፡

፲፯፤ ወነጸሩ በአዕይንቲሆሙ ወር እይዎ ለዝክቱ ብእሲ ነጋዲ ውስተ መርህበ ሀገር ወይቤሎ ዝክቱ ልሂቅ አይቴ ተሐውር ወእምአይቴ መጻእከ ፤

እሊህም ሰዎች አንገታቸውን አቅንተው ቢመለከቱ ያን እንግዳ ሰው ከአገሩ አደባባይ ተቀምጦ አዩት፤ ያም ሽማግሌ ከወዴት መጣህ? ወዴትስ ትሄዳለህ? አንድም የመጣኸው ከወዴት ነው? የምትሄደውስ ወዴት ነው? አለው ፡

፲፰፤ ወይቤሉ ኃለፍት ንሕነ እም ቤተ ልሔም ዘይሁዳ እስከ አመ ንበጽሕ ደብረ ኤፍሬም እስመ እምህየ አነ ወሖርኩ እስከ ቤተ ልሔም ዘይሁዳ ወአአተ ቤትየ ወአልቦ ዘአግህሠኒ ውስተ ቤቱ ፤

እኛ የመጣን የይሁዳ ዕጣ ከምትሆን እስክንደርስ ነው ፤ እኔ ከኤፍሬም ዕጣ ወደ ይሁዳ ዕጣ ወደቤተልሔም ሄጄ ነበርና አሁንም በኤፍሬም ዕጣ ወደአለው አገሬ መሄዴ ነው ፤ ዛሬስ ወዴት ታድራለህ ቢለው ዛሬስ ወደቤት ወስዶ የሚያሳድረኝ የለም /አላገኘሁም/ አለው ፡

፲፱፤ ወሐሠርኒ ወእክልኒ ብነ ለአዕዱጊነ ወኅብስትኒ ወወይንኒ ብነ ለዓመትከኒ ወለገብርከኒ ወለቍልዔከኒ አልቦ ዘነኃጥእ እምኵሉ መፍቅድነ፤

ለአህዮቻችንም ገለባ /ገፈራ/ አለን፤ ለአገልጋይህ ለሚስቴም ለብላቴናህም የምንጠጣው ወይን የምንበላው እንባሻ አለን ከምንፈልገው ሁሉ የምናጣው የለም አለው ፡

፳፤ ወይቤሎ ዝክቱ ብእሲ ልሂቅ ሰላም ለከ ወኵሉ ዘአልብከ ላዕሌየ ወባሕቱ ውስተ መርህባሰ ኢትኅድር ፤

ያም ሽማግሌ ሰው ደስ ይበልህ፤ ለአንተ የሌለው ሁሉ

www.ethiopianorthodox.org

ከኔ ዘንድ አለ ፣ ነገር ግን በአደባባይ አትደር አለው ፤

፳፩፣ ወአብኦ ውስተ ቤቱ ወአቅ ምሐ ለአዕዱጊሁ ወሐፀቦሙ እገሪ ሆሙ ወበልዑ ወሰትዩ ፣

ዋዌውን ጥሶ ማሠር ነው ፣ ወደቤቱ አገባው ፣ ለአህዮቹም ገፈራ ማለሳቸው ፣ እግራቸውንም አጠባቸውና የሚበሉትን የሚጠጡትን አቀረበላቸው ፣ በሉም ጠጡም ፤

፳፪፣ ወእምዝ ተፈሥሐሙ ልቦሙ ናሁ ደቂቀ ኃጥአን ሰብአ ሀገር አገትዎ ለውእቱ ቤት ወጐድጐዱ ኆኅቶ ወይቤልዎ ለዝክቱ ብእሲ ልሂቅ በዐለ ቤት አውፅእ ለዝክቱ ብእሲ ዘቦአ ውስተ ቤትከ ከመ ንሑሮ ፣

ከዚህ በኋላ በልተው ጠጥተው ልቡናቸውን ደስ ባለው ጊዜ እነሆ ኃጥአን የሚሆኑ የሀገሩ ሰዎች የገቡበትን ቤት ከበው በሩን መቱ ፣ ያንንም የቤቱን ባለቤት ሽማግሌ ሰው እንደርስበት ዘንድ ወደቤትህ የገባ ያንን ሰው አውጣልን አሉት፣ ግብረ ሰዶም ለምደው ነበርና ኢትሑር ኀበ ብእሲተ ብእሲ ያለውን ይዘው ከመ ንሑሮ አሉ ፤

፳፫፣ ወወፅአ ኀቤሆሙ ዝክቱ ብእሲ በዐለ ቤት ወይቤሎሙ ሐሰ ለክሙ አኃዊነ ኢትግበሩ እኩየ እምድኅረ ቦአ ብእሲ ውስተ ቤትየ ኢትግበሩ ዘንተ ዕበደ ፣

ያም የቤቱ ባለቤት ወደ እነርሱ ወጥቶ ወንድሞቼ ለእናንተ አገባባችሁ አይደለም ፣ ሰው ከገባ በኋላ ስንፍና የሚሆን ይህን ክፉ ነገር አታድርጉ አላቸው ፤

፳፬፣ ናሁ ወለትየ ድንግል ወዕቅብቱ ወአውፅኦን ወአኅስርዎን ወግበሩ ላዕሌሆን ዘይኤድመክሙ ወውስተ አዕይንቲክሙ ወላዕለ ዝክቱሰ ብእሲ ኢትግበሩ ዘንተ ነገረ ዕበድ ፣

ግድ ቢሉት እንቢ ካላችሁ እነሆ ባል ያላገባች ልጄና ሚስቱ አሉ ወስዳችሁ ድረሱባቸው አላቸው ፣ ባልተሠራለት በወንድ የማይገባ ሥራ ከሚሠሩ በተሠራላቸው በሴቶች የሚገባ ሥራ ይሥሩባቸው ብሎ ፣ በዚያ ሰው ላይ ግን ስንፍና የሚሆን ይህን ክፉ ነገር አታድርጉ አላቸው፤

፳፭፣ ወኢፈቀዱ እሙንቱ ሰብእ ይስምዕዎ ወነሥአ ዝክቱ ብእሲ ለዕቅብቱ ወአውፅኣ አፍአ ኀቤሆሙ ወአኅሰርዋ ወተዋነይዋ ኵላ ሌሊተ እስከ ጸብሐ ወፈነውዋ ሶበ ዐርገ ጎህ ፣



እነዚያም ሰዎች ይሰሙት ዘንድ አልወደዱም ፣ ያም ሰው ሚስቱን እነእርሱ ወደአሉበት ወደውጭ አው ጥቶ ሰጣቸው እነዚያም ሰዎች ተቀብለው አሥራ ሁለት ሰዓት ሌሊት ሁሉ በፈረቃ ተጫወቱባት ፣ አጐሳቈሏት ፣ ሲነጋም /ጎህ በቀደደ ጊዜ/ አሰናበቷት ፡

፳፮፣ ወመጽአት ይእቲ ብእሲት በጽባሕ ወወድቀት ኀበ መድረከ ኆኅት ዘውእቱ ብእሲ በዐለ ቤት ኀበ ሀለወ ሀየ እግዚኣ እስከ ጸብሐ፣

ያችም ሴት ሲነጋ ወደባሏ መጥታ ባሏ ባለበት ቤት ደጃፍ መድረክ እስኪነጋ ድረስ ወድቃ አደረች ፤

፳፯፣ ወተንሥአ እግዚኣ በጽባሕ ወአርኀወ ኆኅተ ውእቱ ቤት ወወፅአ ከመ ይሑር ፍኖቶ ወረከባ ለዕቅብቱ ውድቅተ ኀበ ኆኅተ ውእቱ ቤት ወእደዊሃ ላዕለ መድረክ ፣

ባሏም ሲነጋ ከመኝታው ተነስቶ የዚያን ቤት ደጃፍ ከፍቶ መንገዱን ይሄድ ዘንድ ቢወጣ ሚስቱን እርሱ ካለበት ቤት ከደጃፍ ላይ ሁለቱን እጆቿን ከመድረኩ ላይ ዘርግታ ወድቃ አገኛት ፤

፳፰፣ ወይቤላ ተንሥኢ ንሑር ወኢያውሥአቶ እስመ ሞተት

ወፀዓና ዲበ አድጉ ወተንሥአ ውእቱ ብእሲ ወአተወ ብሔሮ፣

ያለች መስሎት ተነሽ እንሒድ ቢላት እሷ ሙታለችና አልመለሰችለትም ፣ ያም ሰው እንደ ሞተች አይቶ ሬሳዋን በበቅሎ ላይ ጭኖ ከገባያን ተነሥቶ ወደ አገሩ ገባ ፡

፳፱፣ ወቦአ ቤቶ ወነሥአ መጥባሕቶ ወአኀዛ ለዕቅብቱ ወመተራ እመለያልየ አዕፅምቲሃ ፲ወ፪ተ ክፍለ ረሰያ ወፈነዋ ውስተ ሕዝበ ፳ኤል ፣

ያም ሰው ወደቤቱ ከገባ በኋላ ወቅለምንት /ካራ/ አንስቶ የሚስቱን አጥንት ከአጽቅ ከአፅቋ ላይ ይቈርጣት ጀመር፣ አጥንቷንም አሥራ ሁለት አድርጎ ወደ አሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ላከላቸው፣ በሀገራችሁ እንዲህ ያለ ግፍ ተደረገ ለማለት፣ ምነው አንዱ ነገድማ አድራጊዎች አይደሉ ቢሉ ግብረ አበር ያልሆኑ ብዙ ሰዎች ነበሩና ፤

፴፣ ወእምዝ ኵሉ ዘርእየ ይቤ አልቦ አመ ኮነ ከመዝ ወአልቦ አመ አስተርአየ እምአመ ወፅኡ ፳ኤል እምግብፅ እስከ ዮም ፣

ከዚህ በኋላ የአየት ሰው ሁሉ እንደዚህ ያለ ግፍ የሆነበት ጊዜ የለም ፣ እስራኤልም ከግብፅ ከወጡ ጀምሮ

www.ethiopianorthodox.org

እስከ ዛሬ ድረስ እንዲህ ያለ ግፍ የታየበት ጊዜ የለም አሉ፤

፴፩፤ ወአዘዘሙ ውእቱ ብእሲ ለእልክቱ ሰብእ እለ ፈነዎሙ ወይቤሎሙ ከመዝ በልዎሙ ለኵሉ ሰብአ ፳ኤል ቦኑ አመ ኮነ ከመዝ እምአመ ወፅኡ ፳ኤል እምግብፅ እስከ ዮም ወረሰዩ ለክሙ ምክረ ወተናገሩ ዘይሜኒ ፤

ያም ሰው ልኮ የሰደዳቸውን ሰዎች የ፳ኤልን ልጆች እንዲህ በሏቸው ብሎ አዘዛቸው፤ በውኑ የያዕቆብ ልጆች ከግብፅ ከወጡ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እንዲህ ያለ ግፍ የሆነበት ጊዜ አለን ይህን አይታችሁ ለእናንተ የሚበጀውን ነገር ተናግራችሁ ምክር አጽንታ ችሁ ነገር ቁረጡ በሏቸው ብሎ አዘዛቸው /ላካቸው/ ::

## ምዕራፍ ፳

፩፤ ወወፅኡ ኵሎሙ ደቂቀ ፳ኤል ወአንገለጉ ወተጋብኡ ኵሉ ማኅበሮሙ ከመ አሐዱ ብእሲ እምዳን እስከ ቤርሳቤህ ወገለአድኒ ውስተ መሴፋ ፤

ከገለአድና ከ፳ኤል የተወለዱ ትም ሁሉ እንደ አንድ ልብ መካሪ ፤ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሁነው ከዳን እስከ ቤርሳቤህ በየወገን በየወገ ናቸው ተሰብስበው መጥተው በመሴፋ ተከማቹ ፤

፪፤ ወቆሙ ኵሉ ሕዝብ ወኵሉ ነገደ ፳ኤል ውስተ ማኅበሮሙ ወኵሉ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ፻ እልፍ አጋር ዘይፀውሩ ኵናተ ፤

ሕዝቡ ሁሉ የ፳ኤልም ነገድ ሁሉ በየወገናቸው ተለይተው የእግዚአብሔር ወገን የሚሆኑ ካህናቱም ሁሉ ተሰብስበው በቀኙ የሚወረውር በግራው የሚመክት አራት መቶ ሺህ እግረኛ ነበረ ፤

፫፤ ወሰምዑ ደቂቀ ብንያም ከመ ተጋብኡ ደቂቀ ፳ኤል ውስተ መሴፋ ወይቤሉ ደቂቀ ፳ኤል አይድዑነ በአይቴ ኮነት ዛቲ እኪት ፤

የብንያም ልጆችም አሥራ አንዱ ነገደ ፳ኤል በመሴፋ እንደተሰበሰቡ ሰሙ ፤ ተሰብስ በውም ይህች ኃጢአት የተሠ ራችበት አገር በወዴት ነው ? ንገሩን አሉ ፤

፬፤ ወአውሥአ ዝክቱ ካህን ሌዋዊ ምታ ለእንታክቲ ብእሲት እንተ ቀተሉ ወይቤ በገባዖን ዘብንያም ወመጻእኩ አነ ወዕቅብትየ ንኅድር፤

የብንያም ልጆች የገደሏት የዚያች ሴት ባል የሚሆን ያ ካህንም የብንያም ዕጣ ከምት



ሆን በገባዖን ነው ብሎ መለሰ፤ እኔም ሚስቴም በገባዖን ልናድር መጥተን ነበርና ፤

፭፤ ወተንሥኡ ላዕሌነ ሰብአ ገባዖን ወአገቱ ዲቤነ ውእተ ቤተ ሌሊተ ወኪያየ ፈቀዱ ይቅትሉኒ ወለዕቅብትየሰ አኀሡርዋ ወተዋነይዋ ወሞተት ፤

የገባዖን ሰዎችም ያን የገባን በትን ቤት ከበው በኛ ላይ በጠላትነት ተነሡ ፤ እኔንም ሊገድሉኝ ወደው ነበር ፤ ሚስቴን ግን አሥረው አጒሳ ቁሏት በፈረቃም ተጫወቱ ባት ፤ እርሷም ሞተች ፤

፮፤ ወነሣእክዋ ለዕቅብትየ ወመተ ርክዋ በበመለያልያ ወፈነውኩ ውስተ ኵሉ ደወለ ርስቶሙ ለ፳ኤል እስመ ገብሩ ዕበደ ውስተ ፳ኤል ፤

እኔም ሬሳዋን ወስጄ አጥንቷን ከአሥራ ሁለት ቁርጬ ለአሥራ ሁለቱ ነገደ ፳ኤል በየርስታቸው ላክሁላቸው ፤ የብንያም ልጆች በ፳ኤል ውስጥ ስንፍና የሚሆን ሥራ ሠርተዋልና ፤

፯፤ ወናሁ ኵልክሙ አንትሙ ደቂቀ ፳ኤል ዝየ አቅሙ ለክሙ ቃለ ወምክረ ፤

አሁንም የ፳ኤል ልጆች ሁሉ እናንተ ናችሁና ለእናንተ የሚ በጀውን ምክር አጽንታችሁ ነገር ቁረጡ ፤

፰፤ ወቆሙ ኵሉ ሕዝብ ከመ ፩ዱ ብእሲ ወይቤሉ ኢነአቱ አብያቲነ ወኢንገብእ በሐውርቲነ ፤

ሕዝቡም ሁሉ እንደ አንድ ልብ መካሪ ፤ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሁነው ፤ አንድም እንደ አንድ ሰው እንደ ሌዋዊ ሁነው በጠላትነት ተነሥተው ደም ሳንመልስ ወደቤታችን አንገባም ወደሀገራችንም አንመለስም አሉ ፤

፱፤ ወይእዜኒ ከመዝ ግበሩ ላዕለ ገባዖን ነዐርግ ላዕሌሆሙ በበመክ ፈልትነ ፤

አሁንም በገባዖን ላይ እንዲህ አድርጉና በየክፍላችን ወደ ገባዖን እንዘምታለን ፤

፲፤ ወንነሥእ በበ፲ቱ ዕደው ለ፻ ለኵሉ ሕዝበ ፳ኤል፤ ወከማሁ ፻ተ ለ፲ ፻ ወ፲ተ ፻ተ ለእልፍ እለ ይፀውሩ ስንቀ ለሕዝብ ውስተ ፍኖት ለእለ የሐውሩ ይትቃተልዎሙ ለገባዖን ዘብንያሚ በበይነ ኵሉ እበድ እንተ ገብሩ ላዕለ ፳ኤል ፤

ስንዘምትም ለ፳ኤል ወገኖች ሁሉ በአሥር በአሥር አርበኛ አንድ አንድ ገባር ፤ ለ፻ው አርበኛ አሥር ገባር ይዘን በ፳ኤል ላይ ስለአደረጉት ኃጢአት እንደብንያሚን /የብንያምን ልጆች/ ያጠፉ ዘንድ ለሚሄዱ ወገኖች

www.ethiopianorthodox.org

የመንገድ ስንቅ የሚሸከሙ ለአሥሩ ሺህ ወታደር ሺህ ገባር፣ በሺሁ ወታደር መቶ ገባር አድርጉ ፤

፲፩፡ ወተጋብኡ ኵሉ ፳ኤል እም አህጉሪሆሙ ፣

አሥራ አንዱ ነገደ ፳ኤልም ይህን ተመካክረው ሁሉም ከየሀገራቸው ተሰበሰቡ ፤

፲፪፡ ወለአኩ ኵሉ ሕዝበ እስራ ኤል ውስተ ኵሉ ነገደ ብንያሚ እንዘ ይብሉ ምንት ዛቲ እኪት እንተ ኮነት በውስቴትክሙ ፣

የ፳ኤል ወገኖች ሁሉ ገባያን ደርሰው በእናንተ የተደረገች ይህች ኃጢአት ለምንድን ነው? ብለው ወደብንያም ነገድ ሁሉ ላኩ ፤

፲፫፡ ወይእዜኒ አምጽኡ ዕደወ እለ አበሱ በገባዖን ደቂቀ ዓመፃ ወንቅትሎሙ ወናወጽእ እኪተ እምደቂቀ ፳ኤል ወአበዩ ደቂቀ ብንያሚ ሰሚዖቶሙ ለደቂቀ ፳ኤል ፣

አሁንም በገባዖን ይህን ኃጢአት የሠሩ የበደል ልጆች የሆኑትን ሰዎች እንገድላቸው ዘንድ አምጡ ፣ ይህን አድርገን ከ፳ኤል ልጆች በደልን እናርቅ አሏቸው ፣ የብንያምም ልጆች ወንድሞቻችንን ለደም አሳልፈን አንሰጥም ሲሉ የ፳ኤልን ልጆች አንሰማችሁም አሏቸው ፤

፲፬፡ ወተጋብኡ ደቂቀ ብንያሚ እምአህጉሪሆሙ ውስተ ገባዖን ከመ ይፃዑ ይትቃተልዎሙ ለደቂቀ ፳ኤል ፣

የብንያም ልጆች የ፳ኤልን ልጆች /አሥራ አንዱን ነገድ/ ይገጥሟቸው ዘንድ ከየሀገራቸው በገባዖን ተሰበሰቡ ፤

፲፭፡ ወተኈለቁ ደቂቀ ብንያሚ በይእቲ ዕለት እምአህጉሪሆሙ ፳፻፻ ወ፯፻ ብእሲ እለ ይፀውሩ ኵናተ እንበለ እለ ይነብሩ ውስተ ገባዖን ፣

የብንያምም ልጆች በዚች ቀን ከየሀገራቸው ወጥተው ቢቈጠሩ በገባዖን ከሚኖሩ ሰዎች በቀር ሊጦር የደረሱ ሃያ አምስት ሺህ ሰዎች ተገኙ ፤

፲፮፡ ወእሙንቱኒ ተኈለቁ ፯፻ ወራዙት ኅሩያን እለ ፪ኤሆን እደዊሆሙ የማናውያን ኵሎሙ ወኵሎሙ እሉ ወጸፍያን በሞጸፍተ እብን ወየሐይጹ ሥእርተ ወኢይስሕቱ ፣

እነዚያም የተመረጡ ሰባት መቶ አርበኞች ቢቈጠሩ ሁሉም በቀኛቸውና በግራቸው የሚወረውሩ ናቸው ፣ እነዚህም ሁሉ በወንጭፍ ደንጊያ



የሚወረውሩ የማይስቱ ከራስ ጸጉር ስንኳን አንዲቱን ለይተው የሚመቱ ናቸው ፤

፲፯፡ ወተኈለቁ ኵሎሙ ደቂቀ ፳ኤል እንበለ ደቂቀ ብንያሚ ፵፻፻ ብእሲ ፀዋሬ ኵናት ወኵሎሙ እሉ ዕደው መስተቃትላን ፣

የአሥራ አንዱም ልጆች ሁሉ ቢቈጠሩ ከብንያም ልጆች በቀር ሊጦር የደረሱ አርባ ፻፻ ሰዎች /አራት መቶ ሺህ/ ተገኙ እነዚያም ሁሉ አርበኞች ናቸው ፤

፲፰፡ ወተንሥኡ ወዐርጉ ውስተ ቤቴል ወተሰአሉ ኀበ እግዚአብሔር ወይቤሉ ደቂቀ እስራኤል መኑ የዐርግ ለነ መስፍነ ዘይትቃተሎሙ ለነ ለብንያሚ ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ይሁዳ ይዕርግ ለክሙ መስፍነ ፣

በዚያ ወራት ታቦተ ጽዮን በቤቴል ተተክላ ነበርና ከሀገራቸው ተነሥተው ወደቤቴል ወጡ ፣ ለነ ለደቂቀ ፳ኤል ብሎ ይገጥሟል ፣ ለአሥራ አንዱ ነገድ ለኛ ነገደ ብንያምን መስፍን ሁኖ የሚዋጋልን ማን ይዝመት ብለው ቃለ እግዚአብሔር ጠየቁ ፣ እግዚአብሔርም በዚያ ወራት ይሁዳ የሚባል ሰው መስፍን ተሹሞ ነበርና ይሁዳ አለቃ ሁኖ ይዝመትላችሁ ፤ አንድም ነገደ ይሁዳ ፊታውራሪ ይሁን አላቸው ፤

፲፱፡ ወተንሥኡ ደቂቀ ፳ኤል ወኃደሩ ላዕለ ገባዖን ፣

አሥራ አንዱ ነገደ ፳ኤልም ከቤቴል ተነሥተው ገባዖን ሠፍረው አደሩ ፤

፳፡ ወወፅኡ ኵሎሙ ዕደወ ፳ኤል ውስተ ቀትል ምስለ ብንያሚ ወተአኃዝዎሙ በገባዖን ፣

አሥራ አንዱም ነገደ ፳ኤል ጓዝ ጠባቂ ሳይተዉ ከብንያም ልጆች ጋራ ለመዋጋት ወደ ሰልፍ ወጥተው በገባዖን ተያያዟቸው /ተቈራቈሷቸው/ ፤

፳፩፡ ወወፅኡ ደቂቀ ብንያሚ እምሀገር ወቀተሉ እም፳ኤል ፪ተ ፻፻ ወ፳፻ተ ብእሴ ይእተ አሚረ እለ ወድቁ ውስተ ምድር ፣

ነገደ ብንያምም መንገድ ሳይ መታቸው ከሀገራቸው ወጥተው ገጠሙ ከ፳ኤል ልጆችም ሁለት ዕልፍ ከሁለት ሺህ ገደሉ ያን ጊዜም በገደል ወድቀው በባሕር ጠልቀው የሞቱ ብዙ ናቸው ፤

፳፪፡ ወተጸንኡ ደቂቀ ፳ኤል ወደገመ ወፅኡ ይትቃተሉ ውስተ ዝንቱ መካን ኀበ ተቃተሉ አመ ቀዳሚት ዕለት ህየ ፣

የእስራኤል ልጆችም /አሥራ አንዱ ነገድ/ ተጽናንተው በመጀመሪያ ቀን ወደተዋጉበት ቦታ ይዋጉ ዘንድ ዳግመኛ ወጡ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፫፤ ወዐርጉ ደቂቀ ፳ኤል ወበከዩ ቅድመ እግዚአብሔር እስከ ሠርክ ፤

የእስራኤልም ልጆች ድል በመሆናቸው ወደ እግዚአብሔር ማደሪያ ወደቤቴል ወጥተው እስከ ሠርክ /ማታ/ አለቀሱ ፡

ወተስአሉ ኀበ እግዚአብሔር ወይቤሉ ንድግምኑ ዓዲ ተቃትሎ ምስለ ብንያሚ እኁነ ወይቤሎሙ እግዚአብሔር እርጉ ኀቤሆሙ ፤

ከወንድማችን ከብንያም ልጆች ጋር ዳግመኛ እንዋጋን ብለው እግዚአብሔርን ጠየቁ እግዚአብሔርም ወደ እነርሱ ዝመቱ አላቸው ፡

፳፬፤ ወመጽኡ ደቂቀ ፳ኤል ኀበ ብንያሚ አመ ማኒታ ዕለት ፤

የእስራኤል ልጆች ይህ በተደረገ በማግሥቱ ወደ ነገደ ብንያም መጡ ፡

፳፭፤ ወወፅኡ ደቂቀ ብንያሚ ወተቀበልዎሙ ወተቃተልዎሙ አመ ሳኒታ ዕለት እምገባዖን ፤

የብንያም ልጆችም በማግሥቱ ወጥተው በጦርነት ተቀብለው ተዋጓቸው ፡

ወቀተሉ እምኔሆሙ ፲፻፰ወ፰ተ ብእሴ እለ ወድቁ ውስተ ምድር ወኵሎሙ እለ ይፀውሩ ኵናተ ፤

ከነሱም አሥራ ስምንት ሺህ ሰው ገደሉ፤ በጎደል ወድቀው በባሕር ጠልቀው የሞቱም ብዙ ናቸው፤ ሁሉም ለጦር የደረሱ አርበኞች ነበሩ ፡

፳፮፤ ወዐርጉ ኵሎሙ ደቂቀ ፳ኤል ወኵሉ ሕዝብ ወሖሩ ውስተ ቤቴል ወበከዩ ወነበሩ ህየ ቅድመ እግዚአብሔር ፤

ከሞት የተረፉት የእስራኤል ልጆች ሁሉ አሁንም ወደ ቤቴል ወጥተው በእግዚአብሔር ፊት ሁነው አለቀሱ ፡

ወጾሙ ደቂቀ ፳ኤል እስከ ሠርክ ወዐረጉ መሥዋዕተ መድኃኒት ለእግዚአብሔር ፤

የእስራኤል ልጆችም ከጧት እስከ ማታ ሲጾሙ ውለው ድኅነት የሚያስጥ መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር አቀረቡ ፡

፳፯፤ ወተስአሉ ደቂቀ ፳ኤል ኀበ እግዚአብሔር ወህለወት ህየ ታቦተ እግዚአብሔር በእማንቱ መዋዕል ፤

በዚያ ወራት የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ ታቦት በዚያ ነበረችና የእስራኤል ልጆች መሥዋዕት ሠውተው ቃለ እግዚአብሔር ጠየቁ ፡

፳፰፤ ወፊንሐስ ወልደ አልዓዛር ወልደ አሮን ይቀውም ቅድሜሃ በእማንቱ መዋዕል ወይቤሉ ንድግምኑ ዓዲ ወፂአ ውስተ ቀትል ምስለ ደቂቀ ብንያሚ እኁነ አው ንኅድግ ፤

ወልደ አሮን ብሎ ለአልዓዛር ቀጠለ ፤ በዚያም ወራት የአሮን የልጁ የአልዓዛር ልጅ ፊንሐስ በደብተራ ኦሪቱ



ደጃፍ ቁሞ ነበር ፤ የእስራኤል ልጆችም ወደፊንሐስ ቀርበው ከወንድማችን ከብንያም ልጆች ጋራ ዳግመኛ ወጥተን እንዋጋን ወይስ እንተው ? አሉት ፡

ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ዕርጉ እስመ ጌሠመ አገብዖሙ ውስተ እዴክሙ ፤

እግዚአብሔርም ነገ የብንያም ልጆች በእጃችሁ አሳልፌ እሰጣችኋለሁና ዝመቱ አላቸው ፡ /ሐተታ/ እስከ አሁን ዕርጉ እንጂ አገብኦሙ አላለም ነበር ፤ እስራኤልን የተጣላበት ነገር ነበርና ፤ ከአሥራ አንዱ ነገድ ክፉ ክፉ ሰዎች ነበሩና ክፉዎቹ በክፉ ሰዎች እጅ ይጥፉ ብሎ፤ አሁን ግን ነገደ ብንያምን በአሥራ አንዱ ነገድ እጅ የሚጥላቸው ነውና ፡

፳፱፤ ወአንበሩ ደቂቀ ፳ኤል እለ የዓግትዋ ለገባዖን ፤

አሥራ አንዱ ነገድ የገባዖንን ዙሪያ የሚከቡ ድብቅ ጦር አኖሩ ፡

፴፤ ወተአኀዝዎሙ ደቂቀ ፳ኤል ለብንያሚ አመ ሣልስት ዕለት ወተቃተልዎሙ በኀበ ገባዖን ከመ ቀዲሙ ፤

በሦስተኛውም ቀን አሥራ አንዱ ነገድ እስራኤል የብንያ ምን ልጆች በገባዖን ገጠሟ ቸው፤ እንደመጀመሪያውም ይዋጓቸው ጀመር ፡

፴፩፤ ወወፅኡ ደቂቀ ብንያሚ ወተቀበልዎሙ ለሕዝብ ወጐዩ እምኀበ ሀገር ወአኀዙ ይትቃተሉ እምሕዝብ ከመ ቀዲሙ በውስተ ፍኖት አሐቲ እንተ ታዐርግ ለቤቴል ወአሐቲ እንተ ታዓርግ ለገባዖን በውስተ ገዳም ወየአክሉ ፴ ፻፻ ብእሲ እም፳ኤል ፤

የብንያምም ልጆች ወጥተው አሥራ አንዱን ነገድ ገጠሟ ቸው ፤ የእሥራኤልም ልጆች ከከተማው ሸሽተው አንዲቱ ወደቤቴል አንዲቱ ወደገባዖን በምታወጣ ጐዳና እንደ ቀድሞው ይዋጉ ጀመር ፤ ያን ጊዜም ከአሥራ አንዱ ነገድ የነበሩ ሰዎች ሦስት መቶ ሺህ ያህላሉ ፡ /ሐተታ/ የወጡት አራት መቶ ሺህ ነበሩ አርባው ሺህ በሁለት ጊዜ ጦርነት ስሳው ሺህ በገደል ወድቀው በባሕር ጠል ቀው አልቀዋልና ፡

፴፪፤ ወይቤሉ ደቂቀ ብንያሚ ይመውቱ ቅድሜነ ከመ ቀዲሙ ወይቤሉ ደቂቀ ፳ኤል ንጕየይ ወናርኅቆሙ እምሀገር ውስተ ፍናዊ ፤

የብንያምም ልጆች እንደ ቀድሞው ከፊታችን ይሸሻሉ፤ ብለው አጽንተው ይዋጓቸው

www.ethiopianorthodox.org

ነበርና አሥራ አንዱ ነገደ እስ ራኤል የሸሸን መስለን ከሀገር ወደጐዳና እናርቃቸው አሉ ። ለመክበብ እንዲመቻቸው ፤

፴፫፡ ወተንሥኡ ኵሎሙ ዕደወ እስራኤል እምነ መካኖሙ ወተቃተሉ በበአልታምር ወማዕገቶሙኒ ለእስራኤል ተበአሰ በመካኖሙ እም ዐረቢሃ ለገባዖን ፡

የእስራኤል ወገኖች ሁሉ ሸሽተው በበኣልታምር ከደረሱ በኋላ አግባ መልስ ብለው ይዋጉ ጀመር ፡ ከባቢ /ድብቅ ጦር/ አድርገው ያኖሯቸውም ሰዎች ከገባዖን ምዕራብ ከተሠ ወሩበት ቦታ ሁነው ያወኩ ይደነፉ ጀመር ፤

፴፬፡ ወገብኡ እንተ ቅድሜሃ ለገባዖን ፲፻ ብእሲ ኅሩያን እም እስራኤል ወጸንዐ ቀትል ወኢያእመሩ ከመ በጽሐቶሙ እከዮሙ ፡

ከእስራኤል የተመረጡ ዕልፍ ሰዎች ወደገባዖን ፊት ለፊት ገቡ ፡ ሰልፉም እየጸና ሄደ፡ የብንያም ወገኖች ግን ፍዳ ኃጢአታቸው እንደደረሰባ ቸው አላወቁም ነበርና ፤

፴፭፡ ወአውደቆሙ እግዚአብሔር ለብንያሚ ቅድመ እስራኤል ወቀተል ዎሙ ደቂቀ እስራኤል ለብንያሚ ፳፭ቱ ፼ ወ፻ ወ፩ደ፻ቱ ወኵሎሙ እለ ይፀውሩ ኲናተ ፡

እግዚአብሔርም የብንያምን ወገኖች በእስራኤል ፊት ጣላ ቸው፡ የእስራኤል ልጆች ነገደ ብንያምን አጠፏቸው ፤ ያን ጊዜ የሞቱት ሃያ አምስት ሺህ አንድ መቶ ናቸው ፡ የሞቱትም ሁሉ በቀኝ እጃ ቸው የሚወረውሩ በግራ እጃቸው የሚመክቱ አርበኞች ናቸው፡ /ሐተታ/ ሲወጡ ሁለት እልፍ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ነበሩ፡ ስድስቱ መቶ በኰኵሐ ሬሞን ገብተው ድነዋል ፤

፴፮፡ ወርእየ ብንያሚ ከመ ተቀትለ ወወሀብዎሙ እስራኤል መካነ እስመ ተአመኑ በማዕገቶሙ ዘሜሙ ላዕለ ገባዖን ፡

የብንያም ወገኖችም ድል እንደ ሆኑ አይተው እስራኤል በገባዖን ባኖሯቸው ከባቢ ጦራቸው ታምነዋልና የሚሸሹበት የወንድ በር ሰጧቸው ፤

፴፯፡ ወሖሩ እልክቱ እለ ዐገቱ ወቀተልዋ ለሀገር በአፈ ሐፂን ፡

ገባዖንን ከበው የተቀመጡትም አርበኞች ከተማ ገብተው አገሩን በእሳት ሰውን በሰለት አጠፉ ፤

፴፰፡ ወአዘዝዎሙ እስራኤል ለእለ የዓግቱ ከመ በሐፂን ይቅትልዎሙ ወያዕርግዎሙ ለጢስ ሀገር ከመ ማኅፈድ ፡



እስራኤልም ገባዖንን የከበቡ ሰዎችን ከሰልፍ ያመለጡትን በጦር ወግተው ይገድሏቸው ዘንድ ፡ የአገሪቱንም ጢስ እንደ ግንብ ተጠቅሎ እንዲ ወጣ ያደርጉ ዘንድ አዘዋቸው ነበርና ፤

፴፱፡ ወተመይጡ ዕደወ እስራኤል በውስተ ቀትል ወለብንያሚስ አኀዘም ይቅትልዎ ዕደወ እስራኤል ፡

«ወወሀብዎሙ እስራኤል መካነ» ብሎ ነበርና የእስራኤል አርበ ኞች መንገድ ከሰጧቸው በኋላ የተረፉትን ወደመውጋት ተመለሱ ፡ «ወለብንያሚኒ» ሲል ነው ፡ ተመልሰውም የብንያምን ወገን ይወጉት ጀመር ፡ ቢርቀው ደገመው ፤ አንድም የሞቱትን ተናግሮ ነበርና የተረፉትንም እንዲጠ ፏቸው ለመናገር ፤

ወየእክሉ ፴ቱ ፲ቱ ብእሴ እስመ ይቤ እንበለ ይቅትሉኒ ቀተልክዎሙ በቅድሜየ ከመ ቀትል ዘቀዲሙ ፡

እንደመጀመሪያው ጦርነት እነእርሱ ሳያጠፉኝ አጠፋቸ ዋለሁ ብሎ ነበርና እነዚህም ስድስት መቶ ያህሉ ነበር ፤

፵፡ ወዝክቱ ጢስ ማኅፈድ የዐርግ እምሀገር ከመ ዓምድ ወነጸረ ብንያሚ ድኅሬሁ ወናሁ ዐርገ ጥፍዓተ ሀገር ውስተ ሰማይ ፡

ያም የግንቡ ጢስ ከከተማው እንደምሰሶ ቀጥ ብሎ ወጣ ፡ የብንያምም ወገን ወደኋላው ተመልሶ ባየ ጊዜ አገሩ በእሳት ተቃጥሎ ጢስ ወደ ሰማይ ሲወጣ አየ ፤ አንድም የአገሩ ጥፋት በዝቶ እንደ ተደረገ አወቀ ፤

፵፩፡ ወተመይጡ ዕደወ እስራኤል ወተ ወላወሉ ደቂቀ ብንያሚ ወርእዩ ከመ በጽሐቶሙ እከዮሙ ፡

የእስራኤል አርበኞችም ወደ ከተማው በተመለሱ ጊዜ የብንያም ወገኖች ተሸበሩ ፡ የክፋታቸውም ፍዳ እንደደ ረሰባቸው አወቁ ፤

፵፪፡ ወነትዑ ቅድሜሆሙ ለእስራኤል ውስተ ፍኖተ ገዳም ወበጽሖሙ ቀትል ወእለሂ እምሀገር ቀተል ዎሙ በማዕከሎሙ ፡

በእስራኤል ፊት ወደምድረ በዳ ሸሹ ፡ ሰልፉም ደረሰባቸው ፡ ከገሀር የወጡትን በድንገት ጦር ተሥቶ በመካከል ሳሉ አጠፉቸው ፤

፵፫፡ ወቀተልዎሙ ለብንያሚ ወአጥፍዕዎሙ ወደምስሶ ደምስ ዎሙ በቅድመ ገባዖን ጽባሒሃ ፡

በከተማ የቀሩ የብንያምንም ወገኖች ወግተው በገባዖን በምሥራቋ አንፃር ፈጽመው አጠፏቸው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፵፬፤ ወወድቁ እምብንያሚ ፼ ወ፰፻ ብእሲ ወኵሎሙ እሉ ጽኑዓን ዕደው ፤

ያን ጊዜም ከብንያም ወገኖች አሥራ ስምንት ሺህ ሰዎች በጦር ተወግተው ወደቁ /ሞቱ/ እነዚህም ሁሉ ሰዎች አርበኞች ነበሩ ፤

፵፭፤ ወጐዩ ኀበ ኰኵሐ ሬሞን ወአረደይዎሙ በፍኖት ፶፻ተ ብእሴ ወዴገንዎሙ ወቀተልዎሙ እስከ ጌዴዓም ወቀተሉ እምኔሆሙ ፳፻ተ ብእሴ ፤

የተረፉትም በሬሞን ወዳለ ዋሻ ሸሹ ፤ ተከትለውም ጌዴዓም እስኪደርሱ ድረስ አጠፏቸው ፤ አምስቱን ሺህ ሰዎች መንገድ ለመንገድ በጦር ለቀሟቸው ፤ ከዚያም ያመለጡትን /የቀሩትን/ ሁለት ሺህ ሰዎች ተከትለው አጠፉ ፤

፵፮፤ ወኮኑ ኵሎሙ እለ ወድቁ እምብንያም ፪፼ ወ፶ወ፩፻ ብእሲ እለ ይፀውሩ ኲናተ በይእቲ ዕለት ወኵሎሙ እሉ ዕደው ዕኑዓን ፤

በዚያችም ቀን ከብንያም ወገን የሞቱ ለጦር የደረሱ ሃያ አምስት ሺህ አንድ መቶ ሆኑ፤ እነዚህም የሞቱት ሰዎች ሁሉ አርበኞች ነበሩ ፤

፵፯፤ ወነትዑ ወጐዩ ውስተ ኰኵሐ ሬሞን ፮፻ብእሲ ወነበሩ ውስተ ኰኵሐ ሬሞን ፬ተ አውራኃ ፤

ያን ጊዜም ከሞት የተረፉ ስድስት መቶ ሰዎች ወደ ሬሞን ዋሻ ውስጥ ሸሽተው ሄደው በሬሞን ዋሻ አራት ወር ተቀመጡ ፤

፵፰፤ ወአፀውዎሙ ሰብአ ፳ኤል ለደቂቀ ብንያሚ ወቀተልዎሙ በአፈ ሐፃን፤

አሥራ አንዱ ነገደ ፳ኤልም ወደከተማ ተመልሰው የብንያ ምን ልጆች እንዳይወጡ በሩን ዘጉባቸው ፤ በጦርም አጠፏቸው ፤

ወሀገሮሙኒ አውዐዩ ወእንስሳሆሙ ወኵሎ ዘተረክበ ውስተ አህጉር ወአህጉሪሆሙኒ እለ ረከቡ አውዐዩ በእሳት ፤

አገራቸውንና ከብቶቻቸውን በአገር የተገኘውንም ገንዘባቸውን ሁሉ ያገኙትንም ከተማ ሁሉ በእሳት አቃጠሉ ።

## ምዕራፍ ፳፩

፩፤ ወተማሐሉ ሰብአ እስራኤል በመሴፋ እንዘ ይብሉ ከመ ኢየሀብ ብእሲ እምኔነ ወለቶ ለብንያሚ ያስተዋስብ ፤

አሥራ አንዱ ነገደ እስራኤል ነገደ ብንያምን ድል ከነሱ በኋላ በመሴፋ ተሰብስበው ከኛ አንድ ሰው ልጁን ለነገደ ብንያም እንዳይሰጥ ሲሉ ተማማሉ ፤



፪፤ ወሖሩ ኵሉ ሕዝብ ውስተ ቤቴል ወነበሩ እስከ ሠርክ ቅድመ እግዚአብሔር ወጸርሑ ወበከዩ ዐቢየ ብካየ ፤

ሕዝቡም ሁሉ በቤቴል ተሰብስበው በእግዚአብሔር ማደሪያ በታቦቱ ፊት እስከ ሠርክ /ማታ/ ድረስ ተቀምጠው እየጮሁ ጽኑ ልቅሶ አለቀሱ ፤

፫፤ ወይቤሉ ለምንት እግዚኦ ኮነት ዛቲ እኪት በውስተ ፳ኤል ከመ ትኃሥ የዮም አሐቲ ሕዝብ እም፳ኤል ፤

አቤቱ ከአሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ዛሬ አንዲቱ ነገድ ትለይ ዘንድ ይህች ኃጢአት ክፉ ሥራ በ፳ኤል ውስጥ ለምን ተደረገች ? እያሉ አለቀሱ ፤

፬፤ ወእምዝ በማኒታ ጌሡ ሕዝብ ወነደቁ በህየ ምሥዋዐ ወአዕረጉ መሥዋዕተ መድኃኒት ፤

ከዚህ በኋላ ሕዝቡ በማግሥቱ ገሥግሠው ሄደው በዚያ መሠዊያ ሠሩ ፤ በመሠዊያውም ላይ ድኅነት የሚያሰጥ መሥዋዕትን አቀረቡ ፤

፭፤ ወይቤሉ ደቂቀ ፳ኤል መኑ ዘኢዐርገ እማኅበር እምኵሉ ሕዝበ ፳ኤል ኀበ እግዚአብሔር ፤

የእስራኤል ልጆችም ከ፳ኤል ወገኖች ሁሉ ወደእግዚአብ ሔር ማደሪያ ወደቤቴል ያልወጣ ማነው ? አሉ ፤

እስመ ዐቢይ መሐላሆሙ ከመ ዘኢዐርገ ኀበ እግዚአብሔር ውስተ መሴፋ ሞተ ለይሙት ይቤሉ ፤

ወደእግዚአብሔር ማደሪያ ወደ መሴፋ ያልወጣ የሞት ሞት ይሙት ሲሉ ፤ የተማማ ሉት መሐላቸው ጽኑ ነውና ፤

፮፤ ወተዐረቅዎ ደቂቀ ፳ኤል ለብንያሚ እኁሆሙ ወይቤሉ ትወዕእኑ ዮም አሐቲ ሕዝብ እም ፳ኤል ፤

አሥራ አንዱ ነገደ ፳ኤልም ወንድማቸው ነገደ ብንያምን ከ፳ኤል አንዲቱ ነገድ ትለያ ለችን ብለው ታረቁት ፤

፯፤ ምንተ እንከ ንሬስዮሙ ለእለ ተርፉ በእንተ አንስት ናሁ መሐልነ ንሕነ ለእግዚአብሔር ከመ ኢነሀቦሙ አምአዋልዲነ ያውስቡ ፤

ከልጆቻችን ያገቡ ዘንድ እንዳ ንሰጣቸው እነሆ እኛ በእግዚ አብሔር ምለናል ፤ እንግዲህ ከሞት የቀሩ ሚስቶችን እንግዲ ያገኙ ምንእናድርግ ? አሉ ፤

፰፤ ወይቤሉ መኑ እምአኃዊነ ሕዝበ ፳ኤል ዘኢዐርገ ኀበ እግዚአብሔር ውስተ መሴፋ ወናሁ ፩ዱ ብእሲ ኢመጽአ እምነ ኢያቢስ ዘገለዐድ ውስተ ማኅበሮሙ ፤

የ፳ኤል ልጆችም ከወንድሞ ቻችን ከ፳ኤል ወገን የእግዚ አብሔር ማደሪያ ወደሚሆን

www.ethiopianorthodox.org

ወደመሴፋ ያልመጣ ማነው ? አሉ ፣ እነሆ የገለዓድ ወገን ከሚሆን ከኢያቢስ አንድ ሰው አልመጣም ነበር ፤

፱፣ ወተፋቀዱ ሕዝብ ወናሁ አሐዱ ብእሲ ዘእምኢያቢስ ዘገለዓድ ኢሀለወ ፣

ሕዝቡም በየወገናቸው ቢቈጠሩ የገለዓድ ዕጣ ከሚሆን ከኢያቢስ አንድ ሰው ስንኳ ሳይመጣ ተገኘ ፤

፲፣ ወለአኩ ህየ ማኅበሮሙ ፻፲፻ፈ ወ፳ ፻ተ ብእሴ እምደቂቀ ኃይል ወአዘዝዎሙ እንዘ ይብሉ ሑሩ ወቅትሉ ኵሎ እለ ይነብሩ ውስተ ኢያቢስ ዘገለዓድ በአፈ ሐፂን አንስተኒ ወሕዝበኒ ፣

የ፳ኤልም ወገኖች ኃይል ካላቸው ልጆች አሥራ ሁለት ሺህ ሰዎች ወደኢያቢስ ልከው የገለዓድ ዕጣ በምትሆን በኢያቢስ የሚኖሩትን ሁሉ ሴቶችንም ወንዶችንም በጦር እየወጋችሁ አጥፉ ብለው አዘዟቸው ፤

፲፩፣ ወከመዝ ግበሩ ኵሎ ተባዕተ ወኵሎ አንስተ እለ የአምራ ብእሴ ቅትሉ ፣

እንዲህም አድርጋችሁ ባል ያገቡትን ሴቶችንና ሚስት ያገቡ ወንዶችንም አጥፉ አሏቸው ፤

፲፪፣ ወረከቡ እምእለ ይነብሩ ውስተ ገለዓድ ፬ተ ፻ተ አዋልደ ደናግለ እለ ኢያእመራ ብእሴ ወአምጽእዎን ውስተ ትዕይንት ውስተ ሴሎ ውስተ ምድረ ከነዓን ፣

በገለዓድ ከሚኖሩ ሰዎችም ወንድ የማያውቁ ፬ መቶ ደናግል ሴቶች አገኙ ፣ እኒህንም በከነዓን ምድር ውስጥ ወደ አለች ወደሴሎ ከተማ አመጧቸው ፤

፲፫፣ ወለአኩ ኵሎ ማኅበሮሙ ኀበ ብንያም እለ ውስተ ኰኵሐ ሬሞን ወጸውእዎሙ በሰላም፣

አሥራ አንዱ ነገደ እስራኤልም ሁሉ በሬሞን ዋሻ ውስጥ ወዳሉ ወደ ብንያም ወገኖች ሰው ልከው በፍቅር ጠሯቸው ፣ አሁን ወሀብዎሙ አንስተ የሚል ነውና እንደ አርእስት አነሣቸው ፤

፲፬፣ ወገብኡ ብንያሚ ኀበ ደቂቀ እስራኤል በእማንቱ መዋዕል ወወሀብዎሙ አንስተ ዘአሕየዉ እምአንስተ ኢያቢስ ዘገለዓድ ወሠምሩ በዝንቱ፣

በዚያም ወራት ከሞት የተረፉት የብንያም ልጆች ወደ ፳ኤል ልጆች መጡ ፣ የ፳ኤል ልጆችም የገለዓድ ዕጣ ከሚሆን ከኢያቢስ ከሞት ያዳኗቸውን ሴቶች ሚስቶች ይሁኗችሁ ብለው ሰጧቸው ፣ የብንያም ልጆችም በኢያቢስ ሴቶች ግቢ ደስ አላቸው ፤



፲፭፣ ወሕዝብኒ ተኳነንዎሙ ለብንያሚ እስመ ገብረ እግዚአብሔር ቀትለ በውስተ ፳ኤል፣

እግዚአብሔር በአሥራ አንዱ ነገደ ፳ኤል መካከል ሰልፍን /ጥፋትን/ አዝዞ ነበርና ሕዝቡም የብንያምን ልጆች ተዋቀሷቸው ፤

፲፮፣ ወይቤሉ ሊቃናተ ማኅበር ምንተ ንግበር በእንተ እለ ተርፋ ሕዝብ በበይነ አንስት እስመ ጠፍአ አንስት እምብንያሚ ፣

የማኅበሩም ሽማግሌዎች ከብንያም ነገድ ሴቶች ጠፍተ ዋልና ከሞት ስለተረፉት ስለስድስቱ መቶ ሰዎች የሚስ ቶቻቸውን ነገር ምን እናድርግ አሉ ፤

፲፯፣ ወይቤሉ ርስት ተርፈ ለብንያሚ ወኢትደምሰስ ሕዝብ እም፳ኤል ፣

ለብንያም ልጆች ርስት ቀረባ ቸው ፣ አንዲቱ ወገን ከእስራ ኤል ተለይታ አትጥፋ አሉ ፤

፲፰፣ ወንሕነኒ ኢንክል ውሂቦቶሙ አንስተ እምአዋልዲነ እስመ መሐሉ ደቂቀ ፳ኤል እንዘ ይብሉ ርጉም ውእቱ ዘይሁብ ብእሲተ ለብንያሚ፣

እኛም ከልጆቻችን ሚስት እንዳናጋባቸው ለብንያም ልጆች ሚስት የሚሰጥ ሰው ርጉም ይሁን ብለው የ፳ኤል ልጆች ምለዋልና ፤

፲፱፣ ወይቤሉ በዓለ እግዚአብሔር በሴሎ እመዋዕል በበመዋዕሊሁ ውእቱ እመንገለ መስዐ ለቤቴል ወበጽባሒሃ ለፍኖት እንተ ተዐርግ እምቤቴል ለሰቂማ ወእመንገለ ዓዜባ ለሌብና ፣

እንግዲህ ወዲህ ከአንዱ ዘመን በየወራቱ የሚደረግ የእግዚአ ብሔር በዓል ከቤቴል ወደ ሰቂማ በምታወጣው ጐዳና ምሥራቅና በቤቴል አንፃር በሌብና በስተግራ ባለች በሴሎ ይሁን አሉ ፤

፳፣ ወአዘዝዎሙ ለደቂቀ ብንያሚ ወይቤልዎሙ ሑሩ ወተኀብዑ ውስተ ዓፀደ ወይን ወተዐቀቡ አዋልዲሆሙ ለእለ ይነብሩ ውስተ ሴሎም እንዘ ይትዋነያ በመስንቆ ፣

የብንያምንም ልጆች ሔዳችሁ በወይን ቦታ ተሠወሩ በሴሎም የሚኖሩ ሰዎች ልጆችን መሰንቆ እየመቱ ሲጫወቱ ተጠባበቁ ፤

፳፩፣ ወትወፅኡ እምዓፀደ ወይን ወምሥጡ ለክሙ አንስተ እምአ ዋልደ ሴሎም ወእትዉ ውስተ ብንያሚ ፣

ያን ጊዜ ከተሠወራችሁበት ከወይኑ ቦታ እየወጣችሁ በሴሎም ካሉ ልጆች ለእናንተ አንዳንድ ሚስት እየነጠቃችሁ ወደ ብንያም ዕጣ ተመለሱ ብለው አዘዟቸው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፪፣ ወለእመ መጽኡ አበዊሆን ወአኃዊሆን ይሳነኑክሙ ንብሎሙ መሐርዎሙ እስመ ኢያውዕኡ አንስቲያሆሙ እምቀትል እስመ አኮ አንትሙ ዘወሀብክምዎሙ በእማንቱ መዋዕል ኢትነስሑ ፤

አባቶቻቸውና ወንድሞቻቸውም ይጣሏችሁ ዘንድ ቢመጡ ሚስቶቻቸውን ወደ ጦርነት አላወጡምና ማሯቸው ፤ በዚያ ወራት ልጆቻችሁን እናንተ የሰጣችኋቸው አይደለምና አትጸጸቱ እንላቸዋለን አሏቸው ፡

፳፫፣ ወገብሩ ከማሁ ደቂቀ ብንያሚ ወነሥኡ አንስተ በኊላቄ ሆሙ እምእለ ይትዋነዩ ወተማሠጥዎን ወአተዉ ወገብኡ ውስተ ርስቶሙ፤

የብንያም ልጆችም እስራኤል እንደ ነገሯቸው አደረጉ ፤ ከሚጫወቱት ልጆች በቍጥራቸው መጠን ሴቶችን ነጥቀው ይዘው ወደርስታቸው ተመለሱ ፡

ወነደቁ ሎሙ አህጉረ ወነበሩ ውስቴቶን ፤

እኒህንም ሴቶች ይዘው ተመል ሰው የጠፋውን አገር አቅን ተው ኖሩ ፤ «ወለአህጉሪ ሆሙኒ አውዓይዎን በእሳት» ብሎ ነበርና እንዲህ አለ ፤

፳፬፣ ወአተዉ እምህየ ደቂቀ እስራኤል ብእሲ ብእሲ ውስተ ሕዝቡ ወውስተ ነገዱ ወአተዉ እምህየ ብእሲ ብእሲ ውስተ ርስቱ ፤

የ፳ኤል ልጆችም አንዱም አንዱ ከሴሎ ተነሥተው ወደየወገናቸው ገቡ ፤ ነገደ ብንያምም አንዱም አንዱ ከሴሎ ተነሥተው ወደርስ ታቸው ገቡ ፡

፳፭፣ ወበእማንቱ መዋዕል አል ቦሙ ንጉሥ ለ፳ኤል ብእሲ ብእሲ ዘአደሞ ቅድመ አዕይንቲሁ ይገብር፤

በዚያም ወራት ለ፳ኤል ንጉሥ አልነበራቸውምና አንዱም አንዱም ሰው በፊቱ የወደደ ውን ያደርግ ነበር ፤ ሐተታ የማይገባ ሥራ መሥራታቸው የሚሠራ የሚቀጣ ንጉሥ ባይኖራቸው ነው ለማለት፣ ንጉሥ የሚነግሥበት ጊዜም ደርሷልና አልፎ አልፎ አነሣው ፡

ተፈጸመ ኦሪት ዘመሳፍንት የመሳፍንትን ነገር የሚናገር መጽሐፍ ደረሰ ተፈጸመ ።

ለእግዚአብሔ ክብር ምስጋና ይግባው፤

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



# ኦሪት ዘሩት

ዜና ዘሩት ሲል ነው ፤ የሩትን ነገር የሚናገር መጽሐፍ ይህ ነው ፤ ይህ አርእስት ነው፣ ፫ቱ ፲ት ለመጻሕፍት አርእስት ሲሰጡ አርእስት ሰጥተውታል፣ እሷ ግን ነገሯን «ወኮነ በመዋዕለ ይኴንኑ መሳፍንት» ብላ ትጀ ምራለች ።

## ምዕራፍ ፩

፩፣ ወኮነ በመዋዕለ ይኴንኑ መሳ ፍንት መጽአ ረኀብ ውስተ ብሔር፣

መሳፍንት በሚገዙበት ወራት እንዲህ ተደረገ ፤ በሀገሩ ረኀብ ሆነ ፤ ኮነ ያለውን መጽአ ረኀብ ብሎ ገለጠው ፤

ወሖረ ፩ ብእሲ እምቤተልሔም ዘይሁዳ ከመ ይንበር ውስተ ሐቅለ ሞዓብ ውእቱ ወብእሲቱ ወ፪ቱ ደቂቁ ፤

አንድ ሰው ከሚስቱና ከሁለቱ ልጆቹ ጋራ በሞዓብ አውራጃ ይኖር ዘንድ የይሁዳ ክፍል ከምትሆን ከቤተልሔም ተነ ሥቶ ወደ ሞዓብ ሔደ ፤

፪፣ ወስሙ ለውእቱ ብእሲ አቤሜ ሌክ ወስመ ብእሲቱ ኑሐሚን ፤

የዚያ ሰው ስሙ አሜቤሌክ ነው፣ የሚስቱም ስም ኑሐሚን ይባላል ፤ ኑሐሚን ማለት ጥዕምት ፍሥሕት ብዝኀት ማለት ነው ፤

ወአስማተ ደቂቁ ፪ቱ መሐሎን ወኬሌዎን ኤፍራታውያን እም ቤተልሔም ዘይሁዳ ወሖሩ ውስተ ሐቅለ ሞዓብ ወነበሩ ህየ ፤

የሁለቱ ልጆቹም ስማቸው የይሁዳ ዕጣ ከምትሆን ከቤተ ልሔም ወገን የሚሆኑ የኤፍ ራታ ሰዎች መሐሎንና ኬሌ ዎን ይባላል ፤ እነሱም ወደ ሞዓብ አውራጃ ሔደው በዚያ ተቀመጡ ፤

፫፣ ወሞተ አቤሜሌክ ምታ ለኑሐ ሚን ወተርፈት ይእቲ ወደቂቃ ፪ኤሆሙ ፤

የኑሐሚን ባሏ አቤሜሌክ በሞዓብ ሞተ ፤ እርሷ ከሁለቱ ልጆቿ ጋራ ብቻዋን ቀረች ፡

፬፣ ወነሥኡ ሎሙ አንስተ ሞዓብ ውያተ ስማ ለአሐቲ ኡርፋ ወስማ ለካልዕታ ሩት ወነበሩ ህየ ወአከለ ፲ተ ዓመተ ፤

እነሱም ዘመድ እናብጅ ብለው ከሞዓባውያን ሴቶች ሚስት አገቡ ፤ /ሞዓባውያት ሴቶችን አገቡ/ ፤ የአንዲቱ ስሟ ዑርፋ የሁለተኛዪቱ ስሟ ሩት ይባላል ፤ በዚያም አሥር ዓመት ያህል ኖሩ ፤

www.ethiopianorthodox.org